# የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርአት እና የማስረጃ ሕግ/ረቂቅ/ አጭር ማብራሪያ

## ማውጫ


የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርአት እና የማስረጃ ሕግ አጭር ማብራሪያ ..... 3

1. አጠቃላይ ..... 3

1.1. መግቢያ ..... 3

1.2. የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ ..... 7

1.3. ረቂቆችን የማለስና ድጋሚየማርቀቅ ሥራን የማከናወን ሂደት ..... 8

2. የወንጀለኛ መቅጫሥነ ሥርዐት ሕግ ለማርቀቅ የተለዩ ተጨማሪ ችግሮች፤ ..... 9

2.1 የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ችግሮች ..... 10

3. መግቢያና ጠቅላላ ጉዳዮች ..... 11

4. ስያሜው ..... 13

5. የተፈጻሚነት ወሰንና ቀን ..... 14

6. ትርጉም ..... 16

7. የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ መርሆዎች ..... 17

8. የሕጉ አላማ ..... 19

9. የተከላካይ ጠበቃ ጉዳይ ..... 20

10. የፍትሕ አካላት ስለሚኖራቸውተግባራት ..... 21

11. የወንጀል ምርመራ ተግባራት ..... 22

12. ማስረጃ አሰባሰብ ..... 29

12.1. የዋስትና ጉዳይ ..... 35

12.2. በምርመራ መዝገብ ላይ መወሰን ..... 38

12.3. የጥፋተኛት ድርድር ..... 40

12.4. አማራጭመፍትሔዎች ..... 42

12.5.ክስ የመመስረት ወሳኔ ..... 44

13. ዳኝነት ነክ ጉዳዮች ..... 46

13.1 የዳኝነት ሥልጣን ..... 47

13.2 ችሎትና ግልፅነት ..... 53

13.3. ከፍርድ እና ከፍትሕ ሂደት ስለመነሳት ..... 54

13.4. መጥሪያ ..... 55

13.5.የቅድመክስ ማስማት ተግባራት ..... 57

13.6. የክርክር ሥርአቶች ..... 59
13.7. ቀጠሮ፣ መቃወሚያና እምነት ክህደት ..... 66
13.8. የማስረጃ ደንቦች ..... 68
14.ፍርድና ቅጣት ..... 74
14.1 የቅጣት ውሳኔ ..... 76
15. ፍርድ እንደገና የሚታይባቸውአግባቦች ..... 81
15.1 ይግባኝ ..... 82
15.2 ሰበር ..... 84
15.3 ፍርድን እንደገና ማየት ..... 87
16. በወንጀል ጉዳይ አለምአቀፍ የወንጀል ጉዳዮች ትብብር ..... 88
16.1. የዓለምአቀፍትብብርምንነት ..... 90
16.2. አሳልፎ ማስጠት (Extradition) ..... 91
16.3 በወንጀል ጉዳዮች መረጃ ማለዋወጥ እና መተባበር (Mutual legal assistance) ..... 91
16.3.1.ፍርደኞችን ማስጠት ወይምመቀበል (Transfer of sentenced persons) ..... 92
16.3.2. የወንጀል ክስን ወደ ሌላ ሃገር ማስተላለፍ ..... 92
16.3.3. ሌሎች የዓለምአቀፍ ትብብር ዓይነቶች ..... 92
16.4 የዓለምአቀፍ ትብብርንና የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫሕግ ሥነ ሥርዐት ..... 93
17. ኪሳራና ወጪን በተማለከተ ..... 95
18. ደንብ፣ መመሪያ እና ቅፃ ቅፆችን ማውጣትእንዲሁምሕጉን ስለማሻሻል ..... 96
19. ሰንጠረዥ ..... 97

## የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርአት እና የማስረጃ ሕግ አጭር ማብራሪያ

### 1. አጠቃላይ

አሁን በስራ ላይ የሚገኘዉ የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫስነ ስርአት ሕግ ለማሻሻል ከዚህ በታች በተገለጹት ምክንያች ከ10 አመት በላይ የፈጀ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል፡፡ በዚህ ሂደት ወስጥም በርካታ ማሻሻያዎች የተደረጉባቸውየሥነ ሥርአቱ ሕጎች እየተዘጋጁ ወይይት የተደረገባቸውሲሆን ከወይይቶቹ የሚገኙ ግብአቶችን ጭምር በማካተት ይህ የሥነ ሥርአትና የማስረጃ ሕግ የሚጨፈሻ ሆኖ ተዘጋጅቷል፡፡ ይህ ማብራሪያ በረቂቅ ሕጉ ወስጥ ምን እንደተካተተና ለምን እንደተካተተ በጥቅሉ የሚያመለክት ሰንደ ሆኖ ነውየተዘጋጀው፡፡ በመሆኑም በረቂቅ ሕጉ ወስጥ የተካተቱት እያንዳንዳቸውአንቀጾች የሚብራሩት በሃተታ ዘምክንያት በመሆኑ ይህ ማብራሪያ ረቂቁ የያዛቸዉን ጉዳዮች ጠቅለል ካለ ምክንያት ጋር እንዲያመለክት የተዘጋጀ ማብራሪያ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

### 1.1. መግቢያ

የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት በመግቢያው ላይ በግልፅ እንዳስቀመጠው በህግ የበላይነት ላይ የተመሰረተ ዘላቂ ሰላምና ዘላቂ ልማት የሚረጋገጥ ግብ አለው፡፡ የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት የአገሪቱ የበላይ ህግ ከመሆኑምበላይ በርካታ የወንጀል ስነ ስርአትና የማስረጀ ድንጋዎችንም ያቀፈ ነው፡፡ የስነ ስርአትና የማስረጀ ድንጋጌዎቹ አንዳንዶቹ በቀጥታ በፍትሕ አካላቱ ወደ ተግባር ሊለወጡ የሚችሉ ሲሆን ሌሎቹ ድንጋጌዎች ደግሞ ለማስፈፀሚያነት ሌሎች ዘርዘር ያሉ ድንጋጌዎችን የሚሹ ናቸው፡፡ በተመሳሳይም አገራችን የአለም አቀፍ ድንጋጌዎችን በተለይም ሰበአዊ የሲቪል፣ ፖለቲካል፣ የሕጻናት፣ ሴቶችና እና ሌሎች መብቶችን የተመለከቱ አለም አቀፍና አሕጉራዊ ስምምነቶችን የተቀበለች በመሆኑ በስራ ላይ ያሉትን የስነ ስርአትና የማስረጃ ህጎቻችንና አሰራራችን ከእነዚሁ ስምምነቶች አንጻር መቃኘት ይገባል፡፡

የህገ መንገስቱ ግቦች የሆኑት የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ እና ዘላቂ ሰላምና ልማትን ማምጣት ሊሳኩ የሚችሉት የሃገር፣ የሕዝብና የግለሰቦች ሰላምንና ደህንነት ሲጠበቅ በመሆኑ መንግስት በዚህ ሜኩ የሚለፁትንና መሠረታዊ የሆኑትን የግለሰብና የቡድን መብት እና ጥቅም የማሟት፣ የማክበርና የማስከበር ግንባር ቀደም ኃላፊነት ተጥሎብታል፡፡ በዚህ ረገድ መንግስት ኃላፊነቱን ለመወጣት በቅድሚያ እና በዋነኛነት መከናወን ከሚገባቸውተግባራ ወስጥ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ እ.ኢ.አ በ2003 ዓ.ም ያወጣ ሲሆን በ1949 የወጣዉ

የወንጀል ሕግ የተካወን የወንጀል ሕግንም በ1997 በስራ ላይ አውሏል፡፡ ይህ የወንጀል ሕግ ስነ ስርአትና የማስረጃ ሕግምየዚሁ ጥረት አካል ተደርጎ ማውጣት ያስፈልጋል፡፡

የወንጀል ህግ ሥነ ሥርዐት እና የማስረጃ ሕግ ሲደነገግ በማሰረቱ በሁለት ትላልቅ ጎራዎች ወስጥ የሚታዩ የተለያዩ ጥቅሞችንና ፍላጎቶችን በማመዛዘንና ግምት ወስጥ በማስገባት ነው፡፡ በአንድ በኩል የህብረተሰቡን ሰላምና ደህንነት ለማጠበቅና ለማስጠበቅ የወንጀል ድርጊት ፈፃሚዎችን ለፍርድ አቅርቦ ተገቢወን ቅጣት እንዲያገኙ ማድረግ የሚያስፈልግ ሲሆን በሌላ በኩል እውነቱን ለይቶ በማውጣት አጥፊወን በትክክል ለይቶ በማወጣት አጥፊዎቹ ብቻ ተመጣጣኝ ቅጣት እንዲቀጡለማድረግ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ እነዚህን በሁለት ጎራ ስር የሚታቀፉ ልዩ ልዩ ፍላጎቶችን አጣጥሞ የወንጀል ሕጉን ትርጉም ባለው ሜኬኩ ለማስፈፀም የሚያስችል ወጤታማ፣ ቀልጣፋ፣ ዘመናዊ፣ ወጪቆጣቢ፣ ተደራሽ እና ከፍተኛ የሕዝብ አመኔታ ያለው አሠራር ሊዘረጋ ይገባል፡፡ ወንጀል ተፈፅሞ ሲገኝ ወንጀሉ በማን፣ እንዴት፣ መቼ ወዘተ እንደተፈፀመ ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ማስረጃዎች የሚሰበሰቡበት፣ ለፍርድ ቤት የሚቀርቡበት እንዲሁም የማስረጃዎቹ ዓይነት፣ ክብደት እና ብቃት በአግባቡ የሚመዘኑበት ወጤታማ የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ ያስፈልጋል፡፡

ኢትዮጵያ ከ1940ዎቹ ወዲህ የተለያዩ የወንጀል ሕጎችን በመደንገግ እና የተለያዩ የፍትሕ ተቋማትን በማቋቋም ዘመናዊ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሥርአትን እየገነባች ያለች አገር ናት፡፡ በ1940ዎቹ ከተደነገጉ ሕጎች መካከል በ1949 ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫሕግ እና ይህንን ሕግ ለማስፈፀም በ1954 ዓ.ም የተደነገገው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዐት ሕግ በዋናነት ከሚጠቀሱት ወስጥ የሚገኙ ሲሆኑ እነዚህን ሕጎች ጨምሮ በሌሎች የፍሬ እና የሥነ ሥርዐት ሕጎች ወስጥ በተለያዩ ክፍሎችና ድንጋጌዎች የተካተቱ ዘመናዊ የማስረጃ ሕግ መርሆዎችና ሥርዓቶችም ተጠቃሽ ናቸው፡፡

በ1949 ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫሕግ አሁን ከደረስንበት ዘመን አዳዲስ አስተሳሰቦች፣ የቴክኖሎጂ ዕድገቶችና የሰብዓዊ መብት አጠባበቅ ፅንሰ ሃሳቦች ጋር የሚጣጣም ሆኖ ባለመገኘቱ በ1997ቱ የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ ተሽሯል፡፡ በአንፃሩ የወንጀለኛ መቅጫሕግ ሥነ ሥርዐት እና በሌሎች ሕጎቹ ወስጥ ተበታትነው የሚገኙ የማስረጃ ሕጎች እንደ የፀረ ሙስና፣ የጉሙሩክ እና የፀረ ሽብርተኝነት ወንጀሎችን አስሜኬቶ ከተደረጉ ለወጦች በስተቀር ላለፉት ግማሽ ምዕተ ዓመታት መሠረታዊ ማሻሻያ ሳይደረግበት እየተሰራበት ይገኛል፡፡ በመሆኑም የወንጀለኛ መቅጫሕግ ሥነሥርአት ሕግና በተለያዩ ቦታዎች ተካተው የሚገኙ የማስረጃ ድንጋጌዎች አሁን ዘመኑ ከደረሰበት አስተሳሰብ እና መርሆዎች ጋር ማጣጣም ያስፈልጋል፡፡

አሁን ባለንበት ዘመን ወንጀሎች (በተለይም እንደ ሽብርተኝነት፣ የኢኮኖሚ ወንጀሎች፣ በተደራጁ ቡድኖች የሚፈፀሙ ወንጀሎች) አለም አቀፍ ገፅታን እየያዙ በአይነታቸው፣ በብዛታቸው እና በአፈፃፀማቸው እየተወሳሰቡና በየጊዜውም ስልታቸውን እየቀያየሩ የሚፈፀሙ ሆነዋል፡፡ ከዚህ እድገት ጋር ለማጣጣም ታልሞም የ1949ኙ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በ1997ቱ የወንጀል ሕግ የተተካ ቢሆንም የወንጀል ሕጉን አላማ ግብ በተሟላ ሁኔታ ለማስፈፀም የሚያስችል የሥነ ሥርአት ሕግ ያልወጣ በመሆኑ የወንጀል ፍትሕ ስርአቱ የተሟላ ሊሆን አልቻለም፡፡ ይህ በመሆኑም የመንግስት ተቋማት በሚቋቋሙበት ሕግ ወስጥ እንዲሁም ስነ ስርአትና ማስረጃ ነክ ባልሆኑ የወንጀል ሕጎች ወስጥ በርካታ የስነ ስርአትና ማስረጃ ድንጋጌዎች እየተካተቱ እንዲወጡ ሆኗል፡፡ ይህም በመሰረቱ በፍሬ ሕግና በስነ ስርአትና ማስረጃ ህግ መካከል በከፍተኛ ደረጃ መደበላለቅን የፈጠረና የፍትህ ሥርአቱን ቅርጽ ያዛባ የህግ አወጣጥ እንዲሰፍን አድርጓል፡፡

በሌላም በኩል በስራ ላይ ያለው የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ በበርካታ ጉዳዮች ላይ ግልፅነት የጎደለው፣ በዘመኑ ከሚፈጸሙት ውስብስብና የረቀቁ ወንጀሎች አንጻር እንዲሁም ዘመኑ ከደረሰበት የወንጀል ሳይንስ ጋር ሲታይ ከዘመኑ ጋር የማይሄዱ በርካታ ድንጋጌዎች የተካተቱበትና መሰረታዊ ክፍተት ያለበት ነው፡፡ ዘመኑ በዚህ መስኩ ቀድሞ ከመሄዱም በላይ የወንጀል ጉዳይ ሕብረተሰቡ ባዳበረው የረጅም ጊዜ ልምድም አንጻር እየታየ ጎን ለጎን በባህላዊ ስርአቶች የሚፈታበት አግባብም በዛውልክ አቅፎ የሚጓዝ ቢሆንም ይህም ስርአት ቢሆን በስነ ስርአትና ማስረጃ ህግ ወስጥ በአግባቡ የተካተተ አይደለም፡፡ ይህ በመሆኑም በሳራ ላይ ያለው የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ በዘመናዊም ሆነ በባህላዊ አግባብ የሚታዩ እድገቶችን እና ተግባሮችን አሟልቶ ያልያዘ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉን ከሕገ መንግስቱ፣ አለም አቀፍ ድንጋጌዎች እንዲሁም አለም አቀፍ ተቀባይነት ካላቸው የዘመኑ አሰራሮች ጋር በማጣጣም ማሻሻል ይስፈልጋል፡፡

የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉን ለማሻሻል የሚያስችለው ረቂቅ ከመዘጋጀቱ በፊት በመስኩ የሚታዩ ችግሮች ለዚሁ በተቋቋመ አጥኚ ቡድን የተለዩ ከመሆናቸውም በላይ ችግሮቹ በወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው፣ በፍትሕ አካላት የአሰራር ለውጥ ጥናት እንዲሁም በተግባር በየጊዜው የሚስተዋሉ ችግሮች ለመሆናቸው የተረጋገጡ ናቸው፡፡ በተለይ ጎልተው ከታዩት ችግሮች ወስጥም የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

የመጀመሪያው ችግር የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ በወንጀል ስነ ስርአትና ማስረጃ ጉዳይ ላይ የተሟላ የህግ ማዕቀፍ የሌለው መሆኑን ይመለከታል፡፡ ይህም ሕገ መንግሥቱ ከፀደቀ በኋላ በሥራ ላይ

የዋለውን የወንጀል ሕግ አሟላቶ የሚያስፈጽም የተሟላ የወንጀል ሥነ ሥርዐት ሕግ ካለመኖሩ ጋር የሚያያዝ ሲሆን መፍትሔውም በዚሁ አግባብ የሚታይ ነው፡፡ ይህን ዘርፈ ብዙ ክፍተት ለማየት ለዚሁ ተግባር የተቋቋመው አጥኚ ቡድን በቅድመረቂቅ ጥናቱ በግብአትነት ከተጠቀማቸው ሰነዶች መካከል የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት፣ በስራ ላይ ያለው የ1954ቱን የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዐት ሕግ፣ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ፤ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲን ለማርቀቅ ጥቅም ላይ የዋሉ ሰነዶች፣ በፌዴራል መንግሥት የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር አካላት አሰራርን ለማሻሻል የተሰራ የጥናት ሰነድ፣ በክልል ፍትሕ አካላት የወንጀል ፍትሕ ሂደቱን አስመልክቶ የተዘጋጀ መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ የጥናት ሰነዶች፣ ከተለያዩ ፍትሕ አካላትና የሕግ ባለሞያዎች የተሰበሰቡ የናሙና መረጃዎች፣ ለጥናቱ መዳበር አስተዋፅኦ ያደርጋሉ ተብሎ የታመነባቸው ከተለያዩ ምንጮች የተገኙ የተለያዩ መጣጥፎችና የፍርድ ቤት ውሳኔዎች እንዲሁም የሌሎች ሃገሮች ህጎችና ልምዶች እና ሌሎች ሰነዶች እንደማጣቀሻ ተወስደው ህጉን ለማርቀቅ አገልግለዋል፡፡ በዚህ የቅድመ ረቂቅ ጥናት የወንጀል ሥነ ሥርዐት ሕግ ውስጥ የሚታዩ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን የተተነተኑ ሲሆን የተለዩት ችግሮችና የችግሮቹ ጥልቀት የ1954ቱን የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዐት ሕግን በማጠነኛ ማሻሻያና ጥገና ከማስቀጠል ይልቅ በመሰረቱ ሙሉ በሙሉ ሊሻሻል እንደሚገባው ድምዳሜላይ አድርሰዋል፡፡

በዚህ መልክ የተለዩትን ችግሮች የሚፈታ እንዲሁም ወረድ ብሎ እንደሚመለከተው የወንጀል ማስረጃ ሕግን ያካተተ ረቂቅ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ እንዲያዘጋጅ በፍትሕ ስርአት ማሻሻያ ቦርድ በተወሰነው መሰረት ወንጀልን የሚመለከቱ የማስረጃ ድንጋጌዎችን አጠቃልሎ የያዘ የወንጀል ሥነ ሥርዐት ሕግ የመጀመሪያ ረቂቅ ተዘጋጅቷል፡፡ በዚህ መሰረት የተዘጋጀውና 600 አንቀጾች ያሉትን የመጀመሪያ የወንጀል ሥነ ሥርዐት ረቂቅ ሕግ በተለያዩ መድረኮች ለማስተዋወቅ የተሞከረ ሲሆን በችግር ከተለዩት ጉዳዮች ውስጥ ለረቂቁ መነሻ የሚሆን የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ ያልነበረ በመሆኑ ረቂቁ በወቅቱ የተነሱ በርካታ ፖሊሲ ነክ ጥያቄዎችን መመለስ አልቻለም፡፡ ረቂቁ ሃገር አቀፍ ተፈፃሚነትን ታሳቢ አድርጎ የተዘጋጀ ስለነበር የወንጀል ሥነ ሥርዐት ሕግን የመውጣት ሥልጣን በክልል ሥር መሆን አለበት ወይስ በፌዴራል የሚሉ አስተያየቶች በመኖራቸው ይህንን ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችል የፖሊሲ አቅጣጫ አልነበረም፡፡ የፍትሕ ሥርዐት ማሻሻያ ቦርድ ይህንን ጥያቄ ተመልክቶ የተዘጋጀው ረቂቅ ተፈፃሚነት በፌዴራል ሥልጣን ሥር እንዲሆን በማሰብ በሰጠው አቅጣጫ መሰረት ከቦርዱ የተውጣጣው የሕግ ባለሞያ ቡድን የመጀመሪያውን ረቂቅ በመከለስ በፌደራል ስልጣን ስር የሚፈጸም 409 አንቀፆች ያለው ሁለተኛ የስነ ስርአትና ማስረጃ ረቂቅ ያዘጋጀ ቢሆንም ይህም ረቂቅ በተመሳሳይ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ በሌለበት የተዘጋጁ በመሆኑ ተመሳሳይ እና ሌሎች በአሁኑ ረቂቅ የተካተቱ የፖሊሲ ጉዳዮችን

በአግባቡ ለመጣስ አልቻለም፡፡ በመሆኑም በወንጀል ስነ ስርአትና ማስረጃ ጉዳይ ላይ አገሪቱ የምትመራበት ፖሊሲ የግድ የሚያስፈልግ ለመሆኑ ሂደቶች አረጋግጠዋል፡፡

## 1.2. የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ

ከፍ ሲል እንደተመላከተው ቀደም ብለው የተዘጋጁት ረቂቆች በማስረቱ በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር የመንግሥትን አቋምና የመፍትሔ አቅጣጫ የሚያሳይ መነሻ ሰነድን ማስረት ያደረጉ ባለመሆናቸው ፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ሚሉስ የሚሰጡ አልነበሩም፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ አጽድቆ በስራ ላይ ማዋል ችግሩን ሊቀርፍ የሚችል በመሆኑ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ የካቲት 25 ቀን 2003 ዓ.ም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፀድቆ በስራ ላይ ወሏል፡፡ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው በኢትዮጵያ የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ወስጥ የታዩ አንኳር አንኳር ችግሮችን ግምት ወስጥ በማስገባት ለችግሮቹ አጠቃላይ የሆነ የመፍትሔ አቅጣጫና የመንግሥትን አቋም አመላክቷል፡፡ ፖሊሲው ለሚወጡ የወንጀል ህጎች ተፈፃሚ የሚሆኑ አግባብ ያላቸውን መርሆዎች፣ ድንጋጌዎችና እና እሴቶችን አካቶም ይዟል፡፡ በተለይ የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ችግሮችን በማለት በወንጀል ፍትሕ ስርአቱ ወስጥ አዲስ ለሚወጡ ሕጎች ማስረት የሚሆኑ አቅጣጫዎችንም ያስቀመጠ ነው፡፡

የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው ያካተታቸውን በርካታና ዘመናዊ አስተሳሰቦች እንዲሁም በለውጥ ስራዎች የተለዩ የተሻሉ አሰራሮችን ተግባራዊ ከሚድረግ አንጻር በስራ ላይ ያለው የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ በርካታ ርቀቶች የሚቃሩት መሆኑን ፖሊሲው በድጋሚ አመላክቷል፡፡ በነዚህ አግባቦች ከተለዩት ችግሮች ወስጥም፤

- ✓ ነባር የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጎች ግልጽ አቅጣጫ ያልያዙ መሆናቸው፤
- ✓ ሕጎችን በስራ ላይ ለማዋል የሚያግዝ አላማ እና መርህ ያልነበራቸው መሆኑ፣
- ✓ በፍትሕ አካላት መካከል የየተቋማቱን ልዩ ባህሪ ባናዘበና በመርህ ላይ የተመሰረተ ግልጽ የሆነ የአሠራር፣ የግንኙነት እና የአመራር ትስስር አለመኖሩ፣
- ✓ በከፊልም ሕጎቹ ከፈጠሩት ክፍተት በመነሳት በፍትሕ አካላት ወስጥ የሚገኙ የሕግ ባለሙያዎች የእውቀት፣ ተግባራቸውን በተመለከተ የአመለካከት፣ የሥነ ምግባርና የክህሎት ማነስ ችግር ያለባቸው መሆኑ፣
- ✓ ሕብረተሰቡን በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ወስጥ በበቂ ሁኔታ እንዲሳተፍ የሚያደርጉ መሆናቸው፤ በዚህም መደበኛውን የፍትሕ አስተዳር ውጤታማ ከሚድረግ አንጻር ከሕብረተሰቡ

ተሳትፎ ሊገኝ የሚቻለውን ከፍተኛ ጥቅም ማግኘት ያልተቻለ መሆኑና ሕዝቡ በፍትሕ ሥርዐቱ ላይ ያለው እርካታና አመኔታ እንዲቀንስ ያደረጉ መሆናቸው፣

የሚሉት ይገኙበታል፡፡ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው በወንጀል መከላከል፣ በወንጀል ምርመራ፣ በዐቃቤ ሕግ አገልግሎት፣ በፍርድ አሰጣጥ ሂደት፣ በውሳኔ ማስፈጸም እና በአለም ዓቀፍ ጉዳዮች ለታዩ ችግሮች መፍትሔ ያመላከተ ሲሆን ከተለዩት ችግሮችም አንጻር የአገሪቱን ፍላጎት አመላክቷል፡፡ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲውከዚህ ቀደም ያልነበረ ከመሆኑም በላይ የኢትዮጵያን የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ሚሉዕ ለማንባት እና ለማቋቋም የሃገራችንን ተጨባጭሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት የዘመኑን አዳዲስ ሃሳቦችንና ፍልስፍናዎችን ማካተት እንደሚገባ ዝርዝሩ ያመላክታል፡፡ ቀደም ብለው ይነሱ ለነበሩ የፖሊሲ ጥያቄዎች ምላሽ እና አቅጣጫየሰጠ በመሆኑ ለስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ በግብአትነት አገልግሏል፡፡

ይህንን ፖሊሲ በአግባቡ ሥራ ላይ ለማዋል ለለወጡአስፈላጊ የሆኑ በሥራ ላይ ያሉ ሕችንን ማሻሻልና ከፖሊሲው አቅጣጫጋር ማጣጣም የግድ አስፈላጊ ነው፡፡ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲውበየደረጃውመሻሻል ይገባቸዋል ካላቸው ዝርዝር የፍትሕችግሮች ውስጥ አብዛኛዎቹ በወንጀል ሥነ ሥርዐት እና የማስረጃ ሕጉ ውስጥ መካተት የሚገባቸው ናቸው፡፡

## 1.3. ረቂቆችን የመከለስና ድጋሚየማርቀቅ ሥራን የማከናወን ሂደት

የኢፌዴሪ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲን መጽደቅ ተከትሎ ከፍ ሲል የተጠቀሱትን ረቂቆች እንደገና መፈተሽና አስተካክሎ ማርቀቅ የግድነበር፡፡ ከዚህ አንፃር ፖሊሲውቀደም ሲል ይነሱ ከነበሩ የፖሊሲ ጥያቄዎች ወስጥ ለበርካቶቹ ምላሽ የሰጠበመሆኑና የሃገሪቱን የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ አቅጣጫያመላካተ በመሆኑ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲወን መሠረት ያደረገና የአፈፃፀም ወሰኑምአገር አቀፍ ተፈፃሚ ት ያለውየወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዐት ማውጣትና መከለስ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህንንም ተከትሎ የፍትሕ አካላቱን መፍትሔየሚሹ ችግሮችን ከሁሉም አቅጣጫ መሚለከተ እንዲቻልም ከተለያዩ የፍትሕ አካላትና እና የሕግ ትምሕርት ቤት የተወጣጡ የሕግ ባለሞያዎችን ያካተተ አርቃቂ ቡድን የተደራጀ ሲሆን አርቃቂ ቡድኑም የቀደሙረቂቆቹን በመከለስ በድጋሚ የማርቀቅ ሥራውን አከናወኗል፡፡ ተግባሩንምየፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ እንዲከታተልና እንዲቆጣጠር ተደርጓል፡፡ አርቃቂ ቡድኑምቀደም ብለውየተዘጋጁትን ረቂቆቹን በሙሉ ከማገናዘቡምበላይ፤

- የሕገ መንግሥቱን መሠረታዊ መብቶችና ድንጋጌዎች፣
- የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲውዝርዝርና አጠቃላይ አቅጣጫ

- የ1996 ዓ.ም የወንጀል ሕግ፣
- በፍትሕ አካላት ለወንጀል የፍትሕ ስርአት አስተዳደር መሻሻል ይረዳሉ ተብለው የተጡ ተጨማሪ ትናችን እና ልዩ ልዩ ጽሁፎችን፣
- በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የፌዴራል ሰበር ሰሚችሎት የሰጣቸወን የሕግ ትርጉሞች፣

በመሜልከት ረቂቁን ከማዘጋጀቱም በተጨማሪ ከዚሕ በላይ በተመለከቱት ጉዳዮች ያልተካተቱ ችግሮችን በማየት፣ የወጪተሞክሮዎችን በመቀመር፣ ሕግ ሊወጣላቸው የሚገባቸወን ጉዳዮች በማዘርዘር፣ በሥነ ሥርዐት ሕጉ ወይም ሌላ ሕግ መካተት ያለባቸወን የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ ጉዳዮች በማየት፣ ሕጉ ሃገራዊ ተፈፃሚነት እንዲኖረው የክልሎችን ጉዳይ በማካተት እንዲሁም በወንጀል ሥነ ሥርዐት ሕግ የጋራ አቋም ሊያዝባቸው የሚገባ ጭብጦችን በማየትና ከተለያዩ መድረኮች ግብአቶችን በማሰብሰብ ሕጉ ተረቋል፡፡

ከፍ ሲል የተመለከቱትን የሃገራችን የወንጀል ፍትሕ አስተዳር ችግሮችን መቅረፍም የሚቻለው ወንጀልን የሚመለከቱ የማስረጃ ድንጋጌዎች በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዐቱ ወስጥ አካቶ በመደንገግም ጭምር በመሆኑ የማስረጃ ድንጋጌዎች ላይ ልዩ ትኩረት በማድረግ ከሥነ ሥርዐቱ ጋር የማዋሀድና የማደራጀት ሥራ ተከናወኗል፡፡ በተጨማሪም በወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው የተካተቱትንና የሕግ እና የአፈፃጸም ክፍተትን ለማየት የሚረዱ እንደ የአለም ዓቀፍ ግንኙነት ጉዳዮች፣ አሳልፎ ማስጠት ሂደት (Extradition)፣ የጋራ የሕግ ጉዳዮች ትብብር (Mutual legal assistance) እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ጥናት በማካሔድ በሕጉ እንዲካተት ሆኗል፡፡

## 2. የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዐት ሕግ ለማርቀቅ የተለዩ ተጨማሪ ችግሮች፤

በኢትዮጵያ የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ወስጥ የተስተዋሉ ዋና ዋና ችግሮች፣ የችግሮቹ መንስዔዎች እና መፍትሄዎች በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዐት ሕግ ቅድመ ረቂቅ ጥናት በሰፊው ተመልክተዋል፡፡ ከወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዐት ጋር ተያይዘው ያሉ ችግሮች እጅግ በርካታ መሆናቸው በተመሳሳይ ተለይቷል፡፡ በዚህ መሠረት ሕጉ ወስጥ የሚስተዋሉ የሕግ እና የአሠራር ክፍተቶችን፣ የሕጉ ድንጋጌዎች ግልፅነት ማጣደል፣ አገሪቱ እንዲሁም አለም አሁን ከደረሰበት የዕድገት ደረጃ አንጻር ያልተጣጣመ የሥነ ሥርዐት ሕግ ይዘቶች፣ መካተት የሚገባቸው አዳዲስ አስተሳሰቦች ካለመካተታቸው ጋር ተያይዞ የተነሣ በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ላይ ያስከተለው ችግር ሲሆኑ በጥናት እና በወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው የተመለከቱ አጠቃላይ ችግሮችን ሲሆኑ እንደሚከተለው በጥቅሉ ተመልክተዋል፡፡

## 2.1 የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ችግሮች

የወንጀለኛ መቅጫሕግ ሥነ ሥርዐት፣ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ በመሆኑ በሕገ-መንግሥቱ እና በወንጀል ሕጉ የተደነገጉ ድንጋጌዎች ለማስፈጸም የሚወጣ ሕግ ነው፡፡ ሕጉ ራሱን ችሎ አዋጅ ሆኖ ቢወጣም ዓላማው እና ግቡ በሕገ-መንግሥቱ እና በወንጀል ሕጉ ወስጥ የተቀመጡትን ዓላማዎች እና ግቦች ለማስፈጸም የሚወጣ ነው፡፡ ለግማሽ ምዕተ ዓመት ሲያገለግል የነበረው የወንጀለኛ መቅጫሕግ በ1997 ዓ.ም የተሻረ ቢሆንም የተሻረውን የወንጀለኛ መቅጫሕግ ተከትሎ የወጣው የ1954 የወንጀለኛ መቅጫሕግ ግን ሕገ መንግስቱም ሆነ የወንጀል ሕጉ ከደረሰበት ደረጃ እንዲሁም አለም ከደረሰበት ደረጃ ጋር በሚጣጣም መልኩ ሳይሻሻል ቆይቷል፡፡ በመሆኑም በሕግ ማስረት ወጤታማና ፍትሃዊ የፍትሕ አገልግሎት ለማስጠት የሚደረግ ጥረት ላይ ቀላል የማይባሉ ችግሮችን አስከትሏል፡፡ ከዚህም አንጻር በተለይም የወንጀል ፍትሕ አስተዳደሩ ያጋጠሙት ችግሮች ሲጠቃለሉ፤

- ✓ የስነ ስርአትና ማስረጃሕጉ ሕገ-መንግሥቱን እና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን ተቋማዊ በሆነ ው አግባብ ማገልገል አለመቻሉ፣ በፌዴራልም ሆነ በክልል እየተሰሩ ላሉት የማሻሻያ ለውጥ ስራዎች በቂ የህግ ማእቀፍ ሆኖ በማገልገል የለውጡን ወጤታማነት ቀጣይነት ለማረጋገጥ በሚያስችል ደረጃ ላይ አለመገኘቱ፣
- ✓ የሕዝብ ጥቅሞች እና ፍላጎቶች በበቂ ሁኔታ የሚረጋገጡበትና የሚከበሩበት የሕግ ማዕቀፍ ሆኖ ለማገልገል አለመቻሉ፣
- ✓ በአሁኑ ሰአት እየተወሳሰቡ የመጡትን ወንጀሎችና አፈፃጸማቸውን ለመከታተልም ሆነ ተፈጽመው በተገኙ ጊዜ መርምሮ እውነቱን ለማውጣት የሚያስችል የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ አለመሆኑ፣
- ✓ ከወንጀል ፍትሕ ሂደቱ የሚገኙ ወጤቶች የሕብረተሰቡን ሰላም እና ደህንነት በበቂ ሁኔታ ለማረጋገጥ የሚያስችል የሕግ ሥርዓት ለመፍጠር አለመቻሉ፣
- ✓ የሚፈጸሙየተለያዩ ወንጀሎችን አስመልክቶ በማስረጃ በማረጋገጥ እውነቱን አንጥሮ ለማውጣት የሚያስችል የወንጀል ፍትህ ስርአት ከመገንባት አንጻር የስነስርአት ህጉ ያለው ሚና ከሚጠበቅበት በታች መሆኑ፣
- ✓ የሕብረተሰቡን ተሳትፎ በተገቢውሁኔታ የሚያረጋግጥ አለመሆኑ፣
- ✓ የወንጀል ተጎጂዎችን በፍትሕ ሂደቱ የሚሳተፉበትን አግባብ በአግባቡ የሚያስችል አለመሆኑ፣

- ✓ አገሪቱ በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ዘርፍ ከዓለም አቀፍ ሕግጋት እና የአሠራር ሥርዓት አንጻር ያሏትን መብቶች ለማስከበርና የተጣሉባትን ግዴታዎች ለመወጣት የሚያስችል የህግ ማእቀፍ አለመሆኑ፣
- ✓ የሰዎችን ሰብዓዊ መብቶችና ነጻነቶች በተሟላ ሁኔታ ለማክበር እና ለማስከበር የሚያስችል የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ከመፍጠር አንጻር የወንጀል ሥነ ሥርዐት ሕጉ መጫወት ያለበትን ሚና በሚፈለገው ደረጃ አለመወጣቱ
- ✓ አለማቀፍ ትብብርን በተመለከተ እንደሀገር የምንመራበት ስርአት አለመኖሩ፣
- ✓ አማራጭየመፍትሄ እርምጃዎች፣ ባህለዊ ስርአቶችና ሌሎች መፍትሄዎችን አስመልክቶ ስርአት ያለተበጀ በመሆኑ የብሄሮች ብሄሮችና ህዝቦችን ባህላዊ ስርአቶች ተግባራዊ ማድረግ አለመቻሉ የሚሉት እና ሌሎች ማሳል ጉዳዮች

ዋና ዋና ተጠቃሽ ችግሮች ናቸው፡፡ እነዚህን እና ተያያዥ ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ የሚያስፈልግ በመሆኑ በስራ ላይ ያለውን የስነ ስርአትሕግ በሚከተለው ሁኔታ ያሻሻለና የሚከተሉትን ዋና ዋና ነጥቦች ያካተተ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ ተዘጋጅቷል፡፡

## 3. መግቢያና ጠቅላላ ጉዳዮች

የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ **በአስር መጽሃፎች የተከፋፈለ ሆኖ 444 አንቀጾችን** ያካተተ ነው፡፡ ሕጉ የተደራጀውሁሉንም የፍትሕ አካላት በወልና በጋራ ከሚመለከቱ ጉዳዮች አንስቶ የወንጀል ፍትሕ ሐደቱን የሥራ ፍሰት ተከትሎ ነው፡፡ ሕጉ አዳዲስ ጉዳዮችን ያካተተ ከመሆኑም በላይ አጠቃላይ የወንጀል ፍትሕ አስተዳደሩ የሚመራበትንና ሕጉ የሚተረጎምበትን መንገድ በማመልከት ነውየሚጀምረው፡፡ ይህም በስራ ላይ በነበረው ሕግ ወስጥ ያልነበረ ሲሆን የአሁኑ ረቂቅ የሕጉ አካል በሆነው በመግቢያው ክፍል የሕጉን አላማ በግልጽ አስቀምጧል፡፡

የቀድሞውየሥነ ስርአት ሕግ መግቢያ ያልነበረውበመሆኑ ሕጉን ለመተርጎምአጋዥሊሆን የሚችል ትልቅ ማሳሪያ ጎድሎት ቆይቷል፡፡ የፍትህ አካላት በወንጀል ጉዳይ ላይ በምን ማስመር ህጎቹን መተርጎም እንዳለባቸው ለተለያዩ አላማዎች ከተጻፉ የተለያዩ መጣጥፎች ለሚረዳት ከማማከራቸውበስተቀር የስነ ስርአት ሕጉን አላማ በግልጽ ሳይረዱ ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ በመሆኑምነባሩ የስነ ስርአት ሕግ የነበረበትን ክፍተት እና የግልጸኝት

ችግር በመቅረፍ በሕግ አወጣጥ ስርአታችን በበርካታ ሕጎቻችን ወስጥ እንደምናገኘው ይህ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ ግልጽ የሆነ መግቢያን እንዲያካትት ሆኗል፡፡ ይህ መግቢያ በዋነኛነት ሕጉ ለምን፣ በማንና በምን ስልጣን እንደወጣ የተመለከተበት ነው፡፡ ሕጉን ለማውጣት አስፈላጊ ከሆኑት ምክንያቶች ወስጥም ከፍ ሲል የተዘረዘሩት የፍትሕ አስተዳደር ችግሮችን በመቅረፍ በሕገ መንግስቱ የተመለከቱትን የሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶችን አሟልቶ ተግባራዊ ለማድረግ በስራ ላይ ያለውስነ ስርአትህግ ያልቻለና የማይችል መሆኑ፣ አገራችን ያፀደቀቻቸውን፣ የገባችባቸውንና የምትገባባቸውን አለም አቀፍ ስምምነቶች (እንዲሁም የሁለትዮሽ እና ባለ ብዙ ሃገራት ስምምነቶች) እና መርሆዎች በተሟላ ሁኔታ መተግበር የሚገባ በመሆኑ፣ በዚህ ረገድ በግንኙነቱ አለም አቀፍ ግዴታን በአግባቡ ለመወጣትና በዚህ ረገድ የሚኖሩ ጥቅሞችንና መብቶችን በአግባቡ ማግኘትና ማስከበር በማስፈለጉ፣ እየበዙና እየተወሳሰቡ የመጡትን ወንጀሎች ወጤታማ ባለው ሁኔታ በመመርመር እወነቱ ላይ መድረስ የሚያስፈልግ በመሆኑ፣ ሕብረተሰቡን በወንጀል ፍትሕ ስርአቱ ወስጥ ማሳተፍ የሚያስፈልግ በመሆኑ እንዲሁም ተበታትነው የሚገኙ ልዩ ልዩ የስነ ስርአትና ማስረጃ ህጎችን አጠቃሎ በመፅሃፍ መልክ በማውጣት ለአጠቃቀም የተመቸና ይበልጥ ግልፅ የሆነ ሕግ እንዲሆን ለማድረግ በማለም የወጣ እንደሆነ መግቢያው በግልጽ ያመለክታል፡፡ የወንጀል ሂደቱን ወጤታማነት እና ፍትሓዊነት ማረጋገጥ በተለይ በእለት ተእለት የፍትሕ አካላት ሊተገበሩ የሚገባቸው እሴቶች ናቸው፡፡ መግቢያው በሕጉ አላማ ወስጥ አጠር ብሎ የተቀመጠ ቢሆንም ሕጉን በቀጥታ ለሚፈፅምም ሆነ ተርጉሞ ለሚፈፅም አይነተኛ የአፈፃፀምና የትርጉም መሳሪያ በመሆን ያገግላል ተብሎ ይታሰባል፡፡

የሕጉ መግቢያ የሕጉ አላማ የወንጀል ፍትሕ አስተዳደሩን ወጤታማት ማረጋገጥ ነው ሲል ወጤታማነት የተደራሽነት፣ ቅልጥፍና፣ ግልጽነት፣ ነጻነት እና ተጠያቂነት ድምር ወጤት መሆኑን በመወሰድ ነው፡፡ በተመሳሳይም የፍትሓዊነት አላማ በፍትሕ ሂደት ወስጥ የሚያልፉ ተከራካሪ ወገኖች እኩል፣ ለአንዱ ወገን ብቻ ያላደላ በፍትህ ሂደት ወስጥ የሚያልፉ ወገኖች ሁሉ በህግ ላይ የተመሰረተ ትክክለኛና ሚዛናዊ እድል ማግኘት ያለባቸውመሆኑን የሚያሰምር እሴት ነው፡፡

የሥነ ስርአት ሕጉን የፌዴራል መንግስቱ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 55(5) መሰረት የወንጀል ህግን ለማውጣት በተሰጠውስልጣን መሰረት፣ በሕገ መንግሰቱ አንቀፅ 55(1) ስር የተመለከቱትን የኢኮኖሚ፣ ፖለቲካ፣ ንግድ፣ ፀጥታ፣ አለም አቀፍ ወዘተ ጉዳዮችን ለማስፈፀም የሚያስችል ሕግ ለማውጣት እንዲችል እንዲሁም የፌዴራል መንግስቱ ያወጣውን ሕግ የማስፈጸም ኃላፊነት የፌዴራል መንግስቱ ከመሆኑ የተነሳ ለፌዴራል መንግሰቱ በተሰጠውስልጣን መሰረት የወጣ መሆኑም በመግቢያውላይ ተመልክቷል፡፡

## 4. ስያሜው

የህጉ ስያሜየስነ ስርአትጉዳይንና የማስረጃ ጉዳይን ማካተቱን በሚያመላክት አግባብ የተቀረጹ ሁለት ሀረጎች ያሉት ነው፡፡ ስያሜው በወንጀል ስነ ስርአትና ማስረጃ ጉዳይ ላይ የሚይታለፉ ሁለት ጉልህ ጉዳዮች በህጉ ውስጥ መካተታቸውን በቀጥታ እና በግልጽ ያመላክታል፡፡ ሕጉ አንድ ወንጀል ተፈፀመ ከተባለበት ጊዜ አንስቶ ወንጀል አድራጊው በምርመራ የሚለይበት፣ ለፍትሕ ሂደት የሚቀርብበት እና አጥፊው በአግባቡ ታርሞ ሕብረተሰቡ ጋር የሚቀላቀልባቸውን ሂደቶች እና ስርአቶች አሟልቶ የያዘ በመሆኑ እና በስራ ላይ ያሉትን የወንጀል ህጎች ለማስፈፀም የሚያገለግል በመሆኑ የወንጀል ህግ ስነ ስርአትና ማስረጃ የሚል ስያሜን አካቷል፡፡ በሌላ መልኩ በወንጀል ፍትህ አስተዳር ስነ-ስርአት ውስጥ ከምርመራ እስከ ውሳኔ አሰጣጥ ያለው ሂደት ያለ ማስረጃ ሊከናወን የሚችል አይደለም፡፡ በሒደቱ ሁሉ ማስረጃ ምን እንደሆነ፣ ማን ሊሰበስበው እንደሚችልና እንደሚገባ፣ በየደረጃው የሚፈለገው የማስረጃ አይነትና መጠን ምን መምሰል እንዳበት ካልተመላከተ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ የተሟላ ሊሆን አይችልም፡፡ የማስረጃ ደንቦቹ የስነ ስርአትሕጉ አካል ሆነው መውጣታቸው የወንጀል ጉዳዮች ከወንጀል ሕጎች ጋር በቀላሉ እንዲዋሃዱ ስለሚያደርግ፣ በወንጀል ጉዳይ ላይ በተቻለ መጠን የወንጀልን ጉዳይ ያጠቃለለ መፅሐፍ እንዲኖር ስለሚያስችል፣ ሕጎቹን በወጥነት ለመፈፀም ወይም ለመተርጎም ስለሚያግዝ የሌሎች ሃገራትን ልምድም በመመልከት ከስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ጋር ተጣቃሎ የወጣ በመሆኑ ስያሜውም ማሟላት ይገባዋል፡፡ በዚህ መሰረት ዋናው ርእስ የሕጉን አወጪ የሚፈፀምበትን ወሰን እንዲሁም የሕጉን ይዘት ሊያመላክት በሚችል መልክ የተቀረፀ ሲሆን "የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ ሥነ-ሥርዐት እና የማስረጃ ሕግ" የሚል ሆኗል፡፡

ይህ የሕጉ ዋና ስያሜ የሁልጊዜ ማጠሪያው ነው፡፡ ይሁን እንጂ ስያሜው ረጅም ከመሆኑ የተነሳ የፍትሕ አካላት በየእለቱ በእያንዳንዱ ደቂቃ ለሚያከናወኑት ተደጋጋሚ ሥራ ለየተግባራቱ ሁሉ ሁል ጊዜ ይህንን ርእስ ማጠቀም ያስቸግራቸዋል፡፡ በመሆኑም ህጉ ለእለት ከእለት ስራ ማጠሪ የሚሆነው አጭር ርእስ ያስፈልገዋል፡፡ የህጉ አጭር ርእስ የፍትሕ አካላት በእለት ከእለት ተግባራቸው ረጅሙን ርእስ ለማጠቀም የሚቸገሩ በመሆኑ ከላይ የተመላከተውን አላማ ማሳየቱን እንደተጠበቀ ሆኖ ለአጠቃቀም እንዲመች ተብሎ ያጠረ ስያሜ ነው፡፡ አጭሩን ርእስ የፍትሕ አካላት በእለት ተእለት ስራቸው የሚጠቀሙበት ይሆናል፡፡ ስለሆነም ሕጉ አጭር ርእስ ተሰጥቶታል፡፡ በዚህ አግባብም አጭሩ ርእስ "የ፳፻፻፳ ዓ.ም የወንጀል ሕግ ሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ" የሚል ሆኗል፡፡

## 5. የተፈጻሚነት ወሰንና ቀን

የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ በማናቸውም የወንጀል ስነ ስርአትና ማስረጃ ጉዳዮች ላይ ወንጀል ከተፈፀመበኋላ በሚኖሩ የስነ ስርአትና ማስረጃ ጉዳዮች ላይ ሁሉ በወንጀል ጉዳዮች ላይ የመመርመር፣ የመክሰስ፣ የመዳኘት፣ አግባብ ያለውን መፍትሔ የማስጠት እና አጥፊን አርሞ የመቀላቀል ስልጣን በተሰጣቸው አካላት ሁሉ ተፈፃሚ የሚሆን ነው፡፡ ሕጉ የሚፈጸመው በወንጀል ጉዳዮች ላይ ሁሉ ነው፡፡ የወንጀል ጉዳዮች የሚባሉት በ1996 በወጣው የወንጀል ሕግ ውስጥ የተካተቱትን ጨምሮ በሌሎች ልዩ ሕጎችና ደንቦች ላይ የተመለከቱ የወንጀል ሕጎችን ሁሉ ያካትታል፡፡ የወንጀል ሕግ ሲባል በ1996 የወጣውን የወንጀል ሕግ ብቻ የሚመለከት አድርጎ የመረዳት አዝማሚያ ሰፊ በመሆኑ ሌሎች የወንጀል ጉዳዮችም በዚህ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ እንደሚሸፈኑ ሕጉ ሰፋ ያለ ትርጉም ይዟል፡፡

ሕጉ በመጽሐፍ መልክ የወጣ በመሆኑ በወንጀል ጉዳይ ላይ የወጡ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጎችን በሙሉ ማጠቃለል ይገባዋል፡፡ የወንጀል ፍትሕ አካላት በተለያዩ አካላት ስር ይተዳደሩ በነበረት ጊዜ የፍትህ አካላቱ ከሥነ ሥርአቱ ሕግ ጋር በሚጋጩበርካታ ልዩ የሥነ ሥርአትና የማስረጃ ሕጎች በተለያዩ ሕጎች ሲመሩ የቆዩ ናቸው፡ ሕጎቹም በተለይ ለወጡላቸው ጉዳዮች ብቻ የሚፈጸሙ በመሆናቸው የሥነ ሥርአትና የማስረጃ ጉዳይ ላይ ወጥ ወይም በመርህ ደረጃ የተቀራረበ አረዳድ ያልነበራቸው ድንጋጌዎች በርካቶች ናቸው፡ ይህንን በመርህ ላይ ተመስርቶ ማመሳሰልና ሰዎች ሁሉ በእኩል የሚዳኙበትን እድል መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ ተለይቶ የሚታይ ጉዳይ ቢኖር እንኳን ልዩነቱን መፍጠር ያስፈለገበትን ምክንያት በግልጽ በሚያሳምን አግባብ በዚሁ ስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ ውስጥ መደንገግ ይቻላል፡፡ በመሆኑም በወንጀል ጉዳይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ ሕጎችን በዚሁ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ውስጥ በማካተት በዚሁ ሕግ ውስጥ ተካተው እንዲወጡ ተደርጓል፡፡

በመሆኑም ሕጉ የተሻሩትንና ሕጉ በሸፈናቸው የወንጀል ስነ ስርአትና ማስረጃ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ የማይሆኑትን ሕጎች ለይቶ አስቀምጧል፡፡ ለምሳሌ የፀረ ሽብር ሕግ እና የፀረ ሙስና ሕግ እና ማስል ሕጎች የያዟቸው የሥነ ሥርአትና እና የማስረጃ ድንጋጌዎች በዚህ ሕግ የተሸፈኑ በመሆናቸው በልዩ ሕጎቹ ውስጥ የተካተቱት ድንጋዎች ተፈጻሚ አይሆኑም፡፡ ይሁን እንጂ ከሥነ ሥርአትና የማስረጃ ወጪ ያሉ ጉዳዮችን የሚመለከተቱ ት የልዩ ሕጎች ድንጋጌዎች አፈፃፀም በዛው በልዩ ሕጎቹ መሰረት ይቀጥላል ማለት ነው፡፡

ሕጉ በመፅሀፍ መልክ የወጣ በመሆኑ ከሕጉ ጋር የሚጋጩ ሌሎች የወንጀል ሕግ ምርመራ፣ ማስረጃንና በዚህ ሕግ የተመለከቱ ጉዳዮችን የተመለከቱ ሕጎችን በዝርዝር ለይቶ ሽሯል፡፡ ሕጉ ከሕገ መንግስት በታች ስለሆነ በዚህ

አግባብ "ሕግ" የተባለው ሕገ መንግስትን እንደሚይመለከት ሕገ መንግስትን እንደሚይሸር ግልፅ ነው፡፡ በሌላ በኩልም ልማዳዊ ሕጎች በተለየ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲሆኑ በሕጉ የተፈቀደ በመሆኑ ተፈፃሚ የሚይሆኑት በዋነኛነት ከሕገ መንግስቱ ጋር የሚጋጩ ሲሆኑ እንዲሁም እንዳግባቡ በጠቅላይ አቃቤ ሕግ መመሪያ ወይም ጉዳዩን በያዘው ፍርድ ቤት እይታ ከሕግና ከሞራል ጋር የሚጋጩ ሆነው ከተገኙ ነው፡፡ ስለሆንም ባህላዊ ሥርአቶች በሕጉ በተፈቀዱ ጉዳዮች ላይ ከሥነ ሥርአቱ በተለይ አካሄድና በተለየ መፍትሔ ተፈጻሚ ስለሚሆኑ በድፍኑ ይህንን ሕግ የሚቃረን ልማዳዊ አሰራር ሁሉ ተፈጻሚ አይሆኑም የሚለውን የተለመደውን አደነጋግ ይህ ሕግ አልመረጠም፡፡

ሕጉ በሁሉም የወንጀል ሥነ ሥርአታዊ ጉዳዮች ላይ ሁሉ ተፈጻሚ የሚሆን ነው፡፡ ይህ በሕጉ መግቢያ ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በመሰረቱ ሕጉ የሚፀናው በህግ አወጪው ፀድቆ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ከታተመበት ቀን አንስቶ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሕጉ በርካታ አዳዲስ ሀሳቦችን ያካተተ በመሆኑ ለፍትሕ አካላት በሙሉ በዝርዝር ጉዳዮች ላይ ዝርዝር ስልጠና ሳይሰጥ መፈፀም ያስቸግራል፡፡ ሕጉ ተሟልቶ የሚፈፀመውም ልዩ ልዩ ደንቦችና መመሪያዎች ወጥተው ነው፡፡ በሌላ በኩል ሕጉን በተሟላ ሁኔታ ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑ ተጨማሪ ተቋማትን (ለምሳሌ አማራጭ ቅጣቶችን የሚያስፈፅም ተቋም፣ የተከላካይ ጠበቃ ፅሕፈት ቤት፣ እውቅና የሚሰጣቸው ባሕላዊ ተቋማት፣ አማራጭ ቅጣት የሚፈጸምበትን ስርአት ማዘርጋትና ተቋም ማንባት) ማቋቋም ያስፈልጋል፡፡

በሌላም በኩል በነባሩ ሕግ የተጀመሩ ጉዳዮችም አዲስ ከወጣው ጋር ለማጣጣም የሚያስቸግርበት ሁኔታም ሊያጋጥም ይችላል፡፡ የይርጋ ጊዜ እስካላገደው ድረስ ማናቸውም የወንጀል ጉዳዮች ለምርመራ እና ለፍርድ መቅረባቸው አይቀርም፡፡ በልምድ እንደሚታየውም ያለፉ ጉዳዮች ለረዥም ጊዜ ከአዲስ ጉዳዮች ጋር አብረው መታየታቸው ይቀጥላል፡፡ ነባሩ ሕግ ለነባር ጉዳዮች እየተፈጸመ ይቆይ ቢባል ይህ ሂደት በማያቋርጥ ሁኔታ ይቀጥላል፡፡ የወንጀል ፍትሕ ስርአቱ ላይ ትርምስ ይፈጥራል፡፡ የእኩልነት እና ማስል የህገ መንግስት ጥያቄም ያስነሳል፡፡ ስለሆነም ተመራጩ የሚሆነው ይህ ሕግ መፈጸም ከሚጀምርበት ጊዜ አንስቶ ለሁሉም ጉዳዮች ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግና ምናልባት ነባሩ ሕግ ለነባር ጉዳዮች የሚጠቅም ከሆነ በወንጀል ሕግ መርህ መሰረት ጉዳዩ በልዩ ሁኔታ በነባሩ ሕግ እንዲታይ ማድረግ ነው፡፡

ስለሆነም በእነዚህ እና መሰል ጉዳዮችን ተጨማሪ ችግር እንዳይሆኑ አስቀድመው የሚደረጉ ዝግጅቶች መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ሕጉ በሕግ አወጪው አካል ከፀደቀበት ጊዜ አንስቶ ሊያሰሩ የሚችሉ ተጨማሪ ዝግጅቶች ከተደረጉ በኃላ ስድስት ወር ቆይቶ በሁሉም ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ መሆን እንደሚገባው ተደንግጓል፡፡

## 6. ትርጉም

የሕጉን አፈጻጸም እና አተረጓጎም ምቹና ቀላል ከሚድረግ አንጻር የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ከዚህ ቀደም ትርጉም ላልተሰጣቸው ቃላት ወይም ሐረጎች እንዲሁም በሕጉ ለተካተቱት አዳዲስ ሃሳቦች ትርጉም ሠጥቷል፡፡ በዋነኛነትም ትርጉም የተሰጣቸው አገሪቷ ከምትከተለው ስርአት በማሳትም ሆነ አለም ከደረሰበት እወቀት አንፃር ለፍትህ ስርአቱ አዲስ ለሆኑ ወይም በሕጉ ወስጥ ተደጋግመው ጥቅም ላይ ለዋሉ ወይንም ግልፅ ላልሆኑ ሃሳቦች፣ ቃላቶችና ሀረጎች ነው፡፡ ይህ ትርጉምም የፌዴራል እና የክልል ተቋማትን እንዲያካትት ሆኖ የተቀረጸ ነው፡፡ ለአብነትም በሚከተሉት ላይ ሕጉ ትርጉም ይሰጣል፡፡

አገሪቷ ከምትከተለው የፌዴራል ስርአት አንጻር ፍርድ ቤት፣ አቃቤ ሕግ፣ ፖሊስ፣ ማርሚያ እና ማረሚያ ቤት የተባሉት አካላት እና ተቋማት ትርጉም ያስፈልጋቸዋል፡፡ ለምሳሌ በወንጀል ጉዳይ ላይ የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸውአካላት ወሱን ስለሆኑ (ማሆንም ስላለባቸው) ፍርድ ቤት በፌደራል እና በክልል የተቋቋሙትን መደበኛ ፍርድ ቤቶችን እና ወታደራዊ ፍርድ ቤትን ብቻ እንዲያመላክት ተደርጎ ትርጉም ተሰጥቶታል፡፡ በሌላ በኩልም በወንጀል የተጠረጠረ ሰው በምርመራ፣ በክርክር እና በቅጣት ዘመን በእስር የሚቆዩ ከሆነ የመቆያ ቦታው የተለየ ሊሆን ይገባዋል፡፡ ወንጀል የፈፀመ ሰው ታርሞ ከሕብረተሰቡ ጋር በተሳካ ሁኔታ ሊዋሃድ የሚችለው በየደረጃው ያለው አያያዙ ጉዳዩ ያለበትን ሁኔታ ግምት ወስጥ ያስገባ እንደሆነም ጭምር ነው፡፡ በማሆኑም ተጠርጣሪ ማያዝ/ማታሰር ካለበት በምርመራ ወቅት ፖሊስ በሚያዘጋጀውማቆያ ቦት፣ በክርክር እና በቅጣት ዘመን ደግሞ እንደ ቅደም ተከተሉ ማረሚያ ቤት ለያይቶ በሚያደራጃቸው የማረፊያ እና የማረሚያ ቦታዎች ማያዝ ይገባዋል፡፡ በማሆኑም ሕጉ ለ "ማቆያ፣ ማረፊያ እና ማረሚያ" ቦታዎችም ትርጉም ይሰጣል፡፡

የወንጀል ጉዳዮች ከምርመራ አንስቶ እስከ ማረም ድረስ በተለያየ መንገድ መመራት ያለባቸውናቸው፡፡ ጉዳዮች ተለይተውየሚይሙ በማሆናቸውቀላሉም ሆነ ከባዱ ጉዳይ በአንድ ማስመር እያለፉ በአኩል ሲጓተቱ ማስተዋላቸው የተለመደ ነው፡፡ በማሆኑም ጉዳዮችን በደረሱበት ደረጃ ሁሉ እንደ ክብደታቸውማስተናገድ እንዲችሉ ደረጃቸው በቀላል፣ ማካከለኛ እና ከባድ ወንጀሎች ተከፍለዋል፡፡ ለአጠቃቀም ያመች ዘንድም ትርጉም የተሰጣቸው የወንጀል አይነቶች ድልድል በሰንጠረዥ ተለይተውተቀምጠዋል፡፡ የዚህ ትርጉምም በተማሳሳይ ተሟልከቷል፡፡

የሥነ -ሰርአት ሕጉ ፍርድ፣ ወሳኔ፣ ብይንና ትእዛዝ የሚሉትን ቃላት በተደጋጋሚከሕጉ መጀመሪ እስከ ሜጨረሻው ድረስ ይጠቀምባቸዋል፡፡ በየትኛወም የፍትህ አካላት የእልት ከእለት ስራ ወስጥ በተደጋጋሚሳይጠሩ ስራ ሊሰራ አይችልም፡፡ ቃላቶቹ ጽንሰ ሃሳብን ያቀፉ ቃላት ከማሆናቸወም በላይ ተደጋግመው ማኘታቸው ትርጉም

እንዲሰጣቸውግድ ይላል፡፡ ይሁን እንጂ ቃላቶቹ ግልጽ ትርጉም ሳይሰጣቸውቀርቷል፡፡ እስካሁን እየተሰራበት ያለውየስነ ስርአትሕግም ቢሆን ብይን የሚለውን ቃል የሚጠቀም ቢሆንም ፍርድ፣ ወሳኔ፣ እና ትእዛዝ ለሚሉት ቃላት ግልፅ ትርጉም ያልሰጠ በመሆኑ የቃላቱ አጠቃቀም ጽንሰ ሃሳብ የራቀውእና ወጥነት የጎደለውሆኗል፡፡ በየትኛው ደረጃ ትእዛዝ ተሰጠ ሲባልም ተግባሩ በእርግጥ ትእዛዝ ለመሆኑ ከስያሜው ሳይሆን ከተግባሩ ይዘት ብቻ ለሚዳት ግድ ሲል ቆይቷል፡፡ ይህ በመሆኑም በፍርድ ቤት በተሰጠው ፍርድ፣ ወሳኔ፣ ብይን ወይም ትእዛዝ ላይ ይግባኝ የሚባልበት ለመሆኑ ወይም ላለመሆኑ ለሚዳት የተግባሩን ይዘት እንጂ ስያሜውእምብዛም የሚረዳ ሆኖ ቆይቷል፡፡ በመሆኑም በተግባር የገጠመውን ሰፊ ችግር ለመቅረፍ ይቻል ዘንድ የትርጉም ክፍሉ "ፍርድ፣ ወሳኔ፣ ብይን እና ትእዛዝ" ለሚሉት ቃላት ግልፅ ትርጉምአስቀምጧል፡፡

የትርጉም ክፍሉ የያዛቸው ትርጉሞች በስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ለተማከቱት ጉዳዮች ሁሉ የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ከስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ወስጥ ለተወሰነ ክፍል ብቻ የሚያገለግሉ ትርጉሞች ባጋጠሙ ጊዜ ወይም ለአንድ ወይም ለተወሰነ አንቀፆች ብቻ የሚያገለግሉ ትርጉሞች ባጋጠሙጊዜ ትርጉሙበሚፈለግበት በተለየውክፍል ወስጥ ብቻ እንዲቀመጥ ሆኗል ይህም ከህግ አረቃቀቅ መርህ አንፃር ተገቢነው፡፡

በሕጉ የሚታወቁት ፍርድ ቤቶች የመደበኛው እና ወታደራዊ ፍርድ ቤቶች በመሆናቸው ለመደበኛው አሰራር የተቀመጡት ትርጉሞች በሙሉ እንዳግባቡ ለወታደራዊ ፍትሕ አካላትም (ወታደራዊ ፍርድ ቤት፣ ወታደራዊ አቃቤ ሕግ፣ ወታደራዊ ፖሊስ እና ወታደራዊ ተከላካይ ጠበቃ) የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ የሚረም ጉዳይ ድንጋጌዎችም በተማሳሳይ የሚፈጸሙናቸው፡፡

## 7. የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ መርሆዎች

ምንም ያህል የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉን አፈጻጸም ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ ጥረት ቢደረግም ትርጉም የሚፈልጉ ጉዳዮች ሚጋጠማቸውን ማስቀረት አይቻልም፡፡ ሕግን በመተርጎም ሚፈፀም የግድ አስፈላጊ ነው፡፡ ተገቢው ነገር ሕጉ በዘፈቀደ እንዳይፈጸም እንዲሁም እንዳይተረጎም ማድረግ ነው፡፡ ፍርድ ቤቶች ሕጉን መተረጎም የሚያስፈልጋቸው በሚሆንበት ወቅት በማላቸው ወይም አግባብ ነው ብለው በተረዱት መንገድ ሁሉ መተርጎም የሚይገባቸው በመሆኑ ወጥ ወይም ተቀራራቢ ትርጉም ሊያማጡየሚችሉበትን ማስመር ማመልከት የተገባ ነው፡፡ ይህንን አፈጻጸምና ትርጉም ወጥ አቅጣጫ ከሚያስዙት ወስጥ አንዱ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ የሚመራባቸውን አጠቃላይ መርሆዎችን እና አላማዎችን በሕጉ ወስጥ በግልጽ ማስቀመጥ ነው፡፡

እነዚህ መርሆዎች በህገ መንግሰቱ፣ በወንጀል ሕጉ ወይም አገራችን ባጸደቀቻቸው አለም አቀፍ ሰነዶች ውስጥ ተካተው የሚገኙ ቢሆንም በስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ውስጥ መካተታቸው የራሱ ጠቀሜታ አለው፡፡ በመርህ ስር ከተካተቱት ድንጋጌዎች ውስጥም እንደ ጥፋተኛ አለመቆጠር፣ በአንድ ወንጀል በድጋሚ አለመከሰስ/አለመቀጣት፣ በሕግ ፊት እኩል መሆን፣ ያለ በቂ ምክንያት አለመያዝ፣ ኢሰብአዊ አያያዝ ስለመከልከሉ፣ በጠበቃ ስለመወከል፣ ቀልጣፋ ውሳኔ በግልጽ ችሎት ስለማግኘት፣ እውነትን ስለማውጣት፣ ስለእኩልነት፣ ስለጠበቃ ውክልና፣ ሕጋዊነት እና የወንጀል ሕግ የመንግስት መሆኑን ናቸው፡፡ መርሆዎቹ ሥነ ሥርአታዊ በመሆናቸውም አለመከበራቸው በሰብአዊ መብት ላይ የራሱን አፍራሽ ወጤት የሚያስከትል ነው፡፡ መርሆዎቹ መደንገጋቸው በራሱ ወጤት ላያመጣ የሚችልበትን እድልንም ለመቀነስ መርሆዎቹ በሌሎች ህጎች በተቀማጠበት አግባብ ደግሞ የማስቀማጡ ፋይዳ በስነ ስርአትና ማስረጃ ጉዳይ ላይ እምብዛም እንዳይሆን በፍትሕ ሐደቱ ባይከበሩ ሊከተል ስለሚገባው ወጤትም በሕጉ በተመሳሳይ ተመልክቷል፡፡ ለምሳሌ **የተከላካይ ጠበቃ አስፈላጊ በሆነበት ጉዳይ ያለጠበቃ የተደረገ ክርክር እንዳልተካሐደ እንዲቆጠር የሚያደርግ ግልፅ ድንጋጌን** ሕጉ ይዟል፡፡ አብዛኛዎቹ በሕገ መንግስት ውስጥ የተመለከቱ በመሆናቸው ዝርዝር ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸው አይደሉም፡፡

መርሆዎቹ መካተታቸው ካለው ጥቅም ውስጥ ለአብነትም የሕገ መንግሰቱ ድንጋጌዎችን በወንጀል ጉዳይ ላይ በቀጥታ ተፈጻሚ ማድረግ፣ መርሆዎቹን ሥነ ሥርታዊ በማድረግ ሕጉ የሚታረቅንምበትን አግባብ ማመላከት፣ ሕገ መንግሰቱ ውስጥ የተመለከቱትን የሰብአዊ መብቶች የማክበርና የማስከበር ግዴታን በቀጥታ ለመወጣት እንዲቻል እና የሕገ መንግስቱን ድንጋጌዎች አፈጻጸም ከእለት ከእለት ሥራ ጋር ለማስተሳሰር እንዲቻል መሆኑ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

መርሆዎቹ በሕጉ ውስጥ መካተታቸው በተወሰነ መልኩም ቢሆን በሕገ መንግሰቱ የተቀመጡትን አነስተኛ ግዴታዎች ከፍ በማድረግ መብቶች የተሻለ ጥበቃ እንዲያገኙ የሚያደርግ እድልን ይፈጥራል፡፡ ለአብነትም የትርጉም አገልግሎት የማግኘት እና በጠበቃ የመወከልን ፍልጎት በፍርድ ሂደት ላይ ብቻ የሚያስፈልግ ሳይሆን ከፍርድ ሂደቱ በፊት ባሉ ስርአቶችም የሚያስፈልግና አለመሟላቱ የሰብአዊ መብት ጥሰትን ሊያስከትል የሚችል በመሆኑ በጠበቃ የመወከል መብት በወንጀል የፍትሕ ሂደቱ ሁሉ ሊሟላ የሚገባው እንደሆነ ሕግ ይደነግጋል፡፡ በማረሚያ ቤት ያለ ፍርደኛም ከአያያዙ አንስቶ ለይግባኝ፣ ሰበር፣ አመክሮ ወዘተ ጉዳዮች ሰብአዊ መብቱን ባከበር አግባብ መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ በዚህ መብት ሊጠቀም ይችላል፡፡ በተወሰኑ ጉዳዮች ደግሞ (ለምሳሌ በወጣት ጥፋተኞች ጉዳይ) በጠበቃ መወከል ግዴታ እንዲሆን ያስችላል፡፡

ሕጉ ከያዛቸው መርሆዎች ወስጥ የቋንቋ አጠቃቀምን የሚመለከተው መርህ ይገኝበታል፡፡ የፌደራል ፍርድ ቤቶች በሕገ መንግስቱ መሰረት በአማርኛ ቋንቋ የሚሰሩ ሲሆን የክልል ፍርድ ቤቶችም በየክልሉ የስራ ቋንቋ ይሰራሉ፡፡ ሆኖም በክልል አስተዳደሮች ወስጥ የዞን ወይም የወረዳ አስተዳደሮች የሚሰሩበት የተለየ የአስተዳደር ቋንቋ ካላቸው ይኸው ቋንቋ የስራ ቋንቋቸው ይሆናል ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ በአማራ ክልል የአዊ ዞን አስተዳደር በአገውኛ ሊሰራ ይችላል ማለት ነው፡፡

የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ የሚመራበትን መሰረታዊ መርሆዎች በአንድ ክፍል ወስጥ የተቀመጡናቸው፡፡ ይሁንና በተለየ ክፍል ለተለየ አላማ ብቻ ሊፈጸም የሚችል ወይም የሚገባው ተጨማሪ (ልዩ) መርህ ሲኖር በሕጉ በተለየ ክፍል ወስጥ እንዲካተት ሆኗል፡፡ በዚህ አግባብ በሕጉ ልዩ ክፍል ወስጥ ከተቀመጡት መርሆዎች ወስጥ በወንጀል ወስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት ጉዳይ አመራር መርህ፣ የወንጀል የምርመራ እና የክስ ሂደት የትብብር መርህ፣ የሰበር ጉዳይ መርህ፣ የአማራጭ መንገዶችና አማራጭ ቅጣት መርህ፣ የክስ መመስረት መርህ፣ የቅጣት መርህ ወዘተ ይገኙበታል፡፡ እነዚህ መርሆዎች ከአጠቃላዩ የሕጉ መርህ ጋር ተዳምረው በተቀመጡበት ልዩ ክፍል ወስጥ ብቻ የሚፈጸሙ መርሆዎች ናቸው፡፡

ሕጉ መርህን በጠቅላላ እና በልዩ ክፍሉ ወስጥ ያካተተ ቢሆንም በወንጀል ጉዳይ ሌሎች አግባብ ያላቸው የሕገ መንግሰቱም፣ የልዩ ሕጎች ወይም የሌሎች ሕጎች መርሆዎች እንዳግባቡ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉን ለመተርጎም ተፈጻሚአይሆኑም ማለት ግን አይደለም፡፡

## 8. የሕጉ አላማ

የስነ ስርአትና የማስረጃ ሕጉን አላማም በተመለከተ ነባሩ የስነ ስርአትሕግ የሚመራበት ግልፅ አላማ ያልነበረው መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህ በመሆኑም ከወንጀል መከላከል አንስቶ እስከ ማረምና መልሶ መቀላቀል ድረስ ያለው ተግባር ምን አላማን ለማሳካት እንደሚፈጸም የተለያዩ ጫፎችን የያዙ የተለያዩ አመለካከቶች እና ተግባራት እንደነበሩ ይታወቃል፡፡ የነበረው ሰፊ ክፍተትና ልዩነት በወንጀል ሕጉ አረዳድ እና አተረጓጎም ላይም ሰፊ አረዳድ እና የትግበራ ልዩነትን ሲያስከትል የቆየ ሲሆን መነሻ ምክንያታቸው ለሁሉም ፈጻሚ ተርጓሚበእኩል ደረጃ ግልጽ ያልሆኑ የውጪልምዶችንና ፅሁፎችን ጭምር ለሕጉ አፈጻጸም እና ትርጉም መጠቀምን ሲያስገድድ ቆይቷል፡፡ ይህንን ችግር ለመቅረፍም የሥነ ሥርአትና የማስረጃ ሕጉን አላማ በግልጽ ማስቀመጥ የሚያስፈልግ በመሆኑ የሕጉን አላማ የሚያሳይ ግልጽ ድንጋጌ በሕጉ ወስጥ ተካቷል፡፡

በመሆኑም የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ አላማዎስት ማስረታዊ ቁምነገሮችን ሚረጋገጥ እንደሆነ ተሚልክቷል፡፡ በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ወስጥ በሕገ መንግስቱ የተረጋገጠቅን ሰብአዊ መብቶች ማክበርና ማስከበር፣ የወንጀል ፍትሕ ሂደቱ ፍትሓዊነት እና ወጤታማነት (ወጤታማነት ማለት ቅልጥፍና፣ ግልጽነት፣ ተደራሽነት፣ ተጠያቂነት፣ ነጻነትን ያካትታል) በሚረጋገጥ እወነትን ማውጣት እና የህግ የበላይነትን ሚረጋገጥ ናቸው፡፡ እያንዳንዱ የፍትሕ አካል ኃላፊነቱን ይህንን አላማበሚያሳካ ሚልኩ እንዲወጣ ይጠበቃል፡፡

## 9. የተከላካይ ጠበቃ ጉዳይ

በሕገ መንግስቱ ላይ በግልጽ እንደተማለከተው የተከሰሱ ሰዎች ጠበቃ ለማቆም የሚያስችል የገንዘብ አቅም የሌላቸው ከሆነና ፍትሕ ይዛባል ተብሎ ከታመነ በመንግስት ወጪ በጠበቃ የመወከል መብት አላቸው፡፡ አሁን ባለው አሰራር በፍርድ ቤቶች መዋቅር ወስጥ የሚገኘው የተከላካይ ጠበቆች ጽ/ቤት ይህንን ኃላፊነት ከሞላ ጎደል እየተወጣ ይገኛል፡፡ ይሁን እንጂ የተከላካይ ጠበቆች ጽሕፈት ቤት በፍርድ ቤት ወስጥ የሚገኝ ከመሆኑ የተነሳ በተከሳሾች ዘንድ ነጻ አገልግሎት ይሰጠናል የሚል እምነት ያላቸው ለመሆኑ በእጅጉ ያጠራጥራል፡፡ ጽ/ቤቱም የተለያዩ የሎጂስቲክ ችግሮች ያሉበት በመሆኑም በሚፈለገው ደረጃ አገልግሎቱን ሊሰጥ አልቻለም፡፡ ጽ/ቤቱ ሊሰጠው የሚገባው አገልግሎት በሕገ መንግስቱ ለተከሰሱ ሰዎች ካላቸው የመከላከል ሕገ መንግስታዊ መብት አንጻር በሕጉ በተሰጠው ቦታ ልክ መሆን ይገባዋል፡፡ ይህ በመሆኑም የተከላካይ ጠበቃ አገልግሎትን በተማለከተ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው የተለየ ትኩረት ሰጥቶት አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡

በወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው ላይ በግልጽ እንደተማለከተው የተከላካይ ጠበቃ አገልግሎት የሚያስፈልገው የወንጀል ፍትሕ ሂደቱ በማናቸውም ደረጃ (4.7.1) በሚገኝበት ጊዜ ሁሉ ነው፡፡ በሌላ በኩልም ተከላካይ ጠበቃ የሚያስፈልጋቸው በወንጀል ጉዳይ ለሚከራከሩት ብቻ ሳይሆን በፍትሐብሔርም ጉዳይ ያላቸው እንደሆኑ ፖሊሲው ያማለክታል፡፡ በመሆኑም በከባድ ወንጀል ድርጊት ወይም በሰብአዊ መብት መጣስ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ካሳ ለማግኘት በፍርድ ቤት በሚያደርጉት ክርክር ጠበቃ ወክለው ለመከራከር አቅም የሌላቸው ከሆነና በዚህም ፍትሕ ይዛባል በሚል ከታመነ በመንግስት ወጪ ጠበቃ ይመደብላቸዋል፡፡

እነዚህን ከባድ ኃላፊነትን የሚጠይቁ ዝርዝር ተግባራት አሁን ባለው የጠበቃ ጽሕፈት ቤት አደረጃጀት እና አሰራር ማካካት የማይቻል በመሆኑ የራሱ ሥርአትና የማስረጃ ሕጉ ነፃና ገለልተኛ የሆነ የተከላካይ ጠበቃ ጽሕፈት ቤት እንደሚቋቋም ታሳቢ አድርጓል፡፡

## 10. የፍትሕ አካላት ስለሚያከናወኗቸው ተግባራት

ወንጀልን ከመጦርጦር አንስቶ ታራሚን በአግባቡ አርሞ ከሕብረተሰቡ ጋር እስከመቀላቀል ባለው ሂደት ወስጥ በቀጥታ ተሳታፊ የሚሆኑ የፍትሕ አካላት ማለትም ፖሊስ፣ አቃቤ ሕግ፣ ፍርድ ቤት፣ ማረሚያ ቤት እና የተከላካይ ጠበቃ ተቋም በጋራ፣ በወል እንዲሁም በተናጠል ስለሚያከናወኑት ተገባር በሕጉ ወስጥ በግልፅ ተቀምጧል፡፡ በጋራ የሚከናወኑት ተጋባራት የየተቋማቱ ነጻነት እንደተጠበቀ ሆኖ ሁሉንም የፍትህ አካላት በሚያገናኛቸው ጉዳይ ላይ ምን ሊሰራ እንደሚገባ የሚያመላክት ነው፡፡ ለምሳሌም ሁሉም የፍትሕ አካላት በተናጠል (የወል ኃላፊነት) በወንጀል ጉዳይ ጥናትና ምርምር የሚድረግ፣ ዘመናዊ አሠራሮችን የማዘርጋት ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙት ይህንኑ የጥናትና ምርምር ተግባር ሁሉም ተቋማት በአንድነት ሊያከናወኑት ይችላሉ ማለት ነው፡፡

ሕጉ የፍትሕ አካላትን የተናጠል፣ የጋራ ወይም የወል ኃላፊነቶችን ያመላከተ ቢሆንም ተግባርና ኃላፊነታቸው በዚህ ዝርዝር ላይ የተመላከተው ብቻ ነው ማለት ግን አይደለም፡፡ ሕጉ ወስጥ የተመላከቱት ተግባራ በሥነ ሥርአትና በማስረጃ ሕጉ  ላይ በተመላከቱት የፍትሕ አካላቱ ኃላፊነቶች ጋር የታያያዙትና ሊቀሩ/ሊቀነሱ የሚይችሉት አነስተኛ ተግባራት ብቻ ናቸው፡፡ ለምሳሌ መጦርጦር፣ መፍረድ፣ ታራሚን መልሶ መቀላቀል ተግባራት እንደቅደም ተከተላቸውበወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ወስጥ ሊቀሩ የሚችሉ የፖሊስ፣ የፍርድ ቤት እና የማረሚያ ቤት ተግባራት ስለሆኑ በዚህ ሕግ ወስጥ እንዲካተቱ ሆነ ዋል፡፡

በመሆኑም በሕጉ ወስጥ በዚህ መልኩ የተመላከቱት ተግባራት/ኃላፊነቶች እያንዳንዱ ተቋም በተቋቋመበት ሕግ ወይም በሚቋቋምበት ሕግ የተመላከቱትን/የሚመላከቱትን ተግባራትና ኃላፊነቶች የሚይተኩና እና የሚይቀንሱ ናቸው፡፡ በሥነ ሥርአትና ማስረጃ ሕጉ ወስጥ የተመላከቱት ተግባራት ከሥነ ሥርአትና ማስረጃ ሕጉ ወሰን ጋር የተያያዙት ብቻ በመሆናቸው ተግባራቱ በዚሁ ልክ ማዝርዘራቸው በሌላ ሕግ ወይም ለሌላ ተግባር ለተቋማት የሚሰጡ ተግባራትን አያስቀርም፡፡ እያንዳንዱ ተቋም በተቋቋመበት ወይም በሌላ ሕግ የተሰጠዉን ተጨማሪ ተግባር (ለምሳሌ ለፖሊስ አግባብ ባለው ሕግ የተሰጠዉን ዝርዝር የወንጀል መከላከል ተግባራትን) እና የየተቋማቱን ነጻነት አይነካም፣ አይተካም፡፡ ሌሎች የተናጠል ተግባራት የወልና የጋራ ተግባራትን ተከትለው ተዘርዝረው ተቀምጠዋል፡፡ በያንዳንዱ የፍትህ አካል በተናጠል ሊከናወኑ የሚገባቸው ተግባራት (ለምሳሌ ፖሊስን በተመላከተ የወንጀል ክትትል ማድረግ፣ መጥሪያ የማድረስ፣ ብርበራና ፍተሻ የማካሔድ ወዘተ) በተለየ ዝርዝር ለብቻውእንዲቀመጥ ሆኗል፡፡ ይህ የወል እና የተናጠል ተግባራት ዝርዝር በወንጀል ምርመራ፣ ክርክርና ወሳኔ አሰጣጥ ሊፈጸመየሚገባቸዉን ሌሎች ተግባራት አይተካም፡፡

እነዚህ ተግባራትም በሁሉም የፍትሕ አካላት ሊከናወኑ የሚገባቸው ወይም በአንድ የተለየ የፍትሕ አካል ብቻ የሚከናወኑ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የፍትህ አካላቱ እንዳግባቡ ተቋማዊ ወይም/እና የሞያ ነጻነት ያላቸው ከመሆኑ አንጻር የተግባራቱ ማዘርዘር በጋራ ሊያከናወኗቸው የሚችሏቸውን ተግባራት በግልጽ እንዳስፈላጊነቱም በጋራ እቅድ ለይተው እንዲያስቀምጡ ያግዛቸዋል፡፡ በመሆኑም በሁሉም የፍትሕ አካላት ሊከናወኑ የሚገባቸው ተግባራት የወል ተግባራት ተብለው ተዘርዝረዋል፡፡ በዚህ ዝርዝር ውስጥም እንደ ዘመናዊ እንዲሁም በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ አሰራር ማዘርጋትና መተግበር፣ የወንጀል መረጃና ስታትስቲክስን ማያዝ ማደራጀት መተንተን እና ማጋራት፣ ምቹ የተገልጋይ ማስተንግዶን ማመቻቸት፣ በጋራ ጉዳዮች ላይ በጋራና በትብብር መንፈስ ማስራት፣ የወንጀል ቅጣት አላማውን ስለማሳካቱ ማረጋገጥና የመሳሰሉት ተመልክተዋል፡፡

በፍትሕ ሂደቱ ውስጥ ተሳታፊ የሚሆኑት ከላይ ከተመለከቱት አካላት በተጨማሪ በፍትህ አሰጣጥ ሒደት የተያዙ ሰዎች፣ የተከሰሱ ሰዎች፣ የወንጀል ተጎጂዎች፣ ምስክሮች፣ አስተርጓሚዎች ወዘተ ይገኛሉ፡፡ አነዚህ አካላት በሒደቱ እንዲያከናውኑ የሚጠበቅባቸው ተግባራት ያሉ ከመሆኑም በላይ የየራሳቸው መብትና ኃላፊነት ያለባቸው በመሆኑ መብትና ኃላፊነታቸው በሕጉ ውስጥ በግልፅ ሊደነገግ ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ አነዚህ ተግባራት፣ መብትና ኃላፊነቶች የፍትሕ አካላት እንዲያከናውኑ በሚጠበቅባቸው ተግባራት፣ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ በሚመራባቸው መርሆዎች እና አላማዎች ውስጥ በሌላ አገላለጽ የተቀመጡ በመሆኑ ለብቻቸው መደንገግ አላስፈለገም፡፡

## 11. የወንጀል ምርመራ ተግባራት

የወንጀል ምርመራ የሚጀምረው በጥቆማ፣ በአቤቱታ፣ በፖሊስ ምልከታ፣ ክትትል ወይም በጥናት ነው፡፡ የወንጀል ምርመራ ስራ በዐቃቤ ህግ የሚመራ ቢሆንም በዋነኛነት በፖሊስ አማካኝነት የሚከናወን ነው፡፡ ጥቆማው ለፖሊስ ወይም ለአቃቤ ሕግ ሊቀርብ ይችላል፡፡ የወንጀል አቤቱታውን የተቀበለው አካል ወንጀልን የማጣራት ኃላፊነት በሕግ ያልተሰጠው ከሆነ ጥቆማውን/አቤቱታውን ለሚመለከተው አካል ማስተላለፍ ይጠበቅበታል፡፡ በተመሳሳይም አቃቤ ህግ የደረሰውን ጥቆማ ወንጀል ለመፈፀሙ አመላካች የሆነ በቂ መረጃ ያለው ለመሆኑ ከተገነዘበ የወንጀል ምርመራ እንዲጀመር ጉዳዩን ለፖሊስ ያስተላልፈዋል፡፡ ይሁን እንጂ ፖሊስ ማንኛውንም የተጀመረ ምርመራ ምርመራው እንደተጀመረ ለአቃቤ ህጉ ከማስታወቅ አንስቶ ምርመራው በየጊዜው የደረሰበትን ደረጃ እና ስለተወሰዱ (ስለሚወሰዱ) እርምጃዎች ለአቃቤ ሕጉ ተገቢ በሆነው መንገድ ማስታወቅ ይኖርበታል፡፡ አቤቱታ ሲቀርብም ፖሊስ ወዲያውኑ ምርመራ የሚጀምር እንደሆነና ዝርዝሩን ግን ወዲያውኑ ለአቃቤ ሕግ ማስታወቅ

እንደሚባባው የሚያስገነዝቡ ድንጋጌዎች ተካተዋል፡፡ በመሆኑም የሥነ ሥርአትና የማስረጃ ሕጉ አቃቤ ሕግ በወንጀል ምርመራ ሂደት ከመጀመሪያው ጀምሮ በቀጥታ እወቀት የሚሳተፍበት፣ ምርመራውን የሚከታተልበት ከሕግ አንፃር የሚመራት ሥርዐት እንዲዘረጋ ያደርጋል፡፡ መርማሪው በተቀማጠው አቅጣጫ መሠረት የምርመራ ሥራ እየሠራ በየደረጃው ከዐቃቤ ሕጉ ጋር እየተገናኘ እና ከሕግ አንጻር የዓቃቤ ሕግን ምክር እያገኘ የምርመራ ስራው ሁሉ ሕጋዊነትን የተከተለ እንዲሆን የሚያስችሉ ድንጋጌዎች ተካተዋል፡፡ ይህም በስራው ላይ በቅብብል የተነሳ ሊደርስ የሚችለውን ምልልስና በዚህም የሚባክነውን ጊዜ የሚያሳጥር ከመሆኑም በላይ የምርመራ ስራው በተሻለ ጥራት እንዲመራና ህጋዊነቱንም ያልሳተ ለመሆኑ የተረጋገጠ እንዲሆን ያግዘዋል፡፡ ይህ አሰራር በወንጀል ፍትህ ፖሊሲውአቅጣጫከተሰጠባቸውጉዳዮች መካከል አንዱነው፡፡

የወንጀል ምርመራን ለመጀመር ማንኛውም ሰው ወንጀልን በአቅራቢያው ለሚገኝ ፖሊስ ወይም ስልጣን ያለው የህግ አስከባሪ አካል የመጠቆም መብት ያለው ለመሆኑ በሥነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ወስጥ ተመልክቷል፡፡ በሌላ በኩል ወንጀልን የማስተዋቅ ግዴታ በስነ ስርአትና የማስረጀ ሕጉ ወስጥ ማካተት አስፈላጊ ባለመሆኑ ቀደም ሲል የነበረው ድንጋጌ ቀሪ ሆኗል፡፡ ይህ ማለት ግን ወንጀልን የማስታወቅ ግዴታ በአጠቃላይ ይቀራል ማለት ሳይሆን ይህንን ግዴታ መኖር የሚፈልጉ ሕጎች በወጡቁጥር በዛው ፍሬ ህግ ላይ የሚደነገግ በመሆኑ ብቻ የታለፈ ነው፡፡ አሁን በስራ ላይ ያሉትም ሕጎች በተመሳሳይ ይህንን ግዴታ መጣላቸው የሚታወቅ ነው፡፡

ስለሆነው ጉዳዩ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ ጉዳይ ከሚሆን በፍሬ ሕጎች ወስጥ የሚካተት በመሆኑ ከስነ ስርአትና ማስረጃሕጉ ወጪሆኗል፡፡

በሥራ ላይ ያለው የወንጀለኛ መቅጫሕግ ሥነ ሥርዐት የተለያዩ የወንጀል ጉዳዮች አላስፈላጊ በሆነ ሁኔታ በወንጀል ፍትሕ ሂደቱ እንዳይገቡ ማላላከል በሚያስችል እና ከገቡ በኋላም ሥርዓት ባለው ሁኔታ መፍትሔ እንዲያገኙ በሚያስችል አኳኋን ብቃት ባለውመልኩ የተደራጀ አይደለም፡፡ የሕጉ አንቀጽ (22) እንደሚደነግገው ለፖሊስ የሚደርሱ የወንጀል አቤቱታዎች ወይም ክሶች ሁሉ በማጣራት/በምርመራ ሂደት ወስጥ እስከመጨረሻው ማለፍ እንዳለባቸው የሚያስገድድ ሲሆን በማንኛውም ሁኔታ ከምርመራ ወጪወይም የምርመራ ሂደት ሳይጠናቀቅና ወጤቱ ሳይታወቅ ከሂደቱ ወጪመፍትሔየሚያገኙበትን ሁኔታ አልተማለከተም፡፡ በተጨማሪም አቤቱታ ወይም ክስ የቀረበበት ጉዳይ የወንጀል ጉዳይ ቢሆንም እንኳን ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች በሕጉ ተለይተው ስላልተቀማጡ የሕዝብ ጥቅም በከፍተና ደረጃ ከሚነ ዳባቸው ጉዳዮች ይልቅ ቀላል የሕዝብ ጥቅም ያለባቸው ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሚድረግና የምርመራ ሥራ መጀመር ያጋጥማል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አቤቱታ ወይም ክስ ከቀረበባቸው ጉዳዮች

መካከል አብዛኛዎቹ የወንጀል ማዛግብት የምርመራ ሂደትን አልፈው ለዓቃቤ ሕግ ወሳኔ ይቀርባሉ፡፡ ለዓቃቤ ሕግ ለወሳኔ ከሚቀርቡ የምርመራ መዝገቦች ወስጥ ተፈፀመ የተባለው ድርጊት የወንጀል ድርጊት አይደለም የሚባልባቸው፣ ከምርመራ በፊት በእርቅ ቢያልቁ ተመራጭ የሚሆኑ፣ ማስረጃ የተሟላ ባለመሆኑ የሚያስከስሱ፣ በሕግ ተቀባይነት የሌላቸው ማስረጃዎች የሚቀርቡባቸው እና የመሳሰሉ ጉድለቶች ያሉባቸው ሁሉ ይገኙባቸዋል፡፡

ከላይ የተጠቀሰው ችግር እንዲከሰት ከሚያደርጉ ሁኔታዎች መካከል አንዱ የምርመራ ሥራ በሕግ ምክር አለመደገፉ ነው፡፡ ሥራዎች በጋራ በሚይሰሩበት ሁኔታ አብዛኛው የወንጀል ምርመራ ተግባራት ያለ ሕግ ምክር እና ያለ ዓቃቤ ሕግ ተሳትፎ የሚከናወኑ በመሆኑ የምርመራ ሥራ የመርማሪው ኃላፊነት ብቻ ተደርጎ ይታሰባል፡፡ ከዚህም የተነሳ የወንጀል ምርመራ ሥራ ያለዓቃቤ ሕግ ተሣትፎ በመርማሪ ፖሊስ ብቻ ተከናወኖ ስለሚጠናቀቅ በምርመራ ደረጃ ወዲያወኑ ሊቋረጡ የሚችሉ ጉዳዮች አላስፈላጊ ጉልበት፣ ወጪ እና ጊዜ ከወጣባቸው እና የተጠርጣሪዎች መብቶችና ነጻነቶች ከተጣሱ በኋላ በጅምላ ወደ ዓቃቤ ሕግ እንዲቀርቡ ይደረጋሉ፡፡ ዓቃቤ ሕግ ዘንድ ቢቀርቡ አዋጭ ናቸው የሚባሉት እና የወንጀል ድርጊትን የሚያቋቋሙ ጉዳዮችም ቢሆኑ ብዙዎቹ ጊዜ በቂ የሆነ ማስረጃ ሳይሰበሰብባቸውና ሙያዊ ምክር ሳይሰጥባቸው ለአቃቤ ሕግ ስለሚቀርቡ፣ በዓቃቤ ሕግና በመርማሪ አካላት መካከል ተደጋጋሚ ማፃፍ እንዲኖር በዚህም ምክንያት አላስፈላጊ የሆነ የጊዜ ቀጠሮ እንዲጠየቅባቸው ሲደረግ በተግባር ይታያል፡፡ በሥራ ላይ ያለው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዐት ከምርመራ በፊትም ሆነ በምርመራ ወቅት እንዲሁም ከምርመራ በኋላ የሚያዋጡና የመንግሥትን እና የሕዝቡን ሀብት እና ጊዜ የሚያባክኑ እንደዚሁም የዜጎችን መብቶች እና ነጻነቶች ሊጥሱ የሚችሉ ጉዳዮች ሲያስተናግድ ቆይቷል፡፡

የኢፌዴሪ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ ከወንጀል ምርመራ ጋር ተያይዘው ያሉና ከላይ የተብራሩትን አጠቃላይ ችግሮች ከግምት ወስጥ በማስገባት የወንጀል ምርመራ ዓላማና መርህ፣ በወንጀል ምርመራ ሂደት በሕግ ሊደነገጉና ሊተገበሩ ስለሚገባቸው አዳዲስ አሠራሮች፣ በወንጀል ምርመራ ሂደት በፍትሕ አካላት ዘንድ ስለሚኖር ትብብር እና ሚና ግልጽ የሆነ አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡ የወንጀል ምርመራ ዓላማና መርህ በሚያብራራው የፖሊሲው ክፍል የወንጀል ምርመራ ዓላማ በአጠቃላይ ወንጀልን የማወቅ፣ ወንጀል እንዳይፈጸም የማስቆም፣ ወንጀሉ ከተፈጸመ ጉዳቶችን የመቀነስ፣ የወንጀል ኢላማ የሆኑ ሰዎች፣ ንብረቶች ወይም ጥቅሞችን የመከላከል፣ ወንጀል ፈጻሚዎችን ለሕግ የማቅረብ ወይም የወንጀል ተጎጂዎችን መብቶችና ጥቅሞችን የማስከበር እንደሆነ፤ በተለይም በወንጀል ጉዳይ ላይ መረጃ/ ማስረጃ መፈለግን፣ ማግኘትን፣ መተንተንን፣ ማደራጀትን፣ ማኖርንና ለሚፈለገው አላማ ዝግጁ ማድረግን የሚያጠቃልል እንደሆነ አስቀምጧል፡፡

በዚህ ረገድ ፖሊሲው በወንጀል ምርመራ ሂደት ወስጥ የሚስተዋሉትን መሠረታዊ የሆኑ የአፈፃፀም፣ የብቃትና የሕጋዊነት ችግሮች በማስወገድ ውጤታማየወንጀል ምርመራን ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ የተሟላ የአሠራርና የሕግ መሠረት መጣል የሚያስችሉ ቁልፍ አቅጣጫዎችን አስቀምጧል፡፡ እነዚህ አላማዎች በስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ወስጥ በግልፅና በዝርዝር እንዲካተቱ ይጠበቃል፡፡

በዚህም መሠረት ከወንጀሎቹ የተለየ ባህርይና የአፈፃፀም ወስብስብነት የተነሳ የመንግሥትንና የሕዝቡን ደኅንነትና መሠረታዊ ጥቅሞች ለአደጋ የሚያጋልጡ ወንጀሎችን ከተቻለ ከሚፈፀማቸው በፊት አስቀድሞ ለመቆጣጠር፣ በሚፈፀምላይ የሚገኙትንም አስከፊ ጉዳት ከሚድረሳቸውበፊት ለማስቆምእና ተፈፅመውበተገኙም ጊዜ ፈፃሚዎችን በበቂ ማስረጃ አስደግፎ ለማውጣት የሚያስችሉ ዘመናዊ የአሠራር ዘዴዎች መከተል እንደሚገባ ፖሊሲውያመላክታል፡፡ ከአሠራር ዘዴዎቹም ጋር በተያያዘ በወንጀል የተጠረጠሩ ሰዎች ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉትን የመብት ጥሰቶች ከወዲሁ ለመቆጣጠር የሚረዱ የአሠራር ሥርዓቶች ማዘርጋት እንደሚያስፈልግ በፖሊሲው ተመልክቷል፡፡

ከዚህ አንፃር የወንጀል የምርመራ ሥራ ወጤታማእንዲሆን ማስረጃ መር የምርመራ ዘዴን መከተል እንደሚገባ ሕጉ በግልጽ ደንግጓል፡፡ እጅግ የተለዩ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው የምርመራ ስራም በህጉ መጽሐፍ ሁለት በተቀመጠውቅደምተከተል ማሰረት ሚፈጸምያለበት መሆኑ ምርመራን ማስረጃ መር እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ምርመራ ወጤታማእና ፍትሓዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ ሥራውበመርማሪና በዐቃቤ ሕግ በጋራ መከናወን ያለበት መሆኑ፤ የምርመራ ሥራውን የመምራት እና የመከታተል ኃላፊነት የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ስለመሆኑ፤ ዐቃቤ ሕግ ለሚመለከተው መርማሪ አግባብ ያለው ትእዛዝና ምክር የማስጠት የምርመራ ሂደት ሕጋዊነት የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ፤ መርማሪም ከዐቃቤ ሕግ የሚሰጡ ትዕዛዞችና ምክሮችን ተቀብሎ የሚፈጸምና የማስፈጸምግዴታ ያለበት ስለመሆኑ፤ በወንጀል በተጠረጠሩ ሰዎች ላይ ሕግን በተከተለ መንገድ ክትትል ሚድረግ እና ማስረጃ ለማሰብሰብ ሲባል በመካከላቸውሰርጎ መግባት የሚቻል ስለመሆኑ፣ ሊፈፀምየተቃረበ፣ በሚፈፀም ላይ የሚገኝን ወይም የተፈፀመ ወንጀልን ለማውጣት እና በጉዳዩ ላይ ማስረጃ ለማሰባሰብ ሲባል አግባብነት ያላቸውን ሕጎች ተከትሎ የተጠርጣሪዎቹን የግል መገናኛ ዘዴዎች መጥለፍ ስለመቻሉ፣ ከባድና ወስብስብ የወንጀል ጉዳዮች ላይ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችንና ማስረጃዎችን የሚሰጡ የወንጀል ተጠርጣሪዎችን በግልፅ በሰፈሩ የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ሊቀርብባቸውከሚችል ክስ ነፃ እንዲሆኑ፣ በወንጀል ጉዳይ ላይ ምስክርነት የሚሰጡሰዎች ሊደርሱባቸውከሚችሉ የተለያዩ ጥቃቶች ለመከላከል ሲባል እንደሁኔታው አስፈላጊ የሆነ ጥበቃ ሊደረግላቸውየሚገባ ስለመሆኑ፣ እንደሽብርተኝነት፣ ሙስና፣ በሕገመንግሥቱና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱ ላይ

የሚፈፀም፣ በተደራጁ ቡድኖች የሚፈፀም፣ በሴቶችና ሕፃናት የሚገድ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ጋር በተገናኘ ለወንጀሉ ሚፈፀሚየነት ጥቅም ላይ የሚውሉ ወይም ከወንጀሉ ተግባር የተገኙ ገንዘቦችንና ንብረቶችን በሕግ አግባብ ማገድ የሚቻል መሆኑን ወዘተ በምርመራ ተግባራት የሚከናወኑ እንደሆነ ፖሊሲው ያስገነዝባል፡፡ የስነ ስርአትና ማስረጃ ህጉ ይህንን አቅጣጫበመከተል ዝርዝር ድንጋጌዎችን ያካተተ ከመሆኑም በላይ የነባሩ ሕግ ከምርመራ ስራ ጋር በተያያዘ ያለበትን ችግር ለመቅረፍ ጥረት አድርጓል፡፡

ከፍ ሲል በዝርዝር በተመለከተው አግባብ ከወንጀል ምርመራ ጋር ተያይዞ በስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ እንዲካተቱ ከተደረጉ አብይ ጉዳዮች አንዱ የወንጀል ምርመራ ስለሚመራበት ሁኔታና በዐቃቤ ሕግና በፖሊስ መካከል የወንጀል ምርመራን አስመልክቶ የሚኖረውግንኙነት የሚመለከተውድንጋጌ አንዱነው፡፡

በነባሩ ሕግ አንድ ክስ ወይም የክስ አቤቱታ ለፖሊስ ከቀረበ በኋላ ፖሊስ ምርመራውን አጠናቅቄያለሁ ብሎ ሲያምን የተጠናቀቀ የምርመራ መዝገብ ለዐቃቤ ሕጉ የሚቀርብ በመሆኑ ዐቃቤ ሕግ በምርመራ ሥራ ላይ ያለው ተሳትፎ አነስተኛ እንደሆነ የተስተዋለ መሆኑን ከፍ ሲል ተገልጿል፡፡ ነገር ግን ይህ አሠራር ላላስፈላጊ የመዝገብ ምልልስ፣ የጊዜ እና ሃብት ብክነት የሚዳርግ በመሆኑ ወጤታማነት እና የተፋጠነ ፍትሕ አሰጣጥ ላይ ችግር ሲፈጥር ቆይቷል፡፡ አሰራሩም የሁለቱንም አካላት እንቅስቃሴ ለመከታተል እና ለማምገም በሚያስችል አግባብ ተቀርጾ የተሟላ ግልጽነት እና ተጠያቂነት እንዲሰፍን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ችግሩን ለመቅረፍም የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው በቁጥር 3.3 ላይ በግልፅ ባስቀመጠው መሰረት በወንጀል ምርመራ ተግባር ላይ ፖሊስ እና አቃቤ ሕግ በጋራ መስተፍ ይገባቸዋል፡፡ የጋራ ስራ ወንጀል ፈፃሚን ለይቶ ለሕግ ማቅረብ፣ መረጃን ወይም ማስረጃን ሚፈላለግ፣ ማገኘትን፣ መተንትን፣ ሚደራጀት፣ ለክስ ወይም ለሌላ አላማ ማጠቀምንና አግባብ ላላቸውአካላት (ለምሳሌ ለአስታራቂ) ማስረከብ ሂደቶች ሊያካትት ይችላል፡፡ በዚህ መነሻት የስነ ስርአትና ማስረጃ ህጉ ምርመራ የሚደረግባቸውን ጉዳዮች፣ አላማውን፣ በምርመራ የሚስተፉ አካላትን ሚና፣ ተፈፃሚ የሚሆኑ መርሆዎች እና ተዛማጅ ጉዳዮችን አካቷል፡፡

ይህ ማለት ግን አቃቤ ሕግ በሁሉም የምርመራ ስራዎች ወስጥ ይሳተፋል ማለት ሳይሆን ተሳትፎው የወንጀል ምርመራ ስራን በማምራትና በመከታተል ብቻ የሚገለጽ ነው የሚሆነው፡፡ የወንጀል ስራን ማምራትና መከታተል ተቋምን እስከ ማዋሃድ የሚደርስ የተሳሳተ ትርጉም ሲሰጠው የሚስተዋል በመሆኑ ይህንን ግልጽ ለማድረግ ሕጉ ግልጽ ድንጋጌን ይዟል፡፡ በመሆኑም የወንጀል ምርመራ ስራ የሚጀምረውም ሆነ የሚመራው በፖሊስ ሲሆን አቃቤ ሕግ የምርመራውን ስራ በተመለከተ የማምራትና እና የመከታተል ተግባራትን ያከናውናል፡፡

በመሆኑም አቃቤ ሕግም በምርመራ ሂደት ወስጥ የሚኖርበት ሃላፊነት ለምርመራው የሚያስፈልጉ የሕግ ምክርና አስተያየት ለመርማሪው በማስጠት ምርመራ በሕግ ማስረት መካናወኑን ሚረጋገጥ፣ ምርመራውን የመከታተል፣ ለመርማሪው አግባብ ያለወን ትእዛዝ ምክርና ድጋፍ የማስጠት፣ ምርመራው በአግባቡ መካናወኑን የማምራትና ሕጋዊነቱን የሚረጋገጥ እንዲሆን የሚያስችሉ ድንጋጌዎች ተካትተዋል፡፡ መርማሪም ከምርመራው ጋር በተያያዘ ከዐቃቤ ሕጉ የሚሰጥ ማንኛወንም ምክርና ትዕዛዝ የሚፈጸምና የማስፈጸም ግዴታ እንዳለበት በግልጽ በሚደነግግ ሜኩ በረቂቁ የተካተተ ሲሆን ምናልባት መርማሪ በዚህ ዙሪያ ቅሬታ ቢኖረው ለቅሬታወን ሚምለከተው የዓቃቢ ሕግ የበላይ ኃላፊ ማቅረብ የሚችልበት መንገድም ተደንግጓል፡፡

በምርመራ ክፍል ሌላው የተመለከተው ጉዳይ የምርመራ ጊዜን የሚምለከተው ድንጋጌ ነው፡፡ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው የምርመራ ተግባራት የሚጠናቀቁበት ጊዜ ሊቀመጥ እንደሚገባው ባስቀመጠው አቅጣጫ መስረትም የወንጀል ጉዳዮች እንደክብደታቸው ደረጃ የሚጠናቀቁበት የጊዜ ገደብም ተቀምጧል፡፡ ለዚህም አጋዥ የሚሆን የምርመራ ተግባርን ፍትሐዊነት፣ ግልፅነትና ቀልጣፉነት እና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጡ የጉዳይ አስተዳደር ስርአት በፖሊስም ሆነ በጠቅላይ አቃቤ ህግ እንደሚወጡ ይጠበቃል፡፡

የወንጀል ምርመራ የሚጀምርበት ሌላው መንገድ ጥቆማ ነው፡፡ ጥቆማን በተመለከት የወንጀል ጥቆማ በሁለት አይነት መንገዶች ሊቀርብ እንደሚችል ተቀምጧል፡፡ አንደኛ አይነት **ጥቆማ ከወንጀል ፍሬ የሚገኝን** ጥቅም ለመካፈል በማሰብ የሚቀርብ ጥቆማ ነው፡፡ ይህ ጥቆማ በማናቸውም ሰው ሊቀርብ የሚችል ሲሆን ጠቋሚው ሊያገኝ ስለሚችለው የተለየ የጥቅም አይነት እና ማጠን በሌላ ፍሬ ህግ ወይንም የጠቅላይ አቃቤ ሕግ በሚያወጣው መመሪያ መስረት የሚፈጸም ነው፡፡ ሌላው ጥቆማ ከዚህ ወጪ በራስ ተነሳሺነት የአገሪቷ የወንጀል ሕግ ተከብሮ ከማየት ፍልጎትና መበት በማሳት ወይም ህግ በጣለው ግዴታ የተነሳ የሚቀርብ ጥቆማ ሊሆን ይችላል፡፡

በሂደቱም በማናቸወም ሜኩ የቀረበን ጥቆማ ጥቆማው የቀረበለት አካል ጥቆማወን አልቀበልም ለማለት የሚይቻል ለመሆኑና ጥቆማዎች ወይም አቤቱታዎች ሁሉ መመዝገብ የሚገባቸው ለመሆኑ፣ አቤቱታወን የተቀበለው ተቋም በወንጀል ጉዳይ ስልጣን የሌለው ቢሆንም እንኳን ጥቆማወን ለሚምለከተው ፖሊስ ተቋም ማስተላለፍ የሚገባው ለመሆኑ፣ ፖሊስም ጥቆማው/አቤቱታው እንደደረሰው ወዲያወኑ የመጀመሪያ ማጣራት ሚድረግና ሂደቱ መጀመሩን ለአቃቤ ሕግ ወዲያወኑ ማሳወቅ ይገባዋል፡፡ የወንጀልን ጥቆማ የተቀበለ መርማሪም ምንጊዜም ቢሆን የመጀመሪያ ማጣራት ሚድረግ የሚገባው ለመሆኑ፣ በዚህ ማጣራት ሂደትም ጉዳዩ በእርግጥ ወንጀል ለመሆኑ፣ ጉዳዩ ወንጀል

ከሆነና በጉዳዩ ላይም ስልጣን ያለው ከሆነም ጉዳዩ የሚመራበትን መንገድ (የእጅ ከፍንጅ፣ ደንብ መተላለፍ፣ ከባድ ጉዳይ…) እንዲለይ ሕጉ ግድ ይላል፡፡

በወንጀል ህጉ ውስጥ በግል አቤቱታ ብቻ የሚያስቀጡ ወንጀሎች የተደነገጉ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ እነዚህ ወንጀሎችን በተመለከተም ምርመራውን ለማከናወን አቤቱታው እንዴት፣ በማንና ለማን ሊቀርብ እንደሚችል በሥነ ሥርአትና ማስረጃ ሕጉ ውስጥ መደንገግ የሚያስፈልግ ነው፡፡ ይህንኑ ጉዳይ የሚመሩ ድንጋጌዎች በሕጉ ውስጥ የተካተቱ ሲሆን ወንጀሎቹ በግል ተበዳይ የግል ፍላጎት ላይ ተመስርተው የሚንቀሳቀሱ በመሆናቸው ከመደበኛው ወንጀሎች በልዩ ሁኔታ ስለሚታዩ ስርአታቸውም በዛው ልክ ጠበብ ብሎ ተቀምጧል፡፡ ለምሳሌም በስልክ የቀረበ የግል አቤቱታ በአስር ቀናት ውስጥ በግንባር በፅሁፍ ሊቀርብ እንደሚገባው እንዲሁም አቤቱታውን በማናቸውም ጊዜ ማንሳት የሚቻል ቢሆንም በዚህ መልኩ የተነሳ አቤቱታ በድጋሚ ሊንቀሳቀስ የማይገባው ለመሆኑ ተደንግጓል፡፡ የእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረታዊ መሻ ጉዳዮቹ የግል ስለሆኑ የሚንቀሳቀሱትም ሆነ የሚቋጥሉት በግል ተበዳይ ውሳኔ በመሆናቸው በሂደቱ የሚፈጠሩ ክፍተቶች ሂደቱን ባለመቀጠል ጉዳዩን በግል ለመያዝ ወይም ለመጨረስ መምረጥን ያመለክታሉ በሚል እሳቤ የተካተቱ ናቸው፡፡ ከሌሎች ጉዳዮች በተለየ የግል አቤቱታ ጉዳይ የሚመራው የሕብረተሰቡ አጠቃላይ ፍልጎትን በተለይ ለማስጠበቅ ሳይሆን የተጎጂን የግል ፍላጎት ለማስጠበቅ ነው፡፡ በመሆኑም የግል አቤቱታ አቃራቢ ጉዳዩን ባልተከታተለው መጠን ጉዳዩን በአማራጭ መንገዶችና መፍትሔዎች ለመጨረስ እንዳሰበ የሚገመት መሆኑን ታሳቢ ያደረጉ ድንጋጌዎች ተካተዋል፡፡

በምርመራ ስራ ውስጥ ሊያጋጥሙ ከሚችሉት ጉዳዮች ውስጥ ሌላው የሃይል አጠቃቀምን የሚመለከተው ጉዳይ ነው፡፡ የምርመራ ስራ ሳይንስን እንዲከተል የሚጠበቅ ቢሆንም በተወሰኑ ሁኔታዎች ኃይልን መጠቀምን ግድ የሚሉ ሁኔታዎች ሊያጋጥሙ ይችላሉ፡፡ ኃይል መጠቀምን የሚመለከቱ ጉዳዮች በርካታ በመሆናቸው ዝርዝራቸው በሌላ ሕግ በዝርዝር የሚመለከት ነው፡፡ ይሁን እንጂ በምርመራ ወቅት ሊያገጥም የሚችልን ሁኔታ ለመቆጣጠር በሚያስችል መልክ በዚህ ክፍል ውስጥ ኃይልን መቼ እና እንዴት መጠቀም እንደሚቻል በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በዚህ መሰረት ከወንጀል ምርመራ ጋር በተያያዘ ኃይልን መጠቀም የሚችለው መርማሪ ሆኖ በምርመራ ወቅት ተመጣጣኝ ኃይል ተጠርጣሪን ለመያዝ ፣ለብርበራ እና በልዩ የወንጀል ምርመራ ዘዴ ብቻ ሆኖ የሚጠቀመውም ኃይል ለሌላ አላማ ሳይሆን የምርመራ ተግባሩን ለማከናወን ብቻ የሆነ፣ ከገጠመው ተቃውሞ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ፣ የምርመራ ተግባርን በሌላ መንገድ ማከናወን የማይችል በመሆኑ ይህንኑ ኃይል መጠቀም የግድ አስፈላጊ ሲሆንና ሌላ አማራጭ መንገድ የሌለ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

## 12. ማስረጃ አሰባሰብ

የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ፖሊስ በወንጀል ጉዳይ ምርመራ ሂደት ወስጥ በዋነኛነት ማስረጃን ከተከሳሽ ወጪ በሆነ አግባብ በማሰብሰብ እውነቱ ላይ እንዲደርስ ይጠብቃል፡፡ ስለዚህም ወንጀል ተፈፀመ በተባለ ቁጥር አስቀድሞ ተጠርጣሪን በመያዝ ምርመራ መጀመር ተቀዳሚእና ተመራጭ የማስረጃ ማሰባሰቢያ መንግድ ባለመሆኑ ማስረጃ በተቻለ ማጠን ከተጠርጣሪ ወጪ ለማሰበሰብበት መንገድ ሕጉ ቅድሚያ ይሰጣል፡፡ ፖሊስ ተጠርጣሪን ከመያዙ በፊት አስቀድሞ ማስረጃ ማሰባሰብ ያለበት ሲሆን በማስረጃ ማሰባሰብ ሂደት ወስጥም የምስክርን ቃል ስለሚቀበልበት ሁኔታ፣ ብርበራና ፍተሻ ስለሚደረግበት ሁኔታ፣ ከተጠርጣሪ ወጪ በሌላ ሰው ወይም በመንግሰት የሚገኝን ማስረጃ ስለሚቀበልበት ሁኔታ፣ በልዩ ሁኔታ ማስረጃ ስለሚሰበሰብበት እና በመጨረሻም ከተከሳሽ ማስረጃ ስለሚቀበልበት ሁኔታም በዚሁ ቅደም ተከተል ተደንግጓል፡፡ እጅግ የተለየ ሁኔታ ካገጠመ በስተቀር የወንጀል ምርመራ ስራው ሊመራ የሚገባው በሕጉ ላይ በተቀመጠው(ከዚህ በታች በተቀመጠው) ቅደም ተከተል ብቻ ነው፡፡ ቅደም ተከተሉም የምስክርን ቃል መቀበል፣ ብርበራና ተያያዥ ጉዳዮችን፣ የምርመራ ምልከታ፣ ከሶስተኛ ወገን የሚገኝን ማስረጃ፣ የልዩ አዋቂ ቃል መቀበልን፣ ናሙና ተያያዥ ጉዳዮችን፣ የልዩ ምርመራ መንገዶችንና ከተጠርጣሪው ቃል መቀበልን የሚመለከቱትን ያካትታል፡፡

በምርመራ ስራው መጀመሪያ ከሚከናወኑት ተግባራት ወስጥ የምስክር ቃልን መቀበል ይገኝበታል፡፡ ምስክርነትን በተመለከተ በመሰረቱም ሁሉም ሰው ምስክር ለመሆን ብቃት እንዳለው ሕጉ ይገምታል፡፡ ሁሉም ሰው ለመመስከር ብቃት እንዳለው ብቻ ሳይሆን የመመስከር ግዴታም ያለበት ለመሆኑም የህጉ ማሻ ነው፡፡ ከፍትሐብሔር ጉዳይ በተለየ ሚልኩ በልዩ ሁኔታ እስካልተመለከተ ድረስ በወንጀል ጉዳይ ምስክርነት ግዴታ ነው፡፡ ስለሆነም በመርህ ደረጃ የግዴታ ምስክርነት ሊገደብ አይችልም፡፡ ይሁን እንጂ በልዩ ሁኔታ ምስክር የመሆን ብቃት በፍርድ ቤት ውሳኔ ወይም በሕግ ሊገደብ እንደሚቻልና ምስክር መሆን የማይችሉና የማይገደዱትን ሕጉ ለይቶ አስቀምጧል፡፡ ለምሳሌም አንድ ሰው በተያዘው ጉዳይ ላይ ለጊዜው ወይም በጉዳዩ ላይ በአጠቃላይ የመመስከር ብቃት እንደሌለው ጉዳዩን የያዘው ፍርድ ቤት ሊወስን ይችላል፡፡ በሕግም የመመስከር ችሎታቸው የተገደቡ ሰዎች ካሉ (ለምሳሌ የሙያ ምስክር) ምስክር ላይሆኑ ይችለሉ፡፡ በሌላ በኩልም የተወሰኑ ሰዎች (ለምሳሌ በመንግስት ሚስጥር የተባለን ማስረጃ የያዙ፣ ጥበቃ በተደረገለት የተለየ ግንኙነት (ትዳር፣ እምነት፣ ጥብቅና…) በተነሳ የተገኘን ማስረጃ የሚያወቅ ሰው ለምስክርነት አይገደድም፡፡ ከዚህ ወጪ ያሉ ሌሎች ምስክሮችን ግን በፖሊስ ተጠርተው እንዲመሰክሩ ሊገደዱ ይችላሉ፡፡ የምስክር ቃልንም በመሰረቱ በምርመራ ቦታ መቀበል የተገባ ቢሆንም

በልዩ ሁኔታ ለምስክር በተለየ የምርመራ ቦታ ወይም በቂ ምክንያት ሲኖር (ለምሳሌ የጠና ችግር) ለምስክሩ በሚመች ቦታ የምስክርን ቃል መቀበል ይቻላል፡፡

የምርመራ አካል የሆነው ሌላው የፖሊስ ተግባር ብርበራ ነው፡፡ ብርበራ የሚከናወነው በሰው አካል፤ መኖሪያ ቤት ወይም ማስረጃ ይገኝበታል ተብሎ በሚታሰብ ማናቸውም ቦታ (ተሽከርካሪ፣ መጋዘን፣ መንግስት መስሪያ ቤት፣ አውሮፕላን…) እንዲሁም በሰውላይ ሁሉ ነው፡፡ ብርበራ በማስረቱ በተለየ ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር በፍርድ ቤት ትእዛዝ የሚከናወን ሲሆን በብርበራ ሊያዝ የሚችለው ንብረትም በማስረቱ ለምርመራው የሚፈለገው እቃ ብቻ ነው፡፡ ለምርመራ የሚፈለገውን ንብረትንም መርማሪው በእማኝ አረጋግጦ ፖሊስ ምርመራ ቦታ ሊወስደው ይችላል፡፡ ብርበራ በፍርድ ቤት ብቻ የሚከናወን ቢሆንም በተወሰኑና በጠበቡ ሊረጎሙ የሚገባቸው ጉዳዮች የገጠማም እንደሆነ በተለዩት ምክንያቶች (ለምሳሌ የእጅ ከፍንጅ ወንጀል) ያለ ፍርድ ቤት ትዘእዛዝ ብርበራ ለማድረግ የሚቻልበት ሁኔታም ተመልክቷል፡፡

በማስረጃነት የሚፈለገው እቃ መንቀሳቀስ የሚችል፤ በቀላሉ ማስረጃው የሚገኝበት፣ ማስረጃውን የማግኘት ሂደት ነዋሪውን ወይም ሕብረተሰቡን የእለት ተእለት እንቅስቃሴ የሚያውክ እንደሆነ እቃውን በማሸግ ወይም ባለበት ሁኔታ በመውሰድ የሚፈለገውን እቃ መውሰድ እንደሚቻል ተደንግጓል፡፡ የተያዘው ንብረት በማናቸውም መንገድ በግለሰብ እጅ ሊያዝ የሚችል (ምሳሌ ቅርስ፣ የሐይማኖት ተቋም ልዩ ንብረት…) ሲሆን ናሙናን በማስቀረት ንብረቱን ገቢ ማድረግ እንዲቻል እንዲሁም ንብረቱን ለማያዝም ልዩ ፍቃድ የሚያስፈልግ ሲሆን (ምሳሌ የጦር መሳሪያ፣ የውጪ ገንዘብ…) ፈቃድ አለኝ የሚል ሰው የሚያቀርበው አግባብ ያለው የመብት ጥያቄ እንደተጠበቀ ሆኖ ናሙና በመውሰድ ንብረቱን ገቢ ማድረግ ይቻላል፡፡ ሌሎች ንብረቶችን በተመለከተም (ምሳሌ እንስሳት፣ በቀላሉ ሊበላሹ የሚችሉ ንብረቶች፤ ባለቤታቸው አጠራጣሪ የሆኑ ንብረቶች…) አስተዳደራቸው/አያያዛቸውበተግባር አስቸጋሪ ስለሚሆን አነዚህ ንብረቶች ላይ የበለጠ ጉዳት ሳይደርስ ፖሊስ ሊያስተዳድራቸው ስለሚችልበት አግባብም ሥነ ስርአት ሕጉ ደንግጓል፡፡ ይህም በዚህ ዘርፍ በተግባር የሚያገጥሙብርካታ ችግሮችን ይቀርፋል ተብሎ ታስቧል፡፡

በሌላ ሰው ወይም በመንግስት እጅ የሚገኝን ማስረጃ ፖሊስ ለምርመራ ተግባር ተቀብሎ ምርመራ ሊያከናውን የሚችልበት አግባብ ሕጉ የደነገገ ሲሆን ማስረጃውን የያዘው አካል ማስረጃውን ለማጠት የሚችለው በመንግስት ሚስጥር የተባለ ማስረጃ እንደሆነ ብቻ ለመሆኑም ተደንግጓል፡፡ ለምርመራው የሚፈልገው ማስረጃ የባንክ ሂሳብንና እንቅስቃሴውን የሚመለከት ከሆነም ፖሊስ ማስረጃውን በፍርድ ቤታ አማካይነት ማስረጃውን

ከባንክ ጠይቆ በማግኘት ምርመራውን ማከናወን ይችላል፡፡ ከተጎጂም ሆነ ከተጠርጣሪ ላይ ናሙና (አሻራ፣ የእጅ ጽሑፍ፣ የሽንት፣ የደም፣ የጸጉር ናሙና…) በመውሰድ ምርመራን ማከናወንም ይችላል፡፡ ተጠርጣሪው ናሙናዎችን ለማስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ ከተጠርጣሪው ሰውነት በቀጥታ የሚወሰዱትን እንደ አሻራ፣ የእጅ ጽሑፍ የማስሉትን ምርመራው ተመጣጣኝ ኃይል በማጠቀም መወሰድ የሚቻል ሲሆን በሌሎች የናሙና ጉዳዮች ግን ተጠርጣው ናሙና ለማስጠት ፈቃደኛ ካልሆን የተባለው ነገር መኖሩ እንደተረጋገጠ ግምት እንዲወሰድ የሚያስችሉ ድንጋጌዎች ተካተዋል፡፡ ተጠርጣሪው በዚህ መልኩ የሚወሰዱ ግምቶችን በማናቸውም ማስረጃ ማስተባበል ወይንም ማፍረስ ይችላል፡፡

በምርመራ ስራ ወስጥ የግድ መከናወን የሚገባቸው ነገር ግን በነባሩ ስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ ወስጥ ያልተካተቱ ጉዳዮችም በሥነ ስርአት ሕጉ እንዲካተቱ ሆኗል፡፡ በዚህ መሰረት ለምርመራ የሚፈልግ ንብረት የማገድና የማሸግ ተግባራት በምርመራ ሂደት ሊከናወኑ የሚችሉበት አግባብ በህጉ ወስጥ ተካቷል፡፡ የሚታገደው ንብረት ከወንጀሉ ጋር ግንኙነት ያለው፣ በንብረት ወይም በገንዘብ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀልን ለመከላከል የሚያስችል፣ ወንጀል ለመፈፀም በጥቅም ላይ የዋለ ወይም የወንጀል ፍሬ የሆነ አለበለዚያም የሚጠረጠሩ የሂሳብ ሰነዶችን ሊያካትት ይችላል፡፡ በዚህ መልኩ የማገኝ ንብረት የተቀየረ፣ ዋጋው የተለወጠ፣ የተቀላቀለ፣ ወዘተ ከሆነ ምየ ማገዱም ተግባር ይህንን ንብረት ይመለከታል፡፡ በተወሰኑ ወንጀሎች ላይ ግን (እንደ በሕገ መንግስት እና ሕገ ምንግስታዊ ስርአት፣ ሽብር፣ የአገር ክህደት፣ የአገር ደህንነት እና የመሳሰሉ ወንጀሎችን የሚመለከቱ ወንጀሎች ከሆኑ) ማናቸውም የተጠርጣሪው የግል ንብረት ሁሉ ሊታገድ ይችላል፡፡

በዚህ መልኩ ወጡታማ ክስ ለማቅረብ ንብረት እንዲታገድ በወንጀል ህጉ በተመለከቱ ምክንያቶች ፖሊስ ወይም አቃቤ ህግ ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችላሉ፡፡ የንብረት ይታገድልኝ ጥያቄ የወንጀል ክስ ከመመስረቱ በፊት፣ በምርመራ ጊዜ ወይም ከክስ በኃላ በክርክር ወቅት ሊቀርብ ይችላል፡፡ አላማውም የሚወረሱንብረቶች እንዳይበላሹ፣ እንዳይጠፉ፣ እንዳይባከኑ ሟድረግና የገንዘብ ቅጣት የሚፈጸምበት ንብረት መኖሩን ማረጋገጥ እንዲሁም በወንጀሉ ጉዳይ ተጎጂ የሆኑ ሰዎች ካሳ የሚገኙ ቢሆን ንብረት እንዳይጠፋ ለማድረግ ነው፡ በመሆኑም አሰፈላጊ ለሆነ ውጊዜ ያህል ተመጣጣኝ የሆነ ንብረት እንዳይሸጥ፣ እንዳይለወጥ ወይም በማናቸውም መንገድ ወደ ሶስተኛ ወገን ስመ ንብረቱ ሳይዞር እንዲቆይ ሊታዘዝ ይችላል፡፡ የንብረት መታገድ የተሰጠ ቢሆንም የንብረቱ ባለቤት በንብረቱ መደበኛ አጠቃቀም ከማስራት እና ኑሮውን ከማምራት ወይም ተጨማሪ ሀብት ከማፍራት አይከለከልም፡፡ በተጨማሪም ለተጠርጣሪው እና ለቤተሰቡ ኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ንብረቶችም የእግድ ትእዛዝ አይሰጥባቸውም፡

ንብረት በሚታገድበት ጊዜ ተጠርጣሪው ንብረቱን ሆነ ብሎ እያበላሸው ለመሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ንብረቱ ከይዞታው ወጥቶ በሌላ ሰው እጅ እንዲጠበቅ እንዲሁም እንዲተዳደር ለማድረግ የንብረት አስተዳዳሪ ሊሾም ይችላል፡፡ የንብረት አስተዳዳሪ በፍርድ ቤት የሚሾም ሲሆን በህጉ ከተማለከተው ሃላፊነቱና ግዴታዎቹ በተጨማሪ በፍርድ ቤትም ተጨማሪ ሃላፊነት ሊሰጠው ይችላል፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ ጠባቂው እንደ አንድ ሚልካም የንብረት አስተዳዳሪ ማስራት የሚገባው ሆኖ ለአገልግሎቱ ተገቢው ክፍያ በፍርድ ቤቱ ይወሰንለታል፡፡ በየጊዜው ለፍርድ ቤቱ ሪፖርት ማቅረብ ያለበት ከመሆኑም በላይ አንድ ንብረት አስተዳዳሪ የሚኖረው ኃላፊነትና ስልጣንም ይኖረዋል፡፡

ለተመሳሳይ አለማም የንብረትን ማሸግ አስፈላጊነት ፍርድ ቤቱ የተረዳው እንደሆነ ንብረት እንዲታሸግ ሊታዘዝ የሚችል ሲሆን በንብረት ላይ ሊኖሩ የሚችሉ ለወጦችን ለመቆጣጠርም የንብረት ዝርዝር ከማዘጋጀት አንስቶ ተገቢው ጥንቃቄ ሁሉ እንዲደረግ የማዘዝ ስልጣን ለፍርድ ቤት ተሰጥቷል፡፡ የሚይታገዱት ንብረቶች የሚይታሸጉ ከመሆናቸውም በላይ በመታሸጋቸው ምክንያት የሚበላሹ ወይም ዋጋቸው የሚቀንሱ ንብረቶች የሚይታሸጉ ለመሆናቸው ሕጉ ግልፅ ድንጋጌን ይዟል፡፡

የምርመራ ተግባር ሌላው አካል ቀዳሚ ምርመራ ነው፡፡ ይህ ተግባር በነባሩ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ ወስጥ የነበረ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ የነባሩን ህግ አፈጻጸም ይበልጥ ሰፋ በሚያደርግ እና ሂደቱንም ፍትሓዊ ለማድረግ በሚያስችል ሚልክ በአዲስ ሚልክ ተደንግጓል፡፡ በዚህ ማስረት የቀዳሚ ምርመራ አላማ በወንጀል ጉዳይ የተሰበሰቡ ጠቃሚ እና የማስረዳት ዋጋቸው ከፍ ያሉ ማስረጃዎች በአግባቡ ተጠብቀው እንዲያዙ፣ እንዲደራጁ እና ደህንነታቸው እንዲጠበቅ ለማድረግ መሆኑ ተሚልክቷል፡፡ በቀዳሚ ምርመራ የሚያልፉ ወንጀሎች በከፍተኛ ፍርድ ቤት ስር የሚወድቁ ሆነው ቀዳሚ ምርመራ የሚደረገውም በቅርብ በሚገኝ በማናቸውም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ቀዳሚ ምርመራ የሚደረግባቸውም ወንጀሎች እንደ ከዚህ ቀደሙ በግድያ እና በወንብድና ወንጀሎች ላይ ብቻ የተወሰኑ ሳይሆን በከባድ ወንጀሎች ላይ ሁሉ የሚደረግ ነው፡፡ በሂደቱም አቃቤ ህግ ይጠበቁልኝ የሚላቸውን ማስረጃዎች ሁሉ በማስረጃ አሰማም ስርአት ለፍርድ ቤቱ አቅርቦ የማስጠበቅ መብት ያለው ሲሆን ተጠርጣሪውም በተመሳሳይ ይጠበቁልኝ የሚላቸውን ማስረጃዎች አቅርቦ ማስጠበቅ ይችላል፡፡ ማስረጃው የሰው ምስክር በሚሆንበት ወቅትም የተሰሙ ምስክሮችም በተፈለጉ ጊዜ የተፈለጉበት ፍርድ ቤት ለመቅረብ ዋስ እንዲጠሩ ከማድረግ ባሻገር አስሮ ማቆየት የሚያስፈልግ በመሆኑ በዚህ ረገድም የቀድሞው ስርአት ተሻሽሏል፡፡ ጉዳዩ የሚቀርብበት ፍርድ ቤት ላይታወቅ የሚችል በመሆኑም የተጠበቀውን ማስረጃም የሚማከተው አካል አስገልብጦ የሚወስድ ከሚሆን በስተቀር ማስረጃውን የሰማው ፍርድ ቤት ማስረጃውን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት

አስቀድሞ እንዲልክ ይጠበቅበት የነበረው ግዴታም ቀሪ ሆኗል፡፡ የቀዳሚ ምርመራ መዝገብ የሚይዛቸው ጉዳዮች ላይ ከነበረው ሕግ እምብዛም ለውጥ አልተደረገም፡፡

ከፍ ሲል ከተጠቀሱት የማስረጃ ማሰባሰቢያ መንገዶች በተጨማሪ ፖሊስ እንዳስፈላጊነቱ ወንጀል በተፈጸመበት ቦታ በመገኘት ማስረጃ ማሰባሰብ (የክራይም ሲን ኢንቨስቲጌሽን)፣ ማስረጃ እንዳይባክን የሚደረግ እንዲሁም የፎረንሲክ እና ቴክኒክ ማስረጃ እንዳይባክን የሚያስችለውን ምርመራ ለማድረግ የሚያስችለው ግልጽ ድንጋጌ ተካቷል፡፡ የዚህ ምርመራ ዘዴ ማስረጃን ለማሰባሰብ እጅግ ጠቃሚ ሲሆን የማስረጃ ትንተና ስራንም ሊያካትት ይችላል፡፡ በቦታው የሚሰበሰበው ማስረጃ ከሌሎች ማስረጃዎች ጋር እየተገናዘበ መተንተን ያለበት ሲሆን አለዚያም ማስረጃውን ምርመራ ቦታ መውሰድ ማስረጃው ላይ ብክለት/ብክነት የሚያስከትል ከሆነ ምርመራው ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ ሊደረግ ይችላል፡፡ በተመሳሳይም የቤተ ሙከራ እና የሞተ ሰው አካልን ምርመራ ለማድረግ የሚያስችለው ድንጋጌ ተካቷል፡፡

በስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ውስጥ አዲስ የገባው ሌላ ድንጋጌ ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት የምርመራ መንገዶች ውጪ ምርመራ በልዩ ሁኔታ ማስረጃ ማሰባሰብን የሚፈቅዱ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ ድንጋጌዎቹ ከባድ፣ ወስብስብ እና አለም አቀፋዊ ባህሪ ያላቸውን ወንጀሎች (የሽብር ወንጀል፣ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀል፣ በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል፣ የኮምፒዩተር ወንጀል፣ የቴሌኮም ማጭበርበር ወንጀል እና የሙስና ወንጀል) በበቂ ማስረጃ አስደግፎ ለማውጣት የልዩ ምርመራ እና ዘመናዊ ዘዴዎችን በሕጉ ውስጥ ማካተትና አሰራሩን በሕግ አግባብ በጥንቃቄ መምራት የሚያስችሉ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ በዚህ መልኩ ማስረጃ ማሰብሰብ የተፈቀደበት ዋናው ምክንያት በአሁኑ ሰአት በአገራችን ብቻ ሳይሆን በመላው አለም የወንጀል አፈጻጸሞች እጅግ ወስብስብና ድንበር ተሻጋሪ ከመሆናቸውም በላይ (እንደ የኢኮኖሚ ሙስና፣ በተደራጁ እና በታጠቁ ቡድኖች የሚፈፀሙ ወንጀሎች) እስካሁን በተለመዱት መንገዶች ብቻ ማስረጃ በማሰባሰብ እውነት ላይ በመድረስ የሕጉን፣ የሕዝቡን ፍላጎት እንዲሁም የሕገ መንግስቱን አላማዎች ለማሳካት የማይቻል በመሆኑ ነው፡፡ የልዩ ምርመራ መንገዶቹ በተመሳሳይ ምክንያት በሌሎች አገራትም የሚሰራባቸው ናቸው፡፡

ልዩ የወንጀል ምርመራ መንገዶች ተግባራዊ የሚሆነው ሌሎች የምርመራ መንገዶች ተግባራዊ መሆን ያልቻሉ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ የሚተረጎመትም በጠባቡ ነው፡፡ በዚህ መሰረትም ማስረጃ በልዩ ዘዴ ማሰባሰቢ መንገዶች ተብለው በሕጉ ወስጥ እውቅና የተሰጣቸው የተጠርጣሪን ግንኙነት በልዩ የድምጽ ወይም የምስል መቅረጫ መሳሪያ

ማከታተል፣ ሰርጎ በመግባት እና ልዩ ክትትል ማድረግ፣ የተጠርጣሪን ልዩ ልዩ (የግል መገናኛ ዘዴዎችን መጥለፍ) ግንኙነቶችን መጥለፍና የይምሰል ግንኙነቶችን መፍጠር ናቸው፡፡ ልዩ የምርመራ መንገዶችን ለመጠቀም መደበኛ የሆኑት የመረጃ ማሰባሰቢያ መንገዶች (ከላይ የተገለጹት ናቸው) ውጤት ያላመጡ ወይም የማያመጡ መደበኛው የምርመራ መንገድ መጠቀም አስቸጋሪ መሆኑ ወይም ውጤት እንደማያመጣ አስቀድሞ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

በልዩ ዘዴ የመረጃ ማሰባሰቢያ መንገድ ትግበራ ላይ ከሚነሱት ጥያቄዎች ዋነኛው የሰብአዊ መብትን ሊያጣብቡ ይችላሉ የሚለው ስጋት ነው፡፡ ሕጉ ለዚህ ጉዳይ አግባብ ያለውን ጥንቃቄ አድርጓል፡፡ የልዩ ምርመራ ዘዴ ከሰብአዊ መብት ጋር ያለውን ግንኙነት በአግባቡ መቆጣጠር ይቻል ዘንድም በርካታ ገደቦችና የቁጥጥር ሥርአቶችን ሕጉ ዘርግቷል፡፡ ከመነሻው በልዩ ምርመራ ዘዴ መረጃ የሚሰበሰብባቸው የወንጀል አይነቶች ሁሉም አይነት የወንጀል አይነቶች ሳይሆኑ በህጉ ከባድ ተብለው የተመደቡት የተወሰኑ የወንጀል አይነቶች ብቻ ናቸው፡፡ የመረጃ ማሰባሰቢያ መንገዱን ለመጠቀምም ጥያቄው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መቅረብ መፈቀድ ይኖርበታል፡፡ ምርመራው ለተወሰነ ጊዜ የሚቆይ ሲሆን በትእዛዙ መሰረት ስለመፈጸሙ ፈቃዱን ለሰጠው ፍርድ ቤቱ ቀርቦም ማረጋገጥ ያለበት ነው፡፡ የተፈቀደው የተለየው የምርመራ መንገዱና የሚቆይበት ጊዜም በፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ላይ በግልጽ መመልከት ያለበት ሲሆን ሕገ መንግስቱን በተለይም የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎችን በመጣስ ወይም ከተፈቀደው የምርመራ መንገድ ውጪ የሚገኝ ማናቸውም መረጃ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ በሌላ በኩልም በዚህ ምርመራ ወስጥ የሚሳተፍ መርማሪ በሕገ መንግስቱ የተረጋገጡትን ሰብአዊ መብት ጥሰቶች እንዲሁም ከባድ ወንጀሎችን መፈጸም የማይችል ሲሆን በጉዳዩ ላይ ምስክር መሆን አይችልም፡፡

የልዩ ምርመራ ዘዴ በፌዴራል ከፍተኛ (ወይም ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት) አስቀድሞ በሚሰጥ ትእዛዝ መሰረት የሚፈፀም ቢሆንም እንደ ሽብርተኝነት፣ ሙስና ወይም በሰው ህይወትና ንብረት ላይ ከባድ ጉዳት የሚያስከትሉ ወንጀሎች ለመጋጠማቸው በቂ ጥርጣሬ ሲኖርና አስቸኳይ ሁኔታ መኖሩ ሲረጋገጥ ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ በጠቅላይ አቃቤ ህግ ትእዛዝ ልዩ ምርመራው ሊከናወን ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ትእዛዝ በ72 ሰአት ወስጥ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍድ ቤት ቤቱ ቀርቦ መፅደቅ ይገባዋል፡፡ በተለዩ ወንጀሎች ላይ ብቻ ሊተገበር የሚችለው የልዩ ምርመራ አይነት እና ልኩ በሕጉ ላይ ተለይቶ በግልጽ ተቀምጧል፡፡

በምርመራ ሂደት በመጨረሻ የሚከናወነው መረጃን ከተከሳሹ የማግኘቱ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ በመርህ ደረጃ በፍርድ ቤት ትእዛዝ ተጠርጣሪን በማያዝ ወይም በልዩ ሁኔታ ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ (ለምሳሌ የእጅ ከፍንጅ ወንጀል)

ተጠርጣሪን በማያዝ የሚከናወን ነው፡፡ የቀድሞው ሥነ ሥርአት ሕግ በመርህ ደረጃ ተመሳሳይ ይዘት ያለው ቢሆንም ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ ተጠርጣሪዎች ሊያዙ የሚችሉበትን መንገድ ያሰፋው መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህ በቀድሞው ሕግ በመርህ ደረጃ ከተቀመጠው ጋር የሚጋጭና የሰዎች መብት ላይ ያልተገባ የመብት ጥሰት ሊያስከትል የሚችል በመሆኑ መርሁና ልዩ ሁኔታው በልኩ እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡ ይህ በመሆኑም በልዩ ሁኔታ ተጠርጣሪዎች ሊያዙ የሚችሉበት አግባብ በግልጽ ዝርዝር ብቻ ተመልክቷል፡፡ በዚህ ማስረት ተጠርጣሪ ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ሊያዝ የሚችለው ተጠርጣሪው ሊጠፋ የሚችል ሲሆን ወይም ከሶስት ወር በላይ የሚያስቀጣ የእጅ ከፍንጅ ወንጀል ሲፈፀም የተያዘ እንደሆነ ነው፡፡

ማንኛውም የተያዘ ሰው ቃሉን የማስጠት መብት አለው፡፡ በፖሊስ በተጠየቀ ጊዜም ዝም የማለት መብቱ የተጠበቀ ሲሆን ቃሉን ማስጠት ከሚጠም በምልክትም ሆነ በቃል ቃሉን ማስጠት ይችላል፡፡ በማናቸውም መንገድ ቢሆን ተከሳሹ የሰጠው ቃል በሀይል የተሰጠ ነው የሚል ክርክር የቀረበ እንደሆነ ቃሉ የተሰጠው ከሃይል እርምጃ ወጪ ለመሆኑ መርማሪው የማስረዳት ሃላፊነት አለበት፡፡ ለዚህም ፖሊስ የተጠርጣሪን ቃል ሲቀበል የደረጃ ምስክርን ጨምሮ ሌሎች ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በቃል መቀበል ሂደት ወስጥ እንዲጠቀም ይጠበቅበታል፡፡

በአጠቃላይ የወንጀሉ ባህሪና የምርመራ ሳይንስን ማከተሉ እንደተጠበቀ ሆኖ የወንጀል ምርመራ ተግባራት ከላይ በተቀመጡት መንገዶች ብቻ ሳይሆን እንደቅደም ተከተላቸውም እንዲተገበሩ ይጠበቃል፡፡ በማናቸውም መንገድ ምርመራ ሲከናወንም ሆነ ሲጠናቀቅ ስለምርመራው ፖሊስ ለአቃቤ ህግ የማስታወቅ ግዴታ አለበት፡፡ አቃቤ ሕጉም ከምርመራ ጋር በተያያዘው ኃላፊነቱ የሚሰጣቸውን ትእዛዞች ፖሊስ የሚፈጸም ሃላፊነት አለበት፡፡

## 12.1. የዋስትና ጉዳይ

አንድ ተጠርጣሪ በቁጥጥር ስር ከዋለበት ሰአት አንስቶ ከሚነሱት ጥያቄዎች መካከል የዋስትና ጉዳይ ዋናው ነው፡፡ በመርህ ደረጃ በወንጀል ጉዳይ ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው በዋስትና የመለቀቅ መብት አለው፡፡ ይሁን እንጂ ዋስትና ሊከለከል እንደሚችል በህገ መንግስቱም ጭምር በተደነገገው ማስረት ዋስትና የሚከለከልባቸው ጉዳዮችን ሕጉ ዘርዝሮ የያዘ ሲሆን ከዚህ በፊት በተግባር ይስተዋሉ የነበሩ ክፍተቶችንም ለመሙላት ጥረት አድርጓል፡፡ የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት በአንቀጽ 19(6) ስር የተያዙ ሰዎች በዋስ የመፈታት መብት እንዳላቸው ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ መብት ፍጹም ባለመሆኑ በፍርድ ቤት ሊገደብ እንደሚችል ድንጋጌው በተመሳሳይ ያስገነዝባል፡፡ ፍርድ ቤትም ቢሆን የዋስትና መብትን ሊገድብ የሚችለው በሕግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች ማስረት ነው፡ ስለሆነም የስነ ስርአትና የማስረጃ ህጉ ከዚህ ቀደም በሕግ ዋስትና ይከለከል የነበረበትን ሁኔታ አስቀርቶ

ዋስትና ሊከለከል የሚችለው በሥነ ሥርአቱ ወስጥ በተማከቱ ልዩ ሁኔታዎች ብቻ እንደሆነ ግልጽ ድንጋጌ ይዟል፡፡

ዋስትና በፍርድ ቤት በዚህ ሜልኩ ሊከለከሉ የሚችሉትንም በተማከት የቀድሞው ድንጋጌ ወስጥ ሌላ ወንጀል ይፈጽሜል ተብሎ ሲታሰብ ሊከለከል እንደሚችል የተደነገገው አሁን ከተጠረጠረበት ወንጀል ጋር የሚይያያዝ ወንጀል በማሆኑ ቀሪ ሆኖ ሌሎች መማዘኛዎች ለአፈጻጸም በሚሞች ሜልኩ ዘርዘር ብለውተቀምጠዋል፡፡ በማሆኑም ዋስትና በፍርድ ቤት ሊከለከል የሚችለው ተጠርጣሪው በተፈለገ ጊዜና ቦታ ሊቀርብ አይችልም ተብሎ ሲታመን ወይም ተጠርጣሪውምስክርን ያስፈራራል ወይም ማስረጃን ያጠፋል ተብሎ በበቂ ምክንያት ሲታመን ብቻ እንደሆነ ሕጉ ግልጽ አድርጓል፡፡ በቁጥጥር ስር መዋል የተለየ ሁኔታ በማሆኑ ዋስትና ሊከለከል የሚገባውበእነ ዚህ ልዩ ሁኔታዎች ላይ ሆኖ ከዚህ ወጪያሉ ጉዳዮች ከህግ አንፃር የዋስትና መብት የሚያስከለክሉ አይደሉም፡፡

በዚህ ማሰረት የዋስትና ጉዳይ የተፈቀደ እንደሆነ ሌላው አስፈላጊው ጉዳይ ትክክለኛውን የዋስትና ማጠን መወሰን ነው፡፡ ዋስትና ጉዳይ ሲታይ የወንጀሉ ክብደት፣ የተጠርጣሪውያለፍ ሪከርድ፣ የሕዝብ ጥቅምእንዲሁም ተጠርጣሪው በተፈለገበት ቦታ ሊቀርብ እንደሚችል በሚያረጋግጥ ሜልኩ ማከናወን ይገባዋል፡፡ የተያዘው ሰው የሚጠራውዋስትና በተፈለገ ጊዜ በተፈለገበት ቦት እንዲቀርብ የሚያስገድደውማሆን የሚገባውከማሆኑ አንጻር አጅግም ያነሰ ማጠን ማሆን የሌለበት ሲሆን በዋስ ከመውጣት እንዳይከለክለወም እጅግም የበዛ ማሆን አይገባወም፡፡ ይህንን ትክክለኛ ማጠን የመወሰን ሃላፊነት ዝርዝር ጉዳዩን እየተማከተውያለውፍርድ ቤት ኃላፊነት ቢሆንም ከዚህ ቀደም በነበረውሁኔታ ትክክለኛ ማጠን ባለመወሰኑ ይፈጠሩ የነበሩ ችግሮችን መቀነስ የሚያሰችል አማካች መማዘኛዎች በህጉ ወስጥ እንዲካተቱ ሆኗል፡፡ በሌላም በኩል የገንዘብ ዋስትና ማቅረባ ያልቻለ ተጠርጣሪ የዋስትናውገንዘብ ማጠን ሊሻሻልለት ስለሚችልበት ሁኔታም ተሜልክቷል፡፡ ይህም ማንኛወም ሰው አቅም እያለው በእስር ለመቆየት ይፈልጋል ተብሎ ስላሚይታሰብ ፍርድ ቤት ሁኔታውን ሚርምሮ የዋስትና ገንዘቡን የሚለወጥበት፣ የሚያሻሽልበትን እድል ዝግ ላለሚድረግ በማለምየገባ ነው፡፡

ዋስትና በሚፈቀድበት ማናቸውም ሁኔታ ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሹ በተፈለገ ጊዜ እንዲቀርብ የሚያስገድደውን የራስ ዋስተና የሜፈረም ግዴታ ያለበት ለማሆኑ በቀድሞው ህግ የተቀማጠው ግዴታ አስፈላጊ በማሆኑ የቀጠለ ሲሆን በዋሰ የሚለቀቀውን ሰወና የተጠረጠረበትን ወይም የተከሰሰበትን ወንጀል ግምት ወስጥ በማስገባት ተጨማሪ ገደቦች ሊጣሉበት ይችላሉ፡፡ እነ ዚህ ተጨማሪ ገደቦች የሚንቀሳቀስባቸውን ቦታዎች፣ የሚያገኛቸውን ሰዎች፣ ሊከተለውስለሚገባውባህርይ፣ ከመንግስት አካላት ጋር ስለሚኖረውግንኙነት ወይም ፍርድ ቤቱ ተገቢ

ነው የሚለው ሌላ ገደብ ሊሆን ይችላል፡፡ እነ ዚህ ሁኔታዎች በፍሬ ሕጎች (በወንጀል ሕግ) ላይም የሚምለከቱ ናቸው፡፡

አሁን ባለው አሰራር ተጠርጣሪ በየቦታው (ቢያንስ በምርመራ ጊዜና በፍርድ ሐደት) ዋስትና የሚጠራ በመሆኑ ትርጉም የሌለወን ድግግሞሽም ማስቀረት ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ማሰረት በምርመራ ጊዜ የተሰጠ ዋስትና በተለየ ሁኔታ ፍርድ ቤት ሌላ ዋስትና እንዲጠራ ካላደረገው በስተቀር በፍርድ ሂደትም ሊያገለገግል ይገባዋልና ሕጉ ይህንን የሚምራ ድንጋጌን አካቷል፡፡ በዚህ አግባብም በቀላል አስራት ሊቀጡየ ሚችሉትን ተጠርጣሪዎች መርማሪ ዋስትና መልቀቅ እንዲችል ህጉ ስልጣን ይሰጣል፡፡

ዋስትና በመርህ ደረጃ የተፈቀደ በመሆኑ በዋስትና ለማለቀቅ ጥያቄወን ከታሳሪው ሌላ የቅርብ ሰዎችም ማቅረብ እንዲችሉ እድሉ ሰፋ ብሎ ተደንግጓል፡፡ በዚህ ማሰረት ከታሳሪው በተጨማሪ ወኪሉ ወይም የታሳሪው ቤተሰብ የዋስትና ጥያቄወን ለማኘቸወም ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላሉ፡፡ ጉዳዩ በፍርድ ቤት እየታየ ከሆነ ም ጉዳዩን ለሚምለከተው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላሉ፡፡ በማኘቸወም ጊዜ የዋስትና ጉዳይ በቅድሚያ በአጭር ጊዜ ወስጥ እልባት ሊሰጠውይገባል፡፡

የዋስትና ጉዳይ ካለው ህገ መንግስታዊ እንድምታ አንጻር በጉዳዩ ላይ በሚሰጥ ወሳኔ (በዋስትና ማጠን ላይ የሚኖርን ቅሬታ ጨምሮ) ለበላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ለማቅረብ ይቻላል፡፡

ዋስታና ማሰረታዊ መብት ቢሆንም ማክበሩ እንዲሁም አለማክበሩ ወጤት ሊኖረው ይገባል፡፡ በተለይ በቂ ባልሆነ ምክንያት የማይከበር በሚሆንበት ጊዜ የዋስትናውገንዘብ ለመንግስት ገቢ ስለሚሆንበት ሁኔታ፣ በርካታ ሰዎች ለአንድ ሰውበነጠላና በተናጠል ዋስ ሊሆኑ ስለሚችሉበት ሁኔታና ወጤቱ፣ እንዲሁም ዋስትና ባለማክበሩ የተነሳ ተጠርጣሪውየተወሰነ ጊዜ በእስር ቢያሳልፍ በዚህ ምክንያት የታሰረበት ጊዜ ምናለባት በስተመጨረሻ በእስራት ቢቀጣ የሚታሰብለት ስለሚሆኑ የተማለከቱ ድንጋጌዎች ተካተዋል፡፡

የመያዣ ትእዛዝ ላይ ዋስትና ሊሚለከትና ተጠርጣሪው በዚህ ወረቀት ላይ የተማለከተወን ግዴታ ከፈጸመ በዋስ ሊለቀቅ እንደሚችል፣ አዲስ ፍሬ ነገር ወይንም በማነሳት የተሰጠ ዋስትና ከተገኘም ትእዛዝ እንደገና ሊታይ መቻሉ፣ ዋስትና ባይከበር ሊከተሉ ስለሚገባቸው ወጤቶችና ስርአቶች እና ቀሪ የዋስትና ጉዳዮች ከነባሩ ህግ እምብዛም ለወጥ አልተደረገባቸወም፡፡ የዋስትና ጥያቄ በተቻለው ፍጥነት እና በወዲያውኑ ስሜት ወሳኔ እንዲሰጥበት የሚያስችሉ ድንጋጌዎችም በተማሳሳይ ተካተዋል፡፡

## 12.2. በምርመራ መዝገብ ላይ መወሰን

በወንጀል መዝገብ ላይ የመወሰንን ጉዳይ በተመለከተ ወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው ያስቀመጠውን አቅጣጫ የአገራን ልምድና በተግባር የሚገጥሙችግሮችን መሰረት በማድረግ በርካት ለውጦች በስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ወስጥ እንዲካተቱ ሆኗል፡፡ ምርመራው የተጠናቀቀ የወንጀል መዝገብ በርካታ ወሳዎች ሊተላለፉበት ይገባል፡፡ በዚህ ሚለኩ የሚወሰኑ ጉዳዮች ላይ የመወሰን ስልጣን የዐቃቤ ሕግ ነው፡፡ ከነባሩ የሥነ ሥርአት ሕግ በተለየ ሁኔታም የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ለአቃቤ ሕግ ሰፊ የመወሰን ስልጣንን ይሰጣል፡፡ በነባሩ ሕግ አቃቤ ሕግ ለመከሰስ የሚያበቃውበቂ ማስረጃ ካለ ክስ የመመስረት ግዴታ ያለበት መሆኑ የሚታወስ ሲሆን ይህ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ ግን ይህንን ስልጣን ያሰፋዋል፡፡ በመሆኑም በቂ ማስረጃ ያለበት ጉዳይ ሁሉ የግዴታ ክስ የሚመሰረትበት ሲሆን ከመከሰስ ባሻገር የሕጉን አላማበተሻለ አማራጭማሳካትና የሕዝብ ጥቅም በሌላ አግባብ ማሳካት የሚቻል መሆኑን ሲያረጋግጥ በፍርድ ቤት ክስ ላይመሰረት ይችላል፡፡ በአጠቃላይ አቃቤ ሕግ የወንጀል ምርመራ ማጠናቀቁን ተከትሉ የሚወስናቸውወሳኔዎች፤

- የምርመራ መዝገብን የመዘጋት (በሞት፣ በእድሜ..ምክንያቶች)፣
- የበላይ ኃላፊን ትእዛዝ የማጠየቅ፣
- ከሚከተሉት ምክንያቶች አንዱ ሲያጋጥም የክስ አይመሰረትም ወሳኔ የማስጠት
    - ✓ ጉዳዩ ወንጀል ካልሆነ /በቂ ማስረጃ ባመኖሩ፣
    - ✓ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል፣
    - ✓ ተጠርጣሪ ባለመኖሩ ምክንያት ክሱ በሌለበት የማየ ታይ በመሆኑ፣
    - ✓ ያለመከሰስ ልዩ መብት ያለውተጠርጣሪ የሆነ እንደሆነ ፣
    - ✓ ተከሳሽ ለመከሰስ በሚያስችል እድሜወስጥ ካልሆነ ፣
    - ✓ ጉዳዩ ወንጀል ካልሆነ ፣
    - ✓ ጉዳዩ በይርጋ፣ ይቅርታ፣ በምሕረት፣ በእርቅ፣ በቀደመ ፍርድ የተቋጨከሆነ ፣
- ሜሪ ትእዛዝ የማስጠት፣
- የጥፋተኛነት ድርድር የማድረግ፣
- ጉዳዩ ከመደበኛውፍርድ ቤት ወጪበአማራጭእንዲታይ የመወሰን፣
- አማራጭየመፍትሔእርምጃ የመወሰድ፣

- ጉዳዩን በእርቅ የሚጨርስ፣

ወሳኔ ማስጠት ይችላል፡፡

ዓቃቤ ሕግ መዝገብ ከሚዘጋባቸው ምክንያች ወስጥ አንዱ ጉዳዩ ወንጀል ካልሆነ የሚለው ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ከወንጀል ሕግ ቁጥር 23 ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ዓቃቢ ሕግ የቀረበለትን ጉዳይ ወንጀል የሚያደርግ ሕግ ከሌለ ወይም ክስ ለመማስረት የሚያስችለው በቂ ማስረጃ ከሌለው ወይም የተጠርጣሪወኝ ሃሳብ/ቸልተኝነት የሚያሳይ ማስረጃ ከሌለው ክስ አይማስርትም ማለት ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ በነባሩ ሕግ አንቀጽ 42(1)(ሀ) ስር የተማለከተወኝ መማዛኛ ግልጽ እና ሰፋ ያደረገ ነው፡፡

አቃቤ ሕግ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ወሳኔዎች የሚያሳልፈው በሕግ ማሰረት መሆን ስለሚገባው በስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ወስጥ ለእያንዳንዱ ወሳኔ ማስፈርት ሊሆኑ የሚችሉ ዝርዝር መማዛኛዎች ተቀምጠዋል፡፡ ለምሳሌ አቃቤ ሕግ በቂ ማስረጃ የለም ብሎ ክስ የሚይማስርተው በሕጉ ወስጥ በተማለከቱት የማስረጃ ደንቦች መማዛኛነት ነው፡፡ ለዚህም የማስረጃዎችን አግባብነት፣ ተቀባይነት፣ አሳማኝነት መመርመር ያለበት ሲሆን ማስረጃው ግልጽና የሚታመን መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል ማለት ነው፡፡ ለሕዝብ ጥቅም ብሎ ከስ የሚይማስርትባቸው ጉዳዮችም በወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው ላይ በተቀማጠው አቅጣጫ ማሰረት ጉዳዩ በባህላዊ ስርአት ቢታይ የተሻለ ወጤት የሚያስገኝ ሲሆን፣ ክስ መማስረቱ ያልታሰብ የጎንዮሽ ጉዳት የሚያስከትል ሲሆንና የማሰሉት በሕጉ ላይ የተዘረዘሩ ምክንያቶች መኖራቸው ሲረጋገጥ ነው፡፡ ለህዝብ ጥቅም ሲባል ክስ አይማስርትም ማለት ግን ሌላ አማራጭአይወስድም ማለት አይደለም፡፡ ለምሳሌ ወሳኔወኝ ለበላይ አቃቤ ሕግ የማሳወቅ፣ የግል አቤቱታ ያቀረበ ሰው በግሉ ክስ እንዲማስርት በጽሁፍ የመፍቀድ፣ ጉዳዩ በባህላዊ ስርአት እንዲታይ ማድረግ እና ሌሎች በሕጉ የተማለከቱ እርምጃዎች ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡

በተማሳሳይም አቃቤ ሕግ እያንዳንዱን ጉዳይ የሚወስንበት ከፍተኛው የጊዜ ገደብ በሕጉ ወስጥ ተካቷል፡፡ ይህ የጊዜ ገደብ አሁን በስራ ላይ ያለወኝ ልምድ፣ አፈጻጸም፣ የጉዳዮችን ወስብስብነት እንዲሁም እንደ ከዚህ ቀደሙሳይሆን አቃቤ ህግ እያንዳንዱን ጉዳይ ከምርመራ ጀምሮ በቅርብ እና በተሟላ ሁኔታ የሚያወቀው መሆኑን ግምት ወስጥ ያስገቡ ጊዜያት ናቸው፡፡ የጊዜ ገደቦቹም የሚያማለከቱት እያንዳንዱ ተግባር ተከናወኖ የሚጨረሻው ወጤት ለፍርድ ቤት የሚቀርብበተን ጊዜ ነው፡፡ ይህ ጊዜ ለምሳሌ ድርድር አልቆ ስምምነቱ ለፍርድ ቤት የሚጸደቅ ወጤት የሚቀርብበትን፣ ክስ ተዘጋጅቶ ለፍርድ ቤት የሚቀርብበተን ጊዜ ነው ማለት ነው፡፡ ጊዜው ባይጠበቅ የሚኖረው ወጤት በፍርድ ቤት ተግባራት ወስጥ ለሌሎች ጊዜያት አለማከበር የተማለከተው ወጤት ነው፡፡

## 12.3. የጥፋተኛት ድርድር

የጥፋተኛነት ድርድር በፍትህ ስርአታችን ወስጥ አዲስ ከማሆኑም በላይ አፈጻጸሙ ዝርዝር ድንጋጌዎችን የሚፈልግ በማሆኑ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ዘርዘር ያሉ ድንጋጌዎችን አካቷል፡፡ የዚህ አይነት ድርድር በስርአቱ በሕጉ የተካተተ ከማሆኑም በላይ የጥፋተኝነት ድርደር አፈጻጸም ሥር ከሰደደበት የኮመን ሎው የሕግ ሥርዐት በሲቪል ሎው የሕግ ሥርዐትም እየተተገበረ የሚገኝ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ እንደ ፈረንሣይ፣ ስፔይን፣ ጀርመን፣ ጣሊያንና ፖርቹጋል ያሉ ሃገራት ሥርዐቱን በሕጋቸውወስጥ አካትተውይገኛሉ፡፡ የጥፋተኛት ድርድር ከነቀፋ የፀዳ ባለማሆኑ ነቀፋዎቹን ያገናዘቡ ድንጋጌዎች በሕጉ ወስጥ እንዲካተቱ ሆነዋል፡፡

የጥፋተኛነት ድርድር በዋነኛነት አላማው ጥፋትን ማመንን ተከትሎ ጉዳይን በአጭር ጊዜ በመቋጨት የፍትሕ ስርአቱን ቅልጥፍና ማረጋገጥ ነው፡፡ ድርድር ተከሳሹ በመፀፀት ጭምር ጥፋቱን የሚያምንበትን እድል የሚጨምር በማሆኑ ወጪንና ጊዜን ይቆጥባል፡፡ በተመሳሳይም በመደበኛው ስርአት በማለፋቸው በተጎጂዎች፣ ተከሳሾችና ምስክሮች ላይ ሊደርስ የሚችልን የስነ ልቦና ጫናን ይቀንሳል፡፡ ድርድር በጉዳዩ ፍሬ ነገር ላይ፣ በክስ አይነት፣ ብዛት፣ በቅጣት አይነት፣ እና ማጠን ላይ የሚደረግ ነው፡፡ ሥለሆነም የጥፋተኛነት ድርድር በክስ ላይና በቅጣት ላይ ሊደረግ ይችላል ማለት ነው፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ በክስ ላይ የሚደረግ ድርድርን አስመልክቶ ዝርዝር መመሪያ የማውጣት ስልጣን ያለው ሲሆን በቅጣት ላይ የሚደረግን ድርድር በተማለከተ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ የማውጣት ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ የቅጣት አወሳሰን መመሪያወም ተደራዳሪውበሕጉና በሌሎች ቅጣት ማክበጃና ማቅለያዎች ተገናዝበውሊጣልበት ከሚችለውቅጣት ላይ እስከ አንድ አራተኛ ተቀንሶ ሊጠቀም የሚችልበትን መመሪያ ነው ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንዲያወጣ የሚጠበቀው፡ ለምሳሌ የቅጣ ማክበጃ እና ማቅለያ ምክንያች ሁሉ ተገናዝበው ተጠርጣሪው/ተከሰሹ በሃያ አመት ፅኑ እስራት ሊቀጣ ቢችል በጥፋተኛነት ድርድር በማለፉ ቅጣቱ በተጨማሪ እስከ አስራ አምስት አመት ዝቅ ሊልለት ይችላል ማለት ነው፡፡ ለመመሪያዎቹ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች አመላካች መመዘኛዎችም በሕጉ ወስጥ ተመላከተዋል፡፡

የጥፋተኛነት ድርድር ከሚቀፍባቸው ምክንያቶች ወስጥ ተከሣሹ ወንጀሉን አለሚፈጸመ ቢያወቅም ላለሚታሰር ወይም የእስር ጊዜወን ለመቀነስ ሲል ጥፋቱን ሊያምን ይችላል፣ ከድርድሩ የሚገኘው ወጤት ተከሣሹ ወይም የተከሣሹ ጠበቃ ባለው የመደራደር ብቃትና ዕወቀት ላይ የተማሰረተ በማሆኑ ተመሣሣይ ወንጀል የተፈጸመ ነገር ግን የላቀ የድርድር ዕወቀት ያለወን ጠበቃ ማቅጠር የሚችል ተከሳሽ ከድርድሩ የተሻለ ጥቅም ሊያገኝ ይችላል፣ የጥፋተኝነት ድርድር ተከሣሹ በራሱ ላይ እንዲማሰክር የተስፋ ቃል ማስጠት (የእሥራት ቅናሽ) በማሆኑ ከተከሣሹ በራሱ ላይ ላለመማስከር ያለወን ሕገ መንግሥታዊ መበት የሚጋፋ ይሆናል፤ የሕግ አስፈፃሚ አካላት ሕገ

ማንግሥቱን በመጣስ በተከሣሹ የሚፈጽሙቸው ተግባራት በሚርሁ ተግባራዊነት ሳቢያ ገሀድ ሳይወጣ የሚቀርበት አጋጣሚ ይኖራል፣ ሚርሁ ዐቃቤ ሕግ የሕዝብ ደህንነትን አሳልፎ እንዲሰጥ አጋጣሚን የሚፈጥርና በወጤቱም የወንጀል ሕግ ዓላማን የሚጥስ ይሆናል፤ ድርድሩን የተቀበለ ተከሣሽ ያነሰ ቅጣት እንዲቀጣ፤ ድርድሩን ያልተቀበለ ተከሣሽ ሕገ መንግሥቷዊ መብቱን በማጠቀሙ የበለጠ ቅጣት እንዲቀጣ የሚያደርግ ይሆናል፣ የግል ተበዳዩን ፍትሕ የማግኘት መብት ያላገናዘበና ግልጽነት የጎደለውነውየሚሉ እና የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡

እነዚህን ትችቶች በአብዛኛው ከቁጥጥር ማነስ ይነሳሉ በሚል እምነት የሚነሱ በሚሆኑ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ የተለያዩ የቁጥጥር ስርአቶችን ዘርግቷል፡፡ ከተዘረጉት የቁጥጥር ስርአቶች ወስጥም በመጀመሪያ ደረጃ የጥፋተኛነት ድርድር የሚከሔደው በማናቸወም ወንጀሎች ላይ በአቃቤ ሕግ ወይም በተከሳሽ አነሳሺነት ቢሆንም ድርድሩን ለማድረግ ተከሳሹን ለማስቀጣት የሚያስችል በቂ ማስረጃ ሚኖር ያለበት ማሆኑ፣ ዐቃቤ ሕግ ያዘጋጀወን ክስ ለፍርድ ቤት ማቅረብ ያለበትና በተከሳሽ ላይ ክስ ለመመስረትና ለማስቀጣት የሚያስችል በቂ ማስረጃ ያለው መሆኑን ማሳየት (ፕራይማፋሺያ ኬዝ ያለውመሆኑነ)፣ ተከሳሹ በድርድሩ ለመሳተፍ ሚሉ እና ነጻ ፍቃዱል የሰጠ መሆኑን፣ ድርድሩ ያለጠበቃ መካሔድ የማይችል መሆኑ፣ ስለሂደቱም ሆነ ስለወጤቱ ተከሳሹ በአቃቤ ህግም ሆነ በጠበቃው በማካባ ተገልጾለት የተረዳው ማሆኑን ያለበት መሆኑ፣ በድርድሩ ሂደት ሁሉ በአካል የማኘትና የአሰተርጓሚም ሆነ የጠበቃውያለተቆራረጠ ድጋፍ ሚኖራቸው ሊረጋገጥ ይገባዋል፡፡ የሚቻል እስከሆነ ድረስም የወንጀል ተጎጂውበድርድሩ እንዲገኝ መደረግ ይኖርበታል፡፡

በሌላ በኩልምድርድር የሚደረገውከክስ በፊት ባለ ጉዳይ ላይ ቢሆንምክስ እና የክስ መገለጫውጉዳዩን ለማየት ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ሊቀርብ ይገባዋል፡፡ ይህም አቃቤ ሕግ በቂ ማስረጃ ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያግዝ ከመሆኑምበላይ ድርድሩ ባይሳካ ክርክሩን ወዲያወኑ ለመቀጠል ያግዛል፡፡ ጥፋትን ማመን የክስ ወይም የቅጣት ተጠቃሚየሚያደርግ መሆኑ እስካሁን ባለውመደበኛውስርአትም የሚስራበት ከመሆኑ አንፃር የሚነሱት ቅሬታዎች ምን ያህል ሚዛናዊ ናቸውየሚል ጥያቄ ያስነሳል፡፡ ሌሎች በተግባር ይገጥማሉ የሚባሉት ችግሮች እንዳያጋጥማም የአቃቤ ሕግ፣ የጠበቃ፣ የተከሳሽ እንዲሁም የፍርድ ቤትን ኃላፊነት ግልፅ፣ ዝርዝርና ጥብቅ እንዲሆን አድርጓል፡፡ ክስን ከመቀበል አንስቶ ድርድሩን እስከ ማጽደቅ ድረስ ፍርድ ቤትም ጠበቅ ያለ ቁጥጥር የሚያደርግበትን ስርአት ሕጉ ዘርግቷል፡፡

የድርድር ስርአት ቁጥጥር ከሚደረግባቸው መንገዶች ወስጥ ሌላው የሚጠቀሰው የተወሰኑ ድርጊቶች (ለምሳሌ ማደለል፣ ያልተገባ ቃል መግባት፣ መዋሸት፣ ማጋነን…) በድርድር ጊዜ የተከለከሉ መሆናቸውነው፡፡ ደርድር

ለተቀማጠለት አለማእንጂ ለሌላ አላማ ለምሳሌ ማስረጃን ከተቃራኒው ወገን ለማግኘት፣ የሚያዋጣውን የክርክር መድረክ ለማምረጥ ወዘተ መዋል አይገባውም፡፡ ለዚህም ለምሳሌ ድርድርን ምክንያት በማድረግም ማስረጃ በማናቸውም ወገኖች የማግኘትን ያልተገባ ድርጊት ለመቆጣጠርም በድርድር ሂደት የተገኘ ማስረጃ በፍርድ ሂደት በማስረጃነት ሊቀርብ እንደማይቻልም ተደንግጓል፡፡ ድርድር ተፈጻሚ የሚሆነው ከህጉም ሆነ ከሞራል ጋር የማይጋጭ ስምምነት ተደርሷል ብሎ ጉዳዩን የሚመለከተው ፍርድ ቤት ሲያጸድቀው ሲሆን ፍርድ ቤቱ ድርድሩን የሚያጸድቀው ከሆነም ድርድሩን እንደገና የማድረግ ወይም የተለዩትን ችግሮች ማስተካከልን ጨምሮ ጉዳዩን በይግባኝ ማየትም ተፈቅዷል፡፡

በአንድ ጉዳይ ላይ ከሁለት በላይ ተከሳሾች ሲኖሩ ከፊሉ ተከሳሾች በድርድር ለማስተፍ ከፊሉ ደግሞ ክርክሩን በመደበኛው ስርአት ለሜጨረስ የተለያየ ፍልጎት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ምንም እንኳን በጠበበ እድል ቢሆንም በድርድር ስርአት ያለፈው በአነስተኛ ቅጣት ሲቀጣ በመደበኛው ስርአት ያለፈው ማስረጃ በመጥፋቱ፣ በማከኑ ወይም በማሳሰሉት ምክንያቶች በነፃ ሊሰናበት ይችላል፡፡ ይህ ሁኔታ በሚያጋጥምበት ወቅት የፍትሕ ስርአቱን ለመርዳት በድርድር ያለፈው በተለየ ሁኔታ ሊጎዳ የሚገባው አይሆንም፡፡ ፍትሐዊነት የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ አላማ ከመሆኑም በላይ በፍርድ ቤት ጥፋተኛነቱን ያመነ ግለሰብ እንኳን ጥፋተኛነቱ ተነስቶለት ማስረጃ ተሰምቶ ውሳኔ የሚሰጥበት አጋጣሚን ሕጉ ዝግ አላደረገውም፡፡ በተመሳሳይም ይግባኝ ባይሉም ይግባኝ ባሉ ፍርድኞች ላይ በተሰጠ ፍርድ ይግባኝ ያላሉ ሰዎችም ሊጠቀሙ እንደሚችሉ የቀድሞውም ሕግ ድንጋጌን አካቷል፡፡ እነዚህን ሁሉ ምክንያች ስንመለከታቸው በድርድር ያለፈ ሰው በመደበኛው ስርአት ቢያለፍ የሚቀርብበት ማስረጃ አንድ አይነት እና ተመሳሳይ ቢሆንና በድርድር ባያልፍ ኖሮ በመደበኛው ስርአት እንዳለፉት በነፃ ይሰናበት ነበር የሚል መደምደሚያ ላይ ፍርድ ቤቱ ከደረሰ በተደራዳሪው ጥያቄ የድረድሩ ውጤት ተነስቶ በሌሎች አብረው በተከሰሱት ሰዎች ላይ የተሰጠው ውሳኔ ተደራዳሪው ሊጠቀም የሚችልበትንም እድል ሕጉ ደንግጓል፡፡ ይህ አማራጭ የድርድር እድልን የሚያሰፋ ሲሆን ለነቀፌታዎችም ሚዛናዊ ምላሽ ይሰጣል፡፡

## 12.4. አማራጭ መፍትሔዎች

አቃቤ ሕግ ሊወስናቸው ከሚችላቸው ውሳኔዎች ወስጥ በቂ እወቀት ያለውን ባለሙያ ምክር፣ የተጎጂውን ፈቃድ እና የሚመለከታቸውን አካላት ምክር በመቀበል ጉዳዩ በመደበኛው የክርክር ማስመር ከሚቋጭ ይልቅ በሌሎች አማራጭ መንገዶች እንዲታዩ ማድረግ ይገኝበታል፡፡ የአማራጭ እርምጃ የሚወሰደው ከመደበኛው የፍርድ ሂደት በአማራጩ መንገድ በተሻለ ሚልኩ ለበዳይ፣ ተበዳይ እና አካባቢው ማሕበረሰብ ዘላቂ ሰላም ለማስፈን ይጠቅማል፣ የፍትሕ አካላትን ጊዜ መቆጠብ ይቻላል፣ በዚህም የፍትህ አካላቱ የበለጡ ከባድ ጉዳዮች ላይ በማተኮር ይበልጥ ወጤታማ

ይሆናሉ፣ ተያይዞም በስተሜጨሻ በሚኖቸውም አግባብ የሕዝብን ጥቅም ማስጠበቅ የሚቻል መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡ እነዚህ መንገዶች የእርቅ ስርአትን፣ ባህላዊ ስርአትን እና የጥፋተኛት ድርድርን የሚሞከቱ ናቸው፡፡ በሚኖቸውም ደረጃ ያለን ጉዳይ በአማራጭ ስርአት በተከራካሪ ወገኖች አሜካችነት (በፍርድ ቤት አነሳሽነትም) ማየት ይቻላል፡፡ የእርቅ ስርአት ተፈጻሚ የሚሆኑባቸው ጉዳዮች በግል አቤቱታ የሚያስቀጡና በቀላል እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች ሲሆኑ ሚኖቸውም ጉዳዮች በባህላዊ ስርአት ታይተው እልባት ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ ይሁን እንጂ ሚኖቸውም ስርአት ማስረታዊ መብቶችን የሚጥስ ለመሆኑ ሚጋገጥ አለበት፡፡ ለዚሁ ስርአት በዳይና ተበዳይ ግልሰቦች በሚይሆኑበት ጊዜም ስርአቶቹን ተጋባራዊ ማድረግ የሚቻል አይደለም፡፡ በሌላም በኩል እንዚህ መንገዶች በደጋጋሚ ወንጀለኛ፣ በቅርብ በተቀጣ ወይም በአማራጭ መፍትሔ ወስጥ ባለፈ ሰው ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡ በእርቅና በባህላዊ ስርአት ያለፉ ጉዳዮች ከእነዚህ መመዝኛዎች በተጨማሪ ለሕግና ለሞራል የሚይቃረን አካሄድ ተከትለው በተመሳሳይ ማስኪያ ወጤት ላይ የደረሱ መሆናቸው ሲረጋገጥ በፍርድ ቤት ቀርበው የሚጸድቁ ሲሆን በዚህ ሜሉ የጸደቁ መፍትሔዎችም ይግባኝ የሚይባልባቸው ከመሆናቸው በቀር በአንድ የወንጀል ፍርድ ቤት የተሰጡውሳኔዎች ያላቸውውጤት ይከተላቸዋል፡፡

ከአማራጭ መንገዶች ጋር ተያይዞ ሌላው መታየት ያለበት ጉዳይ የሌሎች መፍትሔዎች ጉዳይ ነው፡፡ በወንጀል የተጠረጠሩ ሰዎች በእድሜያቸው፣ በአካል ወይንም በአእምሮ ጤንነታቸው ወይም ለተለዩ ሱሶች የተጋለጡ ከመሆናቸው የተነሳ የወንጀል ፍትሕ ሂደቱን (አማራጭ መንገዶችን ጨምሮ) በሚገባ መከታተል የሚይችሉ ከመሆናቸውም በላይ በስተሜጨሻ የሚደረስበት መደምደሚያም ለተለየ ሁኔታቸው ተስማሚ ላይሆን ይችላል፡፡ የአእምሮ ህመማንን በየትኛውም ስርአት ማካለፉ የወንጀል ሕግን አላማ ከማካካት አንጻር ለውጥ አያመጣም፡፡ እንደዚህ አይነት ሰዎች በወንጀል ጉዳይ ላይ ጥፋተኛ ቢባሉ እንኳን በመደበኛው የሚረምስርአት ወስጥ አልፈው ታርመው ወደ ህብረተሰቡ መቀላቀል የሚቻገሩ/የሚይችሉ ስለሚሆኑ የሚያስፈልጋቸውእንደ ህክምና፣ ሊያድሳቸው የሚችል የቀለም የሙያ ማሰል ትምህርቶችና ስልጠናዎች ማስጠት፣ ምክርና ተግሳጽ፣ በአንድ በተወሰነ ቦታ/አካባቢ ማቆየት፣ እና በሌሎች ሕጎች ሊሜከቱ የሚችሉ ሌሎች መፍትሔዎች ናቸው፡፡ ይህ ስርአት በነባሩ ሕግ ወስጥ ያልነበረ በመሆኑ የፍትሕስርአቱ እንደነዚህ አይነት ሰዎችን ለመርዳ ሲቸገር ቆይቷል፡፡

አማራጭ መፍትሔ ተለዋጭ እርምጃ መወሰድን የሚጠይቅ በመሆኑ የባለሙያ የቅርብ ክትትል፤ መፍትሔውን የሚያስፈጽሙ አከላት በብቃት የሚደራጀት፣ በየጊዜው የተሻሉ መፍትሔዎችን እየቃኙ ለአጥፊው እርምት በሚስማማው ሜልከ የሚስተካከልን፣ መፍትሔው ባለተፈጸመ ጊዜም ሊወሰዱ ስለሚገባቸው ቀጣይ እርምጃዎች እንዲሁም እርምጃው በአግባቡ ተፈጽሞ ለማጠናቀቁ እያጠና ሃሳብ የሚያቀርብ ባለሙያ ወይም ተቋም

ያስፍልገዋል፡፡ ይህ ተቋም ራሱም በቻለ ሕግ የሚቋቋም ሲሆን ከፍትሕ አካላት በተወጣጣ ቦርድ የሚመራ ተቋም ይሆናል፡፡

ሌላ መፍትሔየሚፈልጋቸውሰዎች ከእርቅ ስርአትም ሆነ ከባህላዊ ስርአት ሊማጡየሚችሉ በመሆኑም ከእነ ዚህ አካላትም በወንጀል ጉዳይ ተመሳሳይ መፍትሔየሚፈልግ ጉዳይ ከገጠማቸው በዐቃቤ ሕግ በኩል ወደዚሁ መፍትሔ ሰጪአካላት ሊልኩ ይችላሉ፡፡ መፍትሔወም የሕግ ወጡቅ እንዲኖረወና ከግለሰቦች ሁኔታ ጋር ተለማጭ ሆኖ እንዲፈጸምበአቅራቢያውባለ ፍርድ ቤት ቀርቦ መመዝገብ ይያገባዋል፡፡

እነ ዚህ መፍትሔዎች በባለሙያ ታግዘውማስጠት ያለባቸውናቸው፡፡ በአይነ ታቸውበርካታና በቁጥራቸውም የበዙ ሊሆን ስለሚችሉ በዚሕ ሚልኩ መፍትሔየሚሰጡተቋማትን እንዲሁም ስለዝርዝር አሰራራቸው ጠቅላይ አቃቤ ሕግ በጥናት ላይ የተማሰረተ እወቅና ይሰጣል፡፡

## 12.5.ክስ የመማሰረት ወሳኔ

አቃቤ ሕግ በምርመራ መዝገብ ላይ ሊወስናቸው ከሚችላቸው ወሳኔዎች ወስጥ ሌላው በመደበኛው ፍርድ ቤት ክስ መማስረት ነው፡፡ እንደቀደመው ሕግ ሁሉ ክስ ለመማስረት ተከሳሽን ጥፋተኛ ሊያሰኝ የሚያስችል በቂ ማስረጃ መኖረን ሚረጋገጥ በቂ ነው፡፡ በቂ ማስረጃ የሚባለው በማስረጃ ምዝና ደንብ ማሰረት ተከሳሽን ጥፋተኛ ሊያስብል የሚችል ማስረጃ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ተከሳሽን ጥፋተኛ ሊያሰኝ የሚያስችል በቂ ማስረጃ ቢኖርም በተወሰነ ሚልኩ ክስ መማስረቱ የህዝብን ጥቅም ሊጎዳ የሚችል ሚሆኑ ከተረጋገጥ ክስ ላይማስረት ይችላል፡፡ የሕዝብ ጥቅም ማለኪያ ዋና ዋና ማስፈርቶች በወንጀል ፍትሕ ፖሊሲውወስጥ ተሚልከተዋል፡፡ እነ ዚህ ማስፈርቶች ክስ የሚይማሰረትባቸወንና አማራጭ መፍትሔ የሚወሰድባቸወን አጣምረው የያዙ በሚሆናቸው በስነ ስርአትና ማስረጃ ህጉ ተለይተውእንዲቀማጡሆኗል፡፡ በሕዝብ ጥቅም ማ ሻነ ት የአቃቤ ህግ የመወሰን ስልጣን ከፍ ሲል የተማለከተው ቢሆንም በተወሰኑ ወንጀሎች ላይ የሕዝብ ጥቅም አለ ተብሎ ከወዲሁ ስለሚታሰብ (ለምሳሌ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 28 ስር በተማለከቱ ወንጀሎች) **በቂ ማስረጃ ካለ አቃቤ ሕግ በቀጥታ የወንጀል ክስ ስልጣን ባለውፍርድ ቤት እንዲያቀርብ ይገደዳል፡፡**

የህዝብ ጥቅምየሚባለውበነባሩ ሕግ ወስጥ ተካቶ የነበረ ቢሆንምበኋላ ላይ የተሻረ ሚሆኑ ይታወቃል፡፡ አንዱ ምክንያት በተቻለ ማጠን በግልጽ ባለመቀማጡየሚፈጠሩ ችግሮች ናቸው፡፡ የህዝብ ጥቅም የሚባሉት በአግባቡ በሕጉ ላይ ካልተማለከቱ ለአፈጻጸም አስቸጋሪ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በስልጣን አላግባብ ማ ልገ ልንም ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡ ስለሆነ ም ዝርዝራቸወን ለመመሚያ ወይንም ሰፋ ላለ አገላለጽ ከሙተው በተቻለ ማጠን ጠበው

የሚታዩበትን አግባብ ሕጉ በግልጽ ድንጋጌ አስቀምጧል፡፡ በዚህ ማስረትም ክስ ላለመመስረት የህዝብ ጥቅም አለ የሚሰኘው በጉዳዩ ላይ ክስ ለመመስረት የሚስችል በቂ ማስረጃ ቢኖርም ተጠርጣሪው የፈጸመው የወንጀል ድርጊት በባሕላዊ ሕጎችና ተቋማት በተሻለ ሁኔታ መፍትሔ የሚያገኝ እንደሆነ፣ ክሱ ቢመሠረት ዓለም አቀፍ ግንኙነትን ወይም ብሐራዊ ደኅንነትን የሚጎዳ እንደሆነ፤ ወንጀሉ በማንኛውም ምክንያት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ሳይቀርብ በመቆየቱ ወቅታዊነቱን ወይም አስፈላጊነቱን ያጣ እንደሆነ እና የክሱ መመሥረት ከፍ ያለ የኅንዮሽ ጉዳት የሚያስከትል እንደሆነ ብቻ ነው፡፡

አቃቤ ህግ በውሳኔው ጉዳዩ በፍርድ ሂደት እንዲያልቅ ሲወስን ክስ በማኛቸውም ጊዜ በጽሁፍ የማቅረብ ግዴታ ያለበት ሲሆን ክሱ ስለሚይዛቸው ጉዳዮች አፈጻጸም ወጥነት ሲባልም በክስ ማመልከቻ ወስጥ ሊካተቱ የሚገባቸው ጉዳዮች በስነ ስርአትና ማስረጃ ህጉ ወስጥ በዝርዝር እንዲካተቱ ሆነዋል፡፡ በዚህ ሂደትም የክስ ማመልከቻ ዝግጅት ከነባሩ ህግ ያለተለየባቸው ሁኔታዎች ቢበዙም በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ግን ለወጥ ተደርጓል፡፡ ለምሳሌ ክሶችንም ሆነ ተከሳሾችን አጣምሮም ሆነ ነጣጥሎ ማቅረብ/መክሰስ ስለሚቻልበት ሁኔታ በህጉ ወስጥ ተመላክቷል፡፡ ክስን በአነስተኛ ክስ በአማራጭ ማቅረብ የሚቻል ሲሆን ማስረጃው ባረጋገጠው ልክ እንደአግባቡ በአነስተኛ ወንጀል (መካራ፣ አነሳሽነት፣ አባሪነት...) ተከሳሽን ጥፋተኛ ለማለት ይቻላል፡፡

ክስ የሚቀርብበት የጊዜ ገደብም እንደ ወንጀሉ ክብደት ተደንግጓል፡፡ የጊዜ ገደቡ መደበኛውን የይርጋ ጊዜ የሚይተካ ቢሆንም የጊዜ ገደቡ አለመከበር ወጤት አልባ መሆን የሚይገባው በመሆኑ ክስ ባለመመስረቱ ምክንያት ከእንቅስቃሴ ወጪ የሆኑ ወይንም እንቅስቃሴቸው የተገደቡ ሰዎቸ እና ንብረቶች ላይ ወጤት እንዲኖረው በሚያስችል አግባብ ተደንግጓል፡፡

አቃቤ ሕግ የሚያቀርበው ክስ አማራጮችን ሁሉ ያለፈ በመሆኑ የተሻለ ጥራት ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ይሁን እንጂ በተለያዩ ምክንቶች ክስ የተሻሻለ፣ የተለወጠ ወይም የተጨመረ እንደሆነ ጉዳይ በሕገ መንግስቱ ከተረጋገጠው የተከሳሽ መካላከል መብት ጋር በቀጥታ የሚገናኝ በመሆኑ የወንጀል ሂደቱ ከክስ መስማት አንስቶ በአዲስ መልክ ይካሔዳል፡፡

አቃቤ ህግ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ክስ ለመመስረት ያልፈቀደ እንደሆነ የግል አቤቱታ አቅራቢ (እርሱም የሌለ እንደሆንም እንደቅደም ተከተላቸው የግል ተበዳይ ሚስት/ባል፣ ወላጅና ልጅ) ክስ እንዲመሰርቱ፣ በግል ክስ ሊቀርብ የሚቻለውም በግል አቤቱታ ብቻ በሚያስቀጡ ወንጀሎች ቢሆንም ምርመራው ተጠናቆ ተከሳሽን ጥፋተኛ ሊያሰኝ የሚችል በቂ ማስረጃ መኖሩ በአቃቤ ሕግ ተረጋግጦ ለመክሰስ ፈቃድ ሲሰጥ መሆኑ፣ የግል ክስ አቅራቢ

የመክሰስ ስልጣን ሲፈቀድለት እንደ አቃቤ ሕግ ክሱን በሙሉ ኃላፊነት ማምራትና ማከታተል ለበት መሆኑ፣ ፍርድ ቤትም የግል ክስ ክርክር ከመቀጠሉ በፊት በተቻለ ማጠን ከሳሽንና ተበዳይን ለማስታረቅ ጥረት ሚድረግ ወይንም እድሉን ማስጠት የሚ ባውለመሆኑ የግል አቤቱታ ክስ አቅራቢ መብቱን ከስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ አላማ ወጪ የተጠቀማበት ሆኖ ከተገኘ ወይንም ስልጣኑን ላልተገባ ተግባር ከተጠቀማበት ወይንም በሂደቱ በግል አቤቱታ የሚያስቀጣ ሳይሆን ከፍ ያለ ወንጀል ሚፈጸሙ የሚያማከቱ ማስረጃዎች ከተገኙ ዐቃቤ ሕግ የግል ከሳሽን ተክቶ ክርክሩን ሊቀጥል የሚቻል ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡

ከክስ ጋር ተያይዞ ሌላው በሕጉ ወስጥ የተካተተው ጉዳይ ከወንጀል ክስ ጋር ተጣምሮ ሊቀርብ የሚችለው የፍትሐብሔር ክስ ነው፡፡ የፍትሐብሔር ክስ ከወንጀል ጉዳዩ ጋር ተጣምሮ እንዲታይ በአቃቤ ሕግ ወይም በተጎጂ አማካኝነት ለወንጀሉ ጉዳይ ፍርድ ቤት ሊቀርብ ይችላል፡፡ ተጎጂው ሕጻን፣ ሴት፣ ድሀ ወይም አቅመ ደካማ ከሆነ ም የጉዳት/የኪሳራ ካሳ ክሱን አቃቤ ሕግ የማቅረብ ግዴት ተጥሎብታል፡፡ የወንጀሉም ሆነ የፍትሐብሔር ጉዳዮች በተቻለ ማጠን ተሳልጠው እንዲታዩ ይጠበቃልም፡፡ ያም ሆኑ ጉዳዮቹ ከመወሳሰባቸው የተነሳ በተለይ በተጎጂውመብትና በተከሳሽ ማካላከል መብት ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ከሆነ ፍርድ ቤቱ ሁለቱ ጉዳዮች ተነጣጥለው እንዲታዩ ትእዛዝ ማስጠት የሚያስችለው ድንጋጌም ተካቷል፡፡ በህጉ ላይ የተማለከቱት የፍትሐብሔር ጉዳዮች አሜራርንም በተማለከት ከክስ መማስረት አንስቶ ወሳኔ እስከማስጠትና ወሳኔወን እስከ ማስፈጽም ድረስ ያሉት ጉዳዮች የሚሙት የፍትሐብሔር ጉዳዮች በሚሙበት ሕግና ደንብ ማስረት አንዲሆን ሕጉ ግልፅ ድንጋጌ ይዟል፡፡

## 13. ዳኝነት ነክ ጉዳዮች

በ1954 የወጣው የሥነ ሥርአት ሕግ የፍርድ ቤትን ጉዳይ በተማለከተ የያዛቸው ጉዳዮች ወሱን እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይህ በመሆኑም ፍርድ ቤትን የተማለከቱ በርካታ ሕጎች ከሥነ ሥርአት ሕጉ በኋላ ወጥተው ከስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ጋር ጎን ለጎን በሚፈጸም ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህ ሁኔታም ሕጎቹን በአግባቡ ለማጠቀም የሚያስችል በመሆኑና በአንድ ማጠቃለል የሚያስፈልግ ከመሆኑም በላይ ሕጎቹ አለማቻቸንና አገራችን የደረሰችበትን እድገት በሚያገናዝብ ሜልኩ መቃኘት ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ አንጻር የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ቀድሞ የወጡትን ሕጎች ወደ አንድ ከማሰብሰቡም በላይ ይህንን እድገት ያገናዘቡ ድንጋጌዎችን አካቷል፡፡ የሚከተሉት ክፍሎች ይህንን ያማለክታሉ፡፡

## 13.1 የዳኝነት ሥልጣን

የዳኝነት ስልጣን የመጀመሪያ ገጽታው የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የሚኖራቸውን ስልጣን (ጁዲሺያል ጁሪስዲክሽንን) የተመለከተው ነው፡፡ ይህ ስልጣን በነባሩ የሥነ ሥርአት ሕግ ወስጥ ዘርዘርና ግልጽ ብሎ ያልተመለከተ ነው፡፡ በሌላ በኩል የወንጀል ሕጉ ይህንን ጉዳይ የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን አካቷል፡፡ ጉዳዩ የሥነ ሥርአት ጉዳይ በመሆኑና የአሁኑም የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግም እንደ መጽሃፍ የተሟላ መሆን ስለሚገባው ይህንንም ጉዳይ የተመለከቱ ድንጋጌዎችን አካቷል፡፡ በዚህ መሰረት የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች በዋነኛነት በኢትዮጵያ ግዛት ወስጥ በተፈጸመ ወንጀል ላይ፣ ወደ ወጪ በሚዳዝዝ መዳዝዣ ላይ በሚፈጸም ወንጀል ላይ፣ በወንጀል ሕጉ ቁጥር 238-260፣ 355፣ 374 በመጠስ የተፈጸሙ ወንጀሎች ላይ፣ የሚደፈር መብት ያለው ኢትዮጵያዊ በወጪ በሚፈጽመው ወንጀል ላይ፣ የኢትዮጵያ ወታደር በወጪአገር በሚፈጽመው ወንጀል ላይ፣ ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች በመጠስ በሚፈጸም ወንጀል ላይ እንዲሁም የወጪሃገር ፍርድ ማስፈጸምን በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ የዳኝነት ስልጣን (ጁዲሺያል ጁሪስዲክሽን) አላቸው፡፡

የዳኝነት ስልጣን ሌላው ጉዳይ ሃገሪቱ የምትከተለው ቅርጸ መንግስት ጋር የተያያዘ ሆኖ የስረ ነገርንና የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ስልጣንን የሚመለከት ነው፡፡ የወንጀለኛ መቅጫሕግ ሥነ ሥርዐት በ1954 ዓ.ም በወጣበት ጊዜ ኢትዮጵያ ፍፁም አሃዳዊ አወቃቀር በሚከተል ስርአትና መንግሰት ትመራ ነበር፡፡ በመሆኑም የፍርድ ቤቶች አወቃቀርና ሥልጣንም ይህንኑ አሃዳዊ አወቃቀር የተከተል ሲሆን የፍርድ ቤቶችም ግንኙነት ከላይ ወደታች ወይም ከታች ወደ ላይ ብቻ ነበር፡፡ ይህ አሃዳዊ አወቃቀር እስከ ደረግ መውደቅ (1983) ድረስ ሲሰራበት የቆየ ቢሆንም የደርግ ከስልጣን መወገድን ተከትሎ የአገሪቱ ፖለቲካዊ አወቃቀር ወደ ፌደራላዊ ቅርፀ መንግሥት ማለወጡ ይታወቃል፡፡ በኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 1 መሰረትም የአገሪቷ ስያሜ "የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ" ሆኗል፡፡ ፌደራላዊ አወቃቀሩን ተከትሎም ፍርድ ቤቶች በፌደራልና በክልል መንግስታት ወስጥ በወረዳ፣ ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ደረጃ ተዋቅረዋል፡፡ የክልል ፍርድ ቤቶች ራሳቸውን ችለው በየክልሉ የተቋቋሙ ሲሆን የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተሞችና በጋምቤላ፣ ቤኒሻንጉል፣ አፋር፣ ሶማሊያ እና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልሎች በአዋጅ ቁጥር 322/95 መሰረት ተደራጅተዋል፡፡ የተቀሩት ክልሎች ማትም የትግራይ፣ አማራ፣ ሐረሪ እና ኦሮሚያ ፍርድ ቤቶች በሕገ መንግስቱ መሰረት ወክልና የፌደራል ዳኝነት ስልጣን አላቸው፡፡

የአገሪቱ ፍርድ ቤቶች የፌደራሉን አወቃቀር ተከትለው የተቋቋሙ ከመሆኑ አንጻር በርካታ ጥያቄዎች ይነሳሉ፡፡ የወንጀል ሕግን የማውጣት ስልጣን የፌደራል መንግስት ስልጣን እንደመሆኑ መጠን የወንጀል ጉዳዮችን የመዳኘት

ስልጣን የየትኛው ፍርድ ቤት ነው? የፍርድ ቤቶችን ስልጣን እንዴት ማየት ይቻላል? የፌዴራል መንግስት ሕግ ባላወጣባቸው የወንጀል ጉዳዮችስ? የፌደራል መንግሥት የሚያወጣው የወንጀል ሕግ ከአዲስ አበባና ድሬዳዋ ውጭ እንዴት ይፈፀም? የሚሉና ማስል ጥያቄዎች ይነሳሉ፡፡ ከፍ ሲል እንደተማለከተው ሕገ መንግስቱ በሰጠው ውክልና ማሰረት ክልሎች የፌዴራል ወንጀል ጉዳዮችን በውክልና መሚልከት ይችልሉ፡፡ በሌላ በኩልም አዋጅ ቁጥር 25/88 በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የወንጀል ስልጣን ስር የሚወድቁ ጉዳዮችን የሚዘረዝር በመሆኑ ቀሪ ጉዳዮችን ክልሎች ሊማለከቱ ይችላሉ፡፡ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 7 ማሰረት ከአዋጁ ጋር የሚጋጩ በሥራ ላይ ያሉ የወንጀለኛ መቅጫሥነ ሥርዐት ሕግ እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎች ተፈፃሚነት የሚኖራቸው በመሆኑ በአዋጅ 25/88 ባልሸፈነው ጉዳይ ከዚህ በፊት የወጡት የወ/መ/ሕ/ስ/ስ አንቀጽ 4 እና በዚሁ ሥነ ሥርዐት አንደኛው ሰንጠረዥ ሦስተኛው አምድ የተዘረዘሩት የፍርድ ቤቶች ሥልጣን እና ደንብ ቁጥር 17/67 የሚፈፀማበት አግባብ ይኖራል ማለት ነው፡፡ ከእነዚህ የቀደሙት ህጎች በተጨማሪ አዋጅ ቁጥር 25/88 ለማሻሻል በተከታታይ የወጡ ሕጎች (አዋጅ ቁጥር 25/1988፣ 138/1991፣ 254/1993፣ 321/1995፣ 322/95፣ 454/1995) እንዲሁም በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተለያዩ ጊዜያት የተሰጡ የሰበር ውሳኔዎች የፍርድ ቤቶች ጉዳይ ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ ማለት ነው፡፡

ይህም የፍርድ ቤቶችን አደረጃጀት ወስብስብ፣ በቀላሉ ለማጠቀም የሚይመችና ግልፅነት የጎደለው የሚያደርግ ሲሆን የፍርድ ቤቶቹን ስልጣን በአንድ ሕግ ተጠቃሎ እንዳይገኝና የሕግ አስፈፃሚዎችም (ዳኞችና፣ አቃብያነ ሕግ፣ ፖሊስ፣ አጠቃላይ ሕብረተሰቡ) የፍርድ ቤትን ስልጣን በቀላሉ እንዳይለዩ ያደረገ ነው፡፡ በሌላ በኩልም በነባሩ የሥነ ሥርአት ህግ አንቀፅ /106/ መሠረት አንድ ወንጀል ፈፅሞ የተከሰሰ ሰው የሚዳኘው ወንጀሉ በተፈፀማበት አካባቢ በማገኝ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ይህ በወንጀል ምርመራም ሆነ በአቃቤ ሕግ ስራዎች ላይ ያለው ትርጉም የነባሩ ሥነ ሥርአት ሕግ አይመልስም፡፡

በወንጀል ፍትሕ ሂደት ወስጥ በአዲስ አበባና ድሬዳዋ ማስተዳድር ፍትሕ ተቋማት እና በፌዴራል መንግሥቱ የሥልጣን ክፍፍል እና በክልል ፍትሕ ተቋማት መካከል ሊኖር ስለሚገባው የትብብር እና የግኑኝነት ሥርዓት ግልጽ ድንጋጌዎችን ነባሩ ሕግ ያላካተተ በመሆኑ ተጨባጭችግሮች እየተፈጠሩ ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚሠጡ ትዕዛዞችን፣ ብይኖችን እና ውሳኔዎችን የክልል ፍትሕ አካላት ለሚፈፀም በሕግ የሚገደዱበትን ሁኔታ በሥነ ሥርዐት ሕጉም ሆነ በሌሎች ሕጎች ወስጥ አልተካተተም፡፡ በዚህም ምክንያት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ወንጀለኞችን አስመልክቶ የሚሰጡ የተለያዩ ውሳኔዎች አፈፃፀም ሳንካ እየገጠማቸው በወንጀል ደርጊት የተጠረጠሩ ግለሰቦች ለሕግ ሳይቀርቡ ተመልሰው ህብረተሰቡ ወስጥ በመግባት የኅብረተሰቡን

ሰላምና ጸጥታ የሚያወኩበት ሁኔታ እንዳይፈጠር ማድረግ ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ አልፎ አልፎ ችግሮች ያጋጥማሉ፡፡ በመሆኑም የወንጀል ጉዳዮችን አስመልክቶ በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ የክልል ፍርድ ቤቶች የሚሰጡት ፍርደች ፣ ትእዛዞች፣ ብይኖችና ወሳኔዎች በሌሎች ክልሎች የሚገኙ ፍርድ ቤቶች እውቅና ለማስጠት እና ለማስፈጸምየሚያደርጉበት ሕጋዊ ሥርአት ማንባት ይስፈልጋል፡፡

አገራችን የፌዴራል ስርአትን የምትከተል ከመሆኑ አንፃር የሥነ ሥርአት ሕጉ ያሉበትን ክፍተት ለመሙላት ይህ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ የፌዴራል ቅርፀ መንግስትን ግምት ወስጥ በማስገባት የወንጀል ዳኝነት ስልጣንን በሕገ መንግሰቱ አግባብ በፌዴራልና በክልል ፍርድ ቤቶች መካከል እንዲከፋፈል ያደርጋል፡፡ ይህ የዳኝነት ስልጣን ክፍፍል በማስረቱ ይኑር እንጂ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ዋነኛ ማሻ የወንጀል ጉዳይ በሕገመንግስቱ ላይ እንደተመለከተው ሁሉ የፌዴራል ጉዳይ ነው በሚል ነው፡፡ የፌዴራል መንግስቱ በሕግ የተሰጠውን ስልጣን ማስፈጸም ያለበትም ሲሆን በወንጀል ጉዳይ ላይ የወንጀል ሕግ የማውጣት ስልጣን በተሰጠው ማስረት ሕጉን ያወጣ ሲሆን በተሰጠውስልጣን ማስረት ያወጣውን የወንጀል ሕግ ስራ ላይ ለማዋል የሚስችለውን የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ የማውጣት ግዴታም አለበት፡፡ ስለሆነም በስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ላይ የተቀመጠውየፌዴራል ፍርድ ቤቶች ወንጀል የዳኝነት ስልጣን ከሕገ መንግስቱ በቀጥታ የሚመነጭሲሆን የክልል ፍርድ ቤቶች የወንጀል የዳኝነት ስልጣን የፌዴራል መንግስቱ በዚህ ሕግ ማስረት በሚወስነው ልክ የሚሰጥ ስልጣን ነውየሚሆነው፡፡ የክልል ፍርድ ቤቶች በወንጀል ጉዳይ ላይ በሰንጠረዥ ተለይቶ የተሰጣቸውየዳኝነት ስልጣን የፌዴራል መንግሰቱ በወክልና የሚሰጣቸውመሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚገባና ይህ ስልጣንም በፌዴራል መንግስቱ በየጊዜው መሻሻል ሊደረግበት የሚቻል መሆኑ ሙታወቅ ይኖርበታል፡፡ ይሁን እንጂ ክልሎች በስልጣናቸውወስጥ የክልሉን ተጨባጭሁኔታ ማስረት በማድረግ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የተለየ ወሳኔ መወሰን ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ በሰንጠረዡየተሰጣቸውየክልል ጉዳዮችን አስመልክቶ የትኛውየወንጀል አይነት በየትኛው ደረጃ በሚገኝ የክልል ፍርድቤት ሙታየት እንደሚቻል በተለየ ሁኔታ መወሰን ይችላል፡፡

የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ የወንጀል የዳኝነት ስልጣንን በፌዴራልና ክልል ፍርድ ቤቶች መካከል ሲያለድል አንድ ጉዳይ የፌዴራል ወይም የክልል ሊሆን የሚቻልበትን መመዘኛ ወይም መርህ አስቀምጦነው፡፡ በዚህ መመዘኛ ወስጥ ከተቀመጡት ማስፈረቶች ወስጥም ጉዳዩ የፌዴራል ስርአቱን፣ ሕገ መንግስትን፣ አለምአቀፍ ግንኙነትን፣ ከአንድ ክልል በላይን ወይም ከአንድ ክልል በላይ የሆኑ ሰዎችን እና በሕጉ የተለዩ ቦታዎች (ለምሳሌ አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ) የሚሉት መመዘኛዎች ይገኙበታል፡፡ የፌዴራል ስርአቱን የሚመለከቱ ጉዳዮች የተባሉት

በወንጀል ሕግ ከቁጥር 238 አንስቶ የተማከቱት ናቸው፡፡ የወንጀሉ ጉዳዮች ከእነዚህ ነጥቦች ጋር የሚገናኙ ከሆነ ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ ይሆናሉ፡፡

ይህ አጠቃላይ መመዘኛ የተቀመጠ ቢሆንም በፌዴራል የፍትሕ አካላት የሚታዩት ጉዳዮች በሕጉ ውስጥ በዝርዝር ተቀምጠዋል፡፡ በዚህም መሠረት አፈጻጸማቸው የፌዴራል መንግሥት ወይም አንድ የክልል መንግሥት ከሚያስተዳድረው የአስተዳደር ክልል በላይ የሆኑ ወንጀሎች፣ ዓለም አቀፍ ባሕርይ ያላቸው ወይም ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎች፣ ከውጭጉዳይ ተያያዥነት ያላቸውወንጀሎች፣ በፌዴራል መንግሥቱ ተቋማትና ንብረቶች ላይ የሚፈጸሙወንጀሎች፣ የፌዴራል መንግሥቱ ሕግ እንዲያወጣ በሕገ መንግሥቱ ሥልጣን በተሰጠው ጉዳዮች ጋር ተያያዘው የሚፈጸሙ ወንጀሎች፣ ከኃላፊነት ጋር በተያያዘ በፌዴራል መንግሥቱ ባለሥልጣናትና ሠራተኞች የሚፈጸም ወንጀል፣ የጉምሩክና የፌዴራል መንግሥት ግብርና የገንዘብ ጥቅም ሕጎችን በመተላለፍ የሚፈጸሙ ወንጀሎችና ለፌዴራል መንግሥቱ ተጠሪ የሆኑ ከተሞች ወይም ቦታዎች የሚፈጸሙወንጀሎችና በሕግ መንግሥቱና በሕገመንግሥታዊ ሥርዐቱ ላይ የሚፈጸሙወንጀሎች በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ሥር የሚወድቁ ወንጀሎች ማስረት መሆናቸውበግልጽ እንዲገባ ተደርጓል፡፡

የዳኝነት ስልጣን ክፍፍል በመንግስታት ደረጃ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በየመንግስታቱ ወስጥ ባሉ ፍርድ ቤቶችም የተከፋፈለ ነው፡፡ በፌዴራልም ሆነ በክልል ደረጃ የተቋቋሙት ፍርድ ቤቶች በሶስት ደረጃ የተማከቱ በመሆናቸውየዳኝነቱም ስልጣን በሶስቱ ፍርድ ቤቶች ዘንድ የተከፋፈለ ነው፡፡ በድልድሉ ማስረትም የጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በወክልና ከሚያዩዋቸው ጉዳዮች በቀር የቀጥታ ዳኝነት ስልጣን አይኖራቸውም፡፡ የሌሎች ፍርድ ቤቶች የዳኝነቱ ስልጣን የሕጉ አካል በሆነው ሰንጠረዥ የተማከተ ሲሆን ሰንጠረዡ የእስራት ቅጣትንና የወንጀል አይነትን ማስረት አድርጎ የተዘጋጀ ነው፡፡ በዚህ ማስረት የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ (ለምሳሌ በሙስና፣ ሽብር፣ ሕገ መንግስታዊ ስርአት ላይ በሚፈጸም ወንጀል፣ የባለስላጣናት የወንጀል ጉዳይ ጉዳይ) ቀጥታ የዳኝነት ስልጣን ሲኖረውአብዛኛውየወንጀል ጉዳይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሚታይ ይሆናል፡፡ በክልል ፍርድ ቤቶችም የቅጣት ጣሪያው አስራ አምስትና በታች የሆኑ ጉዳዮች በወረዳ ፍርድ ቤት የሚታዩ ናቸው፡፡ ይህ ጠቅላላ ማስፈርት እንደተጠበቀም ሆኖ እያንዳንዱ ወንጀል እየታየ ቅጣቱ ዝቅ ያለ ቢሆንም ወስብስብ የመሆን እድሉ ከፍተኛ ሲሆን በበላይ ፍርድ ቤት ስር እንዲሆኑም ተደርገዋል፡፡

በዚህ ማስረት በፍርድ ቤቶች አወቃቀር የበታች የሆኑት ፍርድ ቤቶች (የወረዳ/የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች) ማሉ በማሉ በሰንጠረዥ አንድ የተማለከቱት ጉዳዮች ላይ የቀጥታ ክስ ጉዳይን የሚማለከቱ ናቸው፡፡ መካከለኞቹ ፍርድ ቤቶች (የከፍተኛ ፍርድ ቤቶች) በአብዛኛው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ የከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በጣም በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ቀጥታ የዳኝነት ስልጣን አላቸው፡፡ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በወክልና ካላቸው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስልጣን እና ከክስ ይዘወርልኝ ጉዳይ በቀር ማሉ በማሉ ይግባኝ እና ሰበር ሰሚ ፍርድ ቤቶች ናቸው፡፡ ይህ ስልጣን ክፍፍልም ማስረታዊ በማሆኑ ማሻሻልም ቢያስፈልገው የተወካዮች ምክር ቤት በሚያጣው ሕግ ማስረት ብቻ ሊሻሻል የሚገባውነው፡፡ በተማሳሳይም ወደፊት በሚወጣ ሕግ አዲስ ወንጀል በሚደነገግበት ጊዜ ሕግ አወጪው በተለየ ፍርድ ቤት እንዲታይ ካልወሰነ በስተቀር በወረዳ ፍርድ ቤቶች/በመጀመሪያ ፍርድ ቤት እንዲታይ ሃሳብ እንዳለው ይገመትና ወንጀሉ በወረዳ ፍርድ/በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይታያል፡፡

ከፌዴራል እና ክልል ፍርድ ቤት ወጪ የሆኑና ለሌላ አካላት ቀርበው ወሳኔ ሊገኙ የሚችሉ ጉዳዮችም (በሕገ መንግስት ዐጣሪ ጉባኤ የሚታይ እና በወታደራዊ ፍርድ ቤት የሚታዩ ጉዳዮች) በተማሳሳይ ተለይተው ተቀምጠዋል፡፡ በነዚህ ፍርድ ቤቶችም ቢሆን የበታች ፍርድ ቤቶች ቀጥታ ክስን የሚቀበሉ ሲሆን የበላይ ፍርድ ቤቶች ደግሞ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች መሆናቸውን ባገነናዘበ ሜኬ ነው የስልጣን ድልድሉ የተሰራው፡፡ የእነዚህ አካላት ስልጣንም በሕገ መንግሰቱ እና በወታደራዊ ፍርድ ቤት ማቋቋሚያ ሕግ በተቀማጠው አግባብ የተቀማጡ ናቸው፡፡ ከዚህ ወጪያሉት ጉዳዮች (በአፌዴሪ ሕገ መንግሥትና በሌሎች ሕጎች ለፌዴራል መንግሥቱ ፍርድ ቤቶች ባልተሰጡ የወንጀል ጉዳዮች፣ ሰዎች እና ቦታዎች ላይ) ክልሎች የመጀመሪያ ደረጃ፣ የይግባኝና የሰበር የዳኝነት ስልጣን እንደሚኖራቸው በግልጽ ተሜኪቷል፡፡

የክልል ፍርድ ቤቶች የወንጀል ጉዳይን የመሜከት ስልጣን ቢኖራቸውም የወንጀል ጉዳይ የፌዴራል ጉዳይ ከማሆኑ አንፃር በየትኛውም ደረጃ የታየ ጉዳይ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር ሊታዩ የሚችሉ ማሆናቸው ተገቢ በማሆኑ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በሕገ መንግስቱ ማስረት የክልል ጉዳዮችን ጨምሮ የወንጀል ጉዳዮችን በሰበር ማየት የሚያስችለውስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

የዳኝነት ስልጣን በተለያዩ ፍርድ ቤቶች መካከል የተከፋፈለ ከማሆኑም አንፃር አንድ ጉዳይ በተለያዩ ፍርድ ቤቶች የመቅረብ እድል ሊኖረው ይችላል፡፡ ይህም የሕገ መንግስት ጥያቄ ሊያስነሳ የሚችል በማሆኑ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ እንደዚሕ አይነት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ሊፈቱ የሚችሉበትን አግባብም አስቀምጧል፡፡

ጉዳዮቹም በአንደኛው ፍርድ ቤት ተጣምረው እንዲታዩ ዐቃቤ ሕግ ወይም ተከሳሽ ማመልከት እንደሚችልና ጉዳዩን በይግባኝ ለማየት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ከሁለቱ በአንደኛው ፍርድ ቤት ተጣምሮ እንዲታይ ትእዛዝ ማስጠት እንደሚችል በሕጉ ወስጥ ተመልክቷል፡፡ በሌላ በኩልም ከክሶቹ በከፊል በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ በከፊል በከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚታዩ እንደሆነ ከክሶቹ ከባዱን ክስ ለማየት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ሆኖ ክሶቹን በማጣማር ማስማት እንደሚቻል፣ እንደዚሁም ከክሶቹ በከፊል በፌዴራል ፍርድ ቤት እና በከፊል በተለያዩ የክልል ፍርድ ቤቶች ስር የሚወድቁ ከሆነ የፌዴራል ፍርድ ቤት ጉዳዩን በዳኝነት ለመመልከት የዳኝነት ስልጣን የሚኖረው ሲሆን ከፊሉ በክልል ፍርድ ቤቶች ወይም በተለያዩ ክልሎች በሚገኙ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን የሚወድቅ እንደሆነ ከባዱን ጉዳይ ለማየት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ክሶቹን አጣምሮ ማስማት እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ ምናልባት ከቀረቡት ጉዳዮች ወስጥ ከባዱን ማለየት የሚያስቸግር በሚሆንበት ጊዜም የጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ከባድ የሚበለወን ወንጀል ለይተው መወሰን እንዲችሉ ስልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው የፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ክፍፍሉ ከፍ ሲል በተመለከተው መርህ ማስረት ላይ የተማስረተ ቢሆንም የየፍርድ ቤቱ ስልጣን በግልጽ እንዲታወቅ የስነ ስርአትና ማስረጃ ህጉ አካል በሆነው ሰንጠራዥ ተለይቶ ተቀምጧል፡፡ በሰንጠረዡ ሊለይ የሚይችለው የአሰተዳደር ወሰን የዳኝነት ስልጣን ቢሆንም ይህ ስልጣን መንግስት በሚወስነው ማስረት የሚኖርን የአስተዳደር (ፌዴራል/ ክልል/ ዞን/ ወረዳ) ወሰን አከላለል የሚከተል ይሆናል፡፡ መደበኛ የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣንን በሚመለከት ረቂቁ አገሪቱ ከምትከተለው ፌዴራላዊ የመንግሥት ሥርዓት ጋር በሚጣጣም መልኩ የፌዴራሉ መንግሥት ስልጣን በሆኑ የወንጀል ጉዳዮች ላይ በሥረ ነገር ስልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ ወይም ድርጊቱ ወጤት ባገኘበት የፌዴራል የወንጀል ጉዳዮች ላይ የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን እንዳላቸው፤ የክልል ፍርድ ቤቶች በክልሉ የግዛት ወሰን ወስጥ በተፈጸሙ ወይም ድርጊቱ ወጤት ባገኘበት የክልል የወንጀል ጉዳዮች ላይ የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን እንዳላቸው በአዲስ አበባና በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር ወይም በሌሎች በኢትዮጵያ ግዛት ወስጥ በተፈጸሙ የፌዴራል የወንጀል ጉዳይ ላይ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን እንዳላቸው አመላክቷል፡፡

አስተዳደር ወሰኑ በሕግ አግባብ በተለወጠ ቁጥር የዳኝነት አካሉም የአስተዳድር የዳኝነት ስልጣንም ሌላ ሕግ ማወጣት ሳያስፈልገው ይህንኑ ተከትሎ ይለወጣል፡፡ ተደራራቢ የአስተዳደር ዳኝነት ስልጣን ቢያጋጥም የቀደምትነት መርህ ተፈጻሚይሆናል፡፡ ይህ ስልጣንም በትክክል ሊለይ ያልቻለም እንደሆነ የስረ ነገር ስልጣን ባለው በአንደኛው ፍርድ ቤት ሊታይ የሚችል ሲሆን የፍርድ ቤቱ ስልጣን ምርጫግን የስነ ስርአትና ማስረጃ ህግን

አላማ በይበልጥ የሚያስፈጽም መሆን ይገባዋል፡፡ ይህንን ጉዳይ ፈጻሚ አካላት ክስ ሲመሰርቱ አስቀድመው ይለዩታል በሚል እሳቤ ሕጉ የተቀረጸ ቢሆንም በሂደት የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉን አላማ ለማሳካት የሚያስችል አለመሆኑ ከተረጋገጠ ግን ክሱ የተሻለ ውጤት ሊያስገኝ ወደሚችል ፍርድ ቤት ሊያዛወር እንደሚችል ተደነገገ ሲሆን ለዚህ እና መሰል ጥያቄዎች አቀራረብም ሆነ ለውሳኔ አሰጣጥ አመቺነትም ዝርዝር መስፈርቶች በስነ ስርአትና የማስረጃ ሕጉ ውስጥ እንዲካተቱ ሆኗል፡፡

የሌሎች የፍትሕ አካላት (ፖሊስ፣ አቃቤ ሕግ፣ ማረሚያ ቤት) ስልጣንም የፍርድ ቤቶችን ስልጣን ተከትሎ የተቀመጠ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ማረሚያ ቤቶች ካቋቋማቸው የፌደራልም ሆነ የክልል መንግስት ውጪ የሌላ ፍርድ ቤት የሚሰጠውን ትእዛዝ ሊፈፅሙ የማይችሉበትም አግባብ አይኖርም ማለት ግን አይደለም፡፡

## 13.2 ችሎትና ግልፅነት

የሕገ መንግስቱ አንቀፅ 12(1) የመንግስት አሰራር ለሕዝብ ግልፅ ሆኖ መካናወን እንዳለበት የሚያስገድድ ሲሆን አንቀፅ 20(1) በተለይ ስለተከሰሱ ሰዎች ሲደነግግ በተመሳሳይ መልኩ የተከሰሱ ሰዎች ለሕዝብ ግልፅ በሆነ ችሎት የመዳኘት መብት እንዳላቸው ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ ችሎት በዝግ ሊታይ የሚችልባቸውን የተለዩ ሁኔታዎችንም ሕገ መንግስቱ በተመሳሳይ ደንግጓል፡፡ ችሎት በዝግ ሊካሔድ የሚችለውም ጉዳዩን በያዘው ዳኛ ውሳኔ ወይም በሕግ መሰረት ብቻ ነው፡፡ ችሎት በዝግ እንዲታይ ጉዳዩን በያዘው ዳኛ ሊወሰን የሚችለው የጉዳዩ በግልፅ ችሎት መታየት የተከራካሪ ወገንን የግል ሕይወት፣ የሕዝብ ሞራል ወይም የአገር ደሕንነትን ይጎዳል የሚል እምነት ሲኖር ነው፡፡ ሕገ መንግስቱ የዳኛነት ነፃነትን ያረጋገጥ በመሆኑ በዚሕም ጉዳይ ቢሆን ውሳኔ መስጠት ያለበት ጉዳዩን በያዘውና በቅርብም በሚያውቀው ዳኛ እንጂ በፍርድ ቤቱ (በተቋሙ) ወይም በሌላ አካል እንዲሆን አልተመረጠም፡፡ አንድ ጉዳይ በዝግ ችሎት ሊታይ የሚችልበት ሌሎች ምክንያች ጉዳዩ የወጣት ጥፋተኞች ሚመለከት ሲሆን እንዲሁም አንድ ጉዳይ በዝግ ችሎት ይታይ የሚል ጥያቄ የቀረበ እንደሆነ ጥያቄውን ለመመርመር ነው፡፡ እነዚህ ምክንያች በመጀመሪያው ምክንያት ወስጥ የተካተቱ ለመሆናቸው በትርጉምም ቢሆን የሚደረስባቸው በመሆናቸው በህግ መደንገጋቸው ግር የሚል አይሆንም፡፡

አንድ ጉዳይ ለሕዝብ በግልፅ ችሎት ይታያል ማለት ለማናኛ ብዙሃንም ግልጽ ይሆናል ተብሎ የሚወሰድ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ዳኛ በሚወስነው የግልጽነት መጠን ላይ ተንተርሶ የማናኛ ብዙሃን ስለሚዘግቡት/ስለሚይዘግቡት ጉዳይ፣ አዘጋገብ፣ የዘገባ መሳሪያ አጠቃቀም ወዘተ ዳኛው ሊወስን ይችላል፡፡ የሌሎች አገራት ልምዷ

የሚያሳየው የዚህ ጉዳይ አፈጻጸም ዝርዝር ስለሚሆን ወደፊት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚወጧ መመሪያም ጭምር የሚሟሉ እንደሚሆን የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ጥንቃቄን አድርጓል፡፡

በችሎት ማስየምንም በተማለከት እስካሁን የሚሰራበት የ1፣ 3፣ 5 ዳኛ አሰያየም ላይ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ በተወሰነ ሚልኩ ለወጥ አድረጎበታል፡፡ በዚህም መሰረት ችሎት ለሁሉም ጉዳዮች ወጥ በሆነ አግባብ ከሚሰየም ይልቅ በተወሰነ ደረጃ ተለማጭ አሰያየምን ማከተል በሚያስችል ሚልኩ ድንጋጌዎች ተካተዋል፡፡ በመሰረቱ የሕጉ መነሻ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአንድ ዳኛ ያስችላል የሚል ሲሆን የበላይ ፍርድ ቤቶች በሶስት ወይም ከሶስት በላይ በሆኑ ዳኞች ሊያስችሉ ይገባል የሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ቢሆን በፍርድ ቤቱ ከሚታዩ ጉዳዮች ብዛትና ሊያጋጥም ከሚችል የጉዳይ ወስብስብነት አንፃር አንድ ጉዳይ ላይ ወሳኔ ለማስጠት ከአንድ በላይ የሆኑ ዳኞች ማስየም ሊኖርባቸው ይችላል፡፡ በሌላ በኩልም በከፍተኛ እና በጠቅላይ ፍርድ ቤቶችም ቢሆን ሁሉም የዳኛነት ስራ የግድ በሶስት ወይም በአምስት ዳኞች መታየት አያስፈልጋቸውም፡፡ ለምሳሌ ተለዋጭቀጠሮ ማስጠት የዳኝነት ስራ ቢሆንም የግድ በአምስት ዳኛ ሊሰራ ይገባል የሚያሰኝ አይደለም፡፡

በመሆኑም በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሚታይ አንድ ጉዳይ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉባኤ ወሳኔ ሶስት ዳኞች በሚሰየማት ችሎት ሊታይ እንደሚችል የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ድንጋጌ አካቷል፡፡ በሌላ በኩል በከፍተኛ እና በጠቅላይ ፍርድ ቤቶች አንድ ጉዳይ በመሰረቱ በሶስት፣ በአምስት ወይም ከአምስት በላይ በሆኑ ዳኞች መታየት ያለበት ቢሆንም ተለይተው የተዘረዘሩ የተወሰኑ ተግባራት ግን በአንድ ወይም በሁለት ዳኞች መታየት እንደሚችሉ ሕጉ በዝርዝር አሰቀምጧል፡፡

ከሶስት በላይ ዳኞች በተሰየማት ችሎት ወሳኔ በሙሉ ድምጽ የሚሰጥ ይሆናል፡፡ የሙሉ ድምጽ ወሳኔ ባልተገኘበት ጊዜ በድምጽ ብልጫየሚሰጥ ወሳኔ የፍርድ ቤቱ ወሳኔ የሚሆን ሲሆን ይህንንም የድምጽ ብላጫ ማግኘት የማይቻል ቢሆን (ለምሳሌ በባለ አምስት፣ ሰባት...ችሎት ላይ ድምጽ 2፣ 2፣ 1 ሆኖ ቢከፈል) የፍርድ ቤቱ ወሳኔ የሚሆነውም የጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣው መመሪያ እንዲወሰን ሕጉ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስልጣን ይሰጣል፡፡

## 13.3. ከፍርድ እና ከፍትሕ ሂደት ስለመነሳት

ማንኛወም ባለጉዳይ ጉዳዩን በሚማለከተው የፍትሕ አካል ባለሞያ ላይ ቅሬታ ሊኖረው ይችላል፡፡ ይህ ቅሬታም ባለሞያው ጉዳዬን ሊማለከት አይገባወም እስከማለት ሊደርስም ይችላል፡፡ እስካሁን ባለው አሰራር የዚህን

አይነት ጥያቄ በወጥነት የሚያሰተናግድ ሕግም ሆነ አሰራር የለም፡፡ የፌደራል ፍርድ ቤት ዳኞች ከችሎት ስለሚሰጡት ምክንያትና አሰራር በፍርድ ቤቶቹ ማቋቋሚያ ላይ የተመለከተ ቢሆንም የክልል ዳኞችና እና የሌሎች ፍትሕ አካላት ሕግና አሰራር የዚህን ያህል ግልጽ አይደለም፡፡ በመሆኑም በሁሉም የፍትሕ አካላት ባለሞያዎች (ዳኛ፣ ዐቃቢ ሕግ፣ ፖሊስ፣ ተከላካይ ጠበቃ) ላይ ተመሳሳይ ቅሬታ ሊነሳ የሚችል በመሆኑ ይህንንም ጉዳይ የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን ሕጉ አካቷል፡፡ በዚህም መሰረት እያንዳንዱ ባለሞያ ማንኛውንም ስራ በባለሞያነትና በኃላፊነት ስሜት ማስራት እንዳለባቸው፣ አንድን ጉዳይ ማየት የሌለባቸው መሆኑን እንዳወቁ አቤቱታ እስኪቀርብባቸው ማጠበቅ ሳይገባቸው ጉዳዩን መመልከታቸውን ማቆም እንዳለባቸው፣ ባለማወቅ ይህንን ቢያልፉ ወይም በሕጉ ላይ በተመለከቱት ምክንያቶች ከጉዳዩ ላይ እንዲነሱ ጥያቄ ሲቀርብላቸው ወዲያውኑ ወሳኔ ማስጠት እንዳለባቸው የሚያስገነዝቡና ማሰል ድንጋጌዎች በሕጉ ወስጥ እንዲካተቱ ሆኗል፡፡

ከፍትሕ ሂደቱ ሊነሱ የሚችሉባቸው ምክንያች የጥቅም ግጭትን ሊያስከትሉ የሚችሉ፣ ባለሞያውን ገለልተኛነትና ነጻነት የሚመለከቱ በመሆናቸው በስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ወስጥ የተመለከቱ ቢሆንም ሌሎች ምክንያች ባለሞያዎቹ በሚሙባው ደንቦች ወስጥም የሚገኙ ቢሆን ለዚሁ ስርአት ተፈጻሚየ ሚሆኑ ናቸው፡፡

## 13.4. መጥሪያ

የቀድሞው የሥነ ሥርአት ሕግ ለፍትሕ ሥርአቱ የሚፈልገውን ሰው (ተከሳሽ፣ ምስክር፣ ሰነድ አቅራቢ ወዘተ) ስለሚጠራበት መንገድ ዝርዝር ድንጋጌ የሌለው በመሆኑ ስለመጥሪያ አይነቶችም ሆነ ስለ ወጪታቸው በተግባር ሰፊ ክፍተቶች ያጋጥሙነበር፡፡ ይህንን ክፍተት አሁን ካለው የቴክኖሎጂ እድገት ጋር አጣጥሞ መሙላት የሚያስፈልግ በመሆኑ የስነ ስርአትና ማስረጃ ህጉ መጥሪያን አስሜልክቶ ዝርዝር ድንጋጊዎችን ይዟል፡፡ መጥሪያ በወንጀል ጉዳይ ከምርመራ አንስቶ እስከ ፍርድ ማስጠት ድረስ በሁሉም የፍትሕ አካላት ሊወጣ የሚችል ነው፡፡ በመሆኑም የፍርድ ሂደትን በሚደነግገው ክፍል ወስጥ የተመለከተው መጥሪያ ለሁሉም የፍትሕ አካላት (ፖሊስና አቃቤ ሕግ) እንዳግባቡ እንዲፈጸም ሆኖ በሕጉ ተቀምጧል፡፡

በየትኛወም ደረጃ የሚወጣ/የሚታዘዝ መጥሪያ አላማው ፍትሕ የማግኘት መብትን ለማረጋገጥ፣ የማሰማት መብትን ለማረጋገጥ፣ በፍትሕ አካላት ዘንድ የማጠየቅ ግዴታን መወጣት መቻልን ለማረጋገጥና የፍትሕ ሂደቱን ሊያቀላጥፉ የሚችሉ ሌሎች ተግባራትን ለማከናወን ነው፡፡ በማሰረቱ መጥሪያን ማዘጋጀት ያለበት ተግባሩን የሚፈጽመው አካል ሲሆን የሚያደርሰው ግን ፖሊስ ነው፡፡ ለፍርድ ቤት በሚቀርብ ጉዳይ መጥሪያን ፍርድ ቤት የሚያዘጋጅ ሲሆን ጉዳዩን ላመጣው አካል (ምሳሌ ክሱን ላመጣው አቃቤ ሕግ) ፍርድ ቤቱ ወዲያውኑ መጥሪያውን

የማዘጋጀትና የማስጠት ኃላፊነት አለበት፡፡ ፍርድ ቤቱ ይህንን ሚጸምባይችል አቃቤ ሕግ ጽሕፈት ቤት ድረስ መጥሪያወን የሚድረስ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

መጥሪያ ምንጊዜም ቢሆን ለተጠሪው በአካል ሚድረስ ያለበት በማሆኑ ሕጉም ይህንን አደራረስ በሚርሀ ደረጃ አሰቀምጦታል፡፡ መጥሪያን በአካል ለተጠሪ ሚድረስ የሚያስችል በቂና አሳማኝ ምክንያት ከተገኘ ምትክ መጥሪያ ሊታዘዝ ይችላል፡፡ ለምሳሌ ተጠሪውበአገር ወስጥ የሌለ ለማሆኑ በሚገባ ከተረጋገጠበምትክ መጥሪያዎች ሊጠራ ይችላል፡፡ በማሆኑም በህጉ ላይ የተቀማጠው አግባብ መጥሪያ በአክል፣ በፖሊስ በኩል፣ በማናኛ ብዙሃን የሚደርስበትን አድል የሚያሰፋ ነው፡፡ ምትክ መጥሪው በቀጥታ ሚድረሱ ባይረጋገጥ እንኳን ሰፊ ሽፋን ባለው የማናኛ ብዙሃን አማካኝት ከተነገረ መጥሪያውበምትክ እንደደረሰ ግምት ሊወሰድ ይችላል፡፡

ተከሳሽ መጥሪያ ደርሶት ካልቀረበ ጉዳዩ መካከለኛና ከባድ ወንጀሎችን የሚማለከት ከሆነ በሌለበት ታይቶ ፍርድ ሊሰጠ ይችላል፡፡ ተከሳሽ በሌለበት የሚታዩ ጉዳዩች ቀድሞ ከነበረው በሰፋ ሁኔታ የተደነገጉ በማሆቸው መጥሪያውበአግባቡ ለሚድረሱ አጠራጣሪ በሆነ ቁጥር አላስፈላጊ ክርክር እየተነሳ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ አላማ እንዳይሳካ እና ክርክር በጭፍጫ ጉዳይ ላይ እንዲያተኩር ያደርጋል፡፡ በማሆኑም በምትክ መጥሪነት የተሚጠቅ እንደ ፖስታ፣ ራዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ጋዜጣ እና ስልክ ያሉት ሆነው መጥሪያ የደረሰ ለማሆኑ በሚያከራክር ሁኔታ ሊረጋገጥባቸውየሚቻሉ ናቸው፡፡ በዚህ ማስረት ምንምእንኳን መጥሪያ ሊላክ የሚቻልባቸው ሌሎች አግባቦች ቢኖሩም (ምሳሌ የኢ-ሜይል፣ ፋክስ...) መጥሪያውለተጠሪውለሚድረሱ በእርግጠኝነት ማረጋገጥ የሚይቻል በማሆኑ በምትክ መጥሪነት አልተካተቱም፡፡

ከመጥሪያ አላማ አንፃር ምትክ መጥሪያ ቅደም ተከተሉን ጠብቆም ሚላክ ያለበት ስለማሆኑ፣ ለተጠሪውበሚገባ ሚድረሱ ወይም ሰፊ ሽፋን ባለውየፌዴራል ወይም የክልል ማናኛ ብዙሃን ማገሩ ከተረጋገጠ ለተጠሪው እንደደረሰውይቆጠራል፡፡

መጥሪያ ደርሶት ያልቀረበ ተከሳሽ ተይዞ እንዲቀርብ (ለምሳሌ ለከባድ ወንጀል፣ መቅረብ የሚቻል በሆነባቸው ጊዜያት ሁሉ) ሊታዘዝ ይችላል፡፡ በተወሰኑ ጉዳዮች (ከወጣት አጥፊና ከቀላል ወንጀሎች ዉጪ) ላይም መጥሪያ ደርሶት ያልቀረበ ተከሳሽ ጉዳይ በሌለበት ይታያል፡፡ ቀላል ወንጀል የፈጸሙሰዎች በአብዛኛውአካባቢቸወን ለዚህ ብለውየሚለቁ በማሆኑ በአካል ቀርበውሊከራከሩ የሚገባቸውሲሆን በእንደዚህ አይነት ጉዳይ ማዘገቡ ለጊዜው ቢቋረጥ እንኳን ቀላል የወንጀል ጉዳዮች ከወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው አንጻር ከመካከለኛ እና ከከባድ ወንጀሎች ቅደሚያ የሚይሰጣቸውበማሆኑ በቀላል ጉዳይ ተከሳ በሌለበት ማየት አዋጪኤደለም፡፡ በሌልምበኩለ

የወጣት ጥፋተኞች ጉዳይም ከክርክር ይልቅ ለወጣቱ ችግር መፍትሔ መፈለግ ላይ ማተኮር ያለበት በመሆኑ ክርክሩ ምንጊዜም ባለበት መካሔድ ያለበት ነው፡፡

መጥሪያ የሚታዘዝበት ሌላው ምክንያት ማስረጃ እንዲቀርብ ለማስቻል ነው፡፡ በመጥሪያ የተፈለገ ማስረጃ በበቂ ምክንያት ሊቀርብ ካልቻለ በዚህ ምክንያት ብቻ ሁል ጊዜ መዝገብን ማቋረጥ ተመራጭ አይሆንም፡፡ በመሆኑም በቀረበው ማስረጃ መወሰን እስከተቻለ ድረስ ጉዳዩ ተመርምሮ ወሳኔ ሊሰጥበት የሚችል በመሆኑ ሕጉ ድንጋጌ ይዟል፡፡

ከመጥሪያ አላማ አንጻር በመጥሪያ ያልቀረበ ማናኛወም ተከሳሽ ክርክሩ በደረሰበት ደረጃ ወደ ክርክሩ መግባት ይችላል፡፡ ቀድሞ በተጠራበት ጊዜ ሊቀርብ ያልቻለው በበቂ ምክንያት መሆኑን ወይም መጥሪያ ሳይደርሰው በመቅረቱ ምክንያት ለመሆኑ ካስረዳ ክርክር መኖሩን በተረዳ ወይም በቂ ነወ የተባለው ምክንያት በተወገደ በአንድ ወር ጊዜ ወስጥ ወደ ክርክሩ ለመግባት ፍርድ ቤት ቀረቦ ማመልከት ይችላል፡፡ ያቀረበው ምክንያትም ተቀባይነትን ካገኘ ክርክሩን እርሱ ባላበት ለማካሔድ እንደገና እንደ አዲስ ይጀምራል፡፡ በሌላ በኩልም በቂ ምክንያት ከሌለው ወይም መጥሪያ ደርሶት ያልቀረበ ከሆነም ክርክሩ በደረሰበት ደረጃ ገብቶ መከራከር ይችላል፡፡ የበቂ ምክንያት መለኪያን ማስቀመጥ አስቸጋሪ በመሆኑ ጉዳዩን የሚመለከተው ፍርድ ቤት የቀረበውን ምክንያት እና የነገሩን ዙሪ መለስ ተመልክቶ የሚወስነው ምክንያት ነው፡፡

## 13.5.የቅድመ ክስ መስማት ተግባራት

አሁን ባለው ሕግና የችሎት አመራር ዳኞች ሙሉ ትኩረታቸውን በጉዳዩ መሰረታዊ ነገሮች ላይ ከሚያተኩሩ ይልቅ በጉዳዩ ዋና ነገር ላይና በጭፍጫፊ ጉዳይ ላይ ሁሉ ተጠምደው ወድ ጊዜያቸውን ሲያባክኑ እንደሚውሉ ግልፅ ነው፡፡ ይህ ችግር በመሰረቱ ሊቀረፍና ዳኞች ሙሉ ጊዜያቸውን በፍሬ ጉዳዩ ላይ ብቻ አተኩረው ወጤታማ ፍትሕ ሊሰጡ የሚችሉበትን እድል ማስፋት ያስፈልጋል፡፡ ዳኞች ጉዳዩን ወጤታማ በሆነው አግባብ የሥነ ሥርአትና ማስረጃ ህጉን አላማ አሳክተው መቋጨት ያለባቸው በመሆኑ አሁን በስራ ላይ እንደሚታየው በጥቃቅን ጉዳይ ወድ የሆነውን የችሎት ጊዜም ማባከን አይኖርባቸውም፡፡ በዚህ መሰረት የሕጉ ዋነኛ ትኩረት ዳኞች በጉዳዩ ፍሬ ነገር ላይ እንዲያተኩሩና ቀሪ አስተዳደራዊ ተግባራት ከችሎት ስራ ወጪ ሆነው እንዲጠየናቅቁ ማስቻል ነው፡፡

በመሆኑም ክስ እንደቀረበ የመጀመሪያው ተግባር አስተዳደራዊ የሆኑና የዳኛውን ትኩረትና ጊዜ የግድ የማይፈልጉ ጉዳዮችን ለይቶ ተገቢውን ስራ በማስራት የችሎት ጊዜን የሚፈልጉትን ለይቶ ማዘጋጀት ይሆናል፡፡ ይህ ስራ በሕጉ ላይ የቅድመ ክስ ስራ ተብሎ ተለይቷል፡፡ እስካሁን ያለተሰራበትም ሲሆን በጸረ ሙስና ጉዳዮች

ላይ በሕግ ከተፈቀደው የቅድመ ክስ ማስማት ጋርም ግንኙነት የለውም፡፡ የቅድመ ክስ ማስማት ተግባራት አስተዳደራዊ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ተግባራትን የሚያካትት በመሆኑ በዋናኘነት በሬጂስትራር አማካኝነት መከናወን የሚገባው ነው፡፡ በዚህ መሰረት የፍርድ ቤቱ ሬጂስትራር የክሱን ብቃት የሚያረጋግጥ ሲሆን የክስ ብቃቱ የተረጋገጠው ክስ ዳኛ መጥሪያ ከማዘዙ **በፊት የክሱን ሕጋዊ ብቃት ያረጋግጣል፡፡ ይህም በክሱ ላይ ወደኋላ ሊነሳ የሚችልን ተቃውሞ አስቀድሞ** እልባት በመስጠት ለማስቀረት ያግዛል በሚል እሳቤ የገባ ነው፡፡ የክሱ ሕጋዊነት እንደተረጋገጠም መዝገቡ ለዳኛ የሚቀርብ ሲሆን ዳኛውም ጉዳዩ የሚመራትን የክርክር ማስመር ማለየት ይኖርበታል፡፡ ይህ ተግባር ይከናወን/አይከናወን የሚለውንና በማን አማካኝነት (በዳኛው ወይም በሬጂስትራር) ይከናወን የሚለውን በሕግ ከማስቀመጥ እንደጉዳዩ የተለየ ባህሪ ጉዳዩን በቅርብ በሚያውቀው ዳኛ ቢወሰን የሚመረጥ በመሆኑ በሕጉ ላይ የማምረጥ ስልጣኑ ለዳኛው ተትቷል፡፡ ክሱን ተመልክቶም ሁለት ነገሮች ላይ ትእዛዝ ማስጠት ይችላል፡፡ እነዚህም አንደኛ በጉዳዩ ላይ የቅድመ ክስ ተግባራት ማከናወን ያስፈልጋል አያስፈልግም በሚለውና በሁለተኛ ደረጃም የቅድመ ክስ ተግባራት መከናወን የሚገባው ከሆነ ው በማን አማካኝነት (በሬጂስትራር ወይም በዳኛው) መከናወን ያለበት ስለመሆኑ በማለየት ትእዛዝ ይሰጣል፡፡ ስለሆነም ከመደበኛው ችሎት አስቀድመው ማለቅ ያለባቸው ጉዳዮችም በወቅቱ ማለቅ እንዲችሉ አቃቤ ሕግና ተከሳሹ በራሱ በዳኛው ፊት ወይም በሬጂስትራሩ ፊት ቀርበው መፈጸም ያለባቸው ጉዳዮች ካሉ ተለይተው እንዲፈጸሙ ጉዳዩን በሚመለተው ዳኛ ተጨማሪ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል ማለት ነው፡፡

ይህ ተግባር የቅድመ ክስ ማስማት ተግባራት በሚል በሕጉ እንዲካተት የሆነ ሲሆን በዚህ ተግባር ውስጥም አቃቤ ሕግና ተከሳሹ በዳኛው ወይም በሬጂስትራሩ ፊት ቀርበው እንደ የተከላካይ ጠበቃና አስተርጓሚ አስፈላጊነትን የማለየትና የማሟላት፣ ክርከሩ የሚመራበትን ሥርአት የማለየት፣ ለምስክር ወይም ለሌላ ማስረጃ አቀራረብ አስፈላጊ የሆነውን የመጥሪያ አይነት የማለየት፣ ለክርክሩ አስፈላጊ የሆኑትን ቅድመ ሁኔታዎችን የማለየት፣ ክርክሩ የሚጠናቀቅበትን አጠቃላይ እቅድ የማውጣትና የማሰሉት ተገባራት ሊያከናወኑ ይችላል፡፡ እነዚህና መሰል ጉዳዮች አስቀድመው ከተጠናቀቁ ክሱ በሚሰማት እለት ጠበቃ የለም፣ አሰተርጓሚ አልተገኘም፣ ችሎቱ በአግባቡ አልተዘጋጀም...እየተባለ የሚነሱትን አላስፈላጊ ክርክሮች መቀነስ (ማስወገድ) የሚቻል በመሆኑ ችሎቱም ክርክሩ በሚሰማበት እለት ሙሉ ትኩረቱን በዋናው ፍሬ ነገር ላይ ብቻ በማድረግ ጊዜውን ጉለበቱን በአግባቡ መጠቀም እንዲችል እንዲሁም ክርክር ሳይቆራረጥ ወዲያውኑ ውሳኔ የሚሰጥበትን እድል መፍጠር ይቻላል፡፡

በቅድመ ክስ ማስማት ዝግጅት ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆን የክስ ማከፈቻ ንግግር በግልፅና በተሟላ ሁኔታ ማዘጋጀቱ አስፈላጊ ነው፡፡ ለፍርድ ቤት ከሚቀርበውክስ እና ማካላከያ ጋር የክስ እና የማካላከያ ማሉ መግለጫ መቅረብ እንዳለባቸው ሕጉ የሚደነግገው መግለጫው አቃቤ ሕጉ ወይም ተከሳሹ ክርክሩን እንዴት ሊያስኬደው እንዳሰበ የሚያማለከተወን እቅድ ፍንትው አድርገው ስለሚያሳዩና ክርክር በድብቅ ሳይሆን በግልጽነትና አስቀድሞበሚታወቅ አቅድ የሚመራ መሆኑ የስነ ስርአትና ማስረጃ ህጉ ያሰበወን አላማለማሳካት ያግዛሉ በሚል እምነት ነው፡፡ እስከአሁን በሚደረጉ ክርክሮች ይህንን ጉዳይ በግልጽ የሚመራ ሕግ በተሟላ ሁኔታ ያልነበረ በመሆኑ አንድ ጉዳይ መቼ ተጀምሮ መቼ እንደሚጠናቀቅ እንኳን አስቀድሞለማ መት አይቻልምነበር፡፡ ተከራካሪ ወገኖችም በአግባቡ እንዳይተጉ እድሉን ሲከፍትና የክርክር ጥራትም እንዲጓደል የበኩሉን አስተዋጽዎ ሲያበረክት ቆይቷል፡፡ ይህም በመሆኑ በተያዘውጉዳይ ላይ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ጉዳዮች አመራር ላይም ሳንካ ሲፈጥር የቆየ በመሆኑ በሕጉ ወስጥ ይህንን በግልጽና በግዴታ ሚፈጸም የሚያስችል ድንጋጌ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

## 13.6. የክርክር ሥርአቶች

በሕገ መንግስታችን ዕወቅና ካገኙ መሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶች ማከከል አንዱ የተከሰሱ ሰዎች ክስ ከቀረበባቸው በኋላ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ወስጥ በመደበኛ ፍርድ ቤት የማስማት እና ፍትሐዊ ወሳኔ የማግኘት መብት ነው፡ ይህ መብት በወንጀል ድርጊት የተጠረጠሩ እና ክስ የተማሰረተባቸውሰዎች ሌሎች መብቶቻቸወን ለማስከበር ብቸኛ ዋስትናቸውሲሆን በተለይም ተጠርጥረውለተያዙና በእሥር ላይ ሆነውውሳኔ ለሚጠብበቁ ተከሣሾች እጅግ በጣም ወሳኝ ነው፡ ይህ መብት ለተከሳሹ ብቻ ሳይሆን ለተጎጂዎችና ለህብረተሰቡም ጭምር ትልቅ ጠቀሜታ አለው፡ የተከሰሱ ሰዎች የተከሰሱበት ጉዳይ ለመደበኛ ፍርድ ቤት ቀርቦ በአጭር ጊዜ ወስጥ የሚወሰን ከሆነ የተከሳሾች መብት ብቻ ሳይሆን የሌሎች ባለጉዳዮችምእንዲሁምየሕብረተሰቡ ጥቅምበአጠቃላይ ይጣሳል፡፡

የቀደመውስነ ሥርአት ሕግ (በተለይምከወንጀል ፍትህ አስተዳር የለወጥ ስራ ማሻሻያ ትግበራ በፊት) የተደረጉ ልዩ ልዩ ጥናቶች እንዳረጋገጡት የወንጀል ጉዳይ ከጥቆማእስከ ፍርድ ድረስ በአማካኝ እስከ አራት አመት ጊዜ ይፈጅባቸዋል፡፡ "የዘገየ ፍትሕ እንደተከለከለ ይቆጠራል" የሚለው የሕግ ሊቃወንት አባባል ለዚህ አይነት ማዛግየት ጠቃሚአባባል ነው፡

የተቀላጠፈ ፍትሕ የማግኘት መብት እወን ከማሆንባቸው ህጎች ወስጥ አንዱ ጉዳዮች የሚመሩባቸወን ስርአቶች በአግባቡ የለየ የወንጀል ስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ ማኖሩ ነው፡ ከሥነ ሥርአት ህግ አንፃር አንደ ጉዳይ

እልባት ሳያገኝ ከሚቋተትባቸው ምክንያቶች ወስጥ አንዱ ደግሞ ክርክር የሚመራበት ስርአት ያለበት ችግር በመሆኑ በሥራ ላይ ያለወን የሥነ ሥርአት ክርክር አመራርና አያያዝ ስርአት መፈተሽና ማስተካከል ይገባል፡፡

የነባሩ ሕግ አንዱ ችግር አብዛኛው ጉዳይ በተመሳሳይ ስርአት እንዲመሩ ማድረጉ ነው፡፡ ነባሩ የሥነ ሥርአት ሕግ ከተወሰኑ ጉዳዮች (ወጣት ጥፋተኞች፣ ደንብ መተላለፍ…) ወጪ ያሉ ክርክሮች በተለያየ መንገድ መመራት የሚችሉ ስለመሆናቸው የሚያስቀምጠው ዝርዝር ድንጋጌ የለወም፡፡ ይህም በመሆኑ ጉዳዮች ሁሉ በመርህ ደረጃ ማስረታዊ ልዩነቱ ጎለቶ በሚይታይበት በተመሳሳይ የመደበኛው ማስመር እየተመሩ ይገኛሉ፡፡ በአብዛኛወም የጉዳዮች በፍጥነት ማጠናቀቅ ወይም አለማጠናቀቅ የሚወሰነ ውበየ ፍርድ ቤቱ ባለው መዝገብ ማስ/መበዛት ላይ እንጂ በክርክሩ ማስመር ወሳኝነት አለመሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ይህም የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር ላይ የራሱን ጫና ያሳደረ በመሆኑ ይህ ስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ የተለያዩ ጉዳዮች በተለያዩ የስነ ስርአትና ማስረጃ ማስመሮች እንዲመሩ የሚያስችል ድንጋጌዎችን ይዟል፡፡ በመሆኑም ጉዳዮች እንደገና የሚታዩባቸው የይግባኝ፣ ሰበር፣ ጉዳይን እንደገና የማየት እና የማስየም ስርአቶች እንደተጠበቁ ሆነው አንድ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ማየት ከመጀመሩ በፊት በዋነኛት ጉዳዩ ከተቀላጠፈ፣ ከተፋጠነ፣ ከወጣት ጥፋተኛ ወይም ከደንብ መተላለፍ ስርአቶች ወስጥ በየትኛውስርአት እንደሚመራ አስቀድሞ ማየት ይገባዋል፡፡

የክርክር ማስመሮች የተለያዩ ቢሆኑም ጉዳዮች በጊዜ ገደብ ሊመሩና በጊዜ በታጠረ ገደብ ወስጥ ተከወነው ማጠናቀቅ ያለባቸውናቸው፡፡ የክርክር ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የሌሎች ፍትሕ አካላትም ተግባራት ሁሉ በጊዜ ገደብ ወስጥ ታጥረው መከናወን ያለባቸው መሆኑ በርካታ ጠቀሜታ አለው፡፡ ስራዎች ሁሉ በቅልጥፍና ከተከናወኑ ፈጣንና ጥራት ያለውፍትሕ የሚረጋገጥ እድል ይጨምራል እንዲሁም የፍትሕ አካላትን ተጠያቂነት ለማረጋገጥ ያግዛል፡፡ ስራዎቹ በተቀማጠላቸው የጊዜ ገደብ ያለማጠናቀቃቸው በተጠርጣሪ እና በሌሎች ሰዎች ላይ (በዋስትና፣ በመንቀሳቀስ መብት ላይ፣ …) እንዲሁም በንብረት አስተዳደር ላይ (የታገደ ንብረት የሚለቀቅበት ሁኔታ፣ የታሸገ ንብረት እሽጉ የሚነሳበት ሁኔታ…) አፍራሽ ወጤትን ያስከትላል፡፡ በተጨማሪም ስራው በጊዜ የታጠረ መሆኑ የፈጻሚ ባለሙያ ትጋት በአዎንታ እንዲጨምር የሚድረግ ኃይል ያለው ሲሆን ባልበቃ ምክንየት ስራን በሚያጓትት ባለሙያ ላይም የተጠያቂነትን ስርአት በግልጽ ሕግ አግባብ ተፈፃሚ ለማድረግ ያስችላል፡፡

ይህም በሕገ መንግስቱ የተማከተወን የተፋጠነ ፍትሕ የማጠት ግዴታን ለመወጣት የሚያስችል ከመሆኑም በላይ የሚዘገዩ ጉዳዮችን ለይቶ በአሉታም ሆነ በአዎንታ እገዛ ለማድረግና የሕጉን አላማ ለማሳካት ያግዛል፡፡

በመሆኑም ሁሉም የክርክር ሂደቶች አንድ ጉዳይ በማስመራቸው ሲገባ ሊጠናቀቅ ይገባዋል የሚባልበትን የሚጩሻ ጊዜ አካተውይዘዋል፡፡ የክርክር ስርአቶቹን በአጭሩ እንደሚከተለውተመልከተዋል፡፡

የተቀላጠፈው ስርአት በሥነ ስርአት ህጉ የተመለከተው መደበኛው ስርአት ሆኖ በማስረቱ በስነ ስርአትና የማስረጃ ህጉ ወስጥ የተቀመጠው ስርአት በሙሉ (እንዳስፈላጊነቱ) ማለፍን የሚጠይቅ ስርአት ነው፡፡ የተሟላ ማስረጃ እስከቀረበ ድረስ ማናቸውም ክርክር በተቀላጠፈ መንገድ መመራት እንደሚገባው ህጉ የሚያስገነዝብ ሲሆን ክርክር እንደተጠናቀቀም ፍርድ/ወሳኔ ወዲያውኑ እንዲሰጥ ሕጉ ግድ ይላል፡፡ ቀጠሮ የሚሰጠው ፍትሐዊ ወሳኔ ለማስጠት ይረዳል ተብሎ በተከራካሪዎች ጥያቄ ወይንም በፍርድ ቤቱ አስተያየት ሲታመንበት ነው፡፡ አንድ ጉዳይ የሚመራበት የተለየ ስርአት ባልተመለከተበት ጊዜ ወይም የተለየው ስርአት ክፍተት ባለበት ጊዜ ሁሉ ለሁሉም ጉዳዮች የሚፈጸመው ስርአት ይኸውየተቀላጠፈው ስርአት ነው፡፡ ሌሎች ስርአቶች ከመደበኛው ስርአት የተለየና ጉዳይን በአጭር ጊዜ መቋጨት የሚያስችሉ ድንጋጌዎችን ይዘዋል፡፡ በዚህ ስርአት የሚያልፍ ጉዳይ እልባ የሚያገኝበት ከፍተኛው ጊዜ ሁለት አመት ነው፡፡ ቀላል እና መካከለኛ ጉዳዮች እንደቅደምተከተላቸው በሶስት እና በስድስት ወራት ጊዜ ወስጥ እልባት እንዲያገኙ ይጠበቃል፡፡ ከባድ ጉዳይ ደግሞ እስከ ዘጠኝ ወር ባለው ጊዜ እልባት ያገኛሉ፡፡ ጉዳዮች በዚህ ጊዜ ወስጥ እልባት ስለሚያገኙበት የጉዳይ ፍሰት አስተዳደር የበላይ ፍድ ቤቶች መመሪ ወይንም ማኑዋል እንዲያወጡይጠበቃልም፡፡ ጉዳዮቹ በዚህ ህግ የ3፣ 6 ወይም የዘጠን ወራት ጊዜ የሚይጠናቀቁበት የተለየ ምክንያት ከተገኘ ጉዳዩን የሚመለከተውዳኛ ይህንን ጊዜ እስከ 45 ቀናት፣ 9 ወራት እና 2 አመት ሊያራዝም እንደሚችል በሕጉ ላይ ተመልክቷል፡፡ ይህም የሚሆነው ለተለዩ ጉዳዮች በተለዩት መዝገቦች ላይ በሚሰጥ ትዝዛዝ ነው፡፡ ሁሉም ጉዳይ ከዚህ በታችም ባጠረ ጊዜ ሊጠናቀቅ የሚችልበት እድል ያለም በመሆኑ እያንዳንዱን ጉዳይ ማስረት ያደረገ የጉዳይ ፍሰት አስተዳደር መመሪያ በፌደራል ወይም በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉባኤ እንደሚወጣ ሕጉ ታሳቢ ያደርጋል፡፡

ከመደበኛውስርአት የሚለየውሌላውስርአት የተፋጠነ የክርክር ሂደትን የተመለከተውነው፡፡ በዚህ ስርአት ወስጥ እንደ በወንጀል ጉዳይ ወስጥ የገቡ የወጣት ጥፋተኞች ጉዳይ፣ የደንብ መተላለፍ እና በክለሳ የሚታዩ የደንብ መተላለፍ ጉዳዮች፣ ቀላል የሆነ የእጅ ከፍንጅና የማስረጃ ይዘታቸው ያልተወሳሰቡ እንደ የእጅ ከፍንጅ፣ በቅድመ ክስ ተግባራት የታመኑ ወይም በማናቸውም ደረጃ የታመኑ ጉዳዮች እና ግልፅና የሚያሻማ ማስረጃ የቀረበባቸውጉዳዮች የሚታዩበት ነው፡፡

የወጣት ጥፋተኞች ጉዳይ የወጣቱን የላቀ ጥቅም ማስከበር ያለበት ለመሆኑ ሕገ መንግስታዊ እወቅና ያገኘ ጉዳይ ነው፡፡ የወጣት ጉዳይ አያያዝ ወጣቶች ከገቡበት የተሳሳተ መንገድ እንዲወጡ፣ ቀና አስተሳሰብ እንዲያዳብሩና ሰላማዊና ለህግ ተገዢ የሆኑ ዜጋ እንዲሆኑ የሚያስችል ዘዴን የተከተለ መሆን የሚገባው ለመሆኑ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው ያሰምርበታል፡፡ አላማውም ወጣቶቹን ማስተማር እና ከቤተሰቡና ከህብረተሰቡ ጋር በተሳካ ሁኔታ እንዲዋሃድ ማድረግ ነው፡፡ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው ቁጥር 6.4.2. እንደሚያመለክተው ወጣቶች በፍርድ ሂደትም ቀርበው እንዲማከሩ፣ ጥፋተኛነታቸውን እንዲያምኑ፣ ማስቀልኛ ጥያቄ እንዲጠየቁ ወይም የአቃቤ ሕግ ምስክር ሆነው እንዲማከሩ አይገደዱም፡፡ በተቻለ ማጠን ጉዳያቸው በአማራጭ መፍትሔም ማለቅ የሚገባው በመሆኑ መንገዱም ሆነ መፍትሔው አማራጭ መንገድን ያሰበ ድንጋጌ ተካቷል፡፡

የወጣት ጥፋተኞችን ጉዳይ በተመለከተ የቀድሞው ሕግ ፍላጎታቸውን ማሰረት ያደረገ አሰራር እንዲኖር የሚያስችል ድንጋጌ የነበረው መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ በሕገ መንግስቱ የታወቁትን ድንጋጌዎች ባሟላ መልኩና አለም በደረሰበት ደረጃ ሕጉን መቃኘት የሚያስፈልግ በመሆኑ ተጨማሪ ድንጋጌዎች በሕጉ ወስጥ እንዲካተቱ ሆኗል፡፡ በመሆኑም የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ይህንን የወጣት ጥፋተኛን ጉዳይ አመራርና አያያዝ አላማ ግምት ወስጥ ባስገባ መልኩ ተደንግጓል፡፡ በዚህ ማሰረት የስርአቶቹ ሁሉ ዋነኛ አላማ የወጣቱን ደሕንነትና ጥቅም ማስከበር በመሆኑ በስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ላይ የወጣት ጥፋተኞች ድንጋጌ አላማ/መርህ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ በመርህ ደረጃ በወጣት ፍትሕ አስተዳደር ወስጥ ተፈፃሚ ከሚሆኑ መርሆዎች ወስጥ ፍጥነት፣ አሳታፊነት፣ ምቹነት፣ አያያዙ የሚያስፈራ መሆን፣ መደበኛ ያልሆነ መሆን፣ የተለያዩ ልዩ እወቀት ያላቸው ባለሙያዎች አስተያየት የሚጠብትና የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡ መርሆዎቹ ይበልጥ መከበራቸውን ለማረጋጥ የወንጀል ምርመራ ተግባሩም የሚከናወነው በአቅራቢያው ባለው ፍርድ ቤት መሬነት ነው፡፡ ሕጉ ለወጣቶቹ ጉዳይ የተስማማ ልዩ መርማሪ፣ አቃቤ ህግና ችሎትም እንዲኖር ያስገድዳል፡፡

በማሰረቱ ወጣት ጥፋተኛ የሚባሉት ወንጀል በተፈፀመበት ጊዜ እድሜያቸው ከዘጠኝ እስከ አስራ አምስት አመት ድረስ ያሉት ናቸው፡፡ እነዚህ ወጣቶች ወንጀል በተፈጸመበት ጊዜ እድሜያቸው በዚህ ክልል ወስጥ ቢሆንም የወንጀሉ ምርመራ በሚደረግበት ጊዜ ግን እድሜያቸው ከአስራ አምስት አመት በላይ ሊሆን ይችላል፡፡ እድሜያቸው ከአስራ አምስት አመት በላይ ከሆነ ለወጣቶች የሚደረገው እንክብካቤና አያያዝ ትርጉም የሚያጣበት ሁኔታ ስለሚፈጠር (ለምሳሌ ሞግዚት መመደብ አስፈላጊ ስለማይሆን) የምርመራ አያያዙና የፍርድ ሂደቱ ለወጣቶች በተደነገገው ሕግ ላይመራ ይችላል፡፡ ቅጣት የሚወሰነው የአእምሮን ሁኔታ ግምት ወስጥ በማስገባት በመሆኑ ለወጣቶቹ የተደነገጉት ቅጣቶች የሚፈጸሙት ቢሆንም የጉዳዩ አመራር ግን በዚህ አግባብ ላይቀጥል ይችላል፡፡

ስለሆነም እድሜው ከ15-18 ከሆነ በፍርድ ቤቱ አስተያየት ጉዳዩ በወጣት ጥፋተኞች ደንብ ወይም በአዋቂዎች ስርአት ሊመራ የሚችል ሲሆን እድሜው ከ18 አመት በላይ ከሆነ ግን ጉዳዩ ለአዋቂዎች በተደነገገው ስርአት እንዲመራ የሚያስችል ድንጋጌን ሕጉ አካቷል፡፡

የወጣቱ ጉዳይ ምርመራ የሚጀምረው ወጣቱ ወንጀል ሲፈፅም ያገኘው ሰው/አካል ፍርድ ቤት እንዳቀረበው ሲሆን ያመጣው ሰው/አካል ስለወንጀሉ ያሰማዛግባል፡፡ ይህ ሰው የሚያስረዳው ነገር ወስጥ ወንጀል የሚመስል ነገር ከተገኘ ፍርድ ቤቱ በወጣቱ ላይ የወንጀል ምርመራ እንዲጀመር የሚያዝ ሲሆን ምርመራውም በፍርድ በቱ መሬነት ተከናወኖ ይጠናቀቃል፡፡

የወጣቱ ጉዳይ በፍርድ ቤት የሚታይ ሆኖ በፍርድ ቤትም ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ በአጥፊው ላይ ሊወሰድ የሚችለው እርምጃ ከመደበኛው ቅጣት የተለየ ሆኖ ወጣቱን በመርዳት ላይ የሚያተኩር በመሆኑ የወንጀል ምርመራው ከተለመደው ምርመራ በተጨማሪ ለዚህ መፍትሔ አጋዥ ሊሆኑ የሚችሉ የወጣቱን ባሕሪ፣ ማሕበራዊ፣ ቤተሰባዊ፣ አካባቢያዊ፣ ትምሕርት ነክ እና ሌሎች ባለሞዎች አስፈላጊ ናቸውበሚሏቸውጉዳዮች ዙሪያ የሚያጠነጥኑ መሆን እንዳለባቸው ህጉ ያስገነዝባል፡፡ የሚመለከተቻው አካላትም ለወጣቱ ግንባታ በሚያስፈልግ አግባብ ክትትል እንዲያደርጉ ሊታዘዙ ይችልሉ፡፡ በመርህ ደረጃ ወጣቱ በሞግዚቱ ወይም አግባብ ባላቸው ሰዎች ስር ሆኖ ምርመራውም ሆነ የፍርድ ሂደቱ የሚከናወን ሲሆን በየትኛውም ደረጃ ጉዳይ ክትትል የሚደረገወም በጠበቃ ተወክሎ ነው፡፡ ለወጣቱ ደሕንነትም አስፈላጊ ከሆነ ስለወጣቱ ማሕበረሰባዊ ግንኙነት (የሌሎች ሰዎችን መበት ሊነክ ቢችልም) ጊዜያዊ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ይህ ትእዛዝ ለወጣቱ ጥቅም ሲባል አስተያየቱን በመቀበል የሚሰጥ ሲሆን ትእዛዙም በወጣቱ ቤት ወስጥ ያለ ሰው ቤት እንዲለቅ፣ ወጣቱን የተወሰኑ ሰዎች እንዳያገኙት ወይም እንደይጎበኙት የሚድረግ እና የመሳሰሉት/ን እርምጃዎችን ሊያጠቃልል ይችላል፡፡

ክሱ የዳኝነት ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት የሚታይ ቢሆንም ለወጣቱ ጥቅም ሲባል ወደ ሌላ የስረ ነገር ወዳለው ፍርድ ቤት ሊዛወር ይችላል፡፡ የተዛወረለት ፍርድ ቤትም ጉዳዩን አልቀበልም ለማለት አይችልም፡፡ የፍርድ ሂደቱም የተወሰኑ ሰዎች ብቻ በተገኙበት በዝግ ችሎት የሚካሔድ ነው፡፡ ክስ የቀረበበት እንደሆነም እንደመደበኛው ስርአት ክሱ በንባብ የሚነበብለት ከሚሆን ይልቅ በቃል የሚነገረው ይሆናል፡፡ ሒደቱ በሙሉ መደበኛ ያልሆነ ስርአትን የሚከተል ነው፡፡ በማናቸውን መንገድ ወሳኔው ለሕዝብ የሚገለፅ ቢሆንም እንኳን ዘገባዎቹ ወጣቱ ተለይቶ እንዲታወቅ የሚያደርጉ (እንደ ስሙ፣ ምስሉ፣ አድራሻው፣ ትምሕርት ቤቱ....) ፍሬ ነገሮችን ማያዝ አይገባወም፡፡ ዘገባው ለሕዝብ ማለፁ የራሱ ጥቅም ቢኖረወም ዝርዝር ጉዳዮቹ የወጣቱ

የወደፊት ህይወት ላይ የራሳቸውን አሉታዊ ሚና የሚጫወቱ በመሆኑ ቢዘገቡ ወጣቱ በማኅቸወም መንገድ እንዲለይ በሚያደርግ ሚልክ አይዘገቡም፡፡ ፍርዱም በቅርጽ ደረጃ መደበኛ የፍርድ ቅርፅ ቢኖረውም በይዘቱ ግን የወጣቱን እድገትና ስብእና በማኅቸወም ሚልኩ በሚይጎዳ አግባብ ማፍ ይኖርበታል፡፡ እንደምርመራው ሁሉ የእርምት እርምጃዎች ላይ አግባብነት ያላቸውባለሞያዎች አስተያየት ሊሰጡያስፈልጋል፡፡

በወጣቱ ላይ ሊወሰድ ከሚችለውእርምት እርምጃ በተጨማሪ ወጣቱ ወደ ጥፋት እንዲገባ ያደረገወን እንክብካቤ ያጓደሉ ሰዎች ያልተከሰሱና ራሱን በቻለ ወንጀል ያልተጠየቁ ከሆነ በፍርድ ቤቱ ተጠርተው ተግሳፅ፣ ማስጠንቀቂያ ወይም ሌላ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድባቸው ሊደርግ ይችላል፡፡ ለወጣቱ ደሕንነት አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ አግባብ ያላቸው ባለሞያዎች የሚሰጡትን አስተያየት ማስረት በሚድረግ በወጣቱ ላይ የተሰጡ ማኅቸወም የእርምት እርምጃዎች በማኅቸወም ጊዜ ሊለወጡ፣ ሊቀየሩ ወይምቀሪ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

የተፋጠነ ስርአት ወስጥ ከሚመደቡ ስርአቶች ወስጥ ሌላው የደንብ መተላለፍ ጉዳዮች የሚመለከተው ስርአት ነው፡፡ ደንብ መተላለፍን በተመለከተ በዋነኛነት ጉዳዩ የክልሎች ወይም ከፍትሕ አካላት ወጪያሉን አስፈጻሚ የመንግስት አካላትን የሚመለከት ነው፡፡ በመሆኑም በደንብ መተላለፍ ጉዳይ ላይ ክስ የሚያቀርበወን፣ የዳኛነት ወሳኔ የሚሰጠው፣ የሚጣለው ቅጣት አይነት እና የወሳኔ አሰጣጥ ሥርአቱ ሁሉ ደንቡ በሚወስነው አግባብ የሚፈጸምነውየሚሆነው፡፡ በዚህ አግባብ የደንብ መተላለፍ ጉዳዮች በዋነኛት መተላለፉን በደነገገው ደንብ ወይም በሕጉ ልዩ ክፍል የሚመራ ቢሆንም በልዩ ደንቦች ባላተደነገጉ ጉዳዮች ላይ ብቻ በሥነ ሥርአቱ የተደነገጉት ስርአቶች ተፈጻሚይሆናሉ፡፡

በሕጉ ማስረት የደንብ መተላለፍ ጉዳዮች ሁሉ በቀላል ስርአት አልፈው በሁለት ሳምንት ወስጥ አልባት እንዲያገኙ ይጠበቃል፡፡ በደንብ መተላለፍ ጉዳይ ላይ ከሳሻም የሚሆነው ደንቡን የሚያስፈፅመው አካል ሲሆን ይህም ካልተመለከተ አቃቤ ሕጉ ጉዳዩን በከሳሽነት ሊከታተል ይችላል፡፡ የደንብ መተላለፍ ጉዳዮችም መደበኛ ያልሆነወን ስርአት ሊከተሉ የሚችሉ ከመሆናቸው በላይ በአብዛኛው በገንዘብ መቀጮየሚያስቀጡበመሆናቸው የደንብ ተላላፊው ሌላ ስራ ትቶ ፍርድ ቤት መቅረብ ግድ አይሆንበትም፡፡ በመሆኑም የደንብ መተላለፍ የቀረበለት ፍርድ ቤት ማመልከቻወን ለደንብ ተላላፊውየሚልክለት ሲሆን መጥሪውየተላለፈለት ተከሳሽም ፍርድ ቤት ሳይቀርብ በማመን መቀጫውን ጭምር በወከሉ፣ በፖስታ ቤት ሚልእክት ወይም በሌላ አመቺ በሆነ አግባብ ለፍርድ ቤቱ ሊልክ ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱምየገንዘብ መቀጮብቻ የሚቀጣውከሆነ ቅጣቱን ወስኖ ተከሳሽ ከላከው

መቀጮጋር ልዩነቱ እንዲታሰብ ያደርጋል፡፡ ተከሳሽ ያልቀረበም እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ተመልክቶ ወሳኔ በማስጠት ወሳኔወን እንዲፈጽም ይልክለታል፡፡

ከፍ ሲል በተማለከተው ማስረት የደንብ ተላላፊው ፍርድ ቤት መቅረብ የሚያስፈልገው ቢሆንም የደንብ ተላላፊው በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ፍርድ ቤት ሊቀርብ ይችላል ወይም እንዲቀርብ ሊገደድ ይችላል፡፡ የመጀመሪያው ክሱን የካደ እንደሆነ ነው፡፡ በዚህ ግዜ ተከሳሹ ቀርቦ የመከራከርና የመካላከያ ማስረጃ የማሰማት መብት ይኖረዋል፡፡ ደንብ ተላላፊው ቀርቦ የሚከራከር ቢሆንም ክርክሩ በተቀላጠፈ ሁኔታና በቃል ብቻ የሚደረግ ይሆናል፡፡ የሚሰሙምስክሮች ካሉም በዋናው ፍሬ ነገር ላይ ብቻ የሚማከሩ ሲሆን ቃላቸውም በሙሉ ሳይመዘገብ ከቃላቸው ወስጥ ዋናው ብቻ ተለይቶ ይመዘገባል፡፡ የደንብ መተላለፍ የፈፀመው ሰው ፍርድ ቤት ሊቀርብ የሚችልበት ሌላውምክንያት በፍርድ ቤት የሚወሰነው ቅጣት ከገንዘብ ቅጣት ወጪያ ሆነ እንደሆነ ነው፡፡

በደንብ መተላለፍ ስርአት ወስጥ የሚገኘው ሌላው ልዩ ስርአት የደንብ መተላለፍ ጉዳዮች በክለሳ (ሳመሪ) ስርአት የሚታዩበት ስርአት ነው፡፡ በተወሰኑ የደንብ መተላለፍ ጉዳዮች ላይ የቀረበው ክስ ግልጽና በተከሳሹ የሚይካዱ ሲማስሉ አቃቤ ሕግ (ወይም ከሳሹ) ከክሱ ጋር ተከሳሽ ሊቀጣ ይገባዋል የሚለወን የቅጣት ማጠንና አይነት አካቶ ክስ እንዲያቀርብ ሕጉ የሚፈቀድ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ክሱን እና የቅጣት ማጡኑን እንዳለ በመቀበል ለተከሳሽ ይልክለታል፡፡ ተከሻሽም ጥፋቱን አምኖ ከተቀበለው ፍርድ ቤቱ ከክሱ ጋር የተማለከተወን ቅጣት ተከሳሹ እንደፈጸም ትእዛዝ በማስጠት መዝገቡን ይዘጋዋል፡፡ ተከሳሽ መጥሪያው ደርሶት በሁለት ሳምንት ጊዜ ወስጥ ሜልስ ካልሰጠም ክሱን እንዳማ ተቆጥሮ በተማሳሳይ ወሳኔወን እንዲፈፅም ይታዘዛል፡፡ ተከሳሽ ክዶ ከተከራከረ ግን ጉዳዩ በደንብ መተላለፍ ደንብ ማስረት ይታያል፡፡ በዚህ ሜልኩ ከሚከተቱት ቅጣዮች ወስጥ ማስጠንቀቂያ ብቻ የሆን ቅጣት፣ የስራ ፈቃድን (ላይሰንስን) መማለስን የሚማለከት ቅጣት፣ በገንዘብ ብቻ የሚያስቀጣ የደንብ መተላለፍ፣ በአንድ ነገር ከመገልገል መከልከልን የሚማለከት ቅጣትና የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡

በተፋጠነ ስርአት የሚታው ሌላው ጉዳይ የእጅ ከፍንጅ ጉዳይ ነው፡፡ የእጅ ከፍንጅ ጉዳይ ከዚህ ቀደም ማሳል እና ተማሳሳይ በማባል የሚታወቁትን በማከተት በሕጉ አንድ ወጥ ግልጽ ትርጉም ተሰጥቶታል፡፡ በባህሪው ማስረጃ የተሟላበት ስለሆነ ያለቀጠሮ ያልቃል ተብሎ የሚታሰብ ነው፡፡ ይህ ሂደት የመደበኛ ስርአቶችን መከተልን ግድ ሊል ቢችልም በባህሪው ያልተወሳሰበ እና የተሟላ ማስረጃ የሚቀርብበት በመሆኑ ቢዘገይ በሶስት ወር ጊዜ ወስጥ

እልባት የሚሰጥት ጉዳይ ነው፡፡ ከመደበኛው ስርአት የሚለየው ክርክር የሚቆራረጥበት መሆኑና ይህ አጭር የጊዜ ገደብ ያለው መሆኑ ነው፡፡

የታመሙ እና በአማራጭ መንገዶች የታዩ ጉዳዮችም በዚህ ስርአት ወስጥ የሚካተቱ ናቸው፡፡ እነዚህ ስርአቶች ከሌሎቹ ለየት የሚያደርጋቸው መሉ የክርክር ማስማርን ማለፍ የሚጠበቅባቸው ሲሆኑ ሁነቶቹ እንደተከሰቱ (ለምሳሌ እንደታመመ፣ የእርቅ ወጤት እንደቀረበ) ያለ ቀጠሮ ወዲያወኑ ወሳኔ የሚሰጥባቸው መሆናቸው ነው፡፡

## 13.7. ቀጠሮ፣ መቃወሚያና እምነት ክህደት

ክርክሮች በየትኛውም አግባብ የሚሞሉ ቢሆን ክርክር በማስረቱ ሳይቆራረጥ በተከታታይ መመራት ያለበት ነው፡፡ ይህ መርህ በግልጽ የተማከተ ከመሆኑም በላይ ቀጠሮ ሊያሰጡ የሚገባቸው ምክንያችም (ለምሳሌ ለረፍት፣ ለሬጂስትራር ተግባራት፣ በህግ ጉዳይ ላይ በቀረበ መቃወሚያ ብይን ለማስጠት፣ እና ለማሰል ምክንያቶች) በሕጉ ላይ በግልጽ ተቀምጠዋል፡፡ ጉዳዩ በተከታታይ የታየ ለመሆኑ የሚማከትበት አንዱ መንገድ የእለት ተግባራትን በመዝገብ በአግባቡ መመዝገብ ሲቻል ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ መታይት ከጀመረበት ሰአት አንስቶ እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ ያለው የየእየለቱ የችሎት ክንወኖች እና ሌሎች ፍሬ ነገሮች (ለምሳሌ የችሎቱ ስም፣ የዳኛና ተከራካሪ ወገኖች ስም፣ ፊረማ...) በመዝገብ ላይ ማስፈር ወይም በኤሌክትሮኒክስ ማሪያ መቀረፅ የሚገባቸው እንደሆነ ሕጉ ድንጋጌ የያዘ ሲሆን ይህም ለግልጸኝነት፣ ለተጠያቂነት እንዲሁም ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ተግባር አጋዥነት እንዲሆን ታስቦ የተካተተ ነው፡፡ ይህ ተግባር በክስ ማስማት ጊዜ በተለየ ትኩረት የሚፈፀም ቢሆንም ፍርድ ቤት ማናቸወንም ተግባራት በሚያከናወንበት ጊዜ እነዚህ ኩነቶች መመዝገብ ወይም መቅረፅ ይጠበቅበታል፡፡

ክርክር ተከታታይ ቢሆንም በተወሰኑ ምክንቶች በተለይም ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ሲባል ቀጠሮ ማስጠት የሚያስፈልግ በመሆኑ ይህንን ሁኔታ ያገናዘበ ቀጠሮ የሚሰጥባቸወን ምክንያቶች እና ለቀጠሮ ልክ መወሰኛ መርህን ህጉ ያስቀምጣል፡፡ በዚህ ረገድ ነባሩ ህግ ላይ ማስረታዊ ለወጥ አልተደረገም፡፡

ቀጠሮ ከሚሰጥባቸው ምክንያቶች ወስጥ አንዱ የተከሳሽ የጤንነት ሁኔታ ነው፡፡ የችሎት ተግባር ተከታታይ ቢሆንም ተከሳሽ በአእምሮ ወይም በአካሉ ላይ በደረሰበት የጤና ችግር የተነሳ የችሎት ተግባርን በአግባቡ ለመከታተል የሚችል ሊሆን ይችላል፡፡ የዚህ አይነት አጋጣሚዎች በተግባር የሚያጋጥሙ ቢሆንም ምላሽ ለማስጠት የሚያስችል ህግ የሌለ በመሆኑ የፍትህ አካላት ሲቸገሩ ቆይተዋል፡፡ ይህ ሁኔታ በህግ ሊፈታ የሚገባው በመሆኑ ተከሳሽ በክስ ማስማት ሂደት በጤናው የተነሳ ችሎቱን መከታተል ያልቻለ እንደሆነ

እንደሁኔታው ችሎቱ ለተወሰነ ጊዜ የጉዳዩን ማየት የሚያቋርጥበት ወይም ጉዳዩ ላይ ፍርድ ሰጥቶ ቅጣት የሚወስንበት ነገር ግን አማራጭ እርምጃዎች (መፍትሔዎች) እንዲወሰዱ የሚደረግበት አግባብ ተደንግጓል፡፡ ተከሳሹም የጤንነቱ ሁኔታ በተሻሻለበት ጊዜ ክርክሩ እንደገና እንዲታይ የማጠየቅ መብት አለው፡፡

ፍርድ ቤት በማናቸውም ቀጠሮ በሰጠባቸው ጊዜያት የሚያከናወናቸው ተግባራት አሉ፡፡ ከእነዚህ ተግባራ ወስጥ ተከራካሪ ወገኖች መቅረባቸውን የሚረጋገጥ፣ ማንነታቸውን ማረጋገጥና የመሳሰሉት ተግባራት ይገኙበታል፡፡ ፍርድ ቤቱ የተከሳሽን ማንነት ለማረጋገጥ ከተለመዱት ስም፣ እድሜ ስራና አድራሻ በላይ ሌሎች ጥያቄዎችን ጭምር ጠይቆ መመዝገብ እንደሚችል በሕጉ ተደንግጓል፡፡ ተጨማሪዎቹ ጥያቄዎች ፍርድ ቤቱ በሰተኋላ ለሚያከናወናቸው ተግባራትም ጠቀሜታ አላቸው፡፡ ለምሳሌ የተከሳሽ ቤተሰብ ብዛት ወይም እምነቱ የማንነቱ ማረጋገጫ ከመሆናቸውም በተጨማሪ በቅጣት ወሳኔ ወቅት ወይም ማስረጃ በሚመዘንበት ወቅት ሃሰተኛ ማስረጃ እንደያቀርብ ወይም ለማቅረበው ክርክር ታማኝነት ለማረጋገጥ የሚያግዝ ጠቃሚማ ናዘቢያዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ማንነትን ማረጋገጥን በተመለከተ ሕጉ ዝምከማለት መብት ጋር ያለውን አፈጻጸም የሚዳስስ ድንጋጌን አካቷል፡፡ በክርክር ሒደት ዝም የማለት መብት ያላግባብ ጥቅም ላይ የሚውልበት አጋጣሚዎችም ያሉ በመሆኑ ተከሳሹ ማንነቱን በማረጋገት ሂደት ወስጥ ዝም የማለት መብት አለኝ ሊል እንደሚይችል ተመላክቷል፡፡ በቀሪ ጉዳዮች ላይ ግን ለማቅርብለት ጥያቄ ዝምማለት መብቱ ነው፡፡ የተከሳሽ ማንነት ከተረጋገጥ በኋላ የሚቀጥለውተግባር የቅድመክስ ማስማት ተግባራት እንዲከናወኑ የታዘዘ ከነበረ ይኸው መፈጸሙን ማረጋገጥና ከተፈጸመውተግባር ቀጥሎ ያለውን ተግባር ማከናወን ነው፡፡ ስለሆነው ፍርድ ቤቱ በአብዛኛው በቀጥታ ክሱን (እያዳንዱን ክስ) በንባብ ወደ ማስማትና ተከታይ ተግባራትን ወደ ማከናወን ይገባል ማለት ነው፡፡ ክሱ ከተነበበ በኋላ ተከሳሹ ክሱን (ወይምእያንዳንዱን ክስ) በአግባቡ የተረዳውለመሆኑ ፍርድ ቤት በቀጥታ ጠይቆ ያረጋግጧል፡፡ ተከሳሹም የክስ መቃወሚያ ያለው እንደሆነ ያቀርባል፡፡ የክስ መቃወሚያ የሚቀርብባቸው ምክንያቶች በሕጉ ወስጥ በዝርዝር የተመላከቱት ቢሆንም ዝርዝሩ አመላካች እንጂ ያለቀለት አይደለም፡፡ ስለሆነምፍርድ ቤትን ወደ ፍሬ ነገሩ የሚያስገባ ማናቸውም መቃወሚያዎች ክርክር በሚካሔድበት ወቅት እየቀረቡ ፍርድ ቤቱን ወደ ኋላ የሚመልሱ እንዳይሆኑ ቀድመው መነሳት የሚችሉበትን እድል ማስፋቱ የተገባ ነው፡፡ በሌላ በኩል ህንን ሰፋ ያለ እድል አላስፈላጊ በሆነው አግባብ ጥቅም ላይ በማዋል አላስፈላጊ ፍሬ ነገር ወስጥ እየተገባ ክርክር ያለቦታው እንዳይቀርብም ዳኛው ይቆጣጠራል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ይህ እድል ከመጀመሪያው የሰፋ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ ላይ ወሳኔ እንዳይሰጥ የሚያደርጉ መቃወሚያዎችም ወደፊት በማናቸውም ጊዜ ሊነሱ ይችላሉ፡፡ የዚህ አይነት መቃወሚያዎችን ተከሳሽ በወቅቱ አያነሳቸውም ተብሎ የሚጠበቅ ከመሆኑም በላይ መቃወሚያዎች ሳይፈቱ ፍርድ

ቤቱ የሚጸና ውሳኔ ይሰጣል ተብለው ስለሚታሰብ ወደፊት መሳት እንዲችሉ ሚፈቀዱ ምክንያታዊ ነው፡፡ መቃወሚያ በማስረቱ ከፍሬ ጉዳይ በፊት ያለ ክርክር በመሆኑ በተቻለ ወጠን ወዲያውኑ ወሚሰን ይገባቸዋል፡፡ በተለይም መቃወሚያዎቹ የሕግ ጉዳይን የሚመለከቱ ከሆነ ፍርድ ቤቱ ያለቀጠሮ ውሳኔ ሊሰጥባቸው እንደሚገባ የሚያስገነዝብ ድንጋጌ ተካቷል፡፡

መቃወሚያ ያልቀረበ ወይም መቃወሚያው ውድቅ የተደረገ እንደሆነ የሚቀጥለው ሥነ ሥርአት የተከሳሹን እምነት ክሕደት ቃል መቀበል ነው፡፡ ተከሳሹ የእምት ቃል የሰጠ እንደሆነም አምኗል በሚል ብቻ ተመዝግቦ ውሳኔ የሚሰጥበት ሳይሆን የእምነት ቃሉ ከክሱ ጋር በሚጣጣም መልኩ ተዘርዝሮ መመዝገብ ይገባዋል፡፡ ይህም ተከሳሹ በእርግጥ የክሕደት ቃል እየሰጠ አምኗል በሚል ውስኔ እንዳይሰጥና የመከላከል መብቱ ያላግባብ እንዳይጠበ ያስችላል፡፡ ተከሳሹ በግልጽ ክሱን ከካደ፣ ዝም ያለ እንደሆነ ወይም በከፊል ያመነ እንደሆነ ጥፋተኛ አይደለሁም እንዳለ ተቆጥሮ ክሱ በማስረጃ እንዲረጋገጥ ይሆናል፡፡ ምንም እንኳን ተከሳሹ ክዶ የተከራከረ ቢሆንም በሂደት ወንጀል የፈጸመ ለመሆኑ የእምነት ቃሉን መስጠት ሊፈልግ ይችላል፡፡ በነባሩ ሕግ ይህንን ሁኔታ በቀጥታ የሚያስተናግድ ስርአት አልነበረም፡፡ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ይህንን ክፍተት በመሙላት ተከሳሽ በሒደት የእምነት ቃሉን ሊሰጥ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ ተከሳሹ በዚህ ደረጃ የሚሰጠው ቃል በእርግጥ በመጸጸት የሚሰጠው ቃል እንጂ ክርክ ስለረዘማበት ለማሳጠር፣ ሌላ ወንጀል የፈጸመ ሰውን ለመደበቅ ወይም በማናቸውም ምክንያት እውነቱ እንዳይወጣ ለመደበቅ አለመሆኑን ግን ጉዳዩን የያዘው ፍርድ ቤት የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

## 13.8. የማስረጃ ደንቦች

ኢትዮጵያ በአመዛኙ የሲቪል ሎው የሕግ ሥርዓትን የምትከተል አገር በመሆኗ የአገሪቱ የሕግ መጻሕፍት ወይም ኮዶች የተደራጁትና የዳኝነት ሥርአቱ የሚመራው በዚሁ የሕግ ስርአት ዘንግ አግባብ ነው፡፡ አንዳንድ የኮመን ሎው የሕግ አስተሳሰቦችና ፍልስፍናዎች በሥነ ሥርዐት ሕጎቻችን የተካተቱ ቢሆንም የተደራጁትና የተቀረጹት ግን በሲቪል ሎው የሕግ ሥርዓት እንደሆነ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ የማስረጃ ሕግ ድንጋጌዎች የተደራጁትና የተካተቱት በሲቪል ሎው የአቀራረጽና የአቀራረብ ሥርዓት ነው፡፡ የማስረጃ ሕጎች/ደንቦች በፍሬ ሕግ እና በሥነ ሥርዐት ሕጎች ወስጥ በተወሰነ ደረጃ በየቦታው ተካተው የሚገኙና ሲሠራበቸው የቆዩ መሆናቸው የሚታወቅ ከመሆኑ አንፃር የማስረጃ ሕግ የለንም የሚለው ጥቅል ድምዳሜ መሉ በሙሉ ለመቀበል የሚይቻል መሆኑን ያመለክተናል፡፡ ይሁን እንጂ በፍሬ ሕግም ሆነ በሥነ ሥርዐት ሕጎች ወስጥ ያሉት ደንቦች የተሟሉ ካለመሆናቸውም በላይ ለበርካታ ዘመናት ያገለገሉ በመሆናቸው በአሁኑ ወቅት ዘመኑ የወለደውን

ዘመናዊ የኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ለውጦች እና ማስተጋብሮችን ሙሉ በሙሉ ሊገዙ አልቻሉም፡፡ በመሆኑም በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት እና የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው ተቀባይነት ያገኙ የማስረጃ መርሆዎች በሕጎቹ ወስጥ ሙሉ በሙሉ ያልተሸፈኑ ከመሆናቸውም በላይ ዘመኑ የፈጠራቸው የዳበሩ አዳዲስ መርሆዎችና አስተሳሰቦችም በተመሳሳይ ሁኔታ በሕጎቹ ወስጥ አለመካተታቸው የማስረጃ ሕግ እንዲኖር ግድ ብሏል፡፡ ከዚህ አንፃር የማስረጃ ሕግ መኖሩ ግድ ከሆነ አወጣጡ በተመለከተም የሚኖሩት አማራጮች፤

1. ሁሉንም የማስረጃ ሕግ ደንቦችን የያዘ አንድ የማስረጃ ሕግ ወይም ኮድ ማውጣት፤

2. ዋና ዋና መርህዎችን ብቻ የያዘ ልዩ የማስረጃ ሕግ ማውጣት፤

3. በየኮዱ ወስጥ ያሉትን የማስረጃ ድንጋጌዎችን በማሻሻል የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ አካል አድርጎ ማውጣት፤

ሲሆኑ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ቅድመ ረቂቅ ጥናት ላይ እንደተመለከተው ሶስተኛው አማራጭ ከወንጀል ፍትሕ ስርአቱ ጋር የተጣጣመና በተሻለ ሁኔታ የማስረጃ ሕግ ችግሮችን ሊቀርፍ እንደሚችል በማመልከቱ የወንጀል ነክ የማስረጃ ድንጋጌዎችን የዚህ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ አካል ሆኖ ወጥቷል፡፡

በመሆኑም ከዚህ ቀደም የነበረው የስነ ስርአትና ማስረጃሕግ የተወሰኑ የማስረጃ ደንቦችን የያዘ ቢሆንም ይህ የሥነ ስርአት ህግ ከዚህ ቀደም ከነበረው በመሰረቱ በተለየ ሚሉኩ በወንጀል ጉዳይ ተፈጻሚ የሚሆኑ የማስረጃ ደንቦችን በዝርዝር አካቷል፡፡ የነበረው ሕግ የማስረጃ ደንቦችን እጅግ በተቀነጨበ ሁኔታ እዚህም እዚያም ይዞ የነበረ ቢሆንም በማስረጃ ጉዳይ ላይ የሚነሱ በርካት ጥያቄዎችን ሳይመልስ ቀርቷል፡፡ ስለሆነም በተግባር እንደሚታየው በማስረጃ ጉዳይ ላይ ከአገራችን ስርአት ይልቅ ከፍትህ ስርአታችን ጋር ስለመጣጣሙ በአግባቡ ያልተረጋገጠ ስርአት ወይም የሌሎች አገራት መርሆዎችና አሰራሮች ሲተገበሩ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ይህ ወጥ አሰራር እንዳይኖር ያደረገ በመሆኑ በወንጀል ጉዳይ ወጥ ያልሆነ አሰራር በሰብአዊ መብት ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ከፍተኛ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ የፌዴራል ሰበር ሰሚችሎት በማስረጃ ጉዳይ ላይ በርካት ወሳኔዎችን አሳልፏል፡፡ ይህም ቢሆን የሰበር ወሳኔ የሚሰጠው ለፍርድ ቤቱ የቀረበን ክርክር ብቻ መሰረት አድርጎ በመሆኑ ለሁሉም ጥያቄዎች በአንድ ጊዜ ሚልስ የማስጠት አቅም አይኖረወም፡፡ በመሆኑም ሌሎች አገራትን ልምድ በመወሰድና በወንጀል ጉዳይ ላይ ወጥነትን በሚረጋገጥ ወጤታማ የፍትሕ አስተዳደር እንዲኖር እንዲሁም በክርክር ሂደት

የፍትሕ አካላት እውነትን የማውጣት ሃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ለማስቻል የማስረጃ ደንቦችን በተቻለው ማጠን ግልጽና ለአጠቃቀም በሚያመች መልክ የሥነ ስርአት ህጉ አካል እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

ከዚህ አንፃር ሕጉ በማስረጃ ጉዳይ ሕጉ ማስረጃ ምንድን ነው የሚለውን በመጀመሪያ ደረጃ ግልጽ ያደርጋል፡፡ በዚህ መሰረት ማስረጃ በመሰረቱ አግባብ የሆነን ነገር ሁሉ ለማስረዳት የሚቀርብ ማንኛወም ነገር እንደሆነ የተደነገገ ሲሆን ይህም የተከሳሽ ቃልን፣ ምስክርን፣ የህሊና ግምትን፣ ግንዛቤ የሚወሰድባቸው ጉዳዮችንና ሌሎች ማስረጃዎችን ያካትታል፡፡ እነዚህ ማስረጃዎች በዋነኛት የተካደ ነገርን ለማስረዳ የሚቀርቡ ሲሆን የታመኑ እና በፍርድ ቤት ግንዛቤ የሚወሰድባቸው ነገሮች በማስረጃ ማረጋገጥ የሚያስፈልጋቸው አይደሉም፡፡

ማስረጃ ሁሉ በጭብጥ ለተያዘው ነገር አግባብነት ያለውና ተቀባይነት ያለው መሆን እንደሚገባው ሕጉ ያስቀምጣል፡፡ ጭብጥ የሚባለውም ከሳሽና ተከሳሽ ያልተማመኑባቸው ማናቸውም ነጥቦች ሁሉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ተከሳሽ ክስን ከላይ በተመለከተው ማናቸውም አግባብ ክዷል የሚባል ቢሆን የዐቃቤ ሕግ ክስ ማረጋገጥ የሚገባው ጭብጥ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ጭብጥን የሚያስረዳው አግባብነት ያለው ማስረጃ ሲሆን ለአረዳድ እንዲቀልም አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎች በግልጽ ተዘርዝረው ተመልክተዋል፡፡ ማስረጃዎች ሁሉ ሕጉን ተከትለው የተገኙ መሆን እንዳለባቸው በግልፅ የተደነገገ ከመሆኑም በላይ ሕገ መንግስቱና የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው(ቁጥር 3.16) በሚደነግጉት አግባብ በሕገ ወጥ መንገድ የተገኘ ማስረጃ እንዲሁም በሥነ ሥርአቱ ከተደነገገው ስርአት ወጪ የሰብአዊ መብት ጥሰትን ባስከተለ መንገድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት እንዳይኖረው የሚያስገድድ ሕግም ስነ ስርአትና ማስረጃህጉ አካቷል፡፡

በማስረጃ ዝርዝር ወስጥ መጀመሪያ የተመለከተው የሰው ምስክር ነው፡፡ የሰው ምስክርን በተመለከተ ህጉ ማንኛወም ሰው በወንጀል ጉዳይ የመመስከር ብቃት እንዳለው የሚገመት እንደሆነና የመመስከር ግዴታም ያለበት ለመሆኑ ይደነግጋል፡፡ ማንኛወም ሰው በተያዘው ጉዳይ ላይ ለጊዜው ወይም በአጠቃላይ የመመስከር ብቃት የለውም ሊባል የሚችለው ጉዳዩን የሚመለከተው ፍርድ ቤት ከተከሳሽ ሁኔታ (እድሜ መጃጃት፣ ጤንነት፣ ወይም ሌላ ምክንያት) ላይ ተመስርቶ ምስክሩ በትክክል ጥያቄዎችን ለመረዳትም ሆነ የተረዳወን ለማስረዳት የሚይችል ነው በማለት ሲወስን ነው፡፡ ከመብት የተሻረ ልዩ አዋቂ ግን በሕግ መሰረት ከመብት የተሻረ በመሆኑ የሙያ ምስክር ለመሆን ብቃት አይኖረወም፡፡

ማንኛወም ሰው የመመስከር ግዴታ ቢኖርበትም ከተከሳሽ ጋር ባለው ጥበቃ በሚደረግለት ልዩ ግንኙነት (የሓይማኖት፤ የሕክምና፣ የጥብቅና ግንኙነት፣ የትዳር ግንኙነት) የተነሳ ያወቁትን እንዲመስክሩ

አይገደዱም፡፡ በዚህ ልዩ ግንኙነት የተነሳ የተገኘ እውቀት እንዲመሰከር ግዴታ ቢጣል ግንኙነቶች በጥብቅ ሚስጥር ላይ የሚመሰረቱና ለሕብረተሰቡ ማሕበራዊ ግንኙነትም ማሰረታዊ በመሆናቸው ግንኙነቶቹ እንዳይኖሩ የሚያደርግ ወጤት ስለሚኖረው ጥበቃ መደረጉ ተገቢ ነው፡፡ የግንኙነቱ ባለቤቶች ግን ይህንን መብት ላለማጠቀም ሊፈቅዱ ይችላሉ፡፡ በተመሳሳይ ሚሊኩ በመንግስት ሚስጥር ነውየተባለን መረጃ/ማስረጃ፣ ከአገር ደህንነት ጋር እንዲሁም በልዩ የምርመራ ዘዴ ስለተገኘ ማስረጃ እውቅና ያላቸው ሰዎች በዚህ ረገድ ስለሚያወቁት ነገር መመስከር የማይችሉ ከመኖቸውም በላይ ለመመስከር በግል ቢፈቅዱም እንኳን እንዲመሰክሩ የሚፈቀድላቸው አይደሉም፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ጥበቃ የሚደረግለት ምስክሩ ስለተሳተፈበት ስርአት እንጂ ስለግል ግንኙነት ባለመሆኑ መብቱን ላለማጠቀም በመወሰን መመስከር አልተፈቀደም፡፡

የምስክርን ብዛት እና የአቀራረብ ቅደም ተከተልን የመወሰን መብት ምስክርን የሚያቀርበውወገን መብት በመሆኑ አንድን ጉዳይ (ክስን ጨምሮ) በተለምዶ ከሚነገረው በተቃራኒው በአንድ ምስክር ብቻም ቢሆን ማስረዳት ይችላል፡፡ ምስክርን የሚያቀርብ ወገን ምስክርን በሃሰት ከማስጠናት መቆጠብ ያለበት ሲሆን ምስክሩ ለፍርድ ቤት ቀርቦ ትክክለኛ ቃሉን እንዲሰጥ ግን ቀድሞ አግኝቶ ሊያዘጋጀው ይችላል፡፡ ምስክሩ የሚመሰክርበትን ልክ በተመለከተም ምስክር ቃል ሊሰጥ የሚችለው ስለሚያውቀው ጉዳይ ብቻ እንደሆነ ሕጉ በግልፅ ደንግጓል፡፡ ይህ ድንጋጌም ከዚህ በፊት ቀጥታ/ቀጥታ ያልሆነ፣ የስሚ ስሚ እና ተዘዋዋሪ ማስረጃዎች በሚል ይታዩ የነበሩ የአረዳድ ብዥታዎችን በማጥራት ወጥ አረዳድ እና ትግበራ እንዲኖር ያስችላል በሚል እምነት ተስተካክሎ የገባ ነው፡፡ በሕጉ መሰረትም ምስክር የሚያወቀውን ያስረዳል ማለት አንድ ምስክር ሊመሰክር የሚገባው በአምስቱ የስሜት ሕዋሳቶቹ አማካኝነት በቀጥታ ስለተረዳው ጉዳይ ነው ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ ምስክሩ በአይኑ ስላየው፣ በጆሮው ስለሰማው ወይም በአፍንጫው ስላሸተተው ጉዳይ ሊመሰክር ይችላል፡፡ አንድ ሰው በመሞት ላይ እያለ ለምስክሩ "አከሌ ነው የገደለኝ" ብሎ ቢነግረው ምስክሩ ይህንን የሰማውን ቃል ለፍርድ ቤት ማስረዳት ይችላል፡፡ ይህንን መመስከር ምስክሩን የስሚ ስሚ አያደርገውም፡፡ አንድ ሰው ቤት ያቃጠለ ለመሆኑ ክስ ቢመሰረትበት አንደኛው ምስክር ተከሰሹ ክብሪት ሲገዛ የተመለከተ ለመሆኑ፣ ሁለተኛው ጭስ የሸተተው መሆኑን፣ ሶስተኛው ምስክር ደግሞ ተከሳሹ ጋዝ ሲገዛ የተመለከተ ለመሆኑ መመስከር ይችላሉ፡፡ እነዚህ ምስክሮች ስለ ቃጠሎ የሚያወቁት ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ቢሆንም የሚመሰክሩት የሚያወቁትን ብቻ በመሆኑ ምስክርነቱ ቀጥተኛ መሆን አለመሆን ላይ ለወጥ አያመጣም፡፡ በእነዚህ ሁሉ ጉዳዮች ምስክሮቹ የሚመሰክሩት በቀጥታ በስሜት ሕዋሳታቸውአማካኝነት ስለተረዱት ጉዳይ በመሆኑ ለጉዳዩ አግባብነት እስካላቸውድረስ ተቀባይነት አላቸው፡፡ ስለሆነም ምስክር የሚመሰክረውበቀጥታ ስለሚያወቀውነገር ነውበማለት ህጉ ሲደነግግ ከሌላ የሰማውን፣ ቀጥታ

ባልሆነ መንገድ ያወቀውን አይመሰክርም ማት አይደለም፡፡ ማስረጃው በቀጥታ አይሁ ብሎ እንደሚመሰክረው ሁሉ ሌላ ሰውነገረኝ ብሎ መመስከር ይችላል፡፡ ትልቁ ጉዳይ ምስክሩ በማናቸውም መንገድ ያወቀውን በቀጥታ ሲናገር በዳኛ ምዘና የሚሰጠው የማስረጃት ክብደት ነው፡፡

ምስክር የሚያወቀውን ለማስመስከር ወይም ስለሚያወቀው ጉዳይ በትክክል እየመሰከረ መሆኑን ለማጤተሽ ዋና፣ መስቀልኛ፣ ድጋሚ ማጣሪያ እና ማስተባበያ ጥያቄዎች እንዳግባቡ ሊቀርቡለት ይችላሉ፡፡ የጥያቄዎች ምንነት በሕጉ ወስጥ በግልጽ የተመለከቱ ሲሆን በጥያቄዎቹ አቀራረብ ላይ የተወሰኑ ገደቦች ተደርገዋል፡፡ ለምሳሌ በተወሰነ ምክንያት (አሰጠቂ፣ የረሳ፣ በፍቃድ...) ካለሆነ በቀር ምስክርን የጠራ ወገን ለምስክሩ መልስ በሚጎ ግር ሁኔታ እየመራ ሊጠይቅ አይችልም፡፡ በተመሳሳይ ምክንያት ምስክርን በማዋረድ፣ ማንነቱን በመንካት ማንኛወንም ጥያቄ ማጠየቅ ከስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ አላማ የሚወጣ በመሆኑ እነዚህና መሰል ጥያቄዎችም የተፈቀዱ አይደሉም፡፡ የዚህ መሰል ጥያቄዎች በማናቸውም ሁኔታ ምስክር በትክክል የሚያወቀውን እንዳይመሰክር ሊያደርጉ የሚችሉና እውነት እንዳይወጣ ሊያደርጉ የሚችሉ በመሆናቸው መከልከላቸው የተገባ ነው፡፡ የቀሪ ጥያቄዎች አጠያየቅ ከሞላ ጎደል በነበረው ሕግ አይነት ነው፡፡

በጉዳዩ ላይ የሚቀርቡ ምስክሮች በመሰረቱ በተከራካሪ ወገኖች የተቆጠሩ ቢሆንም ጉዳዩን የሚመለከተው ፍርድ ቤት ትክክለኛ ፍትሕ ለማስጠት ያግዛል ብሎ ካመነ የፍርድ ቤት ምስክርን ጠርቶ ሊሰማና ቃሉን ሊመዝን ይቻላል፡፡ ለዚሕ አይነት ምስክር ጥያቄ የሚቀርበው በራሱ በፍርድ ቤቱ ብቻ ቢሆንም ተከራካሪ ወገኖች ይጠየቁልን የሚሏቸው ጥያቄዎች ካሉ ፍርድ ቤት ሲያምንባቸው በፍርድ ቤቱ አማካኝነት ሊጠየቁ ይችለሉ፡፡ የሚቀረበወን የጥያቄ አይነትም ፍርድ ቤቱ በሚያምቸው አግባብ ሊያቀርበው ይችላል፡፡

ለፍርድ ቤት ሊቀርብ የሚችለው ሌላው የማስረጃ አይነት የሰነድ ማስረጃ ነው፡፡ ሰነድ ማንኛወንም መረጃ የያዘና በመሳሪያ ሊነበብ የሚችል እንደሆነ ሕጉ ሰፋ ያለ ትርጉም ይሰጠዋል፡፡ በዚህ መሰረት ለተለያዩ አላማ የሚደራጁ መዝገባች፣ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች፣ ፅሁፍን ድምጽን ምስልን ወይም ሌላ መረጃን የሚይዙ ሁሉ ሰነድ ናቸው፡፡ ተመራጭ ሚሆነው የማስረጃው ደንብ ዋናወን ሰነድ በማቅረብ ማስረዳት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ዋናው ሰነድ የጠፋ፣ የተቀደደ ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ሊቀርብ ያልቻለ እንደሆነ በዋናው ሰነድ ምትክ በቅጂው ማስረዳት ይቻላል፡፡ በሰነድ ማስረጃ ጉዳይ ላይ አንዱ አሰቸጋሪ ነገር የሰነዱን ትክክለኛነት ማስረዳት በመሆኑ ሕጉ የሰነዶች ትክክለኛነት ሊረጋገጥ የሚችልባቸውን መንገዶችንም አመልክቷል፡፡ ከሰነድ ማስረጃ ወሰጥ የኤሌክትሮኒክስ ማስረጃ የራሱ የተለየ ባህሪ እንዳለው ይታወቃል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይም በሌሎች

አካላት የሚወጡሌሎች እሌክትሮኒክስ ነክ ሕጎችም መኖራቸው ይታወቃል፡፡ ስለሆነም ለተለያየ አላማ የሚወጡ እነዚህን ሁሉ ሕጎች በስነ ስርአትና ማስረጃ ህጉ ወስጥ አንድ ላይ አካቶ ማውጣት የሚይቻል በመሆኑ በሌሎች ህጎች የተመለከቱት ደንቦች እንዳግባቡ ለዚሕ ሕግም ተፈፃሚእንደሚሆኑ ማመለከቱ ተገቢ በመሆኑ በዚህ አግባብ ተመላክቷል፡፡

ሌላው የማስረጃ አይነት ለፍርድ ቤት እይታ ቀርቦ የሚታየው ማስረጃ ወይም ኤግዚቢት በመባል የሚታወቀው ማስረጃ ነው፡፡ ከነበረውህግ በተለየ ሜልኩ ኤግዚቢትን በፖሊስ ሊጠበቅና ሊተዳደር የሚገባውለመሆኑ ይህንን ለማድረግ የሚያስችል ድንጋጌ ሕጉ ይዟል፡፡ ኤግዚቢት ማናቸውንም አይነት ለፍርድ ቤት ቀርቦ ሊታይ የሚችል ቁስን እንደሚያካትት ትርጉም ተሰጥቶታል፡፡ በማናቸወም ደረጃ ኤግዚቢት የሚቆየው መርማሪ ጋር እንደሆነና ኤግዚቢቱ የሚወድም፣ የሚወረስ ወዘተ ባለመሆኑ የተነሳ ለባለቤቱ መመለስ ያለበት ከሆነ በአቃቤ ሕግ ወሳኔ (በፍርድ ሂደት ላይ በፍርደ ቤት ወሳኔ) ለባለቤቱ ሊመለስ እንደሚችል፤ ባለቤቱን ማለየት ካልተቻለ ግን በፍትሐብሔር ደንቦች መሰረት በዐቃቤ ሕግ አማካኝነት ክስ ለፍርድ ቤት ሊቀርብ ይችላል፡፡ ክሱ የሚቀርበወም የኤግዚቢቱ ባለቤት በፍርድ ቤት አማካኝነት ተለይቶ እንዲወሰንና በፍርድ ቤት በሚወሰነውመሰረት ለባለቤቱ ሊመለስ እንደሚችል ህጉ ደንግጓል፡፡ ኤግዚቤትግዙፍ በመሆኑ ወይምበማናቸወምምክንያት ፍርድ ቤት ለማቅረብ የማይመች በሚሆንበት ጊዜምናመፍ ውተወስዶ ሊቀርብእንደሚችል ተደንግጓል፡፡

የአቃቤ ህግ ማንኛወም ማስረጃ ከተሰማበኋላ ፍርድ ቤቱ አቃቤ ሕግ ክሱን አስረድቷል ብሎ ካመነ ተከሳሽ መከላከያ ማስረጃወን እንዲያቀርብ በወሳኔ ያሳወቀዋል፡፡ በዚህ ደረጃ አቃቤ ሕግ ክሱን አስረድቷል የሚባለው ባቀረባቸውማስረጃዎች ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ለፍርድ ቤት ማስረዳቱን ፍርድ ቤቱ ያመነ እንደሆነ ነው፡፡

ተከሳሽ የሚያቀርበውየመከላከያ ማስረጃ ከላይ እንደተመለከቱት አይነቶች ቢሆኑም ተከሳሹ ክሱን ተከላክሏል ለመባል እና በነጻ ለመሰናት ያቀረበውማስረጃ የማስረዳት ደረጃውየአቃቤ ሕግማስረጃ ከ "ምክንያታዊ ጥርጣሬ" ደረጃ በታች መሆኑን የሚስይ መሆን ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም የተከሳሽ ማስረዳት ደረጃ በአቃቤ ሕግ ማስረጃ ላይ በቂ ጥርጣሬ መፍጠር እንጂ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ ደረጃ ማቅረብ አይደለም፡፡ ይህንንም ተከሳሹ በመከላከይ ንግግሩ የሚያመላክት ሲሆን ዝርዝሩና አቀራረቡ ግን በክስ መከፈቻ አይነት ነው፡፡

ማስረጃ በወቅቱ ሳይገለፅ ቆይቶ ከፍርድ በፊት በማናቸወም ጊዜ በድንገት በማናቸወም ወገን ሊታወቅ ይችላል፡፡ እንዲሁም በክርክር ሂደት በተጨማሪ ሊሰማ የሚገባው ማስረጃ መኖሩ ሊረጋገጥ ይችላል፡፡ በሌላ በኩልም ዋናው ማስረጃ በተለያየ ሜልኩ (ለምሳሌ ምስክር በመሞቱ፣ ኋላ በተከሰተ አእምሮ ጉድለት የተነሳ፣ በማናቸወም

ምክንያት ምስክሩን በአካል ለማግኘት ወይም ለማቅረብ ባለመቻሉ ወዘተ) ጉዳዩን በዋናው ማስረጃ ማስረዳት የማይቻልበት ሁኔታ ያጋጥማል፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች በተግባር የሚያጋጥሙ ቢሆንም ጉዳዩን በግልፅ የሚፈታ ሕግ የለም፡፡ በመሆኑም የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ የዚህ አይነት ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ ተጨማሪና በድንገተኛ ማስረጃን ፍርድ ቤት ሊቀበል እንደሚችል የሚደነግግ ሲሆን በሌላ ፍርደ ቤት የተሰጠ የምስክርነት ቃልንም ሊቀበል እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ በፍርድ ቤት የሚሰጥ ቃልም በፖሊስ ከተሰጠ ቃል ጋር የሚጣረስ እንደሆነ በፖሊስ የተሰጠን ቃል ፍርድ ቤቱ የምስክሩን ቃል ለማስተባበል ሲባል ሊመለከተው ይችላል፡፡ ከዚህ ቀደም በዚህ ጉዳይ ይነሳ ለነበረው ክርክርም ሕጉ ግልፅ መልስ ይሰጣል ማለት ነው፡፡

## 14.ፍርድና ቅጣት

የማስረጃ ማሰማት ሒደት እንደተጠናቀቀ ፍርድ ቤቱ አቃቤ ሕግም ሆነ ተከሳሹ ስለጉዳዩ የሚያቀርቡት ክርክር ማቆሚያ ንግግር ካለ እንደአግባቡ በቃል ወይም በጽሁፍ እንዲያቀርቡ እድሉን በማስጠት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ፍርድ በማሰረቱ በተቀጠረበት እለት የሚሰጥ እንጂ ተለዋጭ ቀጠሮ የሚሰጥበት አይደለም፡፡ የክርክር ማቆሚያ ንግግር የማቅረብበትን እድል ለማስፋትና እንደጉዳዩ ሁኔታ አመቺውን መንገድ ለመምረጥም ለፍርድ ቤት ከቀደመው ሕግ ሰፋ ያለ ስልጣን ሕጉ ይሰጣል፡፡ በዚህ ማሰረት ሁለቱም ወገኖች ስለጉዳዩ፣ ስለሕጉና እና ሊፈረድ ይገባዋል ስለሚሉት ጉዳይ በፅሁፍ ወይም በቃል በሚመቻቸው መንገድ የክርክር ማቆሚያቸውን እንዲያቀርቡ ሊፈቀድላቸው ይችላል፡፡ ቀጥሎም ፍርድ ወዲያውኑ ይሰጣል፡፡

ፍርድ የሕዝብ ስራ በመሆኑ ምንጊዜም **በሕዝብ/በመንግሰት ስም የሚሰጥ ነው፡፡** ይህም በፍርዱ ጸሁፍ ወስጥ ይመለከታል፡፡ ከዚህ ቀደም በፍርድ ወስጥ ይታዩ የነበሩ ሰፊ ክፍተቶችን ለመቅረፍ እንዲቻልም ስለ ፍርድ አፃፃፍ ሕጉ ዝርዝር ድንጋጌዎችን አካቷል፡፡ በዚህ ማሰረት እያንዳንዱ ፍርድ በአምስት የተከፈሉ አስራ ስድስት የሚሆኑ ነጥቦችን ባካተተ መልኩ መፃፍ እንዳለበት ሕጉ በግልፅ በአስገዳጅት ደንግጓል፡፡ ዝርዘሩን በሕጉ ወስጥ ማካተት ያስፈለገበት አንዱ ምክንያት የዳኝነት ሥራ በግልፅ ተከናወኗል ሊባል ከሚችልባቸው መመዘኛዎች ወስጥ አንዱ በምክንያት የተተነተነ ግልፅ ፍርድ ሲፃፍ በመሆኑ ነው፡፡ ዝርዝሮቹም ፍርዱን የሰጠው ፍርድ ቤት ጉዳዩን በበቂ ሁኔታ የመረመረው ለመሆኑና ፍርዱን በማናቸውም ጊዜና ቦታ የሚመለከት ሰው አሳማኝ ፍርድ የተሰጠ መሆኑን እንዲረዳና እንዲያምን ያደርጋሉ ተብለውም ይታሰባሉ፡፡ ማንኛውም ማስረጃ እንዳግባቡ በፍርድ ወስጥ የሚጠቀስ ሲሆን ምስል ወይም ሌላ ወደ ፅሁፍ በቀጥታ የማይለወጡ ማስረጃዎችም በፍርድ ወስጥ ሊጠቀሱ የሚችሉበትን መንገድ (ለምሳሌ በማጣቀሻ) የፍርድ አፃፃፍ ደንቡ ያስረዳል፡፡

ፍርድ በመሰረቱ በመርህ ደረጃ እንደተሰጠ የሚፈፀም ነው፡፡ ይሁን እንጂ የተሰጠ ፍርድ አፈፃፀም በተከሳሽ ላይ ወይም በፍትሕ ስርአቱ ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ ጉዳዩ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት እስከሚታይ **ድረስ በፈረደው ፍርድ ቤት አማካኝነት** አፈፃፀሙ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ሊታገድ እንደሚችል ሕጉ ተጨማሪ ድንጋጌን ይዟል፡፡

በፍርድ መሰረት ተከሳሽ ነፃ ከተሰኘ ከእስር የሚለቀቅ ሆኖ (ታስሮ ከነበረ) በንብረቶቹ ላይም የተሰጡ ትእዛዞች ካሉ ፍርድ ቤት ተለዋጭ ትእዛዝ ይሰጥባቸዋል፡፡ በሌላ በኩልም ተከሳሹ ጥፋተኛ ከተባለ በሕጉ መሰረት ቅጣት ሊጣልበት ስለሚችል አቃቤ ሕግም ሆነ ጥፋተኛው ሊጣል ይገባዋል ስለሚለው ቅጣት አስተያየታቸውን ያቀርባሉ፡፡ የሚቀርበውም ቅጣት በድፍኑ ሳይሆን የቅጣት ማክበጃና ማቅለያዎች ከቅጣት አወሳሰን ሕጎች ጋር በማገናዘብ ሊጣል የሚገባውን ቁርጥ ያለውን ቅጣት ነው፡፡ የቅጣት አስተያየትን በተመለከተ አቃቤ ህግ የክስ መክፈቻ ንግግር ሲያደርግ እንዲሁም ተከሳሽ የመከላከያ መክፈቻ ንግግር ሲያደርግ ጥፋተኛ ቢባል ሊጣል ይገባዋል ስለሚሉት ቅጣት አስተያየታቸውን ቀድመው የሚያቀርቡበትን እድል ከሌለ የጥፋተኛነትን ወሳኔ ተከትሎ በስተመጨረሻ ላይ የሚያቀርቡት ይሆናል፡፡

በተለየ ሁኔታ የቅጣት አስተያየት ቀድሞ እንዳይቀርብ ዳኛው ሊያዝ የሚችልበት እድል ግን ዝግ አይደለም፡፡ ዳኞች በትክክለኛው ትርጉሙ በሕግ የሰለጠኑ ባለሙያዎች ናቸው የሚለው ግምት ቀድሞ በሚቀርብ የቅጣት አስተያየት የተነሳ ወደ አንደኛው ወገን እንዲወግኑ እምብዛም አያደርጋቸውም የሚል እምነት አለ፡፡ በአጠቃላይም በአገራችን የፍትሕ ስርአት ዳኞች በፍሬ ነገርም ሆነ በሕጉ ጉዳይ ላይ ወሰኔ የሚሰጡ ሲሆን ከጁሪ ስርአት በተለየ መልኩ በሕግ የተማሩ ባለሙያዎች ስለሆኑ የሚቀርቡ ክርክሮች ከሙያ ደረጃው በታችና ከሙያው ስነምግባር ወጪ አድሏዊ አመለካከት ቀድመው እንዲይዙ አያደርጋቸውም ተብሎ ይታሰባል፡፡ በመሆኑም በክስ መክፈቻ ንግግር ውስጥ ተካቶ የሚቀርብን የቅጣት አስተያየት ሊቀበሉ የሚችሉበት አጋጣሚ ሙሉ በሙሉ ዝግ አይደለም ማለት ነው፡፡ ይህ መሆኑ አቃቤ ሕግም ሆነ ተከሳሽ ስለክርክሩ ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ያለውን ሀቅ በሚገባ እና በተሟላ ሁኔታ ተረድተውት እንዲከራከሩም ደርጋቸዋል፡፡ ያምሆኖ ዳኛው በዚህ መልኩ የቅጣት አስተያየት መቅረቡ በጉዳዩ ላይ ገለልተኛ ወሳኔ ለመስጠት አያስችለኝም ብሎ ካመነ የቅጣት አስተያየት ተከሳሹ ጥፋተኛ የተባለ እንደሆነ ብቻ እንዲቀርብ መደረጉ ይቀጥላል፡፡

## 14.1 የቅጣት ወሳኔ

አቃቤ ሕግ እና ተከሳሹ ያቀረቡትን የቅጣት አስተያየት ከሕጉ ጋር በማገናዘብ ፍርድ ቤቱ ቅጣትን ይወስናል፡፡ ቅጣት በዋነኛነት የሚወሰነው በወንጀል ሕጉ መሰረት ነው፡፡ የቅጣት አይነተቶቹም (የሞት፣ እስራት፣ የገንዘብ፣ ...) የሚወሰኑት በወንጀል ሕጉ መሰረት ነው፡፡ የስነ ስርአትና ማስረጃሕጉ የያዛቸው ድንጋጌዎች በዋነኛነት የቅጣት አላማን ለማሳከት እንዲቻል ቅጣት ሲወሰን ዳኛ ሊከተላቸው የሚገቡ መርሆዎችንና የእያንዳንዱን ቅጣት አወሳሰን ሥርአቶች እንደሚከተለው ጠቅለል ብለው ተሚልከተዋል፡፡ ቅጣት ከተወሰነ በኋላ በሕጉ መሰረት ስለ ሚፈጸመየ መከታተል እና የሚረጋጥ ኃላሲነት የአቃቤ ሕግ ነው፡፡

የሞት ቅጣት አፈፃፀምን በተመለከተ ወሳኔው ተፈፅሞ በፍፁም የማይተካው የሰው ሕይወት ከማለፉ በፊት የስነ ስርአትና ማስረጃሕጉ ስለአፈፃፀሙ ከፍተኛ ጥንቃቄቆችን ያደርጋል፡፡ በዚህ መሰረትም ማንኛወም የሞት ፍርድ የፈረደ ፍርድ ቤት በፍርዱ ላይ ይግባኝ የተባለበት ቢሆንም ወይም ባይሆንም የፍርዱን ግልባጭእንዳግባቡ ለክልል ወይም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መላክ እንዳለበት ሕጉ በአስገዳጅነት ደንግጓል፡፡ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ትክክለኛ ፍርድ የተሰጠ መሆኑን አረጋግጦ ለጠቅላይ አቃቤ ሕጉ ይልከዋል፡፡ በፍርዱ ላይ ይግባኝ የተባለበት እንደሆነ ምየፍርዱ ትክክለኛነት የፍርደኛወን ቅሬታ ጭምር አካቶ ይመረመራል፡፡ በማናቸወም ሁኔታ የሞት ፍርድ ጉዳይ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ደረጃ የሚታየው አምስት ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት ነው፡፡ ጠቅላይ አቃቤ ሕጉም ፍርድ በይግባኛ፣ በምህረት ወይም በማናቸወም ሌላ ሕጋዊ ምክንያት ያለተለወጠ መሆኑን በማረጋገጥ ለአገሪቷ ርእሰ ብሐር ይልከዋል፡፡ የሞት ፍርዱ በርእሰ ብሐሩ ከፀደቀ ለአፈፃጸም ለማረሚያ ቤቱ የሚላክ ሲሆን በወንጀል ሕጉና የጠቅላይ አቃቤ ሕጉ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የፍርደኛወን ክብር ጠብቆ በማረሚያ ቤቱ ወስጥ ይፈፀማል፡፡

የሞት ፍርድ አፈፃጸምን ፍርዱን የሰጠው ፍርድ ቤት በአቃቤ ህግ አመልካችነት የሚከታተለው ሲሆን የሞት ፍርድ ሳይፈፀም ለረዥም ጊዜ መቆየቱ በራሱ በፍርደኛው ላይ የስቃይ አያያዝን የሚያስከትል በመሆኑ በማናቸወም ምክንያት ፍርዱ ሳይፈፀም ሁለት አመት ያለፈው እንደሆነ ወደ እድሜ ልክ እስራት እንዲቀየር ሕጉ ይደነግጋል፡፡

ነፃነትን የሚያሳጣቅጣትን በተመለከተ ቅጣቱ እንደተፈረደ ወዲያወኑ ሚፈጸምስለሚኖርበት ስለቅጣቱ አፈፃፀም ግልፅ ትእዛዝ ጭምር በማስጠት ፍርደ ቤቱ ለማረሚያ ቤት ትእዛዝ ያስተላልፋል፡፡ ቅጣቱ እንደተወሰነ ወዲያወኑ ሚፈፀም ያለበት ቢሆንም በተወሰኑ ምክንያቶች ግን የእስራ ቅጣት አፈፃፀም ለተወሰነ ጊዜ ሊተላለፍ ይችላል፡፡

ነባሩ ስነ ስርአትና ማስረጃሕግ እጅግ በጠበበ ሁኔታ ይፈቅድ የነበረውን የእስራት ቅጣት ማስተላለፍ ጉዳይ የስነ ስርአትና ማስረጃሕጉ ሰፋ በማድረግ ሰዎች በሚሰራቸው ምክንያት የእድሜ ልክ ቅጣት/ችግር በሕይወታቸው ላይ እንዳይገጥማቸው ጥንቃቄ ያደርጋል፡፡ በዚህ ማስረትም በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ቅጣት እንደተወሰነ ሳይፈፀም ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ተላልፎ እንዲቆይ ሕጉ ታሳቢ ያደርጋል፡፡ የቅጣት ወሳኔ አፈፃፀምንበፍርደኛው የግል ሁኔታ ላይ ተመርኩዞ ለተወሰነ ጊዜ ማስተላለፉ በስራው፣ በቤተሰብ ሕይወቱ፣ በምርቱና በምርታማነቱ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት የሚቀንስ ከመሆኑም በላይ ፍርደኛው ቅጣትን ሲፈፅም በሙሉ እምነት በሙታረሙላይ ብቻ እንዲያተኩር ያደርገዋል፡፡ በዚህ ሚልኩ የእስራት ቅጣቱን ፈፅሞ ሲወጣም ይበልጥ የታረመና ምርታማዜጋ ይሆናል፡፡

የቅጣት ወሳኔ አፈፀፀም ሊተላለፍ የሚችለው ቅጣቱ እስከ አምስት አመት የሚደርስ ቀላል የሆነ እንደሆነ፣ ተቀጪው ለሕብረተሰቡ ደሕንነት አደጋ የማይሆኑ እንደሆነና ለአፈፃፀሙ በቂ ዋስታና የሚጠራ ሲሆን ነው፡፡ በዚህ ሚልኩ ቅጣት የሚተላለፍላቸው ሰዎች ወስጥም አንድ አመት ያልሞላት ልጅ ያላት እናት፣ በጠና የታመመና በዚሕ ምክንያት ቅጣትን መፈጸም የማይችል፣ አጣዳፊ ወይም ወቅታዊ ስራ ያለውባለሙያ፣ የማየተላለፍ ወቅታዊ ስራ ለው አርሶ ወይም አርብቶ አደር እና የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡ እንደዚህ አይነት ሰዎች ከፍ ሲል የተማለከተውን ማስፈርት አሟልተውእስከተገኙ ድረስ የገጠማቸውችግር ወይምያሉበት ሁኔታ እስኪለወጥ ድረስ የቅጣት አፈፃፀሙን ለተወሰነ ጊዜ ማስተላለፉ ተገቢና አሳማኝ ነው፡፡ ቅጣቱ የሚተላለፈወምእንደ ምክንያቶች በቂነት ለእያንዳንዱ ምክንያት በተቀማጠውየጊዜ ጣሪያ ልክ ሲሆን (ለጉዳዩ የሚስፈልገውን ያህል ጊዜ ማስጠቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የበዛውእስከ አንድ አመት ነው) ፍርደኛውቅጣቱ የተላለፈበትን ምክንያት ያላግባብ ስራ ላይ ካዋለውወይምየተላለፈበት ጊዜ እንዳበቃ የእስራት ቅጣቱን መፈጸም ይጀምራል፡፡

የገንዘብ ቅጣትን በተማለከተ በተመሳሳይ በወንጀል ሕጉ ማስረት የሚፈጸም ቢሆንም የገንዘብ ቅጣት እስካሁን ባለው ሁኔታ በአግባቡ እየተፈጸመ ባመሆኑ ቅጣቱ ሳይፈፀም እንዳይቀር ሕጉ ጥንቃቄዎችን አድርጓል፡፡ በመሆኑም ገንዘብ ቅጣት ወዲያውኑ ገቢ መሆን ያለበት ከመሆኑ አንስቶ ፍርደኛውበህግ አግባብ ተገዶ የቅጣት ገንዘቡን ገቢ የሚያደርግበትን ስርአት ተቀምጧል፡፡ በዚህ ማስረትምየገንዘብ ቅጣት በፍርደኛውፈቃደኛነት ለመንግሰት ገቢ ካለሆነ ወይም በቀጥታ ገቢ እንዲሆን የሚታዘዝበት ገንዘብ በፍትሕ አካለት ያልታወቀ (ለምሳሌ ለዋስትና የተያዘ ገንዘብ አለመኖሩ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ) እንደሆነ በዋነኛት የመንግስትን ገንዘብ የማስብሰብ ሃላፊነት ያለበት የመንግስት ተቋም (የገንዘብ ሚኒስቴር ወይም የገንዘብ ቢሮ) ማንኛውንም የፍርደኛውን ገንዘብ ወይም ንብረት በሚፈላለግ በፍትሐብሔር ፍርድ አፈጻጸም አግባብ የቅጣት ገንዘቡ ገቢ

እንዲሆን ወይም ንብረቱ ተሸጦ የቅጣት ገንዘቡን ገቢ እንዲሆን የሚድረግ ሃላፊነት እንዳለበት ሕጉ ግልጽ ያደርጋል፡፡ ይህ ስርአት ከዚህ በፊት በአፈጻጸም ይታይ የነበረውን የባለቤትነት ችግርና የአፈጻጸም ክፍተት ይቀርፋል ተብሎ ይታሰባል፡፡

ገንዘብ ተፈልጎ ወይም ንብረት ተሸጦ ገቢ በሚሆንበት ጊዜ የተለያዩ ሰዎች በፍርደኛው ላይ የገንዘብ መብት አለን የሚሉ ክርክር የሚያቀርቡበት አጋጣሚ ሰፊ ነው፡፡ ገንዘቡ የሁሉንም ፍላጎት ሊያሟላ ካልቻለ የመብት ቅደም ተከተል ማስቀመጡ አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም የወንጀሉ ጉዳይ በወንጀል ተጎጂው የመጀመሪያ ጉዳት የጀመረ በመሆኑ ለወንጀል ተጎጂ የተፈረደ የካሳ/የጉዳት ገንዘብ ካለ ከክርክሩ ወጪ ቀጥሎ ነገር ግን ከሁሉ እዳዎች ቀድሞ ይከፈላል፡፡ **የመንግስት እዳዎች ቀጥለው የሚከፈሉ ሲሆን ሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎችን በተመለከተ በሌሎች ሕጎች በተደነገጉት አግባቦች እልባት** ያገኛሉ፡፡

ፍርድ ቤቱ ከላይ ከተመለከቱት ቅጣቶች በተጨማሪ ተጨማሪ ቅጣቶች በፍርደኛው ላይ እንዲፈፀሙ ትእዛዝ ሊሰጥ ይቻላል፡፡ ተጨማሪ ቅጣቶች ንብረት መውረስን፣ ተግሳፅ መስጠትን፣ ይቅርታ ማጠየቅ ወይም ማውረድን፣ ማስጠንቀቂያን መስጠትን ወዘተ የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ቅጣቶቹም ሳይፈጸሙ እንዳይቀሩ ፍርድ ቤት ቅጣቶቹ ሊፈጸሙ የሚችሉበትን ግልጽ አቅጣጫ ማስቀመጥና ግልጽ ትእዛዝ መስጠት እንዳለበት ሕጉ በአስገዳጅነት ደንግጓል፡፡ የተወሰኑ ቅጣቶችም (ለምሳሌ በፍርድ ቤት ሊሰጥ የሚችል ማስጠንቀቂያ) ወዲያውኑ በፍርድ ቤት ተሰጥተውና ተፈጽመው ሊቋጩ ይችላሉ፡፡ የተወሰኑት ተጨማሪ ቅጣቶች መደበኛውንና መደበኛ ያልሆነውን ስርአት በማዋሃድ ሊተገበሩ የሚገባቸው የሚሆንበት አጋጣሚም ይኖራል፡፡ ለምሳሌ ይቅርታ ማጠየቅ ባህላዊ ስርአትን ባካተተ መልኩ የሚፈፀም እድሉ ከፍተኛ በመሆኑ የፍትህ አካላት ስለዚህም ጉዳይ ያላቸው ግንዛቤ ሊዳብር ይገባዋል፡፡ በሌላ በኩል እንደ ከመብት መሻር፣ ከደረጃ ዝቅ ማድረግና ከሰራዊት አባልነት ማሰናበት የመሳሰሉትን ተጨማሪ ቅጣቶች እንደ ሁኔታው ከፍትህ አካላት ወጪ ባሉ ተቋማት (ለምሳሌ በምርጫ ቦርድ፣ በመንግስት ማስሪያቤት ወይም በመከላከያ ሚኒስቴር አማካኝነት) የሚፈፀሙ ይሆናሉ፡፡ የተወሰኑ ተጨማሪ ቅጣቶች (ምሳሌ ንብረት መውረስ) የሶስተኛ ወገን (ለምሳሌ የትዳር ጓደኛን) መብትን ሊነኩ የሚችሉ በመሆናቸው መብት አለን የሚሉ ወገኖች የመብት ጥያቄ አቅርበው ፍትሕ ሊያገኙ የሚችሉበትንም እድል ሕጉ ይፈቅዳል፡፡

የገንዘብ ቅጣት ተከታትሎ በገንዘብ ወይም በንብረት ላይ ማስፈፀም እንዲሁም የንብረት ይወረስ ውሳኔን ተከታትሎ ማስፈፀም ክትትል እና ትጋትን ይፈልጋል፡፡ በሕጉ ሊወረስ የሚችል ንብረት በክርክር ወቅት ተለይቶ ቢያንስ ሊታገድ የሚችል ነው፡፡ ንብረቱ ያላግባብ ለረጅም ጊዜ ያለአገልግሎት ሊቀመጥ የማይገባው ከመሆኑም

በላይ የሰዎች ተጨማሪ ንብረት የማፍራት መብታቸውም በፍትሕ አካላት ትጋት ማነስ የተነሳ ሊገደብ አይገባውም፡፡ የነፃ ኢኮኖሚ ስርአትም ሰዎች በንብረታቸው ተረጋግተው የሚጠቀሙበት እድል እንዲሰፋ ይጠብቃል፡፡ ስለሆነም ሕ ንብረት የሚወረስ እንደሆነ "ወዲወኑ" እንዲፈጸም የሚያደርግ ድንጋጌዎችን ነው ያካተተው፡፡

በሕጉ ወስጥ ሌላው የተካተተው የቅጣት አይነት አማራጭ ቅጣትን የሚያስከተው ነው፡፡ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ማሰረታዊ አቅጣጫ ጉዳዮች በፍርድ ሂደት ከሚያልፉ ይልቅ ከፍርድ በፊት ተጠርጣሪዎች ያጠፉ ከሆነ ጥፋታቸውን የሚያምኑበትንና ለዚህም የሚያበረታቱበትን ስርአት ማዘርጋት ነው፡፡ ስለሆነም አማራጭ መንገዶችና አማራጭ መፍትሔዎች ቅድሚያ ይሰጣቸዋል፡፡ የአማራጭ መፍትሔ እርምጃ ትኩረት ጥፋተኛው ለጥፋቱ በመፀፀት ኃላፊነት እንዲወስድ ማድረግ፣ ማስታረቅና ካሳ ማስከፈልን ሊያካትት ይችላል፡፡ መፍትሔው በዘፈቀደ የሚወሰድ ሳይሆን የሕዝብ ጥቅምን በዚህ መንገድ በተሻለ መልኩ ማረጋገጥ እንደሚቻል ሲታመንበት የሚወሰን ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከተውም ተከሳሽ ምንግዜም የጠበቃ እርዳታ ማግኘት ያለበት መሆኑ በግራ ቀኙ መካከል በእኩል ደረጃ የመሰማት መብትን ለማረጋገጥ ያግዛል፡፡

አማራጭ ቅጣት ቀላል ወንጀል የፈጸሙ ሰዎችን (በተለይ ወጣት ጥፋተኞች፣ አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞች፣ በሴቶች ላይ እና ደጋጋሚ ባልሆኑ ተጠርጣሪዎች) በእስር ከማረም ይልቅ የማህበረሰብ አገልግሎት እንዲሰጡ በማድረግ፣ ለተበዳዩ ካሳ በማክፈል ወይም ይቅርታ በመጠየቅ፣ ወይም የአእምሮ ህክምና እንዲያገኙ በማድረግ ወደ ጤናማ ዜጋነት ለመመለስ የሚረዳ ሥርዐት ነው፡፡ አማራጭ ቅጣቶች የእስረኛን ቁጥር ለመቀነስ፣ የምርመራን ወይም የፍርድ ሂደትን ለማቀላጠፍ ጠቃሚ ናቸው፡፡ ይህ ቅጣት በፍርድ ቤት አነሳሽነት ወይም በፍርደኛው ጥያቄ (በተፈጥሮ ሰው ላይ ብቻ) ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ነው፡፡

አማራጭ ቅጣትም የጉልበት ስራንም ይመለከታል፡፡ የጉልበት ስራ ጉዳይ ራሱን በቻለ የተለየ አዋጅ ጭምር የሚመራ ቢሆንም የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ በቀላል እስራት ወይም በገንዘብ እስራት የተቀጣና ስራ መስራት የሚችል ሰው ከሚታሰር በጉልበት የስራ ቅጣት ማህበረሰቡን ቢያገለግል ለፍርደኛውም ሆነ ለአጠቃላይ ማህበረሰቡ ጠቃሚ ከመሆኑም በላይ ቅጣትን ይበልጥ ውጤታማ በሆነ የተሃድሶ እና የትምህርት መስመር ማጠናቀቅ የሚያስችል ለመሆኑ ሕጉ ታሳቢ ያደርጋል፡፡ የዚህ ቅጣት አፈፀፀም ላይ አገራት ሰፊ ተሞክሮ ያላቸው በመሆኑ ቢተገበርም አገራችን ካላት ሰፊ የስራ እድል አንፃር ታራሚዎች ከስራ እንዳይነጠሉ እንዲሁም የተወሰነ ገቢ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል፡፡ በዚህ መልኩ ሊሰሩ ከሚችሉት ስራዎች ውስጥ የመንገድ ጽዳት ማከናወን፣

የመዝናኛ ቦታዎችን ማጽዳት፣ በተለያዩ የመንግስትም ሆነ የህብረተሰብ ግንባታዎች ጥገናዎች ላይ የተለያዩ ስራዎችን ማስራት (ለምሳሌ ቀለም መቀባት)፣ ህጻናት በሚጫወቡበት ወይም በሚቆዩበት አካባቢ የጥበቃ አገልግሎት ማስጠት፣ አንዳንድ ጊዜ የሚፈጠሩ ድንገተኛ አደጋዎችን (ለምሳሌ የእሳት አደጋን) ለመከላከል ተመድቦ ማስራትና የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡ የአካል ጉዳተኛ የሆኑ ሰዎችን በመርዳትም ስራ ላይ እንዲሰማሩ ሊደረግም ይችላል፡፡

ታሳሪዎች በማሰረቱ ማስራት የሚችሉበት የእድሜ ክልል ወስጥ የሚገኙ ከመሆናቸው አንፃር ከማህበረሰቡ ሳይነጠሉ በዚህ ሜልኩ በጉልበት ስራ የሚቀጡ ከሆነ ሜልሰው ከሕብረተሰቡ ጋር ለመቀላቀል ሳይቸገሩ እጅግ በጣም ወጤታማ የተሃድሶ ስራ ሊሰራበት የሚችል በመሆኑ በሕጉ ወስጥ በግልፅና ዘርዘር ብሎ እንዲካተት ሆኗል፡፡ ይህ ቅጣት እንዳግባቡ በሥነ ልቦና፣ በማህበራዊ ሳይንስ እና ልዩ እወቀት ባለውልዩ ባለሙያ ክትትል የሚፈፀም ሲሆን ከፍርደኛው ሁኔታና ከእርምት አላማ ጋር እየተገናዘበ እንደ ባለሙያው የሙያ አስተያየት በየጊዜው የሚለዋወጥ ወይም የሚሻሻል ይሆናልም፡፡

ከቅጣት አፈፃፀም ጋር ተያይዞ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ትኩረት የሰጠበት ሌላው ጉዳይ ቅጣቶችን የሚያስፈፅመዉን አካል የተማለከተውነው፡፡ በወንጀል ህጉም ሆነ በስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ላይ በዝርዝር እንደተማለከቱት ከቅጣት አይነቶች ወስጥ በሞት እና በእስራት ከሚያስቀጡት ወጪ ያሉ ቅጣቶች በርካታ ከመሆናቸወም በላይ ፍርደኛ በሌላ አግባብ (በገንዘብ፣ በጉልበት፣ በተጫማሪ ቅጣዩች...) የሚቀጣባቸውየ ወንጀል አይነቶችም በርካታ ናቸው፡፡ እጅግ ከባድ ከሆኑት ወንጀሎች በቀርም ሌሎች ወንጀሎች በተሻለ ሁኔታ ፍርደኛን ሊያርሙየ ሚችሉት ከእስራት ወጪበሌሎች ቅጣቶች እንደሆነም በርካት ጥናቶች ያረጋግጣሉ፡፡ በሌላ በኩልም እስራት ቅጣት ወጤታማ ሊሆን የሚችለው በእስራት ጊዜ ሊኖሩ የሚገባቸው በአለም አቀፍ አነስተኛ የእስረኞች አያያዝ ደንብም ሆነ በሕገ መንግስቱ በተማለከቱት ወጤታማየ እርምት እርምጃዎች (እንደ ትምሕርት፣ ስልጠና፣ ጤና፣ ስፖርት፣ አማገብ፣ የወጨግንኙነቶች እና የመሳሰሉት ያሉት) ወጤታማ በሆነው አግባባ ሜፈጸማቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ቅጣት በፍርድ ቤት በሚወሰንበት ጊዜም ሆነ ፍርደኛው ፍርዱን ጨርሶ ወደ ሕብረተሰቡ በሚቀላቀልበት ጊዜ ወጤታማተያያዥና ተከታታይ ተግባራት ሲከናወኑ ነው፡፡ እስረኛን በሚረምሂደት ወስጥ ጥሩ ተሞክሮዎች እንዳሉም ሁሉ በርካታ ችግሮችም እንዳሉ የተለያዩ ጥናቶች (ለምሳሌ በ2003 የወጣውየ ኢተዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ሪፖርትን ጨምሮ) ያረጋግጣሉ፡፡ በሌላ በኩል ፍርድ ቤቶች የቅጣት ወሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ በአቃቤ ሕግና በፍርድኛውየ ቅጣት አስተያየት ላይ ተሞርኩዘውወሳኔ ከማስጠታቸውበቀር በባለሙያ አስተያየት እገዛ አይደረግላቸወም፡፡ እስረኛ እስራን ጨርሶም ይሁን በሌላ አግባብ ወደ ማህበረሰቡ በሚቀላቀልበት ጊዜም

ይህንን የሚከታተልና የሚያስፈፅም አካል የለም፡፡ በተለያየ ምክንያትም ፍርደኛ ለጊዜው ቅጣት ሲገደብለት (በአመክሮ፣ በእግድ፣ በእስራ ቅጣት ማስተላለፍ...) ይህንን የሚከታተል አካል የሌለ በመሆኑ ለጊዜው ማለቀቅ ማለት በወጡቱ የሚጨፈሻ ማለቀቅ ያህል ሀኗል፡፡ እስራቱን ጨርሶ ወደ ማህበረሰቡ የሚቀላቀልንም ሰውበስርአቱ ይዞ በአግባቡ የሚቀላቅል ስርአትም የለም፡፡ እነዚህ ሁሉ ተግባራት በወጤታማ ት ቢከናወኑ የአገራችን የእርምት ስርአት ይበልጥ ውጤታማ ይሆናል፤ በመሆኑም ደጋጋሚ ትም ይቀንሳል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ይህንንም በውጤታማት ለማከናወን የስነ ስርአትና ማስረጃሕጉ ከእስራትና ከሞት ቅጣት ውጪ ያሉትን እና ከላይ የተመለከቱትን ተጨማሪ ኃላፊነቶች እንዲያከናወን ሃላፊት የሚሰጠው ራሱን የቻለ አንድ የመንግስት ተቋም እንዲቋቋምየሚያሰችል ድንጋጌ አካቷል፡፡

## 15. ፍርድ እንደገና የሚታይባቸውአግባቦች

ፍርድ ምንጊዜም እንከን አልባ የሆነ ፍፁምየዳኛ ተግባር ነውተብሎየሚይወሰድ በመሆኑ ፍርዱን በሰጠውም ፍርድ ቤትም ይሁን በበላይ ፍርድ ቤት ስሕተቶቹ ሊታረሙየሚችሉበትን እድል ክፍት ሚድረግ ተገቢ ነው፡ በመሆኑምአንድ ፍርድ ጉዳዩን በቀጥታየተመለከተውፍርድ ቤት ወሳኔ ከሰጠበኋላ ስህተት አለበት ቢባል ፍርዱ በድጋሚ ታይቶ ተገቢው ማስተካከያ የሚደረግበትን ስርአት ሕጉ በዝርዝር አካቷል፡፡ እነዚህ ስርአቶች በአብዛኛው በነባር ሕግጋትም የተመለከቱ ሲሆን በስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ወስጥ ክፍተቶችን፣ ለወጦችን እንዲሁም የሚስተዋሉ ችግሮችን መፍትታ በሚያስችል አግባብ እንዲካተቱ ሆኗል፡፡ እነዚህ ስርአቶችም ማስየምን፣ በሌለበት የተሰጠ ፍርድን እንደገና ማየትን፣ ይግባኝን፣ ሰበርን እና ፍርድን እንደገና የማየት ስርአትን የሚመለከቱ ናቸው፡

የማስየም ስርአትን በተመለከተ በማስረቱ የሚዝገበሩት የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ በማስየም ጉዳይ ላይ የወንጀል ሕጉ ከደነገገውእምብዛምየተለየ ድንጋጌ በስነ ስርአትና ማስረጃሕጉ አልተካተተም፡፡

ፍርድን እንደገና የማየት ጉዳይም ከፍ ሲል የተገለፀ ሲሆን ፍርድ እንደገና ይታይልኝ የሚል ተከሳሽ ወይም ፍርደኛ መጥሪያ ያልደረሰውወይምመጥሪያ የደረሰውቢሆንምበበቂ ምክንያት ቀርቦ ለመከራከር ያልቻለ መሆኑን ሚረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡ በሚኝቸውምጊዜ ይህንን ሚረጋገጥ ባይችል ግን ክርክሩ በደረሰበት ገብቶ ክርክሩን መቀጠል ወይምፍርዱን መፈፀምይጠበቅበታል፡፡

ሌሎች ስርአቶች ጠቅለል ተደርገውእንደሚከተለውተመልክተዋል፡፡

## 15.1 ይግባኝ

ይገባኝን በተመለከት ከዚህ ቀደም የነበረው የፍ/ ሥርአት ህግ ግልፅ የሆነ የይግባኝ አላማን ያላስቀመጠ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ ከነበረው ስርአት በተለየ ሚሉኩ የይግባኝን አላማ የሚያስቀምጥ ሲሆን በዚህ መሰረትም የይግባኝ አላማ በስር ፍርድ ቤት የተፈፀመን የፍሬ ነገርም ሆነ የሕግ ስሕተትን ማረም፣ በአንድ የአስተዳደር ወሰን አካባቢም ተቀራራቢ የሕግ ትርጉም ማስፈን የመሳሰሉና ሌሎች አላማዎች ማካካት ሆኖ ተቀምጧል፡፡ ይህም ይግባኝ ሰሚፍርድ ቤቶች ባላቸውአስተዳደራዊ ክልል ወስጥ በግልፅ የተመለከተወን አላማ ያገናዘበ ስራ እንዲሰሩ ያግዛቸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከአቃቤ ሕግ አንፃር ይግባኝ ሊጠየቅ የሚገባውየ ሕዝብ ጥቅምን የሚረጋገጥ አላማን ለማካካት መሆን እንደሚገባወም ግልፅ ተደርጓል፡፡

አላማው ይግባኝ ሊባልባቸውየሚይገቡ ጉዳዮችን የሚያመለክት ቢሆንም ሕጉ በትርጉም ክፍሉ ትዝዛዝ የሚባሉወን ግልፅ ያደረገ ከመሆኑም በላይ ይግባኝ የሚይባልባቸወን የስር ፍርድ ቤት የትእዛዝ እና ሌሎች ጉዳዮች በግልፅ አስቀምጧል፡፡ ይግባኝ የሚይባልባቸው ጉዳዮች እንደ መዘገብን በዘላቂነት የሚያዘጋ ትእዛዝ፣ ድርድር፣ በእምነት ላይ ተመስርቶ የተፈፀመ ተግባር እና የመሳሰሉት ሲሆኑ እነዚህ ጉዳዮች አንድም በስር ፍርድ ቤት በተለያየ ሚሉኩ ሊታረሙየሚችሉ አለዚያም በተከሳሹ ፍቃድ ላይ ተመስርተውየተከናወኑ ተግባራት በመሆናቸው ይግባኝ ማቅረብ የበላይ ፍርድ ቤትን አላስፈላጊ በሆነ ው አግባብ በስራ ከሚጨናነቅ በቀር ለወጥ የሚያመጣ ትርጉምየሌላቸውናቸው፡፡

የይግባኝ ማመልከቻዎች የተለያዩ ከጉዳዩ ጋር የሚይካተቱ ጉዳዮችን ጨምረው እያካተቱ ግልፅ የሚይሆኑ፣ የሚያደናግሩ እና ጊዜና ጉልበት ብቻ የሚያባክኑ የሚሆኑባቸው አጋጣሚዎች ቀላል አለመሆናቸው በተግባር የሚታወቅ በመሆኑ የይግባኝ ማመልከቻ መያዝ የሚገባቸወን ጉዳዮች ሕጉ ዘርዝሮ ይዟል፡፡ የይግባኝ ማመልከቻወም ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ዘመናዊ **ቴክኖሎጂ** ማጠቀምን ጨምሮ አመቺ በሆነ አግባብ መቅረብ እንዲችሉ እድሉ በስነ ስርአትና ማስረጃ ህጉ ስፍቷል፡፡ ከዚህ ቀደም የነበረው 15 እና የ 30 ቀናት ልዩነት የይግባኝ ማቅረቢያውጊዜ ቢሰፋም የይግባኝ ማጠየቅ እድል ያጠበበ ከመሆኑም በላይ ትርጉም ያለውከፍፍል ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ማለት የሚፈልግ ሰው በ60 ቀናት ወስጥ ይግባኝ ማመልከቻ ማቅረብንም ሆነ ይግባኝ ማቅረብን እድል እንዲጠቀምበት ሆኗል፡፡ ይህ ጊዜም መዝገቡን ለማ ልበጥ የሚወስደውጊዜ ግምት ወስጥ ሳይገባ የሚታሰብ ሲሆን በዚህ ጊዜ ወስጥ ይግባኙን ማቅረብ ያልቻለ ይግባኝ ባይ በቂ ምክንያት ያለውከሆነ ጊዜውያለፈበትን ይግባኝ በይግባኝ ሰሚውፍርድ ቤት ፈቃድ **ሊያቀርብ ይችላል፡፡ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ካሰቀመጠው አላማ አንጻርም በቂ ምክንያት ባይኖር እንኳን በከፍተኛ ደረጃ የሚዛባ ፍትሕ** አለ ከተባለ ጊዜው

ያለፈበት ይግበኝ ሊታይ የሚቻልበትን እድል ሕጉ ዝግ አላደረገም፡፡ ይግባኝ ማቅረቢያ መንገዱ ሰፋ ያለ እንደሚሆኑ ማጠን በማኸቸወም **ምክንያት ይግባኝ ሳይጠየቅ አንድ አመት ያለፈ እንደሆነ ከወንጀል** ቅጣትና ከሥነ ሥርአቱ አላማ ወጪስለሚሆን በይግባኝ እንዲታይ የሚፈቀድ አይሆንም፡፡ በወንጀል ጉዳይ ቅሬታ ያለውአካል ለዚህን ያህል ጊዜ ቅሬታ ያስከተለበትን የወንጀል ፍርድ ተሸክሞ ይቆያል ማለትን አይቻልም፡፡ ጉዳዩ ከተከሳሽ ነጻነት እና ከተጎጂ ፍትሕ የማግኘት መብት ጋር በቀጥታ የሚገናኝ በመሆኑ ስህተት ያለበትን የወንጀል ፍርድ ለማረም ፍርደኛወም ሆነ አቃቤ ሕግ ይህንን ያህል ጊዜ ይግባኝ ሳይጠይቁ ይቆያሉ ማለትም አስቸጋሪ ነው፡፡

የይግባኝ ሰሚፍርድ ቤት ስልጣንን በተማለከተም ይግባኝ ሰሚፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤትን ወሳኔ አፈፃፀም ማገድ የሚቻል ሲሆን ለዚህ አፈፃፀም የሚረዱ ድንጋጌዎችንም ሕጉ ዘርዝሮ ይዟል፡፡ ይህም ከዚህ በፊት እግድን አስሚልክቶ የነበረውን ክፍተት ይሸፍናል ተብሎ ያታሰባል፡፡ ያልተጠየቀ ዳኝነት አይሰጥም በሚለው መርህ ማስረት ይግባኝ ሰሚውፍርድ ቤት ከይግባኝ ቅሬታ በላይ የከበደ ወሳኔ ሊሰጥ እንደሚይችል ሕጉ ታሳቢ በሚድረግ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ስልጣን የስር ፍርድ ቤት ወሳኔን የሚፅናት፣ የማለወጥ፣ የማሻሻል እና የመሻር ስልጣን እንደሆነ በግልፅ አስቀምጧል፡፡ ይግባኝ ሰሚፍርድ ቤቱ በዚህ ስልጣኑ የራሱን ወሳኔ በስር ፍርድ ቤት ወሳኔ የመተካት ወይም ጉዳዩ እንደገና በስር ወይም በሌላ ፍርድ ቤት እንዲታይ የሚድረግ ስልጣንም አለው፡፡ ይሁን እንጂ ባለጉዳይን በወንጀል ጉዳይ ማመላለስ ይበልጥ የሚይደገፍ በመሆኑ እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ በተቻለ ማጠን ያለቀለት ስራ ይሰራል የሚል መሻ ያለ በመሆኑ በተቻለ ማጠን ጉዳዩ ወደ ስር ፍርድ ቤት ሳይመለስ በይግባኝ ሰሚውፍርድ ቤት የመጨረሻ ወሳኔ ቢሰጥበት ይመረጣል፡፡ ክርክሩ ከተጠናቀቀ በኋላም ይግባኝ ባይ ወይም መልስ ሰጭሳይቀርቡ ከቀሩ ወሳኔ ሰጥቶ ወሳኔውእንዲፈጸም ትእዛዝ ማስጠት እንጂ የግድ አሰፈላጊ ባልሆነው አግባብ እንዲቀርቡ ቀጠሮ ሲቀያየር ወይም መዝገብ ሲዘጋና ሲከፈት መቆየት አይኖረበትም፡፡ መዝገብ የግድ የሚቋረጥ ቢሆንም እንኳን ወሳኔ ለሰጥባቸውየሚገቡ (ንብረት እግድ፣ መውረስ፣ ዋስትና ጉዳይ ገነዘብ ገቢ ሚድረግ/አለሚድረግ...) የመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ ወሳኔ ሳይሰጥባቸው ተንጠልጥለው አየቀሩ ከዘመናት በኋላም ጥያቄ እየተነሳባቸው መዝገብ የሚያነቀሳቅሱ በመሆናቸው መዝገብ በተዘጋ ቁጥር ተገቢውማጣራ እየተደረገ ወሳኔ ሊሰጥባቸውእንደሚገባ ሕጉ ድንጋጌ ይዟል፡፡ በይግባኝ ወሳኔ ሊጠቀመየሚችሉ ሌሎች ይግባኝ ያልጠየቆ ፍርደኞች ቢኖሩ ይግባኝ ቢሉ ይጠቀሙየነበሩ ለመሆናቸውበሚገባ ከተረጋገጠ በይግባኝ ሰሚውፍርድ ቤት ወሳኔ ሊጠቀመየሚቻሉበትን እድልም አካቷል፡፡

ከይግባኝ ጋር በተያያዘ የመጥሪያ፣ የሬጂስትራር ስልጣን፣ የተዘጋ መዝገብ የሚከፈትበት አግባብ፣ ተጨሜሪ ማስረጃ አፈቃቀድ...የመሳሰሉት ጉዳዮች ከቀጥታ ክስ ጋር ተቀራራቢ በሆነ አግባብ የሚፈፀሙናቸው፡፡

## 15.2 ሰበር

የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ በሕገ መንግሰቱ ለጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የሰጠው የሰበር ስልጣን የሚመሩትን ሥነ ሥርአት አከቷል፡፡ እስካሁን ባለው አሰራር ሰበር ራሱን ችሎ ለብቻው የወጣ የሰበር ስርአት የሌለው በመሆኑ ልዩ ልዩ ቅሬታዎችን ሲያስከትል መቆየቱ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ሕጉ የሰበር ስርአትን በዝርዝር አካቷል፡፡ ይሁን እንጂ ሰበር በመሰረቱ ፍርድ እንደገና የሚታይበት ስርአት በመሆኑ ከይግባኝ ስርአት ጋር የሚጋሩቸው በርካት ጉዳዮች ያሉት ነው፡፡ በመሆኑም ለሰበር ስርአት የተለየ ድንጋጌ እስካልተቀመጠ ድረስ የይግባኝ ስርአቶች ለሰበር ስርአትም ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

ሕጉ ለሰበር የተለየ ስርአት ያሰቀመጠው በዋነኛነት በሁለት ምክንያቶች ነው፡፡ የመጀመሪያው ሰበር ለተከራካሪ ወገኖች የተሰጠ መብት ሳይሆን ለጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ስልጣን ከመሆኑ የሚመነጭ ነው፡፡ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ሰበር በፍትሕ ስርአቱ ላይ ሊጫወት የሚገባው አጅግ የተለየ አላማ ያለው ከመሆኑ የሚመነጭ ነው፡፡

እነዚህን ምክንያች መሰረት ያደረጉ የሰበር አላማ እና የሰበር መርህ በሥነ ስርአት ህጉ ወስጥ በግልፅ ተቀምጠዋል፡፡ የሰበር አሰራር ከሚታችባቸው ምክንቶች ወስጥ አንዱ ሰበር በተቋቋመበት ሕግ ላይ ግልፅ አላማ ያልተቀመጠለት በመሆኑ ከስልጣኑ እየወጣ ወሳኔ የሚሰጥባቸው ጉዳዮችና አጋጣሚዎች አሉ የሚል ነው፡፡ አላማውና መርሁ በግልፅ መቀመጣቸው ይህንን ችግር ለመቅረፍ ያግዛል ተበሎ ታሰቧል፡፡

ሰበር በመሰረቱ መሰረታዊ ሕግ ስህተት የሚታረምበት ስርአት እንጂ እንደ ይግባኝ ስርአት ስሕተት ሁሉ የሚታረምበት ስርአት አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሚለው ትርጉም ያልተሰጠው በመሆኑ እስካሁን ያለተቋረጠ እና የተደበላለቀ ክርክር የሚደረግበት ሆኗል፡፡ ከዚህ በመነሳትም የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ በሁለት ዋና ዋና መመዘኛዎች ላይ ተንተርሶ ለመሰረታዊ የሕግ ስህተት ትርጉም ያሰቀምጣል፡፡ የመጀመሪያው ስህተት የህግ ስሕተት ሆኖ ስህተቱ በተከራካሪ ወገኖች ላይ ብቻ ሳይሆን በሕግ ስርአቱ ላይ መናጋትን (ሾክ) የሚፈጥር መሆን ይኖርበታል፡፡ ሁለተኛው መለኪያ ህግ የሚባሉት ላይ (ከሕገ መንግስት አንስቶ) በአፈጻጸም ወይም በትርጉም የሚያጋጥሙ ስህተቶችን የሚመለከት ሆኖ ዝርዝራቸው በሕጉ ላይ የተቀመጡት ናቸው፡፡ ስህተቱ መሰረታዊ እንዲባል ሁለቱ መመዘኛዎች በአንድነት መሟላት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ ትርጉም እስካሁን የሚያጋጥምን ችግሮችን በተሻለ ሁኔታ ለመቅረፍ ያግዛል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ሕጉ መሰረታዊ ለሚባሉት የሕግ ስህተቶች ትርጉም ሲሰጥ በፍፁም መሰረታዊ ሊባሉ የማይገባቸው የሕግ ስህተቶችንም ለይቶ አስቀምጧል፡፡

ከተከራካሪ ወገኖች በላይ በህግ ስርአቱ ላይ ሚናጋትን የሚፈጥርን ስህተት የማረም ፍልጎት የሁሉም አካላት ፍላጎት ነውተባሎ ይታሰባል፡፡ ስህተቱ በፍድ ቤት ሥርአት ካልተስተካከለ ስህተቱን ለማስተካከል ህግ አወጪው በጉዳዩ ላይ ግልጽ ህግ ለማውጣት የሚገደድበት እድሉም ከፍተኛ ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ ለተከራካሪ ወገኖች ፍላጎት ብቻ የሚተው ባለመሆኑ ስህተቱ እንዲታረም ጥያቄ ሊያቀርቡ የሚችሉ ሰዎችን ማስፋቱ ተገቢ ነው፡፡ በዚህ መሰረትም የየፍርድ ቤት ፕሬዚዳነቶች በጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንቶች አማካኛነት፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳነቶች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍድ ቤት ችሎት ወይም ሌላ የሚመለከተው አካል በጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አማካኝነት አንድ ጉዳይ በሰበር እንዲታይ ጥያቄ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ በስር ፍርድ ተጠቃሚ ወይም ተጎጂ በሆነው ፍርደኛ ቅሬታ ባያቀርብም የእርሱን መበት በሚይጎዳ ሚሉኩ ሕጉ ተቃንቶ ሊተረጎም ይገባዋል ስለሚገልበት አግባብ ግን በእነዚህ አካላት ጥያቄ ቀርቦ የፍርደኛው መበት ሳይጎዳ ስለ ሕጉ ትርጉም ብቻ ወሳኔ ማጥትም የተገባ ስለሚሆን ይህንን የሚገዛ ተጨማሪ ድንጋጌ ተካቷል፡፡

የሰበር አላማን ለማስካት አሜልካቾች የሚጫውቱት ሚና ምጉልህ ነው፡፡ ለምሳሌ አሜልካቾች ጉዳያቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ላይ እንዲያኩር ማድረግ ይገባቸዋል፡፡ በመሆኑም የሰበር አሜልካቾች ለሰበር የሚያቀርቡት ማመልከቻ ከይግባኝ ማመልከቻም በተለየ ሚሉኩ ተፈፀመ የሚባለውን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሚያመለክትና መሰረታዊው የሕግ ስሕተት ሊታረም ወይም ተቃንቶ የሚታረምበትን/የሚተረጎምበትን ምክንያት በግልጽ ማመልከት ይኖርበታል፡፡

የሰበር ሰሚውን ፍርድ ቤት ስላጣን በተመለከተ ችሎቱ አንድ ይግባኝ ሰሚፍርድ ቤት ያለውስልጣን ያለውቢሆንም በተወሰኑ ጉዳዮች በተለይ በክልል ፍርድ ቤት ጉዳዮች ላይ የሕጉን ትርጉም በማቃናት ጉዳዮ ግን የሚጨረሻ ወሳኔ እንዲሰጥበት ለስር ፍርድ ቤት መመለስን ቢሚጥ ተከራካሪ ወገኖች የሚያራቸውን የማስማት መበት ከፍ ያደርጋል፡፡ ስለሆነም ጉዳዩን ሰፋ ባለ ስልጣን ተሚልከተው ወሳኔ ማስጠት ወደሚችሉት የስር ፍርድ ቤት ቢሚልሰው ተመራጭነው፡፡ የሰበር ወሳኔ በወጡቱ በማናቸውም ፍርድ ቤት ላይ አስገዳጅ ቢሆንም ባይሆንም የሕግ አለዚያም የሞራል አስገዳጅነት ወጡቱ የሚይቀር በመሆኑ "ሰብሮ መመለስ" የሚመከር ነው፡፡

የወንጀል ጉዳይ በዋነኛነት በሕገ መንግስቱ የተመለከቱትን የሰብአዊ መበት ጉዳዮችን የሚመለከቱ መሆናቸው ግልፅ ነው፡፡ እነዚህን ጉዳዮች የማክበርም ሆነ የማስከበር ሃላፊነት የሁሉም አካላት ግዴታ ነው፡፡ አሁን ባለው አሰራር ለሰበር የሚቃርቡት አበዛኛዎቹ ጉዳዮች ለሰበር ችሎቱ ሳይቀርቡ "አጣሪ ችሎት" በሚሰጠው ወሳኔ/ትእዛዝ እንደሚቋጩይታወቃል፡፡ የኃላ ኃላ ቢሆንም አጣሪው ችሎት ለሰበር ችሎቱ ከሚራቸው ጉዳዮች

ውስጥ በርካታ ጉዳዮች ማስረታዊ የሕግ ስህተት የለባቸውም ተብለው ይዘጋሉ፡፡ በሌላ በኩልም አጣሪው ችሎት ከማለሳቸው ጉዳዮች ውስጥ ማስረታዊ የሕግ ስህተት እያለባቸው ተዘግተዋል የሚል ቅሬታም የሚነሣባቸው ይገኛሉ፡፡ ስለሆነም ይህንን አሰራር ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡

አሁን ባለው አሰራር አጣሪ ችሎቱ በሶስት ዳኛ የሚሰራ ነው፡፡ አጣሪ ችሎቱ የመጨረሻ ውሳኔን የመሻር፣ የማለወጥ እና የማሻሻል ስልጣን ባይኖረውም በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመደበኛውችሎት የተሰጠን የመጨረሻ ውሳኔን ግን የሚመረምር ችሎት ነው፡፡ በሌላ በኩል የሰበር ችሎቱምአካል አይደለም፤ ነውየሚል ቢሆን ደግሞ አያስቀርብምየሚለቸውን ውሳኔዎች ጨምሮ ሌሎች ውሳኔዎቹ የሰበር ችሎቱ ውሳኔ ውጤት ይኖራቸዋል፡፡ አነ ዚህን አሰችጋሪ ውጤቶችን ለመቆጣጠር እንዲሁም የሰበአዊ መብት ጉዳዮች በጠራ ሁኔታ እንዲመረመሩ ለማድረግ በወንጀል ጉዳይ ላይ የአጣሪ ችሎት አሰራር ቀሪ እንዲሆን የስነ ስርአትና ማስረጃ ህጉ ታሳቢ አድርጓል፡፡ የሌሎች አገራት ልምድምይህንን ያመለክታል፡፡ አሰራሩ አጣሪ ችሎቱ ቀሪ የሚሆንበትንና የአጣሪ ችሎቱን የሰው ሃይል ጨምሮ የሰበር ችሎቱ ዳኞችን ቁጥር በማብዛት፣ በጉዳዮች አይነት የተካነ ዳኛ በማበርከት እንዲሁም ለስራው በሚያስፈልግ ቁጥር የበረከተ የሰበር ችሎት በማቋቋም ተግባራቱ ሁሉ በመደበኛው የሰበር ችሎት ተጠናቀውእንዲፈፀሙስነ ስርአትና ማስረጃ ህጉ ያስባል፡፡ ይህምየሰብአዊ መብትን በተሻለ ሚልኩ በማስጠበቅ የሰበር ተግባርን ጥራት በእጅጉ ይጨምራል የሚል እሳቤ ይዟል፡፡

ከሰበር አላማ አንፃር ሌላው ድንጋጌ ውስጥ የተካተተው ጉዳይ የሰበር ማመልከቻ ከቀረበ በኋላ የተከራካሪ ወገኖች ያለመቅረብን የሚመለከተውጉዳይ ነው፡፡ ሰበር ከተከራካሪ ፍላጎት በላይ የሚያሳካውየተለየ ተልእኮ ያለው በመሆኑ ተከራካሪዎች ባለመቅረባቸው ብቻ ጉዳዩ መቋረጥ የሌለበት ሆኖ በሕግ ጉዳይ ላይ ችሎቱ የማስለወጥ ውሳኔ ማስጠት እንዳለበት የሚያስገነዝቡ ድንጋገዎች ተካተዋል፡፡

የሰበር ውሳኔ በማናቸውም ፍርድ ቤት አስገዳጅ ውጤት ያለውነው፡፡ አስገዳጅነቱ በፍርድ ቤት ላይ ይሁንም እንጂ በውጤቱ የመገደዱት ተከራካሪ ወገኖችና መላውሕብረተሰቡነው፡፡ ምንምእንኳን ተግባሩ ሕግ መተርጎም ቢሆንም ሕብረተሰቡ በተሳትፎው ያወጣው ሕግ ባልተሳተፈበት ሁኔታ በተተረጎመው ሕግ የሚገደድበት አጋጣሚ ይበዛሉ ማለት ነው፡፡ ስለሆነም የሰበር ውሳኔ አስገዳጅነት የሚቀጥል ቢሆን ከተከራካሪ ወገኖች ፍልጎት በተጨማሪም ሌሎች ፍልጎቶች የሚነሣበትን አድል ማስፋትና ስርአቱን ይበልጥ አሳታፊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም በውሳኔ ማስጠት ሂደት ውስጥ ስለጉዳዩ ሳይሆን ስልህጉ ትርጉም ብቻ የሚመለከታቸውአካላት (የሕግ ትምህርት ቤቶች፣ የህግ ምርምርና ስልጠና ተቋማት፣ የሕግ አወጪውሕግ ጉዳይን የሚመከታተሉ አካላት…) ተገቢ

ነው ስለሚሉት የሕግ ትርጉም አስተያየት በፅሑፍ ማስጠት የሚችሉበትን እድል ሕጉ ክፍት አድርጓል፡፡ ሰበር ሰሚው ችሎት በአስተያየቶቹ የሚይገደድ ቢሆንም አስተያየት መቀበሉ የሕጉ ትርጉም ሊያሳካ ከሚያስበው ግብ አንፃር ተገቢ ነው፡፡ ጉዳዩ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ ውጤት ከተከራካሪ ወገኖች በላይ በመሆኑ የሚመለከታቸውን አካላት አስተያየት መቀበልና መመርመር ሕገ መንግስታዊ አሳታፊነት ነው፡፡ ስለሆነም የሰበር ችሎት በአሰራሩ ይበለጠ አሳታፊ እንዲሆን ታስቧል፡፡

በሌላ በኩል የሰበር ስራ አላማውን ሙሉ በሙሉ ለማሳካት እንዲችል በጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚቋቋም የሕግ ምርምር ክፍል (ወይም የሕግ ጥናትና ምርምር ባለሙያዎች) ስለ ህጉ ትርጉም ጥናትና ምርምር እንዲደረግለት ለማድረግም እንዲችል ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## 15.3 ፍርድን እንደገና ማየት

በአንድ ፍርድ ቤት የተሰጠ ማናቸውም ፍርድ ፍርዱ በተሰጠበት ወቅት በየትኛውም ፍርድ ቤት ያለተገለጠ ስሕተት ያለበት ሆኖ ማስረታዊ የሆነ የፍርደኛ መብት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከተለ የሚሆንባቸው አጋጣሚዎች አሉ፡፡ በእንደዚህ ባለው አጋጣሚ የተሳሳተው ፍርድ የሚስተካከልበት ሁኔታ ሊኖር የሚገባው ነው፡፡ የዚህን አይነት ጉዳይ ሊሰተናግድ የሚችል ሕግም ሆነ አሰራር በአገራችን የሌለ በመሆኑ የፍርደኞች ጥያቄ ቢኖርም ስህተት መኖሩን መርምሮ መልስ የሚሰጥበት ሁኔታ አልነበረም፡፡ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲውን፣ በተግባር የገጠሙ ችግሮችን እንዲሁም የወጪ አገራን ልምድ በመመልከት የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ በዚህ ጉዳይ ላይ ዝርዝር ድንጋጌዎችን አካቷል፡፡

በጠቅላላው አነጋገር የፍርድ እንደገና ይታይልኝ ጥያቄ አቀራረብ ለይግበኝ በሚቀርበው አይነት መሆን እንደሚገባው ሕጉ ያስቀምጣል፡፡ ይሁን እንጂ ከጉዳዩ ልዩ ባህሪ በመነሳት የተለዩ ጉዳዮችንም አካቷል፡፡ የፍርድ እንደገና ይታይልኝ ጥያቄ የመጨረሻ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ የሚቀርብ ቢሆንም ከተፈፀመው ስህተት እና በስህተቱ ምክንያት ከደረሰው ጉዳት ከፍተኛነት አንፃር የጊዜ ገደብ ሳያግደው በማናቸውም ጊዜ እንዲቀርብ ሕጉ ሰፊ መብት ይሰጣል፡፡ ጥያቄ የሚቀርብበት ፍርድ የሞት፣ የእስራት፣ የገንዘብ ወይም ሌላ ቅጣት ቢሆንም በመጨረሻ ደረጃ የፍሬ ነገር ጉዳይ ላይ ውሳኔ በሰጠው ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ ስለሚሆንም ጥያቄውም የሚቀርበው ከሰበር በታች ያለውና ስህተት ያለበትን ፍርድ በመጨረሻ ደረጃ ለሰጠው ፍርድ ቤት ነው፡፡ ፍርድ ቤቱም የቀረበውን ማመልከቻ ከተቀበለው አቃቤ ሕግ በጉዳዩ ላይ መልስ እንዲሰጥበት በማድረግ አንድም ቀድሞ የተሰጠውን ፍርድ ወድቅ በማድረግ አመልካቹን በነፃ ያሰናብታል ወይም ቀድሞ የተሰጠውን ፍርድ ያፀናል

አለዚያም ቀድሞ የተሰጠው ፍርድ በማንሳት ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ያደርጋል አለዚያም ፍርዱን ሙሉ በሙሉ ወድቅ ያደርጋል፡፡ ፍርዱ እንደገና መታየት ያለበት ሆኖ ከተገኘ ማናቸውም የተሰጠ ፍርድ፣ ውሳኔ፣ ብይን ወይም ትእዛዝ ሙሉ በሙሉ ተነስቶ ጉዳዩን ቀድሞ ያላየው ፍርድ ቤት ወይም ችሎት በጉዳዩ ላይ እንደገና ክርክር አድርጎ ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡ ጉዳዩን እንደገና የሚመለከተው የበታች ፍርድ ቤት የመጨረሻው ፍርድ ቤት በወሳኔ መርጦ ሲልክ በጉዳዩ ላይ ትክክለኛ ውሳኔ በማስጠት የስነ ስርአትና ማስረጃሕጉን አላማ ያሳካል የሚባለውን ፍርድ ቤት በማምረጥ ነው፡፡

ፍርዱ የተሻረ እንደሆነ በተሳሳተ ፍርድ ፍርደኛው ወይም ቤተሰቡ መጎዳታቸው እርግጥ ነው፡፡ ይህ ጉዳት የገንዘብና የንብረት ጉዳት ብቻ ሳይሆን የጤናም ጭምር ስለሚሆን ጉዳቱን ሙሉ በሙሉ መካስ ሊያስቸግር ይችላል፡፡ ያም ቢሆን በተሳሳተ ፍርድ ለተጎዳ ፍርደኛ የሞራልም ሆነ የንብረት ጉዳት ካሳ ማገኘት ያለባቸው በመሆኑ ተመጣጣኝ ካሳ ከመንግስት እንዲያገኙ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ፍርደኛው በሕይወት የሌለም እንደሆነ ለትዳር ጓደኛው ወይም ለወራሾቹ ካሳ ሊከፈል ይገባል፡፡ የካሳው አከፋፈልን በተመለከተ በጉዳዩ ላይ የአፈፃፀም ደንብ እንደሚወጣ ሕጉ ታሳቢ የሚደርግ ቢሆንም ደንቡ እስኪወጣ ድረስ ግን የካሳው መጠን ተመጣጣኝነት አግባብ ባለውሌላ ሕግ (በፍትሐብሔር ደንብ) መሰረት የሚሰላ ይሆናል፡፡

በተሳሳት ፍርድ የደረሰን ጉዳት በተለይም የሞራል ጉዳት የገንዘብ ካሳ ብቻ ይተካዋል ተብሎ አይታሰብም፡፡ ሕጉም ይህንን ታሳቢ በማድረግ ከካሳው በተጨማሪ በተጎጂው ላይና በቤተሰቡ ላይ ለደረሰው ጉዳት መንግሰት ይቅርታ እንደሚጠይቅ ይደነግጋል፡፡ የይቅርታ አጠያየቅ የራሱ ስርአት ሊኖረው ስለሚችል ተጨማሪ ደንብ የሚወጣ ሲሆን ደንቡ እስከሚወጣ ድረስ ግን በተመሳሳይ ሜኬኑ ስራ ላይ ያሉ ሌሎች ሕጎች ተፈፃሚይሆናሉ፡፡ ስህተትን በይፋ መቀበልና ይቅርታ ማጠየቅ የካሳን ጉድለት ሊሞላ የሚችል ከመሆኑም በላይ በሕገ መንግስቱ የተረጋገጠው የተጠያቂነት ስርአት ማረጋገጫ የሰለጠነ መንግስት መገለጫም በመሆኑ በሕጉ እንዲካተት ሆኗል፡፡

## 16. በወንጀል ጉዳይ አለምአቀፍ የወንጀል ጉዳዮች ትብብር

ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎች እና ጉዳዮች እየተወሳሰቡ የመጡከመሆናቸውም በላይ አለም አቀፍ ትብብርም እጅግ እየተወሳሰብ መጥቷል፡፡ የፍትሕ አካላት በዚህ ረገድ የሚኖራቸውን የትብብር ድርሻ በአግባቡ መወጣት እንዲችሉ እና አገራችንም አለም አቀፍ ግዴታዋን በአግባቡ መወጣት እንደትችል በወንጀል ህግ ድንጋጌ ያስፈልጋል፡፡ አለም አቀፍ ትብብር በመሰረቱ እንደቅደም ተከተሉ በአለም አቀፍ ህጎችና መርሆዎች፣

በሁለትዮሽ ወይም በብዙ አገራ መካከል በሚደረግ ስምምነተና በአገሪቷ ሕጎች (የወንጀል ስነ ስርአትና የማስረጃን ጨምሮ) አማካኝነት የሚተገበር ነው፡፡ አለም አቀፍ ትብብርን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በማረቱ አለም አቀፍ ተቀባይነትን ያተረፉ እና ደረጃቸውን የጠበቁ አሰራሮችን ለማስራት በሚያስችል መልከ መደንገግ ያለባቸውበመሆኑ ሕጉ ከዚህ ጋር የተጣጣሙድንግጌዎችን ይዟል፡፡

የዓለም አቀፍ ጉዳዮችን በተመለከተ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚያጋጥሙችግሮችን ለመቋቋምና ለችግሮቹ መፍትሔ ለሚፈላለግ አገሮች ለየብቻቸው ከሚያደርጉት ጥረቶች ይልቅ ተባብረው በጋራ የሚሠሩት ሥራ የተሻለ ውጤት እንዳለውይታመናል፡፡ በዚህ የተነሳ አገሮች የጋራ ችግሮቻቸውን ሊቋቋሙና ሊፈቱ የሚችሉበት የጋራ የአሠራር ሥርዓቶችን ቀይሰው ሲሠሩ ኖረዋል፡፡ አገሮችን በጋራ ከሚያጋጥሟቸው ችግሮች መካከል አንዱ ከወንጀልና ከወንጀል ሕጐች ጋር ተያይዞ ያለ ችግር ነው፡፡ ይህንን ችግር ለመፍታትም ይረዳቸውዘንድ በጋራ መግባባት ላይ የደረሱበትን የጋራ አሠራሮችን ቀይሰው አብረው ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ አሁን ባለው የልኡላዊነት ዓለም እንኳ ከወንጀል ጉዳዮች ጋር ተያይዘው ያሉ ችግሮች የሁሉም አገሮች የጋራ ችግሮች ሆነው ከመቀጠላቸውም አልፎ የዓለም ሕዝቦች የጋራ የስጋት ምንጭ ሆነዋል፡፡ አሁን ባለንበት ዓለም የሚፈፀሙወንጀሎች ከጊዜ ወደ ጊዜ በአይነትና በብዛት እንዲሁም በአፈፃፀም ስልቶቻቸው የተወሳሰቡና የተበራከቱ ሆነዋል፡፡ እንደ ሽብርተኝነት፣ በተደራጁ ቡድኖች የሚፈፀሙወንጀሎች፣ ሕገ ወጥ የሰውየጦር መሳሪያ እና መድሓኒት ዝውውር፣ የሳይበር እና የመሳሰሉት ወንጀሎች የዓለማችን የጋራ ችግሮች ሆነዋል፡፡ በመሆኑም ሃገሮች ብሔራዊ ጥቅሞቻቸውንና ደህንነታቸውን በማስጠበቅ ዜጐቻቸውንና ተቋሞቻቸውን ከወንጀል ድርጊት ለመከላከል ሲሉ የዓለም አቀፍ ትብብር አሠራሮችን ለማጠናከር ከምንጊዜም በበለጠ ትኩረት ሰጥተውበት እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ አገራችን ኢትዮጵያም የዓለም አቀፍ ማሕበረሰብ አካል እንደመሆኗ እና ጉዳዩም በቀጥታ የሚመለከታት እንደመሆኑ መጠን የዓለምአቀፍ ትብብር አሠራርን አስመልክቶ ብዙ ሥራ መሥራት ይጠበቅባታል፡፡

የዓለምአቀፍ ትብብር ሥራ የሚመሠረተውበዓለምአቀፍ እና በብሔራዊ ሕጐች ላይ ተመስርቶ ሲሆን በአገር ወስጥ የሚሠራ ሥራንና በዓለምአቀፍ ደረጃ የሚሠራ ስራን ያካትታል፡፡ በሃገር ወስጥ የሚሠሩ የዓለምአቀፍ ትብብር ሥራዎች በዋናነት በሃገር ወስጥ በሚገኙ የተለያዩ ተቋማት መካከል የሚኖረው ግንኙነትና ትብብር እንዲሁም በእነዚህ ተቋማት የሚከናወኑ ሥራዎችን በቀጥታ የሚመለከትነው፡፡ በዚህም መሠረት በአገር ወስጥ በሚገኙ ተቋማት መካከል የሚኖረው ግንኙነትና የአሠራር ሥርዓት አንዱ የዓለም አቀፍ ትብብር ገፅታ ነው ለማለት ይቻላል፡፡

አለም አቀፍ ትብብር በዋነኛት የሚሟራው በዓለም አቀፍ ሕጐችና ስምምነቶች ሲሆን ለሥራው ማካካት በአገራቱ ማካከል የሚኖረው ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነትም ወሣኝነት አለው፡፡ አገራችንን የሚሟከቱ ድንበርተኛጋሪ ወንጀሎችን ለማካላከል፣ ለመሟርመር፣ ለሕግ ለማቅረብ ወይም ለመቅጣት በመጀመሪያ ከሚሟከታቸው አገሮች ጋር የሕግ መሠረት ያለው ግንኙነት መፍጠር የግድ ይላል፡፡ የሌሎች ሃገሮችን የትብብር ጥያቄ ተቀብሎ አጥጋቢ ሜልስ ለማስጠትም ከላይ የተጠቀሰወን የትብብርና የአሠራር ሥርዓት መፍጠር የግድ ነው፡፡ በአገር ወስጥ ያሉ ብሐራዊ ተቋማት ማካከልም ያለወን የሥራ ግንኙነትና ትብብር በሕግ አግባብ ሥርአት ማስያዝ በተማሳሳይ አስፈላጊ ነው፡፡ አገሮች የዓለም አቀፍ ትብብር ሥራዎችን አስሜልክቶ በዓለም አቀፍ ሕጐች አማካይነት የገቧቸወን ግዴታዎች እና ያሏቸወን መብቶች ሜፈፀምና ማስፈፀም የሚቹሉት በሀገራዊ ሕጐቻቸው አማካይነት ነው፡፡ በአንድ አገር በተለያዩ የዓለም አቀፍ ስምምነቶች ወስጥ የተካተቱትን ሥነሥርዓቶች፣ አሠራሮች፣ አደረጃጀቶችና የመሣሠሉትን ሜፈፀምና ማስፈፀም የሚቻለው በአገራዊ ሕጐች ወስጥ በበቂ ሁኔታ ከተካተቱ ብቻ መሆኑን ማንዘብ ያስፈልጋል፡፡ እነዚህ አገራዊ ሕጐች በዋናነት የትብብሩን ፍሬ ነገሮች የሚወስኑ ናቸው፡ ከዚህ በተጨሜሪ የትብብሩን ሥራዎች ለማቀላጠፍ የሚረዱ የአደረጃጀትና የሃገር ወስጥ የፍትሕ ተቋማት የሥራ ግንኙነቶችን ሜልክ የሚያስይዙ ናቸው፡

እስካሁን ባለው ሁኔታ የእነዚህን አይነት ግንኙነቶች በሁለትዮሽ ወይንም በባለ ብዙ አገራት ስምምነቶች እና አለም አቀፍ ሕጎች እየተሟራ ቢሆንም በስነ ስርአትና ማስረጃ ህጉ ወስጥ የተማከተ ወንጀል ነክ ግንኙነትም የሚሟራ ስርአት አልነበረም፡፡ በመሆኑም ከላይ የተማከቱትን ሁኔታዎች ግምት ወስጥ በማስገባት የስነ ስርአትና ማስረጃሕጉ ይህንን ጉዳይ ሊሟራ የሚቹል ድንጋጌ አካቷል፡፡ ግንኙነቱ የሁለትዮሽ በመሆኑም በሕ የተማከቱት ድንጋጌዎች በተለየ ሜልኩ ካልተማከተ በስተቀር ኢትዮጵያ ትብብር ስትጠይቅም ሆነ ትብብር በምትጠይቅበት ወቅት ሁሉ የሚፈጸሙ ናቸው፡፡ የትብብር አይነቶቹ ለወንጀል ጉዳይ አዲስ በመሆናቸወም ምንታቸወን ጨምሮ የተካተቱበትን አግባብ ከዚህ በታች ያሉት ክፍሎች ይማከቱታል፡፡

## 16.1. የዓለምአቀፍትብብር ምንነት

በዓለምአቀፍ ግንኙነት ወስጥ የዓለምአቀፍ ትብብር የቆየ እና የታወቀ ቢሆንምእስከአሁን ድረስ ግልፅ የሆነ የሕግ ትርጉም አልተበጀለትም፡፡ ይህ አሠራር የዓለም አቀፍ ስምምነቶችና የሃገር ወስጥ ሕጐችን መሠረት ያደረገ በሜሆኑ በተለያዩ አገሮችና አገሮቹ በሚከተሏቸው ሥርዓቶች ወስጥ የተለያየ ይዘትና ትርጉም ሲሰጠው ይታያል፡፡ በሃገራችንም ቢሆን የዓለምአቀፍ ትብብር የሚባል በግልፅ ትርጓሜየ ተሰጠው ሥራ የለም፡፡ ይሁንና በተለያዩ የዓለም አቀፍ ሰነዶችና የአገሮች ሕጐች ወስጥ የዓለም አቀፍ ሥራዎች ተዘርዝረው የሚገኙ ሲሆን

በአገራችንም በተለያዩ አካላት የተወሰኑ ሥራዎች በዓለም አቀፍ ትብብር ሥራዎች ውስጥ ተካተው ሲሠሩ ቆይተዋል፡፡ በዚህም መሠረት በተለያዩ የዓለም አቀፍ ሰነዶችና በሃገራችን የነበሩትን ልምዶች መሠረት በማድረግ በዓለም አቀፍ ትብብር ሥራ ወስጥ ሊካተቱ የሚችሉ ዋና ዋና ተግባራት የሚከተሉት እንደሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡

## 16.2. አሳልፎ ማስጠት (Extradition)

የአሳልፎ ማስጠት አሠራር ሁለት ገፅታ አለው፡፡ አንደኛው በኢትዮጵያ ግዛት ወስጥ ወንጀል ፈፅመው ወደ ሌላ ሃገር የሸሹትን ፣ ወይም በውጭ ሃገር ባሉ የኢትዮጵያ ጥቅሞች ላይ ወንጀል ፈፅመው ከኢትዮጵያ ውጭ የሚገኙ ተጠርጣሪዎች ወይም ጥፋተኞች ተላልፈው ለኢትዮጵያ እንዲሰጡ ጥያቄ ማቅረብን የሚመለከት ነው፡፡ ሁለተኛው በሌላ ሃገር ወንጀል ፈፅመው በኢትዮጵያ ወስጥ የሚገኙ ትተጠርጣሪዎች ወይም ወንጀለኞች ተላልፈው እንዲሰጡ የቀረበን ጥያቄ ተቀብሎ እንደ አግባብነቱ የሚስተናገድ አሠራርን የሚመለከት ነው፡፡ ይህ አሠራር በኢትዮጵያ ሕጐችና ኢትዮጵያ የፈረመቻቸው የዓለም አቀፍ እና የሁለትዮሽ ስምምነቶች መሠረት የሚሠራ ሥራ ነው፡፡ የአሣልፎ ማስጠት ሥራ በብዙ የጋራ ስምምነቶች ወስጥ የተካተተ ሲሆን የአገራችን ሁኔታ በተመለከተ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 21 ሥር ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ አገራችን ከተለያዩ አገሮች ጋር የተፈራረመቻቸው የሁለትዮሽ (bilateral) ስምምነት ያለ ሲሆን ከጅቡቲና ከሱዳን መንግሥታት ጋር የተፈራረመቻቸው ስምምነት በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

## 16.3 በወንጀል ጉዳዮች መረጃ መለዋወጥ እና መተባበር (Mutual legal assistance)

ይህ አሠራር ከወንጀልና ከዳኝነት ሥራዎች ጋር ተያይዘው ያሉ መረጃዎችን ሃገሮች ወይም ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እንዲሰጣቸው ሲጠይቁ የተጠየቀውን መረጃ እንዲያገኙ ማድረግ ወይም እነዚህ አካላት በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ መረጃ እንዲሰጡ ጥያቄ ማቅረብንና መቀበልን የሚያጠቃልል አሠራር ነው፡፡ አሠራሩም የዓለም አቀፍ ሕጐችንና የሃገር ወስጥ ሕጐችን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ በወንጀል ጉዳዮች መረጃ የመለዋወጥ ሥራን አስመልክቶ የተለያዩ አሠራሮች ያሉ ቢሆንም ሥራው በዋናነት የሚከተሉትን ተግባራት ያጠቃልላል፡፡ የሚጠየቁ ጥያቄዎች እና የሚላኩ የሥነ ሥርዐት ሰነዶችን ማዘጋጀት፣ የተለያዩ ግንኙነቶችን ለመፐለፍ የሚውሉ ቴክኒካል መሣሪያዎችን በማስለፍ መርዳት፣ የሚታላለፉ መልዕክቶችን ለመቆጣጠር እና ስወር የምርመራ ሥራዎችን በድንበር አካባቢና በድንበር ላይ እንዲሰሩ መፍቀድ፣ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ምስክሮች በቪዲዮ እና በቴሌኮንፈረንስ የሚሰሙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ የታሰረ ሰው ለጊዜያዊ ምርመራ እንዲያግዝ ማስተላለፍ እና የመሣሠሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

አሠራሩ እና የትብብር ደረጃው እንደየሀገሮቹ ብሔራዊ ሕጎች የሚለያይ ከመሆኑ የተነሳ የተለያዩ ችግሮች ያጋጥማሉ፡፡ ሃገራችን በወንጀል ጉዳዮች ሚረጃ ማለዋወጥን አስመልክቶ ምንም ዓይነት ብሔራዊ ሕግ የሌላት በመሆኑ በዚህ ረገድ ብዙ ችግሮች ሲከሰቱ ይስተዋላል፡፡

### 16.3.1.ፍርደኞችን ማስጠት ወይም መቀበል (Transfer of sentenced persons)

በአንድ ሃገር ፍርድ ቤት የተፈረደባቸውን እስረኞች ለሌላ ሃገር ማስጠት ወይም መቀበል የተለመደ የዓለም አቀፍ ትብብር ሥራ ነው፡፡ ይህ የሚሆንባቸው የተለያዩ ምክንያቶች ያሉ ሲሆን በዋናነት ለምስክርነት ወይም ለሌላ የደህንነት ምክንያቶች ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪም በቅጣት መርህ መሠረት ፍርደኛው ይታረማል ተብሎ የሚታሰበው በራሱ ሕብረተሰብ ወስጥ ስለሆነ ፍርደኛው ወደተፈረደበት ሃገር እንዲመለስ ሃገሮች ይጠይቃሉ፡፡ ይህን ጉዳይ የሚገዛ ሕግ በአገራችን ያነበረ ሲሆን ከዚህ አንፃርም የዳበረ ውልምድ እምበዛም ነው፡፡

### 16.3.2. የወንጀል ክስን ወደ ሌላ ሃገር ማስተላለፍ

ይህ አሠራር በአንድ ሃገር እየታየ ያለን የወንጀል ክስ ወደ ሌላ ሃገር ማስተላለፍ ወይም በሌላ ሃገር እየታየ ያለውን ጉዳይ መውሰድን ያጠቃልላል፡፡ ይህ የሚደረገው በተለያዩ ምክንያቶች ቢሆንም በዋናነት የክሱን ሂደት ውጤታማ ለማድረግ ተብሎ የሚሠራ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ስምምነቶች ወስጥ ይህ አሠራር በብዛት የተቀመጠ ሲሆን እንደ UN Convention against Illicit Trafficking of Narcotic Drugs and Psychotropic substance Article (8) እና UN Convention on Transnational Organized Crime Art. 21) የማሳሉትን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ በሃገራችን የወንጀል ሕግም ሆነ በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች ወስጥ ይህ አሠራር ምን እንደሚመስል የሚያመለክት ሕግ በግልፅ እና በዝርዝር ባለመኖሩ የሃገራችን አሠራር ምን እንደሚመስል ለማወቅ ያስቸግራል፡፡

### 16.3.3. ሌሎች የዓለምአቀፍ ትብብር ዓይነቶች

ከላይ የተጠቀሱት ዋና ዋና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉት የዓለምአቀፍ ትብብር ዓይነቶችን መጥቀስ አስፈላጊ ነው፡፡ ከሙስና፣ ከኢኮኖሚ፣ ከፋይናንስና ከሕገ ወጥ ገንዘብ ዝውውር ወንጀሎች ጋር በተያያዘ የወንጀል ምርመራ ለማካሔድ ማስፈቀድ ወይም እንዲካሔድ መተባበር፣ የወንጀል ፍሬ የሆኑ ንብረቶችን ማገድ፣ መውረስ እና ማስወገድ፣ የወንጀል ምስክሮችና ሰለባዎችን ማጠበቅና መንከባከብ፣ በሕግ አስፈፃሚ አካላት መካከል የሚኖሩ ልዩ ልዩ የሥራ ትብብሮች ለምሳሌ ለየት ያለ የምርመራ ዘዴዎችን ማጠቀም፣ እንደዚሁም የወንጀል መከላከል ሥራዎችን በጋራ መሥራት፣ በህግ ጉዳይ ላይ በጋራና በትብብር ማስራትና ሌሎችን ሊካተቱ

ይቻላል፡፡ ከላይ የተጠቀሱ ሥራዎች በዋናነት የዓለም አቀፍ ትብብር ሥራዎች ሲሆኑ በተለያዩ የዓለም አቀፍ ስምምነቶችና የአገሮች ብሔራዊ ሕጎች ወስጥ ተዘርዝረውየሚገኙናቸው፡፡

## 16.4 የዓለምአቀፍ ትብብርንና የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫሕግ ሥነ ሥርዐት

ብዙ ሃገሮች የዓለም አቀፍ ትብብርን አስመልክቶ ያሉ ጉዳዮችንና አሠራሮችን በወንጀል ሕጎቻቸው ወስጥ በዝርዝር ከማስቀመጥ በተጨማሪ አስፈላጊ የሆኑ ልዩ ሕጎችን ያወጣሉ፡፡ ለምሳሌ ካናዳን ብንመለከት አብዛኛው የዓለምአቀፍ ትብብር አሠራሮችን በወንጀል ሥነ ሥርዐት ሕግ ወስጥ በዝርዝር ከማካተቷም በተጨማሪ ለየት ያሉ እንደ "በወንጀል ጉዳይ ላይ የጋራ ትብብር ለማድረግ የሚያስችላት ሕግ" ያሉ ልዩ ሕጎች አሏት፡፡ የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫሕግ ሥነ ሥርዐት የወንጀል ጉዳዮችን አስመልክቶ የዓለምአቀፍ የትብብር ሥራዎችን ለመሥራት የሚያስችሉ በቂ ድንጋጌዎች የሉትም፡፡ ከዓለም አቀፍ ትብብር ሥራዎች ጋር ተያይዞ የአገራችን ሕችጎ በበቂ ሁኔታ ተሟልተው ባይገኙም በአንዳንድ የትብብር ማስኮች (ለምሳሌ አሳልፎ ማስጠትን እና የውጭውሳኔዎችን ማስፈፀም ወዘተ) ላይ የተወሰኑ ድንጋጌዎች አሉ፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ሕችጎ በቂና ግልፅ አይደሉም፡፡ በዓለም አቀፍ ትብብር ጉዳዮች ላይ የእያንዳንዱ የፍትሕ እና የሚመለከታቸው አካላት ተግባርበ ግልፅ ባለመታወቁ እና ሥራዎቹ በማን፣ እንዴት ወዘተ እንደሚሠሩ የሚደነግግ የሕግ ድንገጌዎች ባለመኖራቸው ሥራው ወጥ በሆነ መንገድ መሠራቱን ለመከታተል እና ለመቆጣጠር አልተቻለም፡፡ በመሆኑም በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ዘርፍ ኢትዮጵያ ከዓለም አቀፍ ሕግጋት እና አሠራር ሥርዓት አንጻር ያሏትን መብቶች ለማስከበር እና የተጣሉባትን ግዴታዎች ለመወጣት የሚያስችል ጠንካራ የሕግ ማዕቀፍ ለመፍጠር ተችሏል ለማለት አይቻልም፡፡ የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዐት እነዚህን ችግሮች ከመፍታት አንጻር እጅግ ወሳኝ ሚና ያለው ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ በሥራ ላይ ያለው የወንጀለኛ መቅጫሥነ ሥርዐት ሕግ ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ግልጽ የሆነ ድንጋጌ የያዘ አይደለም፡፡

ይህንን ችግር ግምት ወስጥ በማስገባት የኢትዮጵያ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ ከወንጀል ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የዓለም አቀፍ ትብብር የሚደረግባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤቶች የተመሠረቱ የወንጀል ክሶችን፣ ዓለምአቀፍ ባሕርያት ባላቸውወንጀሎች ላይ የሚደረጉ ምርመራዎችንና ለወንጀል ድርጊት ምስክሮችና ተጎጂዎች የሚደረጉ ጥበቃዎችን በተመለከተ የሚደረጉ ትብብሮች እንዲሁም ለፍርድ ቤት ወሳኔዎች ዕወቅና ማስጠትና ማስፈጸም፣ የወንጀል ጉዳዮችን ወደ ሌላ ሀገር ማስተላለፍ፣ አሳልፎ ማስጠት፣ የጋራ የሕግ ድጋፍ እና የወንጀል ፍሬ የሆኑ ንብረትን ወይምገንዘብን ማገድና መወረስን የሚመለከቱ እንደሆኑ እና በሕግ ጉዳዮች ዓለም ትብብር ማስከ ያሉ ሕጎች ዓለም አቀፍ ትብብር የሚመራባቸው ዘመናዊ የአሰራሮችን፣ መርሆዎችን እና

ሕጎችን በሚያካትቱ እና አፈጻጸማቸውን በሚያቀላጥፍ መልኩ ሊሻሻሉና አዳዲስ ድንጋጌዎችን እንዲያካትቱ ሊደረግ እንደሚገባ በግልጽ አመላክቷል፡፡ ይህን ኑተከትሎ ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ለመፍታት እና የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲውን ለማስፈጸም ይህ የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዐት በወንጀል ጉዳዮች የአለም ዓቀፍ ትብብርን የሚመለከቱ ጠቅላላ ድንጋጌዎች፣ ልዩ ልዩ የትብብር ዓይነቶች የሚፈጸምበትን ሥነ ሥርዓት እና ስለ አሳልፎ ማስጠት ዝርዝር ሥነ ሥርዓቶችን አካትቶ እንዲይዝ ተደርጓል፡፡

በሕጉ ላይ በወንጀል ጉዳይ የሚደረግ ትብብር ዓላማህገሪቱ ከወንጀል ጉዳይ ጋር በተያያዘ በዓለምአቀፍ ደረጃ የሚኖሩ መብትና ጥቅሞችን ለማስከበር እና ግዴታዎችን በአግባቡ ለመወጣት ማስቻል እንደሆነ በግልጽ በመደንገግ በሕጉ  የተካተቱ የዓለም አቀፍ ትብብር ድንጋጌዎች የሚተረጎሙት ከዚህ ዓላማ አንጻር መሆን እንዳለበት ለማስገንዘብ በግልጽ ተካትቷል፡፡ በመርህ ደረጃ ሕጉ በወንጀል ጉዳይ የሚደረግ ትብብር ኢትዮጵያ በምታደረገውስምምነት መሠረት የሚፈፀም መሆን እንዳለበት የሚደነግግ ሲሆን የዚህ አይነት የሁለትዮሽ፤ ባለ ብዙ ሃገራት ወይንምአለምአቀፍ ስምምነት በሌለ ጊዜ ለሚቀርብ ማንኛወምየትብብር ጥያቄ በሕጉ የተካተቱት ዝርዝር ድንጋጌዎች ተፈጻሚእንደሚሆኑ በስነ ስርአትና ማስረጃሕጉ ተመልክቷል፡፡

በወንጀል ጉዳይ አለምአቀፍ ትብብር በስነ ስርአትና ማስረጃሕጉ ወስጥ ሲካተት የራሱን መርህና አላማ ይዞ ነው፡፡ በዋነኛነት አላማውም የአገሪቷን ጥቅምና መብት ለለማስከበር ሲሆን በመርሕ ደረጃም ከስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ይልቅ አገራችን በምትፈርማቸውስምምነቶች የሚመራ ነው፡፡ ለኢትዮጵያ የሚቀርብ የትብብር ጥያቄ የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥትንና ሉዓላዊነት የሚያስከብር፣ የአገሪቱን ሕዝቦች ጥቅም የሚያስጠብቅ፣ በእንካ ለእንካ መርህ እና በጋራ ጥቅምና እኩልነት ላይ የተመሠረተ መሆን እንዳለበት በሕጉ ተመልክቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ትብብር በአገሪቱ ሕገ መንግስተ የተመለከቱ የሰብአዊ መብቶችን በሚጥስ ወይምየእኩልነት መብትን በሚጥስ መልክ ሊፈፀምእንደሚይችል ይደነግጋል፡፡

በአሳልፎ ማስጠት ጊዜም ከተቀማጡት ገደቦች መካከልም ኢትዮጵያዊ ዜጋን አሳልፎ ማስጠት እንደሚይቻል ተደነግጓል፡፡ ትብብር ሊደረግባውየሚቻሉ ተግባራንም (ከወንጀል ምርመራ፣ ከማስረጃ፣ ከምስክር እና ጠቋሚ ጥበቃ፣ ከአሳልፎ ማስጠት፣ ከወንጀል ንብረት ፍሬ ወይምገንዘብ፣ ከተያዘ የተፈረደበት ሰውልወውጥ፣ ከወሳኔ ማስፈፀም፣ እና ከሌሎች በመንግስት ከሚፈቀዱ) ተጋባራት ጋር የሚገናኙ የትብብር ማስኮች እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ ከፍ ሲል የተገለጹትን ችግሮች ግምት ወስጥ በማስገባትም የትብብር ማስመርና የማስፈጸም ሥልጣን (በዲፕሎማሲያዊ ማስመር)፣ የትብብር ወጪ(በጠያቂውእንደሚሸፈን)፣ የትብብር ጥያቄ ማቅረብ ስለሚቻሉ

አካላት (በዋነኛት ጠቅላይ አቃቤ ሕግ ቀጥሎ የፌዴራል አካላት)፣ የጥያቄ አቀራረብ (በዋነኛነት በፅሁፍ)፣ የትብብር ጥያቄ ይዘት፣ የጥያቄወን ተቀባነይት፣ አግባብነት ማረጋገጥ እና ወሳኔ ማስጠት፣ ማረጋገጫ ማስጠት፣ የትብብር ጥያቄ አፈጻጸም፣ የወንጀል ምርመራና ከምርመራ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ትብብር፣ በኢትዮጵያ ወስጥ ያለን ሰው በጊዜያዊነት የማስተላለፍ ትብብር፣ በውጭአገር በቁጥጥር ሥር ያለን ሰው ለትብብር ማጠየቅ፣ ለትብብር ወደ ኢትዮጵያ የገባ ሌላ ሰው፣ በጠያቂ አገር ማረፊያ ወይምማረሚያ ቤት መቆየት ያለውወጤት፣ መጥሪያና ሌሎች ሰነዶች የማድረስ ትብብር፣ ፍርደኛን ማስተላለፍ፣ የፍርድ ቤት ትእዛዝ፣ ፍርድ ወይም ወሳኔ ዕወቅና ማስጠትና ማስፈጸምን፣ በኢትዮጵያ ግዛት እስረኛን ማስተላለፍ፣ ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት፣ በወንጀል ተፈላጊን ሰው አሳልፎ ማስጠትን የሚመለከቱ ዝርዝር ድንጋጌዎች በሕጉ ወስጥ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

የማኛቸወም የትብብር ጥያቄ አፈፃፀም የወንጀል ተጎጂን የካሳ ወይም ሌላ የመብት ጥያቄ በሚገዳ አኳኃን ሚፈጸም እንደሌለበት ሕጉ የሚደነግግ ሲሆን ትብብር እንዲደረግ የተወሰነ እንደሆነ የሚፈጸመው በጠቅላይ አቃቤ ሕግ አማካኝነት በሚመለከተውየመንግስተ ተቋምአማካኝነት እንደሆነ ምይደነግጋል፡፡ ሥለሆነምበወንል ተጎጂ አቤቱታ የተጀመረ ሌላ የወንጀል ጉዳይ ምርመራ ወይምየፍትሐብሔር ክርክር ካለ ጥያቄውለተወሰነ ጊዜ ሊተላለፍ ይችላል ማለት ነው፡፡

በአለም አቀፍ ትብብር ሂደት የፍርድ ቤት ሚናም በተመሳሳይ በሕጉ ወስጥ እንዲካተት ሆኗል፡፡ በዚህ ሚልኩ ከተቀመጡት ሃላፊነቶች ወስጥምአሳለፎ የሚጥን ሰውለጊዜውበእስር እንዲቀይ ትእዛዝ የማስጠት፣ በአሳልፎ ይሰጥ ጥያቄ ላይ በአምስት ቀናት ወስጥ ወሳኔ ማስጠት፣ ለኢትዮጵያ ተላልፎ የተሰጠን ሰውበእስር እንዲቆይ ወይም በስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ማሰረት የተፈለገበት ጉዳይ እንዲፈፀም አስፈላጊወን ትእዛዝ በስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ማሰረት የማስጠት ተግባራት ይገኙበታል፡፡ ይህ የፍርድ ቤት ተግባር መኖሩ ተቀባይነት ያለውአለምአቀፍ አሰራር በመሆኑ የትብብርን ፍላጎት ከፍ ያደርገዋል ተብሎይታሰባል፡፡

### 17. ኪሳራና ወጪ በተመለከተ

በስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ወስጥ በሚጨረሻው ክፍል ወስጥ ተካተተው በወንጀል ጉዳይ የሚወጣ ወጪ እና የሚደርስ ኪሳራን የሚመለከተው ጉዳይ ነው፡፡ አንደ የወንጀል ጉዳይ ተጀምሮ የሚጨረሻ እልባት እስኪያገኝ ድረስ በከሳሽ፣ ተከሳሽ፣ ምስክሮች፣ ፍርድ ቤት ላይ እና ሌሎች አካላት ላይ ወጪ የሚያስከትል በመሆኑ ይህንን ወጪማን ሊሸፍን እንደሚገባ መደንገግ ያለበት ነው፡፡ ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ነባሩ ሕግ ተመሳሳይ

ድንጋጌን የያዘ ሲሆን የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ በነባር ሕጉ ላይ ያስከተለው ማሻሻያ ለውጥ የለውም፡፡ በመሆኑም የወንጀል ጉዳይ በማሰረቱ የሕዝብና የመንግስት ጉዳይ በመሆኑ በየትኛውም ደረጃ ለሚደረግ ክርክር የሚስፈልገው ወጪ በመንግስት የሚሸፈን ይሆናል፡፡ ይሕ ወጪ አስፈላጊ የሆነውን ወጪ ሁሉ የሚሟላከት ሲሆን በተከሳሽ የተለየና ያልተገባ ምክንያት (ምሳሌ ከእስር በመጥፋቱ ፈልጎ በቁጥጥር ስር ለማዋል የሚወጣ ወጪ) የሚወጣን ወጪ በፍርድ ቤት ወሳኔ ተከሳሹ እንዲሸፍን ሊወሰን ይቻላል፡፡ በርካታ ተከሳሾች የሆኑ እንደሆነም እንደሳፈላጊነቱ እየተጣራ በአንድነት እና በነጠላ ሊሸፍኑ ይችላሉ፡፡ በማኛቸውም ምክንያነት ግን የተከላካይ ጠበቃ፣ የአስተርጓሚእና ማሰል ወጪዎች በመንግስት የሚሸፈን ነው፡፡

በተማሳሳይ ምክንያት በግል አቤቱታ የሚቀርብን የወንጀል ፍርድ ሂደት ወጪ የግል ክስ አቅራቢ (በርካታ ከሆኑም በአንድነት ወይም በነጠላ) የሚሸፈን ነው፡፡ የዳኝነት ክፍያን በተማለከተ ጉዳዩ በዐቃቢ ህግ መቅረብ ሲኖርበት ቅድሚያ ስላልሰጠው ብቻ በግል በመቅረቡ የግል ከሳሽን ዳኝነት ማስከፈሉ ፍትሓዊ ስለማይሆን በዚህ ረገድ የቀድሞው ሕግ የጣለው ግዴታ ቀሪ ሆኗል፡፡ ይሁን እንጂ ከቅን ልቦና ወጪ በቀረበ ክስ ምክንያት ተከሳሽ ሲከራከር ቆይቶ በነፃ ከተሰናተም በዚህ ምክንያት ተከሳሹ ያወጣው ወጪ በከሳሹ እንዲሸፈን ፍርድ ቤቱ ሊወስን እንዲችል ሕጉ ድንጋጌን ይዟል፡፡

በማኛቸውም አግባብ በሚደረግ ክርክር አስፈላጊ የሆነውን የምስክር እና ሌሎች ማስረጃ ማቅረቢያ ወጪዎች በተማለከተም ምስክሩ ወይም ማስረጃው እንዲቀርብለት የጠራው ወገን ወጪውን ይሸፍናል፡፡ ወጪው በመንግስት የሚሸፈን በሚሆንበት ጊዜም ስለወጪው መጠን በደንብ በሚወሰነው አግባብ ይከፈላል፡፡ ወጪውን ለመሸፈን አቅም የሌለው ተከሳሽ ካጋጠመም ሥነ ስርአት ሕጉ እውነትን የማውጣትና ወጤታማ ፍትሕ አስተዳደር እንዲኖር የሚያልም በመሆኑ ይህንን አላማ ማሳካት ይቻል ዘንድ ምክንያታዊ የሆነው ወጪ ተለይቶ በፍርድ ቤት ወሳኔ በመንግስት እንዲሸፈን የሚያስችል ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲወጣ ሕጉ ይጠብቃል፡፡

## 18. ደንብ፣ መመሪያ እና ቅፃ ቅፆችን ማውጣትእንዲሁም ሕጉን ስለማሻሻል

እንደሌሎች ሕጎች ሁሉ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንዲሆን አስፈላጊ ከሆነት ነገሮች ወስጥ አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችና መመሪያዎች ሕጉ ስልጣን በሰጣቸው አካላት በአግባቡና በወቅቱ ሲወጡ ነው፡፡ በዚህ ማሰረት በሚኒስተሮች ምክር ቤት ቢያንስ አምስት ያህል ደንቦች እንዲወጡ ይጠበቃል፡፡ በተማሳሳይ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያንስ ስምንት ያህል መመሪያዎች፣ በፌዴራል ጠቅላይ አቃቤ ሕግ ቢያንስ አስራ ሁለት ያህል መመሪያዎች እንዲሁም በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ቢያንስ ሶስት ያህል መመሪያዎች እንዲወጡ

ይጠበቃል፡፡ ደንቦቹ እና መመሪያዎች በጊዜውባለመውጣታቸውየህግ አፈፃፀምክፍተት እንዳይፈጠርና በተግባር የሚስተዋሉ ችግሮች ሳይፈቱ እንደያቀሩ ለማድረግ ይህ ሕግ ከወጣ በኃላ በአጭር ጊዜ ወስጥ ደንቦቹና መመሪያዎች በጥራት መውጣት ይገባቸዋል፡፡ በተመሳሳይ ሜሉኩ እያንዳንዱ ተቋም ለስራውየሚያስፈልጉ ቅፆችን እንዲያወጣም ይጠበቃል፡፡ የቅፃ ቅፆች አስፈላጊነት ስራዎች ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ፣ የተቀራረበና ከሕጉ ጋር የተናበበ አሰራር እንዲኖር፣ ስራዎች በቅልጥፍና እንዲከናወኑ፣ ለዘወትር ስራዎችም እንደ ቼክ ሊስት እንዲያገለግሉ በመሆኑ በተቻለ ፍጥነት ወጥተው እንዲተገበሩ ይጠበቃል፡፡ አሁን ያለውን የባለሙያ ብቃት ግምት ወስጥ በማስገባትም ቅጾችን እንደቀድሞው ሕግ በአስገዳጅነት የሕጉ አባሪ ሟድረግ ግን አላስፈለገም፡፡

የፍትሕ አካላቱ መመሪያ እና አስፈላጊ የሆኑ የሚያወጡ ከመሆናቸውም በላይ ይህንን የሥነ ስርአት ሕጉን በማሻሻል ረገድ የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ይጠበቃል፡፡ ማንኛውም የዚህ ሕግ ማሻሻያ በተሟላ እና በዝርዝር ጥናት ላይ የተመሰረተ መሆን ይገባዋል፡፡ የስነ ስርአቱ ሕጉን የማሻሻል ሂደት በሕገ መንግስቱ በተረጋገጠው አግባብ የሚመለከታቸውን አካላት ሁሉ ማካተፍ ያለበት ከመሆኑም በላይ የፍትሕ አካላቱ በማሻሻያው አስፈላጊነት ላይ በጋራ መምከርና ተገቢነቱን የሚረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ይህንን አነስተኛ ሂደት ያጠናቀቀውን ማሻሻያ ጠቅላይ አቃቤ ሕግ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀጥሎም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ በባለቤትነት እንዲያጸድቅ የሚያስችል ግልፅ ስልጣን በሕጉ ተሰጥቶታል፡፡ የሕጉ ማሻሻያም የዚህ ሕግ አካል ሆኖ ይወጣል፡፡

## 19. ሰንጠረዥ

ከፍ ሲል እንደተመለከተው የፌዴራል እና የክልል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ክፍፍል የሕጉ አካል ሆኖ በአባሪ በተያያዘው ሰንጠረዥ የተመለከተ ነው፡፡ ሰንጠረዡ በመሰረቱ የወንጀል አይነቶችንን ድልድል በደረጃቸው፣ የትኛውን ጉዳይ የትኛው ፍርድ ቤት ይመለከታል የሚለውን የሚያመለክት ከመሆኑም በላይ መነሻ ያደረገበት መርህም ለወደፊቱ ወንጀል አይነት እንደ መነሻ ሊያለግል ይችላል፡፡ ሰንጠረዡ ወንጀሎችን የፌዴራል እና የክልል በማለት የሚከፍላቸው በዚህ ህግ ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን የስልጣን ድልድል መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በሌላ በኩልም አንድ ወንጀል ጉዳይ በፌዴራል ስልጣን ስር ወይንም በክልል ስልጣን ስር የሚያርፍ እንደሆነ ለመለየት የሚያስችል መመዘኛ አልነበራቸውም፡፡ በስራ ላይ ያሉት ህጎች የወንጀሎቹን ዝርዝር በማስቀመጥ ከሚለዩት በስተቀር በመርህ ደረጃ ያሰቀመጡት መመሪያ የለም፡፡ በመሆኑም አንድን ጉዳይ

በፌዴራል የወንጀል ስልጣን ስር ያርፋል ወይንስ የክልል ጉዳይ ይሆናል የሚለወን ለይቶ በስልጣን ድልድሉ ሰንጠረዥ ማስቀመጥ የሚያስፈልግ በመሆኑ "የፌዴራል የወንጀል ጉዳይ" የሚለው ምን ምን አይነት ጉዳዮችን ሊያካትት ይገባል የሚለውከአገሪቱ ሕገ መንግስት አንጻር ታይቶ የስነ ስርአትና ማስረጃሕጉ የዳኝነት ስልጣን ሰንጠረዥን ለማዘጋጀት ጥቅም ወሏል፡፡ ይህ ሞዴህ በሕጉ ላይ ለተማለከተው ሰንጠረዥ ክፍፍል ብቻ ሳይሆን ወደፊት የሚወጡ የወንጀል ሕጎች የዳኝነት ስልጣን ጥያቄ በተነሳም ቁጥር ለመፍትት/ለመደልደል የሚችል ድንጋጌ ይሆናል ማለት ነው፡፡

ወንጀሎቹን በፌፌዴራል ስልጣን ስር እንዲካተቱ የተደረገበት ማስፈርትም ይኸው ማስፈርት ነው፡፡ አንድ ወንጀል በፌዴራል ወይም በክልል የዳኝነት ስልጣን ስር እንደሚያርፍ ከተማለከተ በኋላ ተከታይ ስራውበየትኛው እርከን ላይ የሚገኘውፍርድ ቤት ሊማለከተውይገባል የሚለወን ማለየት ነው፡፡ ለዚህ በማስረታዊነት ማለኪያ ሆኖ የተወሰደው ወንጀሎች በቀላል፣ በመካከለኛና በከባድ ደረጃ የተከፋፈሉ መሆናቸውነው፡፡ በዚህ ማለኪያ ማስረትም አበዛኛው የወንጀል ጉዳይ በስረኛው ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ የሚታይ ሲሆን መካከለኛው ፍርድ ቤት በአብዛኛው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይሆናል ማለት ነው፡፡ በመሆኑም እስከ አስራ አምስት አመት ድረስ የሚያስቀጡወንጀሎች እንዳግባብነ ታቸውበፌዴራል ወይም በክልል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች የሚታዩ ሲሆን ከአስራ አምስተ አመት በላይ የሚያስቀጡወንጀሎች በከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የሚታዩ ይሆናሉ፡፡ ይሁን እንጂ በአንድ ድንጋጌ ወስጥ ከፊሉ ከአስራ አምስት አመት በታች ከፊሉ ከአስራ አምስት አመት በላይ የሚያስቀጡ ድንጋጌዎች ሊገኙ ይችላሉ፡፡ በሌላም በኩል በተማሳሳይ ከፊሉ በፌዴራል ከፊሉ ደግሞ በክልል ፍርድ ቤት ስር የሚያስቀጣ ወንጀል ሊያጋጥም ይችላል፡፡ በዚህ ሜሌኩ አንድ ተከሳሽ በተለያዩ ወንጀሎች የመከሰስ እድል ቢገጥመውስልጣን ያለወን ፍድ ቤት የማለየት ችግር እንዳይገጥምክስን አጣምሮ የማየት ሞዴህን በመተል ጉዳዩ በፌዴራል ፍርድ ቤት ወይንም ከባዱን ጉዳይ ለማየት ስልጣን ለተሰጠው ፍር ቤት እንዲቴ በሚያስችል ሜሌከ ድልድሉ በሰኝተረዡተሰርቷል፡፡